# አዲሱ

## የመጽሐፍ ቅዱስ

# ማብራሪያ

## የማቴዎስ ወንጌል

# የማቴዎስ ወንጌል

## ማ ው ጫ


ገጽ

**የክርስቶስ ልደትና ዕድገት 1:1-2:23 ... ... ... 5**

1:1-17 የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ... ... ... ... ... 5
1:18-25 የኢየሱስ ልደት ... ... ... ... ... ... ... 5
2:1-12 የሰብዓ ሰገል ጉብኝት ... ... ... ... ... ... 6
2:13-23 የኢየሱስ ወደ ግብፅ መሰደድና መመለስ ... ... ... ... 7

**የኢየሱስ መጠመቅና መፈተን 3:1-4:25 ... ... ... 8**

3:1-12 የዮሐንስ አገልግሎት ... ... ... ... ... ... 8
3:13-17 የኢየሱስ መጠመቅ ... ... ... ... ... ... 9
4:1-11 የኢየሱስ መፈተን ... ... ... ... ... ... 9
4:12-25 የኢየሱስ አገልግሎቱን መጀመር ... ... ... ... ... 10

**የተራራው ስብከት 5:1-7:29 ... ... ... ... 10**

5:1-16 የሐዋርያነት መታወቂያ ... ... ... ... ... ... 11
5:17-48 የብሉይና የአዲሱ ሕግ ... ... ... ... ... ... 11
6:1-18 የሃይማኖት ድንጋጌዎች ... ... ... ... ... ... 13
6:19-34 የቁሳቁሳዊ ሀብቶች ... ... ... ... ... ... ... 14
7:1-12 ሰው ፡ ለሰውና ለእግዚአብሔር ሊኖረው የሚገባው አመለካከት ... 15
7:13-29 የእግዚአብሔር መንግሥት ትእዛዞች ... ... ... ... 15

**የክርስቶስ ሥራዎች 8:1-9:34 ... ... ... ... 16**

8:1-17 የመፈወስ ሥራዎች ... ... ... ... ... ... ... 16
8:18-27 እምነት ሲፈተን ... ... ... ... ... ... ... 17
8:28-9:8 ተጨማሪ የመፈወስ ሥራዎች ... ... ... ... ... 17
9:9-17 የማቴዎስ መጠራትና የጾም ጥያቄ ... ... ... ... ... 18
9:18-34 ተጨማሪ የመፈወስ ሥራዎች ... ... ... ... ... 18

**የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ተልእኮ 9:35-10:42 ... ... 19**

9:35-10:4 ኢየሱስ ለሕዝቡ መራራቱና ደቀ መዛሙርቱን መጥራቱ ... ... 19
10:5-42 የተልዕኮው ግዴታዎች ... ... ... ... ... ... 19

**ክርስቶስ የሚጠይቃቸው ነገሮች 11:1-12:50 ... ... 21**

11:1-19 ኢየሱስና ዮሐንስ ... ... ... ... ... ... ... 21
11:20-30 የወንጌሉ መቅረብና የሰዎች አለመቀበል ... ... ... ... 22

12:1-14 ስለሰንበት የተደረገ ክርክር ... ... ... ... ... ... 23
12:15-37 በተጨማሪ የተፈጸመ የመፈወስ ሥራና ክርክር ... ... ... 23
12:38-50 ለሥራ መጠራት ... ... ... ... ... ... ... 24

የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌዎች 13፡1-52 ... ... 25
ክርስቶስን ስላለመቀበላቸው 13፡53-17፡27 ... ... 26

የኢየሱስ መገፋትና የዮሐንስ መገደል ... ... ... ... 27
የኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎችን መመገብና በባሕር ላይ መሄድ ... 27
የሽማግሌዎች ወግና ሥርዓት ... ... ... ... ... 28
ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን እንደገና መፈወሱና አራት ሺህ ሰዎችን መመገቡ 29
ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ... ... ... ... ... ... 29
የጴጥሮስ ምስክርነትና ያስከተለው ውይይት ... ... ... 29
የጌታ በተራራ ላይ መለወጥና ከዚያ በኋላ የተደረጉ ድርጊቶች ... 31

የመሲህ ተከታዮች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው 18፡1-35 ... ... ... ... ... ... ... 32
ኢየሱስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ 19፡1-22፡46 ... ... ... ... ... ... ... 33

ስለ ጋብቻና ስለ ልጆች ... ... ... ... ... ... 34
ባለጠግነትና ሽልማት ... ... ... ... ... ... 34
የመሲህ መከራ መቀበልና ፍቅር ... ... ... ... ... 35
ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱና ቤተ መቅደሱን ማጽዳቱ 36
በአይሁድ መሪዎችና በሕዝብ ላይ የሚሰጠው ፍርድ ... ... 37
ኢየሱስ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ጋር የነበረው ንትርክ ... 38

ክርስቶስ የሰጠው ማስጠንቀቂያና ሊመጣ ስላለው ፍርድ የተነበየው ትንቢት 23፡1-25፡46 ... ... ... ... 38

በጸሐፊዎችና በፈሪሳውያን ላይ የሚደርሰው መከራ ... ... 39
የኢየሩሳሌም ውድቀትና የሰው ልጅ መምጣት ... ... 40
አምስት የፍርድ ምሳሌዎች ... ... ... ... ... 41

የክርስቶስ መከራና ሞት 26፡1-27፡66 ... ... ... 42

የኢየሱስ ሽቱ መቀባትና የይሁዳ ክህደት ... ... ... ... 42
የመጨረሻው እራት ... ... ... ... ... ... 42
ጌቴሴማኔ ... ... ... ... ... ... ... ... 43
ኢየሱስ በቀያፋ ፊት ለፍርድ መቅረቡ ... ... ... ... 44
የይሁዳ ሞትና ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ለፍርድ መቅረቡ ... ... 44
የኢየሱስ ስቅለት ... ... ... ... ... ... ... 45
የኢየሱስ መቀበርና የመቃብሩ መጠበቅ ... ... ... ... 45

የክርቶስ ትንሣኤ 28፡1-20 ... ... ... ... ... 46

የኢየሱስ ከሞት መነሣት ... ... ... ... ... ... 46
የጠባቂዎች መደለል ... ... ... ... ... ... 46
የመጨረሻው ትእዛዝ ... ... ... ... ... ... 46
የወንጌሉ ጥቅም ... ... ... ... ... ... ... 47
የወንጌሉ መነሻ ምንጭ ... ... ... ... ... ... 47
የመጽሐፉ አቀራረብና ይዘት ... ... ... ... ... 47
የወንጌሉ መለያ ባሕርያት ... ... ... ... ... ... 48
ወንጌሉ የተጻፈበት ዘመንና የተገኘበት ቦታ ... ... ... 48
ጸሐፊው ... ... ... ... ... ... ... ... 49
ዓላማ ... ... ... ... ... ... ... ... 50

| | | |
|---|---|---|
| | **የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌዎች 13፡1-52** … … | 25 |
| | **ክርስቶስን ስላለመቀበላቸው 13፡53-17፡27** … … | 26 |
| 13፡53-14፡12 | የኢየሱስ መገፋትና የዮሐንስ መገደል … … … … | 27 |
| 14፡13-36 | የኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎችን መመገብና በባሕር ላይ መሄድ … | 27 |
| 15፡1-20 | የሽማግሌዎች ወግና ሥርዓት … … … … … | 28 |
| 15፡21-39 | ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን እንደገና መፈወሱና አራት ሺህ ሰዎችን መመገቡ | 29 |
| 16፡1-12 | ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን … … … … … … | 29 |
| 16፡13-28 | የጴጥሮስ ምስክርነትና ያስከተለው ውይይት … … … | 29 |
| 17፡1-27 | የጌታ በተራራ ላይ መለወጥና ከዚያ በኋላ የተደረጉ ድርጊቶች … | 31 |
| | **የመሲህ ተከታዮች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው 18፡1-35** … … … … … … … | 32 |
| | **ኢየሱስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ 19፡1-22፡46** … … … … … … … | 33 |
| 19፡1-15 | ስለ ጋብቻና ስለ ልጆች … … … … … … | 34 |
| 19፡16-20፡16 | ባለጠግነትና ሽልማት … … … … … … | 34 |
| 20፡17-34 | የመሲህ መከራ መቀበልና ፍቅር … … … … … | 35 |
| 21፡1-17 | ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱና ቤተ መቅደሱን ማጽዳቱ | 36 |
| 21፡18-22፡14 | በአይሁድ መሪዎችና በሕዝብ ላይ የሚሰጠው ፍርድ … … | 37 |
| 22፡15-46 | ኢየሱስ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ጋር የነበረው ንትርክ … | 38 |
| | **ክርስቶስ የሰጠው ማስጠንቀቂያና ሊመጣ ስላለው ፍርድ የተነበየው ትንቢት 23፡1-25፡46** … … … … | 38 |
| 23፡1-39 | በጸሐፊዎችና በፈሪሳውያን ላይ የሚደርሰው መከራ … … | 39 |
| 24፡1-42 | የኢየሩሳሌም ውድቀትና የሰው ልጅ መምጣት … … … | 40 |
| 24፡43-25፡46 | አምስት የፍርድ ምሳሌዎች … … … … … | 41 |
| | **የክርስቶስ መከራና ሞት 26፡1-27፡66** … … … | 42 |
| 26፡1-16 | የኢየሱስ ሽቱ መቀባትና የይሁዳ ክህደት … … … … | 42 |
| 26፡17-29 | የመጨረሻው እራት … … … … … … | 42 |
| 26፡30-56 | ጌቴሴማኔ … … … … … … … … | 43 |
| 26፡57-75 | ኢየሱስ በቀያፋ ፊት ለፍርድ መቅረቡ … … … … | 44 |
| 27፡1-31 | የይሁዳ ሞትና ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ለፍርድ መቅረቡ … … | 44 |
| 27፡32-56 | የኢየሱስ ስቅለት … … … … … … … | 45 |
| 27፡57-66 | የኢየሱስ መቀበርና የመቃብሩ መጠበቅ … … … … | 45 |
| | **የክርቶስ ትንሣኤ 28፡1-20** … … … … … | 46 |
| 28፡1-10 | የኢየሱስ ከሞት መነሣት … … … … … … | 46 |
| 28፡11-15 | የጠባቂዎች መደለል … … … … … … | 46 |
| 28፡16-20 | የመጨረሻው ትእዛዝ … … … … … … | 46 |
| | የወንጌሉ ጥቅም … … … … … … … | 47 |
| | የወንጌሉ መነሻ ምንጭ … … … … … … | 47 |
| | የመጽሐፉ አቀራረብና ይዘት … … … … … | 47 |
| | የወንጌሉ መለያ ባሕርያት … … … … … … | 48 |
| | ወንጌሉ የተጻፈበት ዘመንና የተገኘበት ቦታ … … … | 48 |
| | ጸሐፊው … … … … … … … … | 49 |
| | ዓላማ … … … … … … … … | 50 |

# ማብራሪያ

## የክርስቶስ ልደትና ዕድገት 1፡1-2፡23

ወንጌሉና የሐዋርያት ስብከት ሁለቱም ከዮሐንስ ጥምቀት ይጀምራሉ ። ማቴዎስ እንደ ሉቃስ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚገልጹ ሁለት ምዕራፎች አሉት ። እነዚህም ምዕራፎች የተጻፉት ስለ ልደቱና ስለ እድገቱ የተነገረው ትንቢት እንዴት ተፈጻሚነትን እንዳገኘ ለማሳየት ነው ። ማቴዎስ በምዕ 1-2 ላይ የተጠቀመበት አነጋገር የሚገኘው በርሱ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው ። እነዚህ ምዕራፎች የተፈጸሙትን ድርጊቶች ሲያትቱ ከዮሴፍ የተገኘውን ዘገባ የሚያቀርቡ ይመስላሉ ። የሉቃስ ወንጌል ግን የሚገልጸው ማርያም ያቀረበችውን ታሪክ ነው ።

## የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሀረግ 1፡1-17

ማቴዎስ በኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ያሉትን ስሞች በሶስት ቡድን ከፍሎ ማቅረቡ የወንጌሉን ዝርዝሮች በእንዴት ያለ መንገድ ለመጻፍ እንዳቀደ ይገልጻል ፤ ለማሰላሰልም የሚጠቀመን ነጥብ ነው ።

1-2/ "የትውልድ መጽሐፍ" የሚሉት የግሪክ ቃላት ቃል በቃል ሲተረጐሙ ፤ የነገሮች ሁሉ መጀመሪያ የተጻፈበት መጽሐፍ ማለት ነው ። ይህ ሐረግ የመጀመሪያውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ለመጥቀስ የተጻፈ አይደለም ፤ "የትውልድ መጽሐፍ" የሚለው አባባል ምናልባት ከኦሪት ዘፍጥ- 5፡1 የተጠቀሰ ይሆናል ። "ኢየሱስ" ፣ ጌታችን በዚህ ዓለም ላይ በኖረበት ዘመን የታወቀበት መጠሪያ ስሙ ነው ፤ በቁ- 21 ላይ ትርጉሙ ተሰጥቶአል ። "ክርስቶስ" ፣ የተቀባ ማለት ሲሆን መሲህና የእሥራኤል ንጉሥ ለሆነው የተሰጠ መጠሪያ ስም ነው ። "ዳዊት" ፣ ከእሥራኤል ንጉሦች ሁሉ ታላቅ ሲሆን ልጁ በዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ ቃል ኪዳን ተሰጥቶት ነበር ፤ 2 ሳሙ- 7፡12-16 ፣ መዝ- 88፡29 ፤ 36 ፤ 37 ፣ 131፡11 ። የ2 ሳሙ- 7 ትንቢት መሲህን በማስመልከት ይተረጐም ነበር ። በ9፡27 ፣ 12፡23 ፣ 15፡22 ፣ 20፡30 ፣ 21፡9 ፤ 15 ፣ 22፡42 ፤ 45 ላይ ኢየሱስ የዳዊት ልጅ ተብሎ ተጠርቶአል ። ይህ አባባል ወንጌሉ ኢየሱስ የዳዊት ዙፋን ወራሽ በመሆኑ ላይ እንደሚያተኩር ያሳያል ። "አብርሃም" ፣ የእሥራኤላውያን ሁሉ አባት ሲሆን ዘሩን እንደሚባርክለት እግዚአብሔር ለርሱ ቃል ኪዳን ሰጥቶት ነበር ፤ ዘፍጥ- 12፡1-3 ፣ 17፡1-8 ። ይህም ተስፋ በውነት ተፈጻሚነትን ሊያገኝ የቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ነበር ። ሉቃስ ዘሩን እስከ አዳም ድረስ የሚቆጥረው የመሲሁ ሥራ ለዓለም ሁሉ መሆኑን ለማሳየት ነው ፤ ሉቃስ 3፡38 ። ማቴዎስ ከአብርሃም የጀመረው እግዚአብሔር በተመረጡት ሕዝቦች አማካይነት እንዴት እንደሚሠራ አጥብቆ ለማስረዳት ነው ።

3/ "ትዕማር" ፣ በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ከተጠቀሱ አንዷ ስትሆን ፤ ስሟ የተጠቀሰውም ንጉሣውያን አባቶች ባልተፈቀደ የጋብቻ ሥርዓት መውለዳቸውን ለማሳየት ነው ፤ ዘፍጥ- 38።5/ "ረዓብ" ፣ ጋለሞታና ከአሕዛብ ወገን የሆነች ሴት ነበረች ፤ ኢያሱ 2 ። "ሩት" ፣ ሞዓባዊት ነበረች ፤ ሩት 1-4 ። 6/ "የኦርዮ ሚስት" ፣ ቤርሳቤህ ስትሆን ዳዊት ከርስዋ ጋር ያልተፈቀደ ጋብቻ መሥርቶ ነበር ፤ 2 ሳሙ- 12 ። 11/ "በባቢሎን ምርኰ ጊዜ" ፣ ይህ ሐረግ የዳዊት ልጆች ነግሠው ይገዙበት የነበረውን መንግሥት ፍጻሜ ከማሳየቱም በላይ ታላቁን ንጉሥ ክርስቶስን ያመለክታል ። 16/ "የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን" ፣ እዚህ ላይ ማቴዎስ እስከ ዮሴፍ ድረስ ያለውን ሕጋዊ ጋብቻቸውን የተከተለ የትውልድ ሐረግ የሚጠቅስ ሲሆን ፤ ሉቃስ ደግሞ የሚጠቅሰው የቤተሰብ የትውልድ ሐረጋቸውን ብቻ ነው ። ከዳዊት ስም በኋላ የተጠቀሱት ዝርዝሮች ልዩነት ይታይባቸዋል ። ማቴዎስና ሉቃስ ያቀረቧቸው የስም ዝርዝሮች በሰላቲያልና በዘሩባቤል ላይ አንድ ይሆኑና እንደገና ደግሞ እስከ ዮሴፍ ስም ድረስ ይለያያሉ ። በዚህ ቁጥር ውስጥ ዮሴፍ የኢየሱስ ወላጅ አባት መሆኑን የሚያመለክት ነጥብ የለም ። ይህን ሁኔታ ግልጽ ያደረገው የማርያም መጠቀስና የሚከተለውም ታሪክ ናቸው ። የደብረ ሲና ብራና ተብሎ በተጠራው በሶርያ ቋንቋ በተጻፈው ጽሑፍ ለሚገኙት ቃላት ማለት ዮሴፍ የኢየሱስ አባት ነው ለሚሉት ፤ በሕግ ፊት አባቱ ነበር ከማለት በቀር ሌላ ትርጉም መስጠት አያሻም ። 17/ ከመጀመሪያዎቹ የስም ቡድኖች ውስጥ ሶስት ሰዎች ሳይጠቀሱ ሲቀሩ ሶስተኛው ቡድን ደግሞ አሥራ ሶስት ትውልዶች ብቻ ስለያዘ የትውልድ ሐረጉ በዘዴ የቀረበ ይመስላል ። ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ አሥራ ሶስተኛ ሆኖ ሲቆጠር ፤ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ "ክርስቶስ" በተባለ ጊዜ አሥራ አራተኛ ሆኖ እንዲቆጠር ለማመልከት የተደረገ አይመስልም ። ምናልባት ማርያም በዚህ ውስጥ ሳትጨመር እንዳልቀረች ይታሰባል ። አሥራ አራት የሚለው ቁጥር በዕብራይስጥ ፊደል ሲጻፍ ዳ-ዊ-ት የሚል ንባብ ስለሚኖረው ኢየሱስ ከንጉሥ ዳዊት ቤት ሰብ መወለዱን ቁጥሩ ያመለክት ይሆናል ።

## የኢየሱስ ልደት 1፡18-25

መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ማለትም ኢየሱስ ያለ ሰብዓዊ አባት በመፀነሱና በቤተ ልሔም በመወለዱ ላይ ምንም እንኳ ማቴዎስና ሉቃስ ቢስማሙም እዚህ ላይ ማቴዎስ በዝርዝር የሰጠው ገለጻ ሉቃስ ከሰጠው በጣም የተለየ ነው ። ዮሴፍና ማርያም በጣም ልዩ ሆኖ የተገኘውን የልደቱን ሁኔታ በምስጢር መጠበቃቸውና በጥንታውያን ቤተ ክርስቲያኖች ስብከት ወንጌል ውስጥ ተጽፎ አለመገኘቱ የሚያስደንቅ አይደለም ። ማቴዎስ ስለ ጌታ ልደትና እድገት ባቀረበው ታሪክ እግዚአብሔር በሕልም በኩል የሰጠውን ምሪትና ከብሉይ ኪዳን የተፈጸመውን ትንቢት አጉልቶ ያሳያል ።

18/ "ታጨች" ፥ በዚያን ጊዜ መተጫጨት እንደ ቃል ኪዳን የሚቆጠር ሲሆን ለቃል ኪዳኑ ታማኝ አለመሆን እንደዘማዊነት ይታይ ነበር ። በኢየሱስ መፀነስ አኳያ "የመንፈስ ቅዱስ" ሥራ ትልቅ ቦታ አለው ፤ ሉቃስ 1፡35 ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር ሰው እንዲወለድ "እግዚአብሔር" ልዩ ሥራ ይሠራ እንደነበረ ተገልጦአል ፤ ዘፍጥ- 18፡11-14 ፥ 1 ሳሙ- 1፡4-20 ። መጥምቁ ዮሐንስ ሲወለድ ተመሳሳይ ድርጊት ተፈጽሞአል ፤ ሉቃስ 1፡5-25 ። ነገር ግን ልጅ ለመውለድ ሁለቱ ወላጆች አለመገናኘታቸውን የሚገልጽ አንድም ጥቅስ የለም ። በዚህና በቁ- 25 ላይ ግን ዮሴፍ ከኢየሱስ ልደት በፊት ከማርያም ጋር ግንኙነት እንዳላደረገ በተለይ ተነግሮአል ። 19/ መተጫጨታቸው በሕግ የጸደቀ እንደመሆኑ መጠን ዝም ብሎ ሊያባርራት አልቻለም ። ጻድቅ ሰው የነበረው ዮሴፍ ሕጋዊ የሆነውን ነገር ለማድረግ አቀደ ። ዮሴፍ የነበሩት ምርጫዎች ፥ 1/ በፍርድ ቤት ፍችን ማጽደቅና 2/ በሁለት ምስክሮች ፊት የፍችን ወረቀት መስጠት ሲሆን ዮሴፍ የፍች ወረቀት መስጠቱን መረጠ ። ፍትሕ በምሕረት መከናወን አለበት ። 20/ "ሕልም" ፥ በ2፡12 ፤ 13 ፤ 19 ውስጥ ደግሞ በሕልም ተመሩ ። "የዳዊት ልጅ" ፥ ኢየሱስ በዮሴፍ የዘር ሐረግ አማካይነት ሕጋዊ የሆነ መሢሕነት ያለው መሆኑን ያስታውሳል ። 21/ በዕብራይስጥ ኢያሱ የሚለው ቃልና በግሪክ ኢየሱስ የሚለው ቃል ጌታ ያድናል የሚል ትርጉም አላቸው ። ጌታ በወንጌሉ ውስጥ ለሠራውና ለተናገረው ኢያሱና ሙሴ ምሳሌ ለመሆን ቢችሉም ይህ አሳብ በየትም ሥፍራ ተገልጾ አልተብራራም ። በመሲህ ዘመን ኃጢአት ይወገዳል የሚል ተስፋ ነበረ ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ይህን ተስፋ የፈጸመው ፍጹም ባልተጠበቀ ሁኔታ ነበረ ።

ቁጥር 22 ልዩ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ከሚያቀርባቸው አባባሎች የመጀመሪያው ነው፤መግቢያውን ተመልከቱ ። 23/ "ድንግል" ፥ በኢሳ 7፡14 የሚገኘው አልማ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ወጣት ሴት ልጅን ያመለክታል ። በኢሳ- 7፡10-17 ላይ የተጠቀሰችው ሴት ፥ የንጉሥ አካዝ ባለቤት ሳትሆን አልቀረችም ። ባልታወቀ ምክንያት በዕብራይስጥ አልማ የሚለው ቃል በግሪክ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ፓቴኖስ ማለትም ድንግል ተብሎ ተተርጉሞአል ። በትንቢት ውስጥ ተጽፎ ቢገኝም እንኳ አይሁድ መሲህ ከድንግል ይወለዳል የሚል ተስፋ አልነበራቸውም ፤ ኢየሱስ ከድንግል ሲወለድ ግን የትንቢቱ ፍጻሜ ሆነ ። ድንግል የሚለው ቃል በግሪክ ብሉይ ኪዳን

ስለሚገኝ ማቴዎስ ተጠቅሞበታል ፤ ነገር ግን ዋና ነጥቡ አማኑኤል በሚለው ቃል ላይ ያተኩር ነበር ። በወንድ ልጅ መወለድ ለንጉሥ አካዝ የተሰጠው ምልክት ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው ለማዳንና ከነርሱ ጋር ለመሆን የሰጠው ቃል ኪዳን ማረጋገጫ ነበረ ፤ 2 ሳሙ- 7፡14-17 ። እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የተገኘው በቤተ መቅደስ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ይበልጥ ለሰዎች ቅርብ በሆነው በልጁ ስለሆነ ፥ የኢየሱስ ከድንግል መወለድ ከላይ የተጠቀሱት ትንቢቶችና የሌሎችም መፈጸም ምልክት ነው ። ይህ ትምህርት ከሞት የተነሣው ክርስቶስ እስከ ዘመን ፍጻሜ ድረስ ከሕዝቡ ጋር የሚገኝ መሆኑ በተብራራበት ተስፋ ቃል ውስጥ ተገልጾ ይታያል ፤ 28፡20 ።

24-25/ ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ ዮሴፍና ማርያም ባልና ሚስት ሆነው እንደኖሩ ሳያመለክቱ አይቀሩም ። በ13፡53-58 የተጠቀሱት የኢየሱስ ወንድሞችና እህቶች የተባሉት ሰዎች የዮሴፍና የማርያም ልጆች ነበሩ ለማለት የሚያዳግት ነገር አይገኝም ።

## የሰብዓ ሰገል ጉብኝት 2፡1-12

በሌሎች ጽሑፎች ውስጥ ተመሳሳይ ታሪኮች ስለሚገኙና በአንድ በኩል ደግሞ እንግዳ የሆነ መልክ ስላለው ይህ ዘገባ ብዙ ጊዜ እንደ አፈ ታሪክ ሆኖ ይቆጠር ነበር ። ነገር ግን ማቴዎስ እንደ እውነት አድርጎ ይተርከዋል ። ኢየሱስ ሥጋ የሆነ አምላክ ከሆነ እድገቱና እንዲሁም ልደቱ አገልግሎቱም ጭምር ፥ ልዩ በሆነ ሥርዓተ ተፈጥሮ ሲገለጽ ማንንም ሊያስደነግጥ አይገባም ።

1/ "ቤተልሔም" ፥ ዳዊት የተወለደባት ሥፍራ ነበረች ፤ 1 ሳሙ- 16፡1 ። ዮሴፍና ማርያም ከዳዊት ዘር ስለሆኑ በሕዝብ ቆጠራ ምክንያት ወደ ቤተልሔም ሄዱ ፤ ሉቃስ 2፡1-6 ። "ይሁዳ" ፥ የሮም አውራጃ ስም ሲሆን ፥ ምናልባት እዚህ ላይ የተጠቀሰው ፥ ኢየሱስ ከንጉሣዊ ዘር ከይሁዳ ነገድ መወለዱን ለማስታወስ ይሆናል ። "ሄሮድስ" ፥ ታላቁ ሄሮድስ በመባል የታወቀው ኤዶማዊ ሰው ነበር ። በሮማውያን ግዛት ሥር ንኡስ ንጉሥ ሲሆን ከክርስቶስ ልደት 40 ዓመታት በፊት የአይሁድ ንጉሥ የሚል ማዕረግ ተሰጥቶት ነበር ። ይኸኛው ሄሮድስ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ መሞቱ ስለተረጋገጠ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ የተወለደበትን ዘመን ለማወቅ የሚረዳ ነጥብ ይህ ብቻ ነው ። "ሰብዓ ሰገል" ፥ ኮከብ ቆጣሪዎች ነበሩ ። ምናልባት የመጡትም ከፋርስ ወይም ከዚያው አካባቢ ይሆናል ። እነዚህ ሰዎች የጥንቆላ ሥራ ይሠሩ የነበሩ ክፉ ሰዎች ነበሩ ብሎ ማሰብ የሚያስችል ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም ።

2/ "የአይሁድ ንጉሥ" ፥ የኢየሱስ ንጉሥነት ከዚህ እስከ መስቀል ድረስ በሙሉ ወንጌል ውስጥ ተገልጦ ይታያል ፤ 27፡11 ፥ 29 ፥ 37 ። እዚህ የተጠቀሰው ሄሮድስ በአይሁድ ላይ ካለው ንጉሣዊ ሥልጣን ጋር ለማወዳደር ነው ። ሉቃስ ደግሞ ፥ ራሱን አዳኝና ጌታ ነኝ ከሚለው ካውግስጦስ ቄሣር ጋር አዳኝና ጌታ የሆነውን ክርስቶስን በሰፊው ያወዳድራል ፤ ሉቃስ 2፡1-11 ። የአይሁድ ንጉሥ የሚለው ስያሜ ጲላጦስን ግራ ሲያጋባው ሄሮድስን ደግሞ አስደንግጦታል ። ስለዚህ ሁለቱም ትርጉሙ አልገባቸውም ፤ 27፡11-14 ። "ኮከቡ" ፥ የአዲስ ኮከብ መታየት አንድ ታላቅ ሰው መምጣቱን ያመለክታል ተብሎ ይታሰብ ነበር ። ኮከቡ በይሁዳ ውስጥ አንድ ታላቅ የሆነ ሰው መወለዱን ቢያመለክትም ፥ ሰብዓ ሰገል ፍለጋ የጀመሩት በታወቀና በተከበረ ሥፍራ ይገኛል የሚል አስተሳሰብ ስለነበራቸው ሲሆን በይፋ እየጠየቁ ኮከቡን ተከትለው ሄዱ ። ስለ ኮከቡ ተጨማሪ መረጃዎች ባይገኙም ፥ ከክርስቶስ ልደት ጥቂት ዓመታት በፊት ጁፒተርና ሳተርን ተቀራርበው ስለነበሩ የነርሱን መቀራረብ ያመለክት ይሆናል ።

3/ አሕዛብ ሊያመልኩት መጡ ፣ 12፡18-21 ። የእግዚአብሔርን ከተማ ማለት ኢየሩሳሌምን የሚገዙት ግን "ደነገጡ" ። 4/ ሰብዓ ሰገል ታላቅ አድርገው የተመለከቱት ሰው ፣ ምናልባት መሲህ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ሄሮድስ አሰበ ። 5/ መሲህ በቤተልሔም እንደሚወለድ ስላለው እምነት በዮሐንስ 7፡42 ከሚገኘው አሳብ ጋር ማወዳደር ይቻላል ። 6/ ይህ አባባል ሚክያስ 5፡2ን የሚያመለክት ሲሆን ከወንጌላዊው እንደተገኘ ማስገንዘቢያ አድርጎ መውሰድ ይሻላል እንጂ ከካህናትና ከጸሐፊዎች የተገኘ ቃል ሊሆን አይችልም ። ማቴዎስ ቤተልሔም አነስተኛ ከተማ መሆኗን በማረጋገጥ ይጀምርና በኋላ በማንኛውም አኳኋን በፍጹም ከማንም እንደማታንስ ያሳያል ። ነቢዩ ሚክያስ ግን ያሰበው በዓለማዊ አመለካከት ብቻ ታናሽ መሆኗን ነው ። "ገዢዎች" ፣ አለቆች የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ትርጓሜ ሲሆን ፣ በግሪክ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ሺ ሰዎች ወይም ነገዶች ተብሎ ተተርጉሞአል ። "የሚጠብቅ" ፣ ፓይማነይ የሚለው የግሪክ ቃል አሰማራ የሚል ትርጉም አለው ። አሳቡ በሚክ- 5፡3 ቢገኝም ፣ ይህ ሐረግ የእሥራኤል ሕዝብ ዳዊትን ለማንገሥ ወደ ኬብሮን መሰብሰባቸው ከሚገልጠው ከ2 ሳሙ- 5፡2 የተጠቀሰ ነው ።

10/ "ኮከብ" ፣ ምንም አይሁዶችና ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ከዘኁልቁ 24፡17 እየጠቀሱ ስለ መሲሕ መምጣት ቢያስተምሩም ማቴዎስ ድርጊቱን ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል ከሚለው ከዚህ ጥቅስ ጋር አለመያያዙ የሚያስገርም ነው ። እንግዲህ በምንም ዓይነት መንገድ የዘኁልቁ 24፡17 ትንቢት ለዚህ ታሪክ መሠረት አይሆንም ። 11/ "ሕጻኑን" ፣ ከተወለደ ብዙ ወራት ያለፈው መሆኑን ሳያስረዳ አይቀርም ። ሰብዓ ሰገል በመጀመሪያ ኮከቡን ያዩበትን ጊዜ ለሄሮድስ ሳይነግሩት አልቀሩም ። ዕድሚያቸው ከሁለት ዓመት በታች ያሉትን ልጆች መግደሉ አንድ የተወሰነ ጊዜ ያለፈ መሆኑን ያስረዳል ፤ ቁ- 16 ። በዚህ ጊዜ ሰብዓ ሰገል እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው የሚለውን አባባል ለመረዳት ሙሉ ዕውቀት ባይኖራቸውም እንኳ "ወድቀው ሰገዱለት" ፤ 1፡23 ። መዝ- 71፡10 ፣ ኢሳ- 49፡7ና 60፡10 ስላቀረቡአቸው ስጦታዎች ቀጥለው ለተገኙት ትርጉሞች መሠረታዊ መረጃዎች ሲያቀርቡ ፣ እነዚህ ሰብዓ ሰገልም ነገሥታት ሆነው የተቆጠሩበትን ምክንያት ያስረዳሉ ። ሰብዓ ሰገል ሶስት ስጦታዎችን ስላቀረቡ ቁጥራቸው ሶስት ነበረ ብሎ መገመት የተለመደ ሆኗል ። ስለ ሰብዓ ሰገል ማንነት ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ነጥቦች አንዳቸውም በማቴዎስ አልተጠቀሱም ፤ ፈጽም አፈ ታሪክ ናቸው ። የእግዚአብሔር ልጅ በመጀመሪያ ትሑታንና ድሆች ለነበሩት አይሁድ ማለትም ለማርያምና ለዮሴፍ ከተገለጸ በኋላ ለተማሩና ሀብታም ለሆኑ ለአሕዛብ ወኪሎች ተገለጸ ።

## ወደ ግብፅ ስለ መሰደዱና ስለ መመለሱ 2፡13-20

አንዳንድ ምሁራን በዚህ ክፍለ ምንባብ ላይ ሲያትቱ ጸሐፊው ብሉይ ኪዳን በትንቢትም ሆነ በድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ለማሳየት በመፈለጉ ያቀረበው አፈ ታሪክ ነው የሚል አሳብ አቅርበዋል ። ነገር ግን ለዚህ ክፍለ ምንባብ ያለን አመለካከት የተመሠረተው እግዚአብሔር በታሪክ ላይ ያለውን አምላካዊ የበላይነት በመቀበላችንና የማቴዎስ ዓላማ ምን እንደነበረ በመረዳታችን ላይ ነው ።

13/ የባርነት ሥፍራ የነበረችው "ግብፅ" ፣ ዘፀ- 20፡2 ፤ አሁን የመዳኛ ሥፍራ መሆኗን መጥቀሱ የቀልድ አነጋገር ይመስላል ። በተስፋይቱ ምድር ላይ ካለው ከንጉሡ ቁጣ ለመሸሽ ኢየሱስ ወደ ግብፅ መወሰድ ነበረበት ፤ ዕብ 11፡27 ። 15/ በሆሴ- 11፡1 ላይ የተጠቀሰው የእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያመለክት ነው ፤ ዘፀ- 4፡22 ። ማቴዎስ እዚህ ላይ ኢየሱስን የሚመለከተው ለየት ባለ መንገድ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎ ሳይሆን ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተወካይ አድርጎ በመቁጠር ነው ። ቀረብ ባለ ጊዜ እርሱ በውኃና በበረሃ መካከል ያልፋል ፤ ይኸውም እሥራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ እንደፈጸሙት ዓይነት ይሆናል ፤ ማቴ 3፡13-4፡11 ። 16/ ሄሮድስ በጭከናው የታወቀ ስለሆነ ይህን ማድረግ ለርሱ በጣም ቀላል ነው ። በቤተልሔም ከተማ ከሁለት ዓመት በታች ያሉት ሕጻናት ከ20 ላይበልጡ ይችላሉ ። ሄሮድስ የፈጸማቸው ከዚህ የበለጠ ብዙ ክፉ ድርጊቶች ስላሉ ይህ ድርጊት በዓለም ታሪክ ውስጥ ተጽፎ አለመገኘቱ የሚያስገርም አይደለም ። የርሱ ሥራ ከፈርዖን ሥራ ጋር ይመሳሰላል ፤ ዘፀ- 1፡15-22 ። ኢየሱስን በአንድ በኩል ከሙሴ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ማወዳደር የሚቻል መሆኑ በዚህ አጻጻፍ ግልጽ ሆኖ ይታያል ። ልዩነቶቹ ብዙ ስለሆኑ ማቴዎስ የኢየሱስን ልምምድ ከሙሴ ጋር አንድ አድርጎ ለማቅረብ ግልጽ የሆነ ሙከራ አላደረገም ።

18/ ይህን ጥቅስ ከድርጊቱ ጋር የሚያገናዝብ መንገድ በቀላሉ ማግኘት አይቻልም ፤ ኤር- 31፡15 ። የማቴዎስ የአቀራረብ ዘዴ ፣ በመጀመሪያ ድርጊቱን መጥቀስ ቀጥሎም አስረጂ ጥቅስ ማቅረብ እንደሆነ በግልጽ ይታያል ። "ራሔል" በምሳሌ ረገድ የእሥራኤላውያን እናት ስትሆን መቃብሯም እሥራኤላውያን በስደት ወደ ባቢሎን በሄዱበት ጎዳና አጠገብ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን 8 ኪሎ ሜትር ርቆ "ራማ" ይገኛል ። ወደ ኤፍራታ በሚወስደው መንገድ ላይ ማለትም በቤተልሔም እንደ ሞተች ይነገራል ፤ ዘፍጥ- 35፡19 ፣ 48፡7 ። እንዲሁም በተጨማሪ ሕጻናቱ በቤተልሔም መገደላቸውን ሊያመለክት ይችላል ። የኤርምያስ ምዕ- 31 ታሪክ ፤ የእሥራኤል ልጆች በባቢሎን መማረክ ጥልቅ ሐዘንና ልቅሶ የሚያስከትል ቢሆንም ፣ ጌታ በፊታችሁ ተስፋ አለ ብሎ ለሚያውጅበት አዲስ ዘመን ዋዜማ ነበረ ፤ ኤር- 31፡17 ። እንዲሁም የእሥራኤል እናቶችም ልቅሶ ለመሲሁ የማዳን ሥራ ዋዜማ ነው ። 20/ ዘፀ- 4፡19 ። 22/ "አርኬላዎስ" ፣ በይሁዳ ፣ በሰማርያና በኤዶምያስ የነበረው የሄሮድስ ግዛት ገዢ ሆኖ ነገሠ ። ሄሮድስ — አንቲጳስ በገሊላና በፌሪያ ፣ ፊልጶስ ደግሞ በገሊላ ሰሜን ምሥራቅ አውራጃዎች የንጉሡ እንደራሴ ነበሩ ። ከአንቲጳስ ይበልጥ አርኬላዎስ ለሕጻኑ ኢየሱስ ደኅንነት እጅግ አደገኛ ሆኖ ተገኘ ። 23/ ይህ ጥቅስ የተጠቀሰበት ሥፍራ ባለመታወቁ በመተርጎም

ረገድ ብዙ ችግር ፈጥሯል ። "በነቢያት" ሲል ብዙ የትንቢት ክፍሎች በአእምሮው ያሰላስል እንደነበረ መረዳት ይቻላል ። በኢሳ 11፡1 ላይ ቅርንጫፍ ተብሎ ከተተረጐመው ናዝር ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ማገናዘብ የተለመደ ነው ። ይህ ትንቢት በተለምዶ መሲሑ ከንጉሥ ዳዊት ተወልዶ ዝቅ ባለ መንገድ መም ጣቱን ይገልጻል ተብሎ ተተርጉሞአል ። ኢየሱስ "በና ዝሬት" ከተማ ማደጉን ማቴዎስ ሲጠቅስ በኢሳ- 11፡1 ላይ ያለው ትንቢት ትዝ አለው ፤ ነገር ግን የከተማውን ስም ከናዝራውያን ጋር ማገናዘብ የሚያስችል ምንም አጥጋቢ ምክንያት የለም ። የናዝሬት ከተማ የተናቀች መሆኗን ዮሐ 1፡46 ያሳያል ። ኢየሱስ ያደገበት አካ ባቢ ገሊላ ቢሆንም በቤተልሔል መወለዱን የሚክድ አለመሆኑን ማቴዎስ የግድ ማሳየት አለበት ።

## የክርስቶስ ጥምቀትና ፈተናው 3፡1-4፡25

ንጉሥ ፤ መሲህና አምላክ የሆነው ኢየሱስ እንዴት እንደመጣ ካሳየ በኋላ ማቴዎስ ስለ ትውልዱና ስለ እድገቱ የተነገሩት ትንቢቶች እንዴት እንደተፈጸሙ ገልጾአል ። ከዚህ በኋላ እስከ ሠላሳ ዓመት ድረስ ኢየ ሱስ የፈጸማቸውን ድርጊቶች አልጻፈም ፤ ሉቃስ 3፡23 ። የማዳኑ ሥራ ከክርስቶስ አገልግሎት ፥ ሞትና ትንሣኤ ጋር የተያያዘ ነው ፤ እነዚህ ሶስቱ ደግሞ የሐዋርያት ስብ ከት ይዘት ናቸው ። የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት በሐዋርያት ስብከት መክፈቻ ላይ ተጠቅሶአል ፤ የሐዋ- 1፡22 ፥ 10፡37 ፥ 13፡24 ። እንዲሁም ከዋናዎቹ የወንጌል ክፍሎች መጀመሪያ ላይ ይገኛል ፤ ማር- 1፡2 -5 ፥ ሉቃስ 3፡1-9 ፥ ዮሐ- 1፡6-8 ። የመሲሑ አዋጅ ነጋሪ ሆኖ የመ ጣው መጥምቁ ዮሐንስ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነቢይ ነበር ፤ ማቴ- 11፡11-13 ፥ ማር- 1፡2 ። ሐዋርያት የትንሣኤው ምስክሮች እንደነበሩ ሁሉ ፥ መጥምቁ ዮሐንስ ደግሞ ክርስቶስ በሥጋ የመምጣቱ ምስክር ነበረ ፤ ዮሐ- 1፡7 ። እርሱ የኤልያስ ምሳሌ ነው ፤ ማቴ- 11፡14 ። የዮሐንስ አገልግሎት ሕዝቡን ተስፋ ወደ ተሰጠቻቸው ምድር ዳርቻ ካደረሳቸው በኋላ ሊገባበት ካልቻለው ከሙሴ ጋር ይወዳደራል ፤ 11፡11 ። ምዕ- 1-2 ላይ ነቢያት ስለ ኢየሱስ የመሰከሩት ቃል ሲገኝ ከምዕ- 3 ጀምሮ ሕያውና የጊዜው ነቢይ ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ወደሚያስተምረን ቃል እንመጣለን ።

ኢየሱስ የተጠራበትን መሲሀዊ አገልግሎት ለመ ፈጸም ዝግጁ መሆኑን በጥምቀቱ ገለጸ ። ከጥምቀቱ ቀጥሎ በመጣበት ፈተና የተቀበለው ጥሪ ተፈተነ ። ኢየሱስ ከተፈተነና የዮሐንስም አገልግሎት ከተፈጸመ በኋላ —4፡12 ፥ ኢየሱስ የራሱን አገልግሎት ለመጀመር መንገዱ ስለተከፈተለት እንዲከተሉት ሰዎችን ወደ ራሱ መጥራት ጀመረ ።

## የዮሐንስ አገልግሎት 3፡1-12

ይህ ክፍል በከፊል ከማርቆስ 1፡2-8 ጋር ይመሳሰላል ፤ ነገር ግን ቁ- 7-10 ንና 12ን ከሉቃስ 3፡2-9ና 16-20 ጋር አወዳድሩት ። ዮሐንስ ኢየሱስን ለማጥመቅ ከመ ጠራቱ በፊት የነበረውን ጠቅላላ የአገልግሎት ይዘት ዘርዝሮ ይገልጻል ።

1-2/ "በዚያም ወራት" ፥ ማቴዎስ ቀኑን በርግጥ ለይቶ ባይናገርም በታወቀ ጊዜ ማለቱ ይሆናል ። ከወ ንጌላውያን ሁሉ ሉቃስ ብቻ ቀኑን ለይቶ ይጽፋል ። "መጥምቁ ዮሐንስ" ለወንጌል አንባብያን በሚገባ የታ ወቀና አስተዋዋቂ የማያስፈልገው ሰው ነው ። "በይሁዳ ምድረ በዳ" ፥ አብዛኛው ቦታ ለከብት ግጦሽ ተስማሚ የሆነውን ሰፊና ያልታረሰ ቦታን ያጠቃልላል ። ምድረ በዳ በተለምዶ አንዳንድ ነቢያትና የባሕታውያን ቡድ ኖች ፥ ኃጢአት ከበዛበት ከተማ ለመራቅ ብለው የሚ ሄዱበት በንጽሕና ከእግዚዘአብሔር ጋር እንኖርበታ ለን ብለው የሚያስቡት ሥፍራ ነበረ ። የዮሐንስ ዓላማ ከነዚህ ቡድኖች በጣም የተለየ ስለሆነ ከነርሱ ጋር ተባብሮአል ብሎ መናገር ፍጹም አፈ ታሪክ ነው ። ዮሐንስ በምድረ በዳ ሄዶ የሰበከው ፥ ንስሐ የገቡ መንፈ ሳዊ ሰዎችን ለመሰብሰብ እንጂ ሰዎችን ከአይሁድ መካከል ሰብስቦ ወደ ምድረ በዳ በመሄድ የተለየ ኅብ ረተ ሰብን ለመፍጠር አልነበረም ። ማቴዎስ የዮሐንስን ስብከት ባብራራበት ቃል የኢየሱስን ደግሞ አጠቃሎ አቅርቦአል ፤ 4፡17 ። "ንስሐ ግቡ" ፥ ስለ ራሳችሁና ስለ እግዚአብሔር ያላችሁን አመለካከት ለውጡ ማለት ነው ። ጥሪው የተደረገው መሲህዊው መንግሥት በመ ቃረቡ ምክንያት ነው ። ማቴዎስ የመሲሁን መንግሥት "መንግሥተ ሰማያት" ብሎ አክብሮት በተሞላበት አጠራር ሲጠራው ሌሎቹ ወንጌላውያን ደግሞ የእግ ዚአብሔር መንግሥት ብለው ጠርተውታል ።

3/ ወንጌላውያን ከኢሳ- 40፡3 ሲጠቅሱ "ጌታ" የሚ ለው ቃል ክርስቶስን ያመለክታል ብለው ተርጉመው ታል። ይህ አዋጅ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከስደት የሚያ ድንበት የዝግጅት ጥሪ ሲሆን አሁን ደግሞ ለቀረበው አዲስ የማዳን ሥራ ተስማሚ የሚሆን ነው ። 4/ ፍጹም የሆነ የኤልያስ ምሳሌ ነው ፤ 2 ነገ- 1፡8 ። 5/ ዮሐንስ በግልጽ በአይሁድ ሥርዓት ትምህርት ውስጥ ታላቅ መናወጥን ፈጥሮአል ። 6/ የጥምቀቱ ሥራ አፈጻጸም እንዴት እንደሆነ በትክክል አይታወቅም ። በኩምራን ኅብረተ ሰብ ልማድ ፥ ሰው ንስሐ ሲገባ ይጠመቅ ነበር ።

7/ ለመጠመቅ ወደርሱ የመጡት የደንበኞች ቁጥር እየበዛ ሄደ ። "ፈሪሳውያን "፥ ሕግን መጠበቃቸውና "ሰዱቃውያን" ደግሞ ሥነ ሥርዓትን ማክበራቸው መንግሥተ ሰማያት ለመግባት እንደ ይለፍ ፈቃድ የሚ ያገለግል መስሎ ይታያቸው ነበር ። ነገር ግን እባብ ከጫካ እሳት ሸሽቶ እንደሚመጣ ብዙዎች የመጡት ከፍርሃት ስሜት የተነሣ ነበረ ። ዮሐንስ አጠር ያለ ስብከት ማቅረቡ የሚያስደንቅ አይደለም ። 9/ በአሁኑ ዘመን እንኳ በእግዚአብሔር ጸጋ ሳይሆን በአባት ትው ልድ የሚመኩ ሰዎች አሉ ፤ ዮሐ 8፡39 ። የመጡት ሰዎች የተጠመቁ መሆናቸው አልተነገረም ፤ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሳይጠመቁ የተመለሱ ይመስላል ፤ 21፡25 ።

11/ የዮሐንስ ጥምቀት የመሲሁን ማንነት የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ሥራውንም ጭምር የሚገልጽ ነበረ ። ዮሐንስ ራሱ እንኳ አገልጋይ መሆን እንደማይገባው ገለጸ ። ኢየሱስ ከዮሐንስ እንደሚበልጥ ሁሉ ጥምቀቱም

ከዮሐንስ ጥምቀት ይበልጣል ። "መንፈስ ቅዱስ" ፥ ምናልባት እዚህ ላይ በበዓለ ሃምሳ ቀን የመንፈስ ቅዱስ ማንነት እንደተገለጸ ሆኖ በሚገባ አልታወቀ ይሆናል ። በልባቸው ውስጥ የሚሠራው የእግዚአብሔር ሥራ ገና አልተጠናቀቀም ። 12/ አውድማውን የሚያጠራው የመንፈስ ነፋስና እሳት የቁርጠኛ ፍርድ ምሳሌዎች ናቸው ።

## የኢየሱስ ጥምቀት 3፡13-17

ይህ ክፍለ ምንባብ ከማር- 1፡9-11 ጋር ይቀራረባል ፤ ሉቃስ 3፡21-22ን አንብቡ ። ነገር ግን ቁ- 14ና 15 የሚገኙት በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው ። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የኢየሱስን ጥምቀት ሲተረጉሙ ፥ የአገልግሎቱን ተልእኮ ለመጀመር መዘጋጀቱን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከግብፅ ምድር ነጻ መውጣታቸውንና አዲሱ እስራኤል ወደ አዲሱ የነጻ መውጣት ደኅንነት መግባታቸውን የሚያሳይ ምሳሌ አድርገው ይመለከቱታል ፤ 21፡23-27 ፥ 1 ቆሮ- 10፡1-4 ። 14/ ዮሐንስ ኢየሱስን ለማጥመቅ ማመንታቱን የጻፈው ማቴዎስ ብቻ ስለሆነ ጥቅሱ በማቴዎስ የተጻፈ ሳይሆን ፥ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ የተጠመቀበት ምክንያት ኃጢአተኛና ከዮሐንስ ዝቅ ያለ ስለሆነ ነው ለሚለው ተቃውሞ መልስ ለመስጠት በኋላ የተጨመረ ነው የሚል የተሳሳተ አሳብ ቀርቦአል ። ዮሐንስ ኢየሱስን እንደመሲህ አድርጎ እንዳልተቀበለው ይታሰባል ፤ ዮሐ- 1፡31 ። ስለ ጥምቀቱ የተጻፈው ዘገባ ዮሐንስ ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ስለመቀበሉም ሆነ ስላለመቀበሉ ምንም አይጠቅስም ፤ ነገር ግን ዮሐንስ በመንፈሳዊ አኗኗር ረገድ ከርሱ ከፍ ያለ ሰው እንዳጋጠመው ይገልጻል ። ዮሐንስ የኢየሱስን ጠባይ በማወቁ ፥ ንስሐ የማያስፈልገውና ኃጢአት የሌለበት መሆኑን ስላረጋገጠ ሊያጠምቀው አመነታ ። ዮሐንስ እርሱን ባጠመቀበት ጊዜ በተፈጥሮ ሁኔታ ኢየሱስ ማን እንደሆነና ምን ለመፈጸም እንደመጣ በጥልቅ ለመረዳት ችሎአል ፤ ዮሐ 1፡31-34 ።

15/ "ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም" ፥ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን እቅድና ጥሪ የተቀበለና ራሱንም ከእውነተኛ እስራኤላውያን ጋር የቆጠረ መሆኑን ያስረዳል ። 16/ "ወጣ" ፥ ይህ ቃል በዘፀ- 13፡18 እስራኤላውያን ከግብፅ መውጣታቸውን ፥ በዘዳ- 1፡21 መሠረት ደግሞ ወደ ተስፋይቱ አገር መግባታቸውን ያመለክታል ። ምንም በሰፊው የሚጠቀምበት ቃል ቢሆንም በዚህ ክፍለ ምንባብ ላይ የቀድሞውን ታሪክ ሳያገናዝብ አይቀርም ። የሰማዮች መከፈት ምናልባት በኢሳ 64፡1 ላይ የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ ሲሆን እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ወደ ዓለም መምጣቱን ያሳይ ይሆናል ፤ ዮሐ- 1፡51 ። መንፈስ "እንደርግብ" ሆኖ መውረዱን ያዩ ቢያንስ ኢየሱስና ዮሐንስ ናቸው ፤ ዮሐ- 1፡33 ። 17/ "ድምፅ" ፥ እግዚአብሔር ራሱ ሲናገር ነው ። የተሰሙት ቃላት ከኢሳ- 42፡1ና ከመዝ- 2፡7 የተውጣጡ ናቸው ። ይህ የቃላት ቅንብር ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ሲያሳይ ፥ መሲህነቱ ኢሳይያስ ስለ ጌታ አገልጋይ በተናገረው መሠረት መተርጎም አለበት ። "ይህ ነው" ፥ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ ማለት አይደለም ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ እንዲሠራ ተሰየመ ማለት ነው ፤ 17፡5 ። "የምወደው ልጄ" ፥ ይህ ሐረግ በአብና በወልድ መካከል ልዩ የሆነ ግንኙነት እንዳለ ያሳያል ፤ ዮሐ- 1፡18 ። በኤፌ- 1፡6 ኢየሱስ "የተወደደ" ተብሎአል ። "በርሱም ደስ የሚለኝ" ፥ እስከዚያን ጊዜ ድረስ በመታዘዙ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ከዚያ በበለጠ በርሱ የማዳኑን ዕቅድ የሚፈጽምበት ስለሆነ ነው ።

## የኢየሱስ ፈተና 4፡1-11

የኢየሱስ ፈተናዎች በማር- 1፡12-13 ባጭሩ ተጠቅሰዋል ። በተጨማሪ ሉቃስ 4፡1-13ን አንብቡ ። በሉቃስ ውስጥ የሚታየው ዓይነተኛ የሆነ ልዩነት የሁለተኛውና የሶስተኛው ፈተናዎች ቅደም ተከተል መዛወር ነው ። የማቴዎስ አተራረክ በኢየሱስ ስሜት ላይ ሲያተኩር ፥ የሉቃስ ደግሞ በይበልጥ የሚጠቀመው የፈተናውን ሥፍራዎች ነው ። ከዮሐንስ ወንጌል በቀር ሶስቱ ወንጌሎችና የዕብራውያን መልእክት ብቻ ስለፈተናው ይጠቅሳሉ ፤ ዕብ 2፡18 ፥ 4፡15 ። እዚህ ላይ ፈተናዎቹ ከግብፅ ነጻ መውጣትን የሚያሳስቡ መሆናቸው እያጠራጥርም ። ኢየሱስ ራሱ የእስራኤል ምሳሌ በመሆን በተደጋጋሚ ታሪካቸውን መፈጸም እንደሚገባው ተረድቶ እስራኤላውያን በምድረ በዳ የነበሩበትን ጊዜ የሚያመለክት አምላካዊ ትንተና የሚሰጠው አራት ዘዳግምን መጥቀሱን ያሳያል ። ፈተናዎቹ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ከሚደርሱት ፈተናዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው ፥ 1 ቆሮ- 10፡1-13 ። ኢየሱስንና የሥራ ዕቅዱን ለመፈተን የመጡ ናቸው ። በተጨማሪ ደግሞ አዳምና ሔዋን ከተፈተኑባቸው ፈተናዎች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው ፤ ዘፍጥ- 3 ። የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ፥ ስለ ገንዘብም መመካት በመባል ከታወቁት ጋር አንድ ናቸው ፤ 1 ዮሐ- 2፡16 ። እነዚህ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ የሚደርሱ ፈተናዎች ናቸው ።

1/ ኢየሱስ ፈተናውን ማሸነፍ ስለነበረበት በመንፈስ ተመርቶ ወጣ ። 2-4/ ከተጠመቀ በኋላ "አርባ" ቀን" በምድረ በዳ መቀመጡ ፥ ልጄ ተብለው የተጠሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከግብፅ ከወጡ በኋላ አርባ ዓመታት በምድረ በዳ መንከራተታቸውን ያስታውሳል ፤ ሆሴዕ 11፡1 ። "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ" ፥ ቁ- 6ንና 27፡40ን ተመልከቱ ። እግዚአብሔር በ3፡17 ላይ ልጄ ነው በማለት የተናገረለትን እንዲጠራጠር ሰይጣን ሲፈታተነው ይታያል ፤ ዘፍጥ- 3፡1 ። ድንጋይን ወደ እንጀራ መለወጥ ከእግዚአብሔር የመፍጠር ዕቅድ ጋር የማይስማማ ድርጊት ነው ። "ተጽፎአል" ፥ ከዘዳ- 8፡3 የተጠቀሰ ቃል ሲሆን እስራኤላውያን እግዚአብሔር ሰጥቶአቸው በነበረው መና ላይ ያደረጉትን ማጉረምረም የሚያመለክት ነው ፤ ዘኍ- 11፡4-9 ። ይህ የሥጋ ምኞት የሆነ ፈተና ነው ፤ 1 ዮሐ- 2፡16 ። ለመብላት ያማረ እንደሆነ አየች ከሚለው ከዘፍ- 3፡6 ጋር አወዳድሩ ። ይህ ፈተና ፥ ኢየሱስን እግዚአብሔር ባቀረበው እንዳይደሰት በተአምር ምግብን ለራሱ እንዲያቀርብ የሚፈ

ትነው ነበር ፡፡ 5-7/ "በመቅደስ ጫፍ" ፤ ይህ ምናልባት እጅግ ከፍ ያለ የግንብ ጫፍ ወይም ምሽግ ሊሆን ይች ላል ፡፡ "በመቅደስ ጫፍ" ላይ አቆመው ሲል በውነት ቤተ መቅደሱ ጫፍ ላይ ወስዶ ያቆመው አይመስልም ፡፡ ሰይጣን ከመጽሐፉ የጠቀሰው ጥቅስ በተንኮል ያቀረ በው ሲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚስ ማማ አይደለም ፡፡ ኢየሱስ በመልሱ ከዘዳ- 6፡16 የጠ ቀሰው ጥቅስ ፤ ሰይጣን ኢየሱስን መፈተን እንደሌለበት የሚያመለክት ሳይሆን እግዚአብሔር አብን መፈታተን እንደማይገባው የሚገልጽ ነው ፡፡ ሕዝቡ በማሳህ የእ ግዚአብሔርን መገለጽ በተአምር እንዲያሳያቸው ሙሴን የጠየቁትን ጥያቄ ያስታውሳል ፤ ዘዳ- 17፡1-7 ፡፡ ይህ እንግዲህ የዓይን አምሮት ወይም የአእምሮ መፈተን ማለት ነው ፡፡ በዘፍጥ- 3፡6 ለዓይን የሚያስጎመጅ ከሚ ለው ጋር አወዳድሩት ፡፡ ይህ ፈተና አእምሮን የሚፈታ ተን ነበረ ፤ ኢየሱስ እግዚአብሔር ባቀደለት ዕቅድ እንዳይስማማና አስገራሚ ድንቆችን በመሥራት ግቡን እንዳይመታ ሰይጣን ተፈታተነው፡፡8-10/ "እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ" ፤ ሥዕላዊ አገላለጽ ሳይሆን አይቀ ርም ፡፡ የተጠቀሰው ጥቅስ ማለት ዘዳግ- 6፡13 ፤ እስራኤ ላውያን የወርቅ ጥጃ በአመለኩ ጊዜ የሆነውን ድርጊት የሚገልጽ ነው ፤ ዘፀአ- 32፡1-6 ፡፡ ይህ ለነፍስ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ፈተና ነው ፡፡ እንደ እግዚአብሔር ትሆ ናላችሁ ከሚለው ጋር አወዳድሩት ፤ ዘፍጥ- 3፡5 ፡፡ ይኸ ኛው ፈተና ፤ እግዚአብሔር ያቀደልኝ አያረካኝም ፤ ስለዚህ ግቤን ለመምታት ባልተፈቀደልኝ መንገድ ልሥራ ብሎ እንዲያስብ የሚገፋፋው ነበረ ፡፡ 11/ ይህም እንደገና አልተፈተነም ማለት አይደለም ፤ ሉቃስ 4፡13 አንብቡ ፡፡

## አገልግሎት ስለ መጀመሩ 4፡12-25

ቁ- 12ና 17-22 ከማር- 1፡14-20 ጋር አንድ ናቸው ፤ ሉቃስ 4፡14 ፡፡ ቁ- 13-16ና 24 የሚገኙት በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ፤ ማቴዎስ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ምኩ ራብ ያደረገው ሳይጽፈው አልፎታል ፤ ማር- 1፡21-28 ፡፡ እንዲሁም የጴጥሮስን አማትና በምሽት የብዙዎች ሰዎ ችን መፈወስ በ8-14-16 ላይ ጽፎአል ፤ ማር- 1፡29-34 ፡፡ ማቴዎስ በማር- 1፡35-38 የተጠቀሰውን ማለትም የኢየ ሱስን ገለል ማለት ሳይጽፍ ቢያልፍም እንደገና በቁ- 23 ላይ የማር- 1፡39ን ታሪክ ያነሣል ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ አምላካዊ ተልእኮውን ለማከናወን የተሾመው መሲህ ፤ በገሊላ ውስጥ ሥራውን ለመጀመር ደቀ መዛ ሙርትን ወደርሱ እንዲመጡ ሲጠራቸው ይታያል ፡፡ በገሊላ ወረዳ ስላከናወነው አገልግሎት አጭር ማጠ ቃለያ ተሰጥቶአል ፡፡

12/ የዮሐንስ መታሠር ፤ ኢየሱስ አገልግሎቱን የሚጀምርበት ጊዜ መድረሱን ያመለክታል ፡፡ 13/ ቅፍ ርናሆም "በዛብሎንና በንፍታሌም" ግዛቶች ውስጥ ስትገኝ ናዝሬት ግን ከነዚያ ውጭ ነበረች ፡፡ ቅፍርናሆም "የገዛ ከተማው" ተብላለች ፤ 9፡1 ፡፡ ኢየሱስ ወደዚያ መሄዱም የትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ያሳያል ፡፡ 15-16/ በኢሳ- 9፡1-7 በሰሜን ክፍለ አገር ባሉት በአሶራውያን መንግሥት አስተዳደር ሥር በሚኖሩት ሰዎች ላይ ያለው ጨለማና ሊያበራላቸው ካለው ብርሃን ጋር ተነ ጻጽረዋል ፡፡ ስለዚህ ማንነቱ ሳይታወቅ መሲህ የሆነው ንጉሥ በዚህች በተናቀች አውራጃ ውስጥ ሥራውን ጀመረ ፡፡ ቁ- 17 በመጀመሪያው አገልግሎቱ ክፍል ኢየሱስ ያቀረበውን መልእክት ያጠቃልላል ፡፡ የሁለ ተኛው ክፍል አገልግሎት ማጠቃለያ ደግሞ በ16፡21 ላይ ተሰጥቶአል ፡፡ የኢየሱስና የመጥምቁ ዮሐንስ መል እክቶች አንድ ዓይነት ነበሩ ፤ 3፡2 ፡፡ 18/ ጌታ ከዚህ በፊት ተገናኝቶአቸው ስለነበረ ሐዋርያት የተደረገላ ቸውን ጥሪ ወዲያውኑ ተቀበሉ ፤ ዮሐ- 1፡35-42 ፡፡ 19/ "በኋላዬ ኑ" ፤ ለነርሱ የተሰጠ ትእዛዝ ነበረ ፡፡ 23/ ኢየ ሱስ በገሊላ ውስጥ ስላከናወነው አገልግሎት የተሰጠ ጠቅላላ መግለጫ ነው ፡፡ "እያስተማረና እየሰበከ" ፤ ይህ አገልግሎት በምዕ- 5-7 ተገልጦአል ፤ እንዲሁም የመፈወሱ ተግባር በምዕ- 8-9 ተመልክቶአል ፡፡ ደቀ መዛሙርቱ በነዚህ ሶስት ሥራዎች ውስጥ ተባብረው ይገኛሉ ፤ 9፡35-37 ፡፡ 24/ "ሶርያ" ፤ በተለይ የገሊላ ሰሜናዊ ክፍል ሳይሆን ፤ ገሊላና ይሁዳ ያሉበትን የሮ ምን ክፍለ አገር የሚያመለክት ቃል ሳይሆን አይቀርም ፡፡ በአካባቢው አሕዛብ በመኖራቸው ምክንያት ቅልቅል ሕዝብ ሳይኖርበት እንዳልቀረ ይታመናል ፡፡

## የተራራው ስብከት 5፡1-7፡29

በዚህ ላይ ማቴዎስ የኢየሱስን ትምህርት በሚገባ መሰብሰቡና በዘዴ ማዘጋጀቱ በግልጽ ይታያል ፡፡ የስ ብከቱ አብዛኛው ክፍል የሚገኘው በማቴዎስ ብቻ ቢሆ ንም በሉቃስም አያሌ ጥቅሶች በተለያዩ ሥፍራዎች ይገኛሉ ፡፡ የማቴዎስ ወንጌል በርግጥ ለክርስቲያኖች መመሪያ የሆነ መጽሐፍ ከሆነ ፤ ማቴዎስ የሚያተኩ ረው ኢየሱስ አባባሎቹን የተናገረባቸውን ጊዜያት ሳይሆን በይዘታቸው ላይ መሆኑን መገንዘብ አለብን ፡፡ ኢየሱስ አዲሱ ሙሴ ስለሆነ አዲስ ኦሪት አወጀ ብሎ መናገር የተለመደ ሆኖአል ፤ 5፡21 ፤ 27 ፤ 31-34 ፤ 38 ፤ 43 ፡፡ ይህ አገላለጽ የኦሪትን ሕግ ስለመሻር አሳሳቢ ጥያቄ ቢያነሣና በሕግ ጥቅም ላይ ቢያተኩርም ፤ ሕግን አክብር የሚል አዲስ ትምህርት አያቀርብም ፤ 5፡17-20 ፡፡ ኢየሱስ ያደረገው ንግግር የሚያተኩረው በብሉይ ኪዳን ሕግ ላይ ሳይሆን ፤ አይሁድ ለሕጉ በሰጡት ትር ጉም ላይ ነው ፡፡ ማቴዎስ እግዚአብሔር የሰጠው መመ ሪያ የሰውን ውስጣዊ ሕይወት የሚለውጥና ሰዎችም በፍቅር መታዘዝ የሚገባቸው መሆኑን ፤ እንዲሁም ሰጭው ከሰዎች የሚፈልገው ምን እንደሆነ ኢየሱስ እንዴት አድርጎ እንዳስተማረ ያሳያል ፡፡ ምንም እንኳ የተራራው ስብከት ሥነ ምግባርን የሚያስተምር ቢሆ ንም ከሐዋርያት ስብከት ይዘት ጋር የተያያዘ ነው ፡፡ በተራራው ስብከት ውስጥ የሚገኙትን መመሪያዎች ሊጠብቅ የሚችል ፤ ኢየሱስ የመንግሥተ ሰማያት ተካፋዮች እንዲሆኑ ለሰዎች ሁሉ ላስተላለፈው ጥሪ መልስ የሰጠና በአምላካዊ ጸጋ ብቻ ተመርኩዞ የሚ ኖር ሰው ነው ፡፡ ኢየሱስ ያዘዘው ፍጹምነት ሁለት ዓይ ነት ነው ማለት አይደለም ፤ 5፡48 ፡፡ የተዘረዘሩት መመ

ሪያዎች የሚፈጸሙት ፣ ሰው በክርስቶስ በተገኘ አዲስ ሕይወት ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው ። ይህ አዲስ ሕይወት ትክክለኛውን አመለካከትና ጠባይ ሊሰጥ ይችላል ፤ መመሪያዎቹ በአፍአዊ ድርጊቶች ሳይሆን ፣ ከሰዎች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሲገለጹ ከፍ ያለ ዋጋ አላቸው ። በመመሪያዎቹ ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታዎች መካከል ምንም ልዩነት ሊኖር አይችልም ።

## የደቀ መዝሙር ጠባያት 5፡1-16

ይህ ምንባብ በዚህ ቅርጽ የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። ነገር ግን የቁ- 3 ፣ 5 ፣ 6 ፣ 11 ፣ 12 ትምህርቶች በሉቃስ 6፡20-26 ውስጥ ይገኛሉ ። ሉቃስ የገለጻቸው ወዮታዎች በማቴዎስ ውስጥ አይገኙም ። የተራራው ስብከት በሉቃስ 4፡16-30 ከተገለጸው ከናዝ ሬቱ ስብከት ጋር የሚመስል ሲሆን ፣ የኢየሱስን ትም ህርት ባጭሩ አጠቃልሎ የሚያቀርብ ነው ። ድሆችና ጭቁኖች የተባሉት ሁሉ በመሲህ ደስታ ተሳታፊዎች መሆናቸውን ይገልጻል ። ከቁ- 13-16 ጋር ፣ ማር- 9፡50ን 4፡21-23ን ፣ ሉቃስ 8፡16-18ን ፣ 11፡33ን ፣ 14፡34ን አወዳድሩ ።

1/ "ተራራ" ፣ የትኛው ተራራ እንደሆነ ለይቶ አይ ገልጽም ። ቃሉ የተራራን ጫፍ ሳይሆን ከሕዝቡ በመ ለየት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብሮ ለመሆን የሚችልበ ትን ቦታ ያመለክታል ። ሙሴ ከተራራ ወርዶ ሕግን ከመስጠቱ ድርጊት ጋር አይነጻጸርም ። "በተቀመጠም ጊዜ" ፣ አስተማሪዎች በምኩራብ ተቀምጦ የማስተማር ልማድ ነበራቸው ፤ ሉቃስ 4፡20 ። 3/ አብዛኞቹ ቡራኬ ዎች በብሉይ ኪዳኑ ውስጥ ይገኛሉ ፤ ኢየሱስ እነዚህን ሰብስቦአቸው በማንኛውም ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እንደሚገባቸው አድርጎ አቀረባቸው ። አንዳንድ የጥንት ትርጉሞች ቁ- 5ን ከቁጥር 4 ያስቀድሙታል ። ይህ ትክ ክለኛ ቅደም ተከተል ከሆነ ቡራኬዎቹ በአራት ይከ ፈላሉ ማለት ነው ። ከቁ- 10-12 ያሉት በአንድ ላይ ተጠቃልለው እንደ ስምንተኛ ቡራኬ ይቆጠራሉ ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ "ድሆች" ይባሉ የነ በሩት ደጋግ ሰዎች ነበሩ ፤ መዝ- 68፡29-36 ፣ ኢሳ- 61፡1 ። 4/ "የሚያዝኑ" ፣ መጽናናትን የሚያገኙት ከመሲህ ነው ፤ ኢሳ 61፡2 ። 5/ ይህ ዐረፍተ ነገር ከመዝ- 36፡11 ጋር በጣም ተመሳሳይነት አለው ። "ምድርን" ሲል አገርን ማለቱ ነው ፤ ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተስፋ ከተሰጠችው ከከነዓን ጋር የተያያዘ አሳብ ነው ። 6/ ኢሳ- 55፡1 ። "ጽድቅ" ፣ ትክክለኛ ሥነ ምግባርንና ጠባይን ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ ከኩነኔ ነጻ ሆኖ መገኘትን ያመለክታል ። 7/ ይህንን ቡራኬ በግልጽ የሚያስተጋባ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ አልተገ ኘም ። 8/ "እግዚአብሔርን ያዩታልና" ፣ መዝ- 23፡3 ። 9/ "የሚያስተራርቁ" ፣ ይህ ቃል በግሪክ ጽሑፎች ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጽፎ አይገኝም ። ቃሉ በኢሳ- 27፡5 ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ማድረግን ይገልጻል ።

10/ እነዚህ ቡራኬዎች ስለ መንግሥተ ሰማያት ተስፋ በመስጠት እንደተጀመሩ ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ ተደምድመዋል ። "ጽድቅ" ፣ በዚህ ላይ ትክክለኛ ጠባይን ያመለክታል ፤ ስደተኞች እንደ ብጹዓን ሊቆ ጠሩ የሚችሉት ይህ ጽድቅ በውስጣቸው ሲገኝ ብቻ ነው ። እነዚህ ቡራኬዎች የሰዎችን ተፈጥሮአዊ አስተ ሳሰብ የተገላቢጦሽ ያደርጉታል ፤ ቁ- 10 ይበልጥ ያልተ ጠበቀና ያልተለመደ አስተሳሰብ ያቀርባል ። በቁ- 11-12 ውስጥ ቡራኬ ተስፋፍቶና በተለይ በደቀ መዛ ሙርት ላይ እንደሚመጣ ሆኖ ተገልጾአል ። 11/ ክፉ ተናጋሪው የሚናገረው ፣ ሐሰት እንደሆነ ማቴዎስ አጥ ብቆ ይገልጻል ፤ ሉቃስ 6፡22 ። 12/ "ደስ ይበላችሁ" ፣ ምንም ዓይነት ስደት ሲመጣ ደስ ይበላችሁ ማለት ሳይሆን የመጣባችሁን ስደት በደስታ ተቀበሉት ማለት ነው ። "ዋጋችሁ" ፣ ለራስ ብቻ መደሰቻ ሳይሆን እግዚ አብሔርንም እጅግ ደስ ለማሰኘትና ለማገልገል የሚያ ስችል ኃይል ነው ። መሳደድ ከነቢያት ጋር የመተባበራ ቸው ምልክት ነው ፤ 23፡37 ። 13/ "ጨው" ፣ መበስበስን የሚከለክል በመሆኑ ዋጋ ያለው ነገር ነው ። የአይሁድ መምህራን ጨው የጥበብ ምሳሌ ነው ብለው ይተረጉ ሙታል ፤ ቆላ- 4፡6 ። የደቀ መዝሙር አኗኗርና አነጋ ገር በማኅበረ ሰብ ውስጥ ለውጥ የሚያስከትል እንዲሆን በክፋት ያልተበረዘ መሆን አለበት ። 14/ የአይሁድ መምህራን ፣ "የዓለም ብርሃን" የሚለው ሐረግ እነዚ ህን ስድስት ነገሮች ማለትም እግዚአብሔርን ፣ አዳምን ፣ እሥራኤልን ፣ ሕጉን ፣ ቤተ መቅደሱንና ኢየሩሳሌምን ያመለክታል ብለው ይተረጉሙት ነበር ። አይሁድ ራሳ ቸውን የዓለም ብርሃን አድርገው ሲቆጥሩ ክርስቲያኖች ደግሞ እንደዚሁ የዓለም ብርሃን እንደሆኑ በጳውሎስ መልእክት ተነግሮአል ፤ ሮሜ 2፡19 ፣ ፊል- 2፡15 ። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ትምህርት ኢየሱስ ከሁሉ በላይ የሆነ የዓለም ብርሃን ነው ፤ ዮሐ- 8፡12 ። 16/ ለታይታ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር በሰው ፊት መልካም ሥራ መሥራት ዋጋ አለው ፤ 6፡1 ። "አባታችሁን" ፣ ይህ በኢየሱስ ትምህርት ልዩ ትርጉም ያለው ቃል ነው ። ደቀ መዛሙርቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ፣ ኢየሱስ ራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ግንኙነት ጋር አስተካክሎት አያውቅም ፤ ዮሐ- 20፡17 ።

## የቀድሞውና አዲሱ ሕግ 5፡17-48

ይህ ክፍል አብዛኛው በማቴዎስ ብቻ የሚገኝ ሲሆን ፣ ከቁ- 38-48 ያሉት ጥቅሶች ከሉቃስ 6፡27-36 ፣ ቁ- 18ና 32 ከሉቃስ 16፡17-18 ጋር ተመሳሳይነት አላቸው ። ቁ- 25 በሉቃስ 12፡57-59 ውስጥ ይገኛል ። ኢየሱስ ስለ ሕግና ስለ ነቢያት የነበረውን አመለካከት ከገለጸ በኋላ የተለያዩትን የብሉይ ኪዳን ትእዛዛት በመጥቀስ የራሱን አስተያየት ያክልባቸዋል ፤ የአይሁድ መምህ ራን ስለነርሱ የሰጡአቸውን ትርጉሞች ይተቻል ፤ ቁ- 17-20 ።

5፡17-20 "ሕግ ያልተሻረ መሆኑ" እነዚህ ቁጥሮች ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ያላስተማረችውና በተራራው ስብከት ያልተደገፈው የብሉይ ኪዳን ትምህርት በሙሉ በሥራ ላይ መዋል አለበት የሚለውን አሳብ የሚያቀርቡ ስለሚመስሉ ብዙ ችግር ፈጥረዋል ። ጥቅሶቹ ለመፍታት አስቸጋሪ በመሆናቸው ማቴዎስ አልጻፋቸውም ማለት

አይቻልም ። ቁ- 19 ጳውሎስ ያስተማረውን ነጻነት ለመቃረን ተጽፎአል የሚለው ትርጉም መሠረት ቢስ ነው ። ጥቅሶቹ ለሕገ ወጥነት የተሰጡ ማስጠንቀቂያ ዎች ሲሆኑ በፈሪሳውያን አቋም ላይ የተሰነዘሩት አቃ ቂሮች ይመስላሉ ።

17 "አይምሰላችሁ" ፣ ኢየሱስ በመጀመሪያ የሠራ ቸው ሥራዎች እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ እንዲያስቡ አድርጎአቸው ይሆናል ፤ ማር- 2፡23-28 ። "ለመሻር" ፣ በጠቅላላው በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን የሕግንና የነቢ ያትን አንድነት ማፈራረስ ማለት ይሆናል ። "ልፈጽም እንጂ" ፣ ልታዘዛቸው ማለቱ ሳይሆን ለተነገሩት ትንቢ ቶች ፍጻሜ ልሆን መጣሁ ማለቱ ነው ። በወንጌሎች ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገኘው "ይፈጸም ዘንድ" የሚለው አነጋገር የሚያመለክተው ኢየሱስ ለዚያ ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ነው ። መሲህ በመጣ ጊዜ ሕግና ነቢያት ጥልቅ የሆነ ትርጉማቸውን ለማግ ኘት ችለዋል ። 18/ አንዳንድ ሰዎች ይህ አባባል የፈሪሳ ውያንን አስተሳሰብ በማስመልከት የተነገረ ነው ብለው ያስባሉ ፤ ነገር ግን ይህ ትክክል አይመስልም ። "የውጣ" ዮድ የተባለውን የዕብራይስጥን ፊደል የሚያመለክት ሲሆን "ነጥብ" የሚባለው ደግሞ ባንዳንድ የዕብራይ ስጥ ፊደላት ላይ የሚጨመር ትንሽ ጭረት ሲሆን ይች ላል ፤ ወይም ዋው የተባለውን ፊደል ሳያመለክት አይ ቀርም ። አንዳንዴ እነዚህ ፊደላት ሳይጻፉ ቢቀሩም በቃሉ ስሜት ላይ ምንም ለውጥ አያስከትልም ። "ሰማይና ምድር እስኪያልፍ" ፣ ፓርኮማይ የሚለው የግሪክ ቃል በአሁኑ ዘመን የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን ዘመኑ ወዲያውኑ የማያልፍ መሆኑን ያሳያል ። "ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ" ፣ ግኖማይ የሚለው የግሪኩ ቃል ትርጓሜ ሲሆን በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚያመለክተው የትንቢቶችን መፈጸም ነው ፤ 1፡21 ፣ 21፡4 ፣ 24፡6 ፣ 26፡54 ፣ 56 ። ግኖማይና ፖርኮማይ የሚሉት የግሪክ ቃላት የሚገኙበት 24፡32-35 ከዚህ ጥቅስ ጋር ተቀራራቢ ነው ። "እስኪፈጸም ድረስ" የሚ ለው አባባል ፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ መሲህ የተጠ ቀሰው ማንኛውም ነገር ሁሉ በዚህ ዘመን ሳይፈጸምና ሙሉ ትርጉም ሳያገኝ አንዳች ነገር የማያልፍ መሆኑን የመግለጽ ዝንባሌ አለው ።

ቁ- 17-18 ክርስቶስ የኦሪት ፍጻሜ መሆኑን ሲያብ ራራ ፣ ቁ- 19-20 ግን ስለ ኦሪቱ የተከታዮቹ አስተሳሰብ ምን መሆን እንደሚገባው ይገልጻል ። "የሚሽር" ፣ የኩምራን ገዳም ነዋሪዎችና ሌሎችም በፈሪሳውያን ላይ የሰነዘሩት ክስ ነው ። ባላቸው ተንኰለኛ ውስብስብ ክርክር ሕጉን ቀላል አደረጉት ። "ትእዛዛት" ፣ ብዙ ዎች የብሉይ ኪዳንን ሕግ ያመለክታል ብለው ያስባሉ ፤ ነገር ግን እነዚህ የሚለው ቃል የኦሪት ሕግ እውነተኛ ፍጻሜ የሆነው ክርስቶስ በሚቀጥለው አነጋገር ውስጥ ስለዚህ ሕግ የሚሰጠውን ጥልቅ ትርጉም ሳያመለክት አይቀርም ። 20/ "ካልበለጠ" ፣ በብዛት ሳይሆን በጥ ራት መብለጥ አለበት ። "ጻፎች" የኦሪትን ሕግ የሚያስ ተምሩ ሲሆኑ "ፈሪሳውያን" ደግሞ በተግባር እንፈጽ መዋለን የሚሉቱ ናቸው ። "አትገቡም" ፣ ወደ መንግ ሥተ ሰማያት መግባት የሚቻለው በአኗኗርና በማስተ ማር የሚገለጠውን አዲስ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር በመመሥረት ነው ።

5፡21-26 መግደልና ቁጣ ኢየሱስ መግደል ከቁጣ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስረዳት ብሎ ከአሥርቱ ቃላተ ኦሪት ጠቀሰ ። በተከታዮቹ አምስት አንቀጾች ውስጥ ተመሳሳይ ሁኔታ ይገኛል ። በተደጋጋሚ የተነ ገረው "እኔ ግን እላችኋለሁ" የሚለው ሐረግ ኢየሱስ ከአይሁድ መምህራን ይበልጥ ሥር ነቀል የሆነ የሥነ ምግባር ትምህርት የመስጠት ሥልጣን ያለው መሆ ኑን ይገልጻል ፤ 7፡28ና 29 ።

22/ ያለ ምክንያት የሚለው ቃል የሚገኘው በጥቂት ብራናዎች ውስጥ ብቻ ነው ፤ ስለሆነም በኋላ የተጨመረ ሳይሆን አይቀርም ። የኢየሱስ ትእዛዝ ቁጣን አጥብቆ ይከለክላል ። "ፍርድ" ሲል ሰብዓዊ ፍርድ ቤትን ቢያ መለክትም እንኳ ጥፋቶችና ቅጣቶች ደረጃ በደረጃ ተያ ይዘው መሄዳቸው ግልጽ አይደለም ። "በወንድሙ ላይ"፣ ይህ ጥቅስ ሙሉ በሙሉ የፈሪሳውያን ዘይቤ ሳይሆን አይቀርም ። እንደዚህ ከሆነ ኢየሱስ ሁለት ጊዜ ዘለዓለ ማዊውን ቅጣት ከጊዜያዊው ቅጣት ጋር አነጻጽሮአል ፤ ለምሳሌ ፣ ሰብዓዊ ፍርድና አምላካዊ ፍርድ ፣ ሸንጎና ገሃነም እሳት ናቸው ። ነገር ግን የግሪኩ ግልጽ ትርጉም ይህ አይደለም ። ጨርቃም የሚለው የግሪኩ ሞሬ ፣ ከሃጂ ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተወሰደ ይሆናል ፤ ኤር- 5፡23 ፣ መዝ- 77፡8 ። 23-24/ በሌሎች ላይ ስለ መቆጣት የጀመረውን ንግግር ትቶ በደቀ መዛሙርት መካከል ስላለው ጥል ወደ መናገር ይሄዳል ። "መባህን"፣ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ በአይሁድ ሥርዓት ላይ የሚያ ተኩር ነው ። እርቅ ካልወረደ በስተቀር ሰው ከጎረቤቱ ጋር ያለው ጥል በማስተሰሪያ ቀን በሚያቀርበው መሥ ዋዕት አይሸፈንም ተብሎ ይታሰብ ነበር ። 25-26/ እነዚህ ጥቅሶች ምናልባት በሉቃስ 12፡57 ላይ እንደ ተመለከተው ስለ መጨረሻው ዘመን የተነገሩ ይሆናሉ ። ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረገው እርቅ ከጎረቤት ጋር ከሚደረገው እርቅ ጋር ተያይዞ የሚሄድ ነው ። ከጎረቤ ቶቻችን ጋር ያለን ግንኙነት የተመሠረተው ራሳችን የጸጋ ተቀባዮችና ዘወትር ከእግዚአብሔር ይቅርታ ለመ ቀበል የምንችል ሰዎች መሆናችንን በመረዳት ላይ ነው ፤ 18፡23-35 ።

5፡27-32 ዝሙትና ፍችወት ። እዚህ ላይ ከአሥርቱ ቃላተ ኦሪት የሚገኘውን ትምህርት ያቀርባል ፤ ስለ ፍችም ማብራሪያ ይጨምራል ።

27-28 "አታመንዝር" ፣ ማመንዘር የሌላውን ሰው ሚስት መውሰድ ሲሆን ፣ ንብረቱን ወይም ሕይወቱን እንደመውሰድ የሚቆጠር ነበር ። ምናልባት ትእዛዙ ከጋብቻ ውጭ የሚደረገውን ማንኛውንም ዓይነት ግብረ ሥጋ የሚያጠቃልል ይሆናል ። መመኘትና ማመ ንዘር አንድ ናቸው ። 29-30/ በ18፡7-9 ላይ ይገኛሉ ፤ ማር- 9፡43-48ን አንብቡ ። በሥዕላዊ አገላለጽ "ዓይን" ክፉ አስተሳሰብን የሚያነሣሣ የአካል ክፍል ሲሆን ፣ "እጅ" ደግሞ በሥራ ላይ የሚያውል የአካል ክፍል ነው ። ማንነትን በሙሉ የሚወክለው ሰውነት ፣ የመጨ ረሻውን ጥፋት ወደሚያመለክተው ወደ ገሃነመ እሳት

ውስጥ ከመጣሉ በፊት ካንዳንድ ክፉ ልማዶች መቆጠቡ የተሻለ ነው ። 31/ ይህ ትእዛዝ በዘዳ- 24፡1-4 ተሰጥቶአል ። ተገቢ ገደብ የሌለውን የጋብቻ ፍች ለማስቀረት የተሰጠ መመሪያ ነው ። ኢየሱስ የአይሁድ መምህር ሻማይ ስለ ጋብቻ ያስተማረውን ጥብቅ ትምህርት ደግፎታል ። 32/ "ያለ ዝሙት ምክንያት" ፣ ተቀራራቢ አሳብ በምዕ- 19፡1-9 ውስጥ ይገኛል ፤ ማር- 10፡2-12 ፣ ሉቃስ 16፡18 አንብቡ ። ማቴዎስ ብቻ "ያለ ዝሙት ምክንያት" የሚለውን ጨምሮአል ፤ ሌሎች ወንጌላውያን አባባሉን አውቀውት ይሆናል ፤ ማቴዎስ አሳቡን ግልጽ ለማድረግ እነዚህን ሶስት ቃላት ጨምሮ ጻፈ ። "ዝሙት" ፣ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው ፤ ነገር ግን በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሰፊ ትርጉም ስለ አለው ያለ አግባብ የሚደረገውን የሥጋ ግንኙነት ሁሉ ሳያጠቃልል አይቀርም ። "አመንዝራ ያደርጋታል" ፣ ምናልባት በድጋሚ ስለምታገባ ነው ። በዝሙት ምክንያት የተፈታች ከሆነ ራስዋን ዘማዊ አድርጋለች ። ይህ ፍጹም የሆነ የመንግሥት ሰማያት ሥነ ምግባራዊ መመሪያ ነው ፤ በዚህ ክፍለ ምንባብ ውስጥ ያሉት መመሪያዎች ሁሉ ያንድ አገር መተዳደሪያ ሕግ እንዲሆኑ አልተሰጡም ።

5፡33-37 መሐላና ታማኝነት ። ይህ ከአሥርቱ ቃላት አራት በዘጠነኛው ትእዛዝ ላይ የተመሠረተ ነው ። የሐሰት ምስክርነትን የከለከለው ትእዛዝ መሐላንም ማክበር እንደሚገባ ያሳስባል ፤ ዘኍ- 30፡2 ፣ ዘዳ- 23፡21 ፣ ያዕ- 5፡12 ። 33/ "አትማል" ፣ ለእግዚአብሔር የሚደረገውን መሐላ ላያመለክት ይችላል ። "መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ" ፣ በእግዚአብሔር ስም ለማንም ሰው የተሰጠን መሐላ መፈጸም ይገባዋል ። 34-35/ የአይሁድ መምህራን በነዚህ ነገሮች መሠረት መሐላ መስጠትን በእግዚአብሔር እንደ መማል አድርገው ባይቆጥሩትም ፣ መሐላ የተደረገባቸውን ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር የተማሉ መሐላዎች ናቸው ፤ 23፡16-22 ። 36/ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መሐላቸውን የሚፈጽሙ ለመሆናቸው ዋስትና የማይሆን ነገር ስም እየጠሩ ይምላሉ ። 37/ አንድ ሰው የተናገረውን እንዲፈጽም የሚያስገድደው ቃለ መሐላው ሳይሆን ፣ በቃሉ ብቻ ታማኝ ሆኖ መገኘቱ ነው ። "ከክፉው" ፣ ምናልባት በኃጢአት የተበከለውን ማኅበረሰብ ያመለክት ይሆናል ፤ ሰይጣንንም ሊያመለክት ይችላል ።

5፡38-48 በቀልና ጸጋ ። በሉቃስ 6፡27-36 ውስጥ ተመሳሳይ አሳብ ይገኛል ። ቅጣቱ እንደ ጥፋቱ መጠን ይሁን የሚለው ሕጋዊ መመሪያ ለምድራዊ ማኅበረሰብ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝም እንኳ በመንግሥተ ሰማያት አስተዳደር ውስጥ ሥፍራውን ለጸጋ መልቀቅ አለበት ። 38/ በዘጸ- 21፡22-25 የተመለከተው የበቀል ሥርዓት የተደነገገው ገደብ የለሽ የነበረውን በቀል ለመግታት ታስቦ ነው ፤ ዘፍጥ- 4፡19-24 ። ኢየሱስ በዘጸ- 21፡23 ለተጠቀሰው ሥርዓት ሰፋ ያለ ትርጉም ይሰጠዋል ። 39/ "አትቃወሙ" ፣ በእምነት ምክንያት የመጣውን ክፉ ነገር እንጂ በሌላ ምክንያት የመጣውን አትቃወሙ ማለት አይደለም ። የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የተወሰደበትን ነገር እንዲመለስለት ላለመጠየቅ ብቻ ሳይሆን ጨምሮ ለመስጠትም ዝግጁ መሆን አለበት ። 40/ "እጀ ጠባብህን" ፣ በውስጥ የሚለበስ ልብስ ሲሆን ለመቀሚ ወይም ለቀብድ መያዣ አድርጎ መውሰድ የተፈቀደ ነበረ ። "መጎናጸፊያህን" ፣ ድሀ ሰው በዕዳ ካስያዘው አበዳሪው ማታ ማታ ይመልስለት ነበር ፤ ዘጸ- 22፡26 ፣ ዘዳ- 24፡12 ። 41/ ሮማውያን በቅኝ ግዛታቸው የሚኖሩትን ሮማውያን ያልሆኑትን ሁለት ኪሎሜትር የሚሆን ርቀት ሸክም እንዲሸከሙ በሕግ ሊያስገድዱአቸው ይችሉ ነበር ፤ 27፡32 ። 42/ ምንም እንኳ ደቀ መዝሙር የተለመነውን ሁሉ እንዲሰጥ ባይታዘዝም የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑን ይገልጻል ፤ የሐዋ- 3፡6 ። 43/ "ባልንጀራህን ውደድ" ፣ ሕጉ ባልንጀራህን ብቻ ውደድ ብሎ ያዛል ፤ ዘሌ- 19፡18 ። ጠባብ አሳብ የነበራቸው ቡድኖች ይህንን ትእዛዝ በማራዘም የኛ ወገን ያልሆኑትን ሰዎች እንድንጠላ ተፈቅዶልናል ይሉ ነበር ። 44/ የኦሪት ሕግ ግን ለጠላት ቸርነት ማድረግን ያዝዛል ፤ ዘጸ- 23፡4ና 5 ። ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚለው ትእዛዝ አስቸጋሪ ነው ። እነርሱን መውደድና ስለነርሱ መጸለይ ዓይነተኛ ርምጃ ነው ። 45/ ይህ ዓይነት አመለካከት ሊፈጠር የሚችለው ከእግዚአብሔር ጋር በሚደረገው የሕይወት ግንኙነት ነው ፤ 5፡9 ። እግዚአብሔር በቸርነቱ ለሰው ልጅ በሚሰጠው ጸጋ አድልዎ አያደርግም ። 46-47/ "ምን ዋጋ አላችሁ ?" ምን ስላደረጋችሁ ዋጋ ትጠይቃላችሁ ? ማለት ነው ፤ በቁ- 47 ከሚገኘው "ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ ?" ከሚለው አገላለጽ ጋር የሚመሳሰል ነው ። ደቀ መዝሙር ከተጠየቀው በላይ አትረፍርፎ በሚሰጥ በእግዚአብሔር አሰጣጥ መሠረት ሊሰጥ ይገባዋል ። በሉቃስ 6፡32-34 ላይ የሚገኙት ፖየ ካርስ የሚሉት የግሪክ ቃላት ምን ዓይነት ቸርነት ታሳያላችሁ ተብለው ሊተረጐሙ ይችላሉ ። ካሁኑ ጥቅስ ጋር ማነጻጸር ጠቃሚ ነው ። 48/ "ፍጹማን ሁኑ" ፣ ሰዎች እንዲኖሩቸው ኢየሱስ የፈለገው ፍጹምነት የሚመነጨው የሰውን አመለካከቶች ከሚለውጠው ከዚህ ግንኙነት ነው ። ሰዎች ይህን ፍጹምነት ሊደርሱበት የማይችሉ ቢሆንም ያለማቋረጥ ዓላማቸው ሊያደርጉት ያስፈልጋል ።

## ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት 6፡1-18

5፡21-48 ስለ ጸፎች ሲናገር ይኸኛው ክፍል ደግሞ ስለ ፈሪሳውያን ሥራ ይናገራል ። ከቁ- 9-13 በቀር 6፡1-18 የሚገኘው በማቴዎስ ብቻ ነው ፤ የጌታ ጸሎት ማለት ከቁ- 9-13 በሉቃስ 11፡2-4 ውስጥ ይገኛል ። ቁ- 1 ዋጋ የሚለውን ቃል በመውሰድ አሳቡን ቀደም ሲል ከተሰጠው ትምህርት ጋር ያገናኘዋል ፤ በሥርዓት አከባበርም ሆነ በሥነ ምግባር ረገድ ቁም ነገሩ የአድራጊው ዓላማ መሆኑን ያሳያል ። ሰው እነዚህን ሥርዓቶች በልጅነት መንፈስ መፈጸም እንደሚገባው ተገልጧል ። ቁ- 2-4 በሰዎች በኩል ስላለው ግዴታ ማለት ምጽዋት ስለ መስጠት ይናገራል ። ቁ- 5-15 በእግዚአብሔር በኩል ስላለው ግዴታ ማለት ስለ ጸሎት ሲያስተምር ቁ- 16-18 ደግሞ በራስ ላይ ስለሚደረገው ቁጥጥር ማለት ስለ ጾም ያስረዳል ።

2/ "ምጽዋት" ፣ ብዙ አይሁድ ምጽዋት ሲሰጡ የኃጢአት ማስተሰሪያ ነው ብለው ያስቡ ነበር ። "ግብዞች" ፣ በግሪክ ተዋንያን ማለት ነው ። ፈጽሞ አታላዮች ነበሩ ማለት ሳይሆን ፣ ሃይማኖት ምን ማለት እንደሆነ ስላላወቁ ሥራቸው አብዛኛውን ጊዜ ምንም ትክክል ቢሆንም ውስጣዊ ከሆነው ከማናቸውም ዓይነት መንፈሳዊ ሐቅ ጋር ያልተያያዘም ነበር ። ይህን የመሰለ አቋም ያላቸው ሰዎች "ዋጋቸውን ተቀብለዋል" ። ፍላጎታቸው የሆነውን የሰውን ምስጋና ለማግኘት ችለዋል ። ዋጋቸውን በሙሉ ከሰዎች ስለ ተቀበሉ ከእግዚአብሔር የሚጠብቁት ዋጋ ሊኖራቸው አይችልም ። 4/ በሰው ያልታየ ምጽዋት በእግዚአብሔር ዘንድ የታየ ነው ። እርሱ ብቻ አስደሳች የሆነውን ዋጋ ይከፍላል ። በዚህ ቁጥር እንዲሁም በቁጥር 6ና በቁጥር 18 ላይ "በግልጽ" የሚለው ቃል በአብዛኞቹ ጥንታዊ ብራናዎች ውስጥ አይገኝም ። 5-6/ እነዚህ መመሪያዎች የተሰጡት ለታይታ ስለሚደረገው ጸሎት ነው ። ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ሆኖ ሳለ በጉልህ ለሰው እንዲታይ ማድረጉ በጣም የሚያስወቅስ ነው ። 7-8/ "በመናገራቸው ብዛት" ፣ ብዙ ቃላት ከመናገራቸው የተነሣ መልስ የሚያገኙ መስሎአቸው ነበር ። ጸሎት በውነት የዚህ ዓይነት ሳይሆን ከእግዚአብሔር አብ ጋር በሚደረግ ግንኙነት የሚፈልቅ ነገር ነው ። የእግዚአብሔር አስቀድሞ የማወቅ ችሎታ ፣ የመተማመንንና የምሥጋናን ስሜት ጥልቅ የሚያደርገውን የግል ጸሎት የማቅረብን ፍላጎት አያጠፋም ።

9-13/ የጌታችን ጸሎት በሉቃስ ወንጌል ደግሞ ተጽፎ ይገኛል ። በሁለት ልዩ ጊዜያት ኢየሱስ ቃላትን በመቀያየር ይህንን ጸሎት ሳያስተምር አልቀረም ። ነገር ግን አስተምሮት የነበረው አንድ ጊዜ ብቻ ከሆነ ማቴዎስ ትርጉሙን የበለጠ ሰፋ ለማድረግ አስፋፍቶ ጽፎታል ለማለት ይቻላል ። ቁጥር 13 ማቴዎስ የጻፈው ሳይሆን በጥንት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ የተለመደ በመሆኑ ከጸሎቱ ጋር ተያይዞአል ። በአይሁድ ጽሑፎች ውስጥ ከኢየሱስ ትምህርት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ብዙ አሳቦች እንደሚገኙ ሁሉ ፣ በጸሎቱ ውስጥ ከሚገኙት አባባሎች ደግሞ ብዙዎቹ በአይሁድ ጽሑፎች ውስጥ ይገኛሉ ። ጸሎቱ እጅግ በጣም ጠቃሚ ሊሆን የቻለው ፣ አጭር ሆኖ ሳለ በውስጥ የእግዚአብሔርን አባትነትና የሚመጣውንም መንግሥት በጉልህ በመግለጹ ነው ። ጸሎቱ በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ክብር ከገለጠ በኋላ ሰብዓዊ ፍላጎትን ስለማርካት ያወሳል ።

9/ "እንዲህ" ፣ እንዲደገም የተሰጠ ከመሆኑም በላይ ለማንኛውም ጸሎት ምሳሌ መሆን ይችላል ፤ ሉቃስ 11፡2 ። "አባታችን ሆይ" ፣ ሉቃስ አባት ብሎ ጽፎአል ፤ ሰማያዊ አባት የሚለው አነጋገር በማቴዎስ ተደጋግሞ ይገኛል ፤ 5፡48 ፣ 6፡14 ፣ 26 ፣ 32 ፣ 15፡13 ፣ 18፡35 ፣ 23፡9 ። ማቴዎስ "አባ" በሚለው በአራም ሰዎች ቃል መጠቀሙ የኢየሱስ ትምህርት የደቀ መዛሙርቱን አነጋገር የቱን ያህል እንደለወጠው ያሳያል ፤ ማር- 14፡36 ፣ ሮሜ 8፡15 ፣ ገላ- 4፡6 ። "ስምህ ይቀደስ" ፣ በአይሁድ ጸሎት ውስጥ አክብሮትን ለመግለጽ በተደራጊ ግሥ መጠቀም የተለመደ ነበረ ። መቀደስ የእግዚአብሔር ቅዱስነት መገለጡንና መታወቁን ያመለክታል ። 10/ "መንግሥትህ ትምጣ" ፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ግዛት ወደ ሰው ሕይወት ውስጥ ትምጣ ማለት ነው ። የኢየሱስ አገልግሎት በተጀመረ ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባ ነበር ፤ 4፡17 ። የመ ጨረሻ ፍጻሜ እስኪያገኝ ድረስ በአገልግሎቱ ዘመን የፈጸመው ነገር ሁሉ የመንግሥቱን መምጣት የሚያቀርብ ነበር ። "ፈቃድህ በሰማይ" ፣ አባባሉ በማቴዎስ ብቻ የሚገኝ ሲሆን የቀደመውን ዐረፍተ ነገር የሚተረጉም ይመስላል ። ጸሎቱ የሚጠይቀው ሥነ ምግባራዊ መልስ ባሁኑ ጊዜ የሚፈለግ ቢሆንም ፣ ሙሉ ፍጻሜውን የሚያገኘው እግዚአብሔር በመጨረሻ ዘመን በሚያከናውነው ሥራ ነው ። 11/ "ዛሬ" ፣ ሉቃስ በቀን በቀን ይላል ። ዛሬ ተብሎ የተተረጐመው እፕኡሲዮን የሚለው የግሪኩ ቃል ብዙ ጊዜ የማይሠራበት ከመሆኑ በላይ አያሌ ምንጮች ሊኖሩት ይችላል ። በይበልጥ ግን "ለነገ" የሚል ትርጉም አለው ። አስተሳሰቡ በዘፀ- 16፡21-29 ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል ። የዚህ ዓይነት ጸሎት ለነገ ላለመጨነቅ መልካም ምክንያት ይሆናል ፤ ቁ- 34 ። ነገር ግን ከሞላ ጎደል በእርግጥ የበጉን ሠርግ እራት ያንጸባርቃል ፤ ራዕይ 19፡9 ። ለጌታ እራት የሚቀርበው ኅብስት ለዚሁ ግብዣ እንደተሰጠ ስጦታና ቃል ኪዳን ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል ። 12/ "በደላችንን" ፣ አይሁድ ኃጢአታቸውን እንደ ዕዳ ይቆጥሩት ነበር ። ኃጢአት የሚለው ቃል ሉቃስ በጻፈው ጸሎት ውስጥም ይገኛል ። 13/ ወደ መጨረሻው ፈተና አታግባን የሚል ትርጉም ያለው ይመስላል ፤ 24፡22 ። "ከክፉ አድነን እንጂ" ፣ ሐረጉ በሉቃስ ውስጥ ባይገኝም የቀድሞውን አባባል የሚያብራራ ይመስላል ። "ክፉ" የሚለው ቃል ሰይጣንን ያመለክት ይሆናል ። ሰዎች በተለይ በክህደት የሚፈተኑት በመጨረሻው የፈተና ሰዓት ነው ፤ 24፡9-13 ።

14-15/ ይቅርታን ስለማድረግ አጥብቀው ያስረዳሉ ፤ 18፡23-35 ። ሰው ለሰው የሚያደርገው ይቅርታ ፣ እግዚአብሔር ለሚያደርገው ይቅርታ መሠረት አይደለም ። ነገር ግን ይቅርታ ፣ አድራጊው በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ ለመኖሩ አንድ ማስረጃ ነው ፤ 5፡43-48 ። 16/ ይህ ስለ ጾም የተሰጠው መመሪያ ጾምን ለታይታ ከማድረግ መቆጠብ እንደሚያስፈልግና መንፈሳዊ ዋጋም እንዳለው ያሳያል ። ሥርዓቱን ፈጽሞ ለማፍረስ ወይም እንደ ጥብቅ ሕግ አድርጎ ለማጽናት የተነገረ አይደለም ። በሁለተኛው ምእት ዓመት የነበረው አንድ ሰው የነጥቡን ትርጉም ፈጽሞ ባለመረዳት ፣— ከግብዞች ጋር አትጹሙ ፣ እነርሱ ሰኞና ሐሙስን ይጾማሉና እናንተ ግን ረቡዕና ዓርብን ጹሙ ብሎ ጽፎአል ።

## ቁሳቁሳዊ ሀብቶች 6፡19-34

ይህ ክፍል ከሉቃስ 11፡34-36 ፣ 12፡22-34 ፣ 16፡13 ጋር በጣም ይመሳሰላል ። ክፍሉ ስለ መልካም ስም መናገር ይጀምርና ስለ ቁሳቁሳዊ ሀብቶች ከጠቀሰ በኋላ ትክክለኛ ዓላማ (ቁ- 19-24) እና እምነት (ቁ- 25-34 ) አስፈላጊ መሆናቸውን ያሳያል ።

19/ "ዝገት" ፣ የዚህ ቃል ትርጉም መብላት ማለት ሲሆን አንዳንድ ጊዜ በግሪኩ ትል ተብሎ ተተርጉሞ

አል ። ሀብት በፈሪሳውያን አስተሳሰብ የእሪትን ሕግ የመጠበቅ ሽልማት ነበረ ። 20/ የሚሰጠው ዋጋ መን ፈሳዊ ከሆነ ራስ ወዳድነት ሊሆን አይችልም ። 21/ ይህ ልብን የሚመረምር ሐቅ ነው ። 22/ "ጤናማ" ፣ ሃፕሉስ የሚለው የግሪኩ ቃል ለጋስ የሚል ትርጉም ይኖረው ይሆናል ፤ ቃሉ በሮሜ 12፥8 ፣ 2 ቆሮ-8 ፥ 2 ፤ 9፥11ና 13 ውስጥ ይገኛል።ሰፋ ያለ ወይም ለጋስ አስተያ የት ማለት በመንፈሳዊ ረገድ የበለጠ ብርሃን ማግኘት ማለት ነው ። 23/ "ታማሚ ብትሆን" ፤ በግሪኩ ፕኖ ሮስ ንፉግ ማለት ሲሆን የጠበበ አስተያየት ተቃራኒ ውጤትን ማለትም አነስተኛ ብርሃን ማግኘትን ያሳያል ። 24/ "ገንዘብ" ፣በማንኛውም ሁኔታ የሚገኝን ሀብት የሚያመለክት ቃል ነው ። የኢየሱስ ጥያቄ የሰው ሕይ ወት ሙሉ በሙሉ ለርሱ የተገዛ መሆን እንዳለበት ያመ ለክታል ።

25/ "ስለ ነፍሳችሁና ስለ ሰውነታችሁ" ፣ ሱኬ የሚ ለው የግሪክ ቃል ብዙ ጊዜ ነፍስ ተብሎ ቢተረጉምም በዚህ ውስጥ ግን ሕይወት የሚል ትርጉም አለው ። ሕይወትና ሰውነት "ከምግብና ከልብስ" ይበልጥ ዋጋ አላቸው ። 26/ አነስተኛ ፍጥረታት ምንም ሳይጨነቁ ምግባቸውን ከእግዚአብሔር ያገኛሉ ። እግዚአብሔር ለሰውም ከዚህ ይበልጥ ሊያደርግለት ይችላል ። 28-30/ እግዚአብሔር ስሜት ለሌለው ፍጥረት የሚያምረውን ካዘጋጀለት ለሰዎችም ከዚያ ይበልጥ ያዘጋጅላቸዋል ። 31/ በዚህ ላይ ኢየሱስ ያወገዘው ፣ ታማኝ አገልጋይ ነትንና አስቀድሞ ማሰናዳትን ሳይሆን መጨነቅን ነው ። 32/ "አሕዛብ" የሚል ቃል እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ በግለሰብ ደረጃ የሚወድና የሚንከባከብ መሆኑን የማ ያውቁትን ሰዎች ይጠቁማል ። 33/ ሰው ለኑሮው ቁሳቁ ሳዊ ሀብት አያስፈልገውም ማለት አይደለም ፤ ነገር ግን ሊያስቀድመው የሚገባው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ መፈጸምን ሊሆን ይገባል ፤ ቁ- 10 ። ቁ- 34 ሁለት የተጣመሩ ምሳሌዎች የያዘ ሳይሆን አይቀርም ። ይህ አባባል ውስጠ ፌዝ የሆነ ንግግር ሳይኖርበት አይቀ ርም ። የሚገኘውም በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ።

## ሰው ለሰውና ለእግዚአብሔር ሊኖረው የሚገባው አመለካከት 7፡1-12

ይህ ክፍል ከሉቃስ 6፥31 ፣ 37-42ና 11፥9-13 ጋር በሰፊው ይመሳሰላል ። የሰዎችን ባሕርይ በትክክል ለመገምገም እንዴት እንደሚቻል መግለጽ ይጀምራል ፤ ቁ- 1-6 ። ከዚያ በኋላ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ትክ ክለኛ ገለጻ ይሰጣል ፤ ቁ- 7-11 ። የክርስቲያኖችን ዓይ ነተኛ መመሪያ በማሳየት ይፈጽማል ፤ ቁ- 12 ።

1/ በሌሎች ሰዎች ላይ ፈራጅ ሆኖ መገኘት አምላካዊ ፍርድን ያመጣል ፤ 6፥15 ። 2/ ሰዎች በእግዚአብሔር የሚያስፈርድባቸውን መከነኛ ሊያዘጋጁ ይችላሉ ። 3/ "በጉድፍና በምሰሶ" መሃከል የተደረገው ማነጻጸር አስቂኝ መሆን አለበት ። 4-5/ ስሕተታቸውን እንዲ ያርሙ አትርዳቸው ወይም ሌሎችን መርዳት አስፈላጊ አይደለም አልተባለም ፤ ገላ- 6፥1-5 ። ነገር ግን ሰው ራሱን ቢመረምርና አካሄዱን ቢያሳምር አማካሪ ነኝ ብሎ ከመኩራት ያግደዋል ። 6/ ይህ ዘይቤ በማቴዎስ ብቻ የሚገኝ ሲሆን መንፈሳዊ ምስጢሮችን ለይተን የማስተማር ግዴታ እንዳለብን ያሳስባል ። "ውሾችና እሪያዎች" ፣ ስድብ ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው ። ላለመስጠትና ላለመናገር ጊዜ አለ ፤ ሉቃስ 23፥9 አንብቡ ። "የተቀደሰው" ፣ ዲዳቄ የተባለው ጥንታዊ መጽሐፍ የጌታ እራትን በማስመል ከት ተርጉሞታል ። 7-8/ እግዚአብሔር ምንም እንኳ እነርሱ በሚጠይቁት መንገድ ጥያቄያቸውን ባይመል ሰውም የሕዝቡን ልመና የሚሰማ መሆኑ የታመነ ተስፋ ተሰጥቷል ፤ 5፥42 ። 9-10/ በሌላ በኩል ደግሞ ጠቃሚ ነገር በሚጠየቅበት ጊዜ የማይጠቅም ወይም አደገኛ የሆነ ነገር አይሰጥም ። 11/ "ክፉዎች ስትሆኑ" ፣ ምንም ንፉጎች ብትሆኑ እንደማለት ነው ፤ 6፥23 ። ምንም ንፉግ የሆነ ሰብዓዊ ጠባይ ቢኖረንም ለልጆቻ ችን የሚያስፈልጋቸውን እንሰጣቸዋለን ። ቸሩና ሁሉን ማድረግ የሚችለው አምላክ ለልጆቹ መልካምን ነገር ይበልጥ ይሰጣቸዋል ። ከሁሉ በላይ የሆነው መልካም ነገር መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በሉቃስ 11፥13 ውስጥ ተጠቅሶ ይታያል ። 12/ ይህ የክርስቲያኖች ዓይነተኛ መመሪያ በአይሁድ መጽሐፍ ውስጥ ፣— በናንተ ላይ እንዲደረግ የማትፈልጉትን ነገር በሌሎች ላይ አታድ ርጉት ተብሎ ተጽፎአል ። በአዎንታ የተገለጸው የኢ የሱስ ትእዛዝ ግን ሰፋ ያለ ትርጉም አለው ። እዚህ ላይ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ማጠቃለያ ነው ብሎ አቅርቦ ታል ።

## የእግዚአብሔር መንግሥት ትእዛዞች 7፡13-29

ይህ ክፍለ ምንባብ ከሞላ ጎደል በማቴዎስ ብቻ የሚ ገኝ ሲሆን አንዳንድ ተመሳሳይ ቃላት በሉቃስ 6፥43-49 ውስጥ ይገኛሉ ። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግ ባት ጥሪ ተደርጎአል ፤ ቁ- 13-14 ። ሐሰተኛ ነቢያት አደገኞች መሆናቸው ተነግሯል ፤ ቁ- 15-23 ። ደግሞም ለክርስቶስ ቃል የመታዘዝ አስፈላጊነት ተገልጾአል ፤ ቁ- 24-27 ። የተራራው ስብከት በሰዎች ዘንድ ምን ዓይነት ውጤት እንዳስከተለ በመግለጽ ተደምድሞ አል ፤ ቁ- 28-29 ።

13-14/ በሉቃስ 13፥22-30 ላይ ያለው ተመሳሳይ አባባል ምናልባት በሌላ ጊዜ የተነገረ ይሆናል ። ሁለት መንገዶች መኖራቸውን የሚገልጽ አነጋገር በኤር- 21፥8 ፣ መዝ- 1፥6 ፣ ምሳሌ 14፥12 ውስጥ ይገኛል ። አንዳንድ ብራናዎች በር የሚለውን ቃል ሁለቴ አያጠ ቅሱትም ፤ ሆኖም ሳይገደፍ ቢነበብ ጥሩ ነው ። ሁለት ዓይነት በሮችና ሁለት ዓይነት መንገዶች አሉ ። ሰፊው በር ወደሰፊው ጎዳና የሚመራ ሲሆን በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅ ይሆናል ። ጠባቡ በር ወደ ቀጭኑ መንገድ የሚመራ ሲሆን የሚመርጡትም ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው ። ወደ ጥፋትና ወደ ሕይወት የመግባት ውሳኔ የተመሠረተው ወንጌልን ባለመቀበልና በመቀበል ላይ ነው ። 15/ ሐሰተኞች ነቢያት በዘመናት ሁሉ ችግር ሲፈጥሩ የኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ፣ ሰዎች ከሕይወትና ከሞት አንዱን እንዳይመርጡ ጥያቄውን ይበርዙ ነበር ፤

24፡11ና 24 ፣ ኤር- 6፡13-15 ። 16/ ቃላት የሚፈተኑበ ትና ጠባይ በውነት የሚታወቅበት የሰው ሥራ ነው ። 17/ ከፍርድ የተያያዙ የዛፍና የፍሬ ምሳሌዎች በ3፡10 12፡33-35ና 15፡13 ይገኛሉ ። 21/ ያለ ተግባር ቃላት፣ ዋጋ እንደሌላቸው እንደገና ተገልጧል ። 22-23/ በፍ ርድ "ቀን" በስምህ ሠርተናል ፤ የመንፈስን ስጦታዎች ተቀብለናል ብለው ቢናገሩም የማይጠቅማቸው ይሆ ናል ። የራሱ ወገን አድርጎ በሚቆጥራቸው ሰዎችና የሕገ ወጥ ሥራ ፈጻሚዎች አድርጎ በሚመለከታቸው ሰዎች መካከል ያለው መለያ የሚሰጠው ፍርድ ነው ። በፍርድ ጊዜ የክርስቶስ መብት የቱን ያህል እንደሆነ ባስገራሚ ሁኔታ ተገልጾአል ። 24-27/ ቀደም ብሎ ድርጊት የሌለው ቃላት እንደተነቀፈ ሁሉ አሁንም ሥራ የሌለው መስማት ተወግዞአል ። ሁለቱ የደኅን ነትና የጥፋት መንገዶች በጉልህ ተጠቁመው ይታያሉ ። እነዚህ የተጣመሩ ማሳሰቢያዎችና ማስጠንቀቂያዎች ለተራራው ስብከት ተስማሚ የሆኑ ማጠቃለያ ናቸው ፤ ዘሌ- 26 ፣ ዘዳግ- 28 ። 28/ ይህ የመደምደሚያ አነጋገር በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በሚገኙት በአምስቱም ንግ ግሮች መጨረሻ ላይ ይገኛል ። 29/ ኢየሱስ "በሥልጣን" ሊያስተምራቸው የቻለው በመጀመሪያ ደረጃ አምላክ በመሆኑ ቀጥሎ የብሉይ ኪዳንን ትምህርት የሰውን ልብ በሚነካ አዲስና አጠቃላይ በሆነ ዘዴ በማቅረቡ ነው ።

## የክርስቶስ ሥራዎች 8፡1-9፡34

ማቴዎስ ክርስቶስ ያስተማራቸውን ዋና ዋና ትምህ ርቶች ሰብስቦ ከጨረሰ በኋላ የክርስቶስን ሥራዎች ወደ መሰብሰብ ይዛወራል ። በዚህኛው የወንጌሉ ክፍል ውስጥ ካሉት አሥራ ሶስት አንቀጾች መሃከል አሥሩ ከማርቆስ ጋር ይመሳሰላሉ ። 8፡5-13 ፣ 18-22ና 9፡32-34 በማርቆስ ውስጥ የማይገኙ ቢሆኑም በሉቃስ ውስጥ ይገኛሉ ። እነዚህም ጥቅሶች ማቴዎስ ብቻ ከመዘገባቸው በስብከቱ ውስጥ ከሚገኙት ከኢየሱስ ቃላት ጋር ሲነ ጻጸሩ ፣ ማቴዎስና ማርቆስ ስለ ኢየሱስ ድርጊቶች በዝ ርዝር የጻፉአቸው ዘገባዎች የቱን ያህል ተቀራራቢ እንደ ነበሩ ያሳያሉ ። በማርቆስ ወንጌል ከ1 እስከ 10 ድረስ ባሉት ምዕራፎች ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ውስጥ ይገኛሉ ። በሶስት መደብ የተከፈሉ ዘጠኝ ከፍተኛ ሥራ ዎች አሉ ፤ ሆኖም ሁሉም ስለ ተአምር የሚናገሩ አይ ደሉም ። ኢየሱስን እከተልሃለሁ ከሚለው ካንድ ጸሐፊ ተስፋ ቃል ቀጥሎ የለምጻሙን መንጻት ፣ የመቶ አለቃ ውን ሎሌና የጴጥሮስን አማት መፈወስ የሚገልጹት ታሪኮች ተዘርዝረዋል ። ነፋሱን ፀጥ ማድረጉ ፣ አጋንን ትን ማስወጣቱና ሽባውን ማዳኑ ከተገለጹ በኋላ የማ ቴዎስ መጠራትና የጾሞች ትምህርት ተጽፈው ይገኛሉ ። የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ከሞት ማስነሣት ፣ ደም የሚፈ ሳትን ሴት ማዳኑን እንዲሁም ዕውሩንና ደንቆሮውን ሰው መፈወሱን አስረድቶ ሲያበቃ ወደ ፊት ስለ ብዔል ዜቡል ስለሚነሣው ክርክር በማስጠንቀቅ ይጨርሳል። ማቴዎስ በ8፡28 ላይ ሌላ ሰው በመጨመሩና በዚህ ክፍለ ምንባብ ውስጥ ሁለተኛውን ዕውር ሰው መጥቀሱ ብዙ ጥያቄን አስከትሎአል ፣ 9፡27 ፣ ማር -5፡2ና 10፡46 ። ይህም ሲሆን የቻለው ምናልባት ማቴዎስ ሌላ መረጃ ዎች ስለነበሩት ወይም የኢየሱስን ቃላት አቀነባብሮ እንደጻፈ ሁሉ ተግባራቱንም ሰብስቦ አጠር ባለ ሁኔታ ስለመዘገባቸው ይሆናል ። እንደዚሁም ኢየሱስ እነዚ ህን የመፈወስ ሥራዎች ከአንድ ጊዜ በላይ የፈጸማቸው መሆኑን ማመልከቱ ሲሆን ይችላል ፤ ወይም እርሱ ያልጠቀሰውን ማለት በማር- 1፡21-28 ፣ 8፡22-26 የተ ጸፈውን ያመለክት ይሆናል ። ቢሆንም እነዚህ ምክን ያቶች ባሁኑ ታሪክ ውስጥ ሁለት ዕውራን የጠቀሰበትን ምክንያት ላያስረዱ ይችላሉ ። በ20፡29-34 ላይ ሁለት ሰዎች መፈወሳቸው የተገለጸው ምናልባት የሁለት ሰዎች ምስክርነት ስላስፈለገ ይሆናል ፤ ዘዳግ- 19፡15 ።

## የመፈወስ ሥራ 8፡1-17

ይህ ክፍል የመጀመሪያዎቹን ሶስት ተአምራት አጠ ቃልሎ ይዞአል ፤ እነርሱም ፡— 1/ ለምጻሙን ማንጻቱ ፤ ቁ- 1-4 ፣ ማር- 1፡40-44 ፣ ሉቃስ 5፡12-14 ፣ 2/ የመቶ አለቃውን ሎሌ መፈወሱ ፣ ቁ- 5-13 ፣ ሉቃስ 7፡1-10 ፣ 3/ የጴጥሮስን አማት ማዳኑ ናቸው ፤ ቁ- 14-17 ፣ ማር- 1፡29-31 ፣ ሉቃስ 4፡38ና 39 ። በቁ- 17 ላይ ከትንቢተ ኢሳይያስ በመጥቀስና የተሠራውን ጠቅላላ የመፈወስ ሥራ በማጠቃለል ይዘጋዋል ፤ ቁ- 16 ፣ ማር- 1፡32-34 ፣ ሉቃስ 4፡40ና 41 ።

1/ ከተራራው ስብከት ጋር የተያያዘ ነው ፤ ነገር ግን የመፈወስ ሥራዎቹ ቅደም ተከተል በትክክል ከትምህ ርቱ ጋር ይሄዳል ማለት አይደለም ። "የለምጻሙ" መንጻት ኢየሱስ ስለ ብሉይ ኪዳን ሥርዓት ያለውን አሳብ ስለሚገልጽ በመጀመሪያ የተፈጸመ ሲሆን ይች ላል ። 3/ ማርቆስ አዘኖለት የሚለውን ቃል ማቴዎስና ሉቃስ አልጻፉትም ። የግል ፍላጎትና የእምነት መልሶች የሆኑቱ የመፈወሱ ተአምራት ውጤቶች ወዲያውኑ የሚታዩ ናቸው ። 4/ ኢየሱስ ለሕዝብ ጤና ጠቃሚ የሆነውን መመሪያና እግዚአብሔርን ማመስገን ተገቢ መሆኑን የሚያስታውሰውን ሕግ ያከብራል ፤ ዘሌ 14፡ 2-32 ። የአሪት ሕግ የመፈወሱን ሥራ ለመፈጸም ኃይል አልነበረውም ። "ለነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክ ተው ሕዝቡን ከሆነ ፣ ኢየሱስ የሕግ ተቃዋሚ አለመ ሆኑን ለማሳየት ያደረገው ነው ፤ ወይም የሚያመለክተው ካህናትን ከሆነ ፣ መፈወሱን እንዲመሰክሩለት ያደረገው ነው ።

5/ በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለሚገኘው የንግግር መለ ዋወጥ ማቴዎስና ሉቃስ ይስማሙበታል ፤ ነገር ግን እያንዳንዳቸው ድርጊቱን የጻፉት በራሳቸው አነጋገር ነው ። 8-9/ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚገኘው መቶ አለቃ በሠራዊቱ ውስጥ ካለው ሥልጣን ጋር በማነ ጻጸር በትህትናና በእምነት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሩቅ የማ ዳን ኃይል እንዳለው ተናገረ ። 10/ በዚህ መንገድ የክ ርስቶስን ሥልጣን በመጀመሪያ ሊያውቅ የቻለው ከአ ሕዛብ ወገን የሆነ ሰው ነው ። 11-12/ ከሉቃስ 13፡ 28-30 ጋር ይመሳሰላል ። "በመንግሥተ ሰማያት ይቀ መጣሉ" ፣ በመሲሀዊው ግብዣ ላይ ማለቱ ነው ፤ ራዕይ 19፡9 ። "አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ" የአይሁድ አባ

ቶች ናቸው ። "የመንግሥት ልጆች" ፥ በእምነትና በተግባር ሳይሆን በተፈጥሮ ዘራቸውም ላይ ስለሚተማመኑ በስም ብቻ የመንግሥት ልጆች ናቸው ።

16/ ማቴዎስ በማርቆስ ውስጥ ያለውን የቃላት አገባብ አዛውሮ በመጠቀም ፥ "ብዙዎችን" እንደመጡና ኢየሱስ "ሁሉንም" እንዳዳናቸው አጉልቶ ያስረዳል ። 17/ "የተባለው ይፈጸም ዘንድ" የሚለው ከኢሳ- 53፡4 የተጠቀሰ ነው ። ምንም እንኳ ብዙዎቹ በመንፈሳዊ ትርጉም ቢወስዱትም ፥ አንዳንድ የአይሁድ መምህራን ቃል በቃል ይተረጉሙታል ። አዲስ ኪዳን በሞላው መከራ የሚቀበለው የእግዚአብሔር አገልጋይ የክርስቶስን መሥዋዕታዊ ሞት የሚያመለክት በመሆኑ ይስማማል ። የተጠቀሱት ቃላት ከዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ናቸው ። እነዚህ የመፈወሱ ተግባራት የርኅራኄ ሥራዎች ብቻ ሳይሆኑ ፥ መሲሑ እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም ውስጥ ካሉት ከማናቸውም ዓይነት ክፉቶች ጋራ ከሚያደርጋቸው ውጊያዎች አንዱ ክፍል መሆናቸውን ገልጸው ያስረዳሉ ። "ድካማችንን ተቀበለ" ፥ "ደዌያችንንም ተሸከመ" ፥ በራሱ ላይ ተሸከማቸው ማለት ሳይሆን አስወገዳቸው ማለት ነው ። ይህም በኀጢአት የወደቀውን ዓለም የሚያጠቃው ሥጋዊ ድካም የሚወገድበትን የአዲስ ዘመን ዋዜማ የሚያበሥር ነው ፤ ራዕይ 21፡4 ።

## እምነት ሲፈተን 8፡18-27

አንድ ጸሐፊ ኢየሱስን እከተለዋለሁ ብሎ ተስፋ የመስጠቱ ታሪክ በዚህ ተጽፎአል ፤ 19-22 ፥ ሉቃስ 9፡57-60 ። ኢየሱስ ነፋሳትን ጸጥ ማድረጉ ተመዝግቦ በታል ፤ ቁ- 18ና 23-27 ፥ ማር- 4፡36-41 ። የመጀመሪያው ታሪክ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ያልሆነውን ሰው በፍጹም ልቡ እንዲከተለው እንደጠራው ያሳያል ። ሁለተኛው ደግሞ ደቀ መዛሙርት በፍጹም ልብ በኢየሱስ እንዲያምኑ የተነገረ ማንቃቂያ ነው ።

18/ የርሱን መልእክት ለመረዳት ባለመፍቀዳቸው ኢየሱስ "ብዙ ሰዎች" ባሉበት ቦታ ለመገኘት አልወደደም ። 20/ ኢየሱስ የተዘዋዋሪ ሐዋርያ ሕይወት ብዙ ዋስትና የሌለው መሆኑን አመለከተ ። ሰውየው ጥሪውን መቀበሉ ወይም አለመቀበሉ አልተጻፈም ። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ስለ ራሱ ለመናገር ሲፈልግ "የሰው ልጅ" በሚለው አባባል የተጠቀመ መሆኑ አያጠራጥርም ። አባባሉ የተመሠረተውም በመዝ- 8ና በዳንኤል 7 ላይ ሲሆን እነዚህ ሁለቱም ምናልባት በዘፍጥረት 1 ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ እኔን ለማለት ሲፈልግ ተጠቀመበት ፤ ለምሳሌ 16፡13 ። አንዳንዴ ደግሞ ስለሚቀበለው መከራ ሲያመለክት ነው ፤ ለምሳሌ 17፡12 ። እንደዚሁም አንዳንድ ጊዜ ክብሩን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል ፤ 16፡27 ። ዘይቤው እምነትን ለማነቃቃት የተነገረ ነበረ ። 21/ አባቱ ገና ያልሞተ ሊሆን ይችላል ፤ ልጁም ከአባቱ የሚያገኘውን ውርስ ገና የሚጠብቅ ይሆናል ። 22/ የመንግሥተ ሰማያት ጥያቄ ፍጹምና አስቸኳይ ነው ። እነዚያ በመንፈስ ሕያዋን የሆኑት ከነዚያ በመንፈስ ከሞቱት ይልቅ ስለሁኔታው የሚያስቡት ፍጹም በተለየ መንገድ ነው ፤ 10፡37 ። ሰውየውም መልስ እንደሰጠ አይታወቅም ። 26/ ይህ ቁጥር ከማርቆስ ወንጌል የተለዩ ብዙ ዝርዝር ገለጻዎች ሲኖሩት ደቀ መዛሙርቱ እምነት ስለጎደላቸው እንዴት እንደወቀሳቸውና የፈጣሪ ኃይል መኖሩን እንዴት እንዳሳያቸው ያመለክታል ፤ መዝ- 88፡9 ፥ 106፡23-32 ። 27/ እርሱን እንደ አስተማሪያቸውና እንደ መሪያቸው አድርገው መከተል ብቻ ሳይሆን ፥ ከአንድ ከተራ ሰው የተለየ መሆኑን ማመን ይገባቸዋል ።

## ተጨማሪ የመፈወስ ሥራዎች 8፡28-9፡8

ይህ ክፍል አጋንንት ያደሩባቸውን ሰዎችና የሽባውን ታሪክ ይገልጻል ፤ 8፡28-34 ፥ 9፡1-8 ፥ ማር- 2፡1-12 ፥ 5፡1-20 ። ኢየሱስ የሰውነት በሽታን መፈወስ ብቻ ሳይሆን የስሜትና የመንፈስንም ሕመም ለማዳን የሚችል መሆኑን ማቴዎስ ያስታውቃል ።

28/ "ጌርጌሴኖን" ፥ ማቴዎስ የጻፈው ትክክለኛውን የቦታ ስም ሳይሆን አይቀርም ። ጋዳራ የምትባለው ከተማ የምትገኘው ከሐይቁ 9 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው ። ስሟም ሊጠቀስ የቻለው ምናልባት ጋዳራ ያውራጃው ዋና ከተማ ስለነበረች ይሆናል ። በአንዳንድ ብራናዎች ውስጥ ያለው "ገርገሲንስ" የሚለው ስም ትክክለኛ ከሆነ ፥ የተጠቀሰችው ከተማ ምናልባት አሁን ኬርሳ ተብላ የምትጠራው ከሐይቁ ምሥራቃዊ ወደብ ላይ የምትገኘው ከተማ ናት ። "እጅግ ክፉዎች" ፥ ማርቆስ ሰፋ ባለ ገለጻ ያተተውን ማቴዎስ አሳጥሮታል ። 29/ "የእግዚአብሔር ልጅ" ፥ ኢየሱስ የሰይጣንን ግዛት ለማጥቃት ስለመጣ ብዙ ሰዎች ማንነቱን ከማወቃቸው በፊት አጋንንት የኢየሱስን ማንነትና ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይሉን ሊያውቁ ቻሉ ፤ 12፡22-29ና ማር- 3፡11 ። "ጊዜው ሳይደርስ" ፥ ስለ መጨረሻ ዘመን ሁኔታ የተጻፉት የአይሁድ መጻሕፍት አጋንንት የሚደመሰሱት በመጨረሻው የፍርድ ቀን ነው በማለት ያስተምሩ ነበር ፤ ነገር ግን በኢየሱስ አገልግሎት አማካይነት የሰይጣን መንግሥት እየተፈነቀለ በመሄድ ላይ ነው ፤ 12፡28 ። 30/ "እርያ" ፥ የዚህ ቃል መጠቀስ ስፍራው አሕዛብ ይኖሩበት የነበረ ሀገር መሆኑን ያሳያል ። 31/ ስለ "አጋንንት" ጠባይ ብዙ ባለማወቃችን ይህን ጥቅስ መተርጎም ያዳግተናል ። አጋንንት በሰው ውስጥ ለማደር የሚፈልጉ ይመስላሉ ። 32/ ሰውየው ከበሽታው እንደዳነ የሚያረጋግጥለት ተጨባጭ ማስረጃ ነው ። ከዚህም በላይ የሰው ሕይወት ከእንስሳት ሕይወት የበለጠ ዋጋ ያለው መሆኑን ያሳያል ።34/በአሳባቸው የሀብት ጥቅም ከመንፈሳዊ ነገር የበለጠ ቀዳሚነት ነበረው ፤ የሐዋ- 19፡23-27 ። አጋንንቱ የእግዚአብሔር ልጅ በሥራቸው ውስጥ ጣልቃ መግባቱን እንዳልፈለጉ ሁሉ ፥ እነዚህ ሰዎችም አልፈለጉትም ፤ ቁ- 29 ።

9፡1/ "ወደ ገዛ ከተማው" ፥ በዚህ ላይ ቅፍርናሆምን ያመለክታል ፤ 4፡13 ። 2/ በዚህ ታሪክ ውስጥ መንፈሳዊው መዳን ከአካላዊው መዳን ቀድሟል ። "እምነታቸው" ፥ የበሽተኛውንና የወዳጆቹንም እምነት ሳይጨምር አልቀረም ። በተባበረ እምነት ውስጥ ታላቅ ኃይል

አለ ፤ 18፡19 ። 3/ "ይሳደባል" አሉ ፤ ምክንያቱም ይቅርታ ማድረግ አምላካዊ ሥልጣን ስለሆነ ነው ፤ ማር- 2፡7 ። 4/ "አውቆ" ፣ ከተፈጥሮ ዕውቀት በላይ የሆነ ችሎታን ላያመለክት ይችላል ፤ ጥልቅ በሆነው መንፈሳዊ መረዳቱ አውቆ ይሆናል ። 6/ በዓይን የሚታይ ነገር ስላይደለ ይቅርታ ስለማድረግ መናገር ቀላል ነው ፤ ዳሩ ግን እውነተኛው የይቅርታ ሥልጣን ፣ ሽባ የሆነውን ሰው ከማዳን የበለጠ ታላቅ ሥልጣንን ይጠይቃል ። ቀደም ሲል በተነገረው ታሪክ ውስጥ አንዳንድ አካላዊ ሁኔታዎች የአእምሮን መፈወስ እንዳመለከቱ ሁሉ ፣ እንደዚሁም እዚህ ላይ አንዳንድ አካላዊ ሁኔታዎች ለመንፈሳዊ መዳን ምልክት ሆኑ ። ሰውየው በኃጢአቱ ምክንያት ሽባ እንደሆነ የሚያመለክት ነገር የለም ፤ ዮሐ- 9፡2 ። 8/ "እግዚአብሔርን አከበሩ" ፣ 5፡16 ተመልከቱ ። የጌርጌሴኖን ሰዎች ካደረጉት ጋር የሚነጻጸር ነው ፤ 8፡34 ። "ለሰውም" ፣ ኢየሱስ እንደ ተራ ሰው ታይቶ ነበር ፤ ነገር ግን እንደ እውነተኛ የሰው ልጅም በመሆኑ በእግዚአብሔር ሥልጣን ለመሥራት የሚችል ነበር ፤ ቁ- 6 ፣ መዝ- 8፡5 ።

## የማቴዎስ መጠራትና ስለ ጾም የቀረቡ ጥያቄዎች 9፡9-17

እነዚህን ሁለት ታሪኮች ከማር- 2፡13-22ና ከሉቃስ 5፡27-39 ጋር አወዳድሩ ። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ እነዚህ ሁለት ታሪኮች ከሽባው መፈወስ ቀጥሎ ተጽፈው ይገኛሉ ።

9/ "ማቴዎስ" ፣ በዚህ ሁኔታ የተጠቀሰው በዚሁ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው ። ማርቆስና ሉቃስ ሌዊ የሚል ስም ሰጥተውታል ። በሐዋርያት ስም ዝርዝር ውስጥ ማቴዎስ ተብሎ ሲጠቀስ ይህ ወንጌል ብቻ ቀራጭ እንደሆነ ይናገራል ፤ 10፡3 ። ለአንድ አይሁድ ሁለት የግል ስም መስጠት ያልተለመደ ነው ። "ማቴዎስ" ምናልባት የክርስቲያን ስም ሲሆን ፣ ትርጉሙም የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ሳይሆን አይቀርም ። ወንጌሉን የጻፈው ማቴዎስ ከሆነ ወይም በአንድ መንገድ ከወንጌል ጋር ከተያያዘ ፣ እዚህ ላይ አዲስ ስሙን መግለጽ ትክክለኛ ነገር ነው ። የስሙ መለወጥ ብቻ ማቴዎስ ጸሐፊው ለመሆኑ መሠረታዊ የሆነ አስተማማኝ ማስረጃ ሊሆን አይችልም ።

10/ በሉቃስ ውስጥ ተጽፈው ከሚገኙት ለእጩ ተከታዮቹ ከቀረቡት ከሶስቱ ጥሪዎች ውስጥ ማቴዎስ ሁለቱን የጻፋቸው መሆኑን ማስተዋል ጠቃሚ ነው ፤ 8፡19-22 ፣ ሉቃስ 9፡57-62 ። ከነዚህ አንዱን ማለት በሉቃስ 9፡57-62 የሚገኘውን ያልጻፈበት ምክንያት ፣ በዚህ በ9፡9-13 የመዘገበው ታሪክ ግልጽ አድርጎ ስለሚተነትነው ሳይሆን አይቀርም ። "በቤቱም" ፣ የማቴዎስ ቤት ማለት ሳይሆን አይቀርም ። "ቀራጮች" ፣ እነዚህ አይሁዳውያን ሲሆኑ የሮሚ ዜግነት ያላቸው የግብር ሰብሳቢዎች ቅጥረኞች ነበሩ ። ሥራቸው ጉቦ ለመቀበልና ለመደለል የሚያመች ስለነበረ በጣም የተጠሉ ሰዎች ነበሩ ። "ኃጢአተኞች" ፣ በሥነ ምግባር ጠባይ የተዋረዱትንና እነዚያንም የሕጉን ሥነ ሥርዓት የማይጠብቁትን ጭምር የሚያጠቃልል ቃል ነው ። ከፈሪሳውያን ትምህርት እጅግ አሳዛኝ የሆነው እነዚህን ሁለት ዓይነት ሰዎች ለመለየት ባለመቻሉ ነው ። ኢየሱስ ሰዎችን የሚመለከተው በግለሰብ ደረጃ ነበር ።

12/ መልሱ ማንም ሊቀበለው የሚችል ዓይነት ሲሆን አምላካዊውን ጸጋ የሚገልጽ ነው ። 13/ ጥቅሱ ከሆሴዕ 6፡6 ላይ የተወሰደ ሲሆን እንደገናም በማቴ- 12፡7 ይገኛል ። "ምህረት" ፣ በእግዚአብሔርና በሰው መሐከል የጋራ ግንኙነት የሆነ ከቃል ኪዳን ጋር የተያያዘ ፍቅር ነው ። ማቴዎስ ከሆሴዕ 6፡6 ባስቀረው ዐረፍተ ነገር ላይ ይህን ምህረት ፣ እግዚአብሔርን ማወቅ ብሎ ጠርቶታል ። ፈሪሳውያን "ጻድቃን" የተባሉት በፌዝ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው ። "ወደ ንስሐ" የሚሉት ቃላት በጥንት ብራናዎች ውስጥ አይገኙም ።

14/ "የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት " ፣ ምናልባት ብዙ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ ፤ የሐዋ- 19፡1-7 ። ጥያቄውን ያቀረቡት እነርሱ መሆናቸውን የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው ። 15/ "ሙሽራው" ፣ መሲህ የተመሰለበት ምሳሌ ነበረ ፤ 22፡2 ፣ 25፡1 ። "እነርሱ የሚወሰድበት" ፣ መስቀሉን ሳይሆን ዕርገቱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ። የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን የጾምን ሥርዓት በትክክል ይጠብቁ የነበሩ ይመስላል ። ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስን ልማድ ተከትላ ለተለያዩ አጋጣሚ ጉዳዮች ትጾም ነበር ፤ 4፡2 ፣ 6፡16-18 ፣ የሐዋ- 9፡9 ፣ 13፡2 ፣ 14፡23 ። ምንም እንኳ ጾም አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም ፣ አሳሳቢ ወደ ሆነው ወደ ከንቱ ውዳሴ ደረጃ ወይም በዚህ ላይ እንደሚታየው በራሱ ጽድቅ ወደመመካት ደረጃ ሊያመራ ይችል ይሆናል ፤ ማቴ- 6፡16 ። 16፡17/ የኢየሱስ መልእክት ፍጹም አዲስ እንደ መሆኑ መጠን በአዲስ ቅርጽ የመቅረብ ግዴታ አለበት ። በኢየሱስ መልእክት የአይሁድ ትምህርት ጉድለት መሟላት አልቻለም ። "አዲሱ የወይን ጠጅ" ፣ ዮሐ- 2፡1-11 ።

## ተጨማሪ የመፈወስ ሥራዎች 9፡18-34

በዚህ ክፍል ውስጥ ሶስት ተጨማሪ የፈውስ ሥራዎች ይገኛሉ ። 1/ የመኰንኑ ሴት ልጅ ከሞት መነሣት ፣ ቁ- 18-26 ፣ ማር- 5፡21-43 ሉቃስ 8፡40-56 ፣ ደም ከሚፈሳት ሴት መፈወስ ታሪክ ጋር ተያይዞ ይገኛል ፤ 2/ ማቴዎስ በልዩ መንገድ የጻፈው የሁለቱ ዕውራን ዓይን መብራት ቁ- 27፡31 ። 3/ ጋኔን ያደረበት ዲዳ ሰው መዳን ፣ ቁ- 32-33 ፣ ሉቃስ 11፡14-16 ። የመጨረሻዎቹ ሁለት ታሪኮች ፣ በማቴዎስ 20፡29-34 ፣ 12፡22-24 ከሚገኙት ታሪኮች ጋር ይመሳሰላሉ ።

18/ ይህ "መኰንን" የምኩራብ ሹም ነበረ ፤ ማር- 5፡22 ፣ ማር- 5፡23 ፣ ሉቃስ 8፡41 ። ኢያኢሮስ ሴት ልጁ እንደሞተች ቆጥሮ ነበር ፤ በርግጥም የሞተች መሆኗ በኋላ ተገልጾአል ፤ ማር- 5፡35 ፣ ሉቃስ 8፡49 ። 20/ ሴቲቱም በማያቋርጥ የደም መፍሰስ ትሠቃይ የነበረች ሲሆን በዚህ ምክንያት ርኩስ ነበረች ፣ ዘሌዋ- 15፡25 ። ከኢየሱስ "በስተኋላ" የመጣችው በዚህ ምክንያት ይሆናል ።

"የልብሱን ጫፍ" ፥ በዘኍ 15፡38 ላይ ተጠቅሶአል ። 21/ የፍርሃትና የእምነት ቅልቅል ሳይሆን አይቀርም ። 22/ "እምነትሽ አድኖሻል" ፥ ይህ ቃል በግሪክ ቋንቋ ውስጥ ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ደኅንነትን ነው ። ምንም ልብሱን በመንካት አካላዊ መዳን የተገኘ ቢሆንም ፥ የነፍስ መዳን የሚገኘው ኢየሱስን በማግኘት ነው ፤ ማር- 5፡29 ። 23/ "እምቢልተኞች" ፥ ሰው ሲሞት ገንዘብ ተከፍሎአቸው ዋሽንት እየነፉ አልቃሾችን የሚያጅቡ ናቸው ። 24/ "ፈቀቅ በሉ አላቸው" ፥ ምክንያቱም ለገንዘብ ብለው የሚያለቅሱ ሰዎች አስፈላጊዎች ስላልሆኑ ነው ። "ተኝታለች" ፥ ሞትን የሚያመለክት አነጋገር ነው ። ነገር ግን በውነት ገና ካልሞተች የሞተች መስላ መጋደሟን ሊያሳይ ይችላል ፤ በሉቃስ 8፡53 ፥ 55 የሚገኘውን የሐኪሙን አነጋገር ተመልከቱ ። 25/ ማቴዎስ የሠራውን እንጂ ኢየሱስ የተናገረውን አልገለጸም ። 26/ ማቴዎስ ብቻ የኢየሱስ ዝና እንዴት እንደተስፋፋ በማተኰር ይገልጻል ።

27/ "የዳዊት ልጅ ሆይ" ፥ መሲህ ሲመጣ ለዕውራን ብርሃን ይሰጣል የሚል ትንቢት ነበረ ፤ ኢሳ- 35፡5 ። 28/ "ወደ ቤትም" ፥ ምናልባት የማቴዎስ ሳይሆን የራሱ የኢየሱስ ቤት ይሆናል ፤ 9፡10 ። ምንም እንኳ "ጌታ" የሚለው ቃል እዚህ ላይ ሙሉ የሆነ ክርስቲያናዊ ስሜትን ባይገልጽም ፥ "አዎን ጌታ ሆይ" የሚሉት ቃላት ኢያኢሮስ በኢየሱስ ኃይል ላይ እምነት እንደነበረው ይገልጻሉ ። "በብርቱ አዘዛቸው" ፥ ከአጉል ተስፋዎች የተነሣ ውዳሴን ከማትረፍ መጠንቀቅ አስፈላጊ በመሆኑ ነው ። 31/ ሰው ወሬ መደበቅ የሚያስችል ባሕርይ ስለሌለው ይህን የመሳሰለ ድርጊት መደበቅ በጣም አስቸጋሪ ነበረ ። 33/ እንደገና ሕዝቡ መደነቅ ሞላባቸው ። "በእሥራኤል ዘንድ" ፥ የተቀደሰ ታሪክ ባላቸው በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እንኳ ማለት ነው ። 34/ ይህ ወደፊት የሚመጣው ክርክርና ንትርክ ጭላንጭል ነው ፤ 12፡24 ።

## የሐዋርያት ተልእኮ 9፡35-10፡42

የኢየሱስን ዓላማዎችና ደቀ መዛሙርቱን ለተልዕኮ መጥራቱን ከሚገልጸው ከመጀመሪያው የወንጌሉ ግማሽ ቀጥሎ ያለው ክፍል የተልዕኮውን መመሪያ ያብራራል ። ይህ ንግግር በወንጌሉ ውስጥ ከሚገኙት አምስት ንግግሮች ሁለተኛው ነው ።

### ኢየሱስ ስለ ማዘኑና ደቀ መዛሙርቱን ስለ መጥራቱ 9፡35-10፡4

እነዚህ ቁጥሮች በማርቆስና በሉቃስ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች ይገኛሉ ፤ ማር- 3፡14-19 ፥ 6፡6-7 ሉቃስ 9፡1 ፥ 10፡2 ፥ 13፡22 ።

35/ "እያስተማረ እየሰበከና እየፈወሰ" ፥ እነዚህ የኢየሱስ አገልግሎት የሚታወቁባቸው ምልክቶች ናቸው ፤ 4፡23 ። 36/ የእሥራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሪ ስላልነበራቸው ኢየሱስ አዘነላቸው ፤ ዘኍል- 27፡17-20 ፥ 1 ነገ- 22፡17 ። የተልዕኮውም ዓላማ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መሪ እርሱ መሆኑን እንዲያውቁ ለመርዳት ነበር ። 37-38/ "ስለ መከሩ" ፥ እነጋገሩ ከማስተማር ይልቅ ወንጌልን ስለ ማስፋፋትና ስለ መስበክ ያመለክታል ። ሌሎችም ከኢየሱስ ጋር ሲተባበሩበት የሚገባ ሥራ ይህ ነው ።

10፡1/ በወንጌሉ ውስጥ "አሥራ ሁለቱ" ደቀ መዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሱት በዚህ ክፍል ነው ። ምንም እንኳ የመፈወስ ሥልጣን ለሰዎች የተሰጠ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም የዚህ ሥልጣን ሰጭ ኢየሱስ ነው ፤ 9፡8 ። "ደዌንና ሕማምን ሁሉ" ፥ የመፈወስ አገልግሎታቸው እንደ ኢየሱስ ሰፊ እንደሚሆን ያመለክታል ፤ 9፡35 ። 2/ "ሐዋርያት" ፥ ደቀ መዛሙርት ተማሪ ማለት ነው ። ሐዋርያት ሊሆኑ የሚችሉት ተማሪዎች ከሆኑ በኋላ ብቻ ነው ። "ሐዋርያት" የሚለው ቃል ኢየሱስ ከሥልጣን ጋር የላካቸው መልእክተኞች መሆናቸውን ያሳያል ። ይህ መጠሪያ አብዛኛውን ጊዜ አሥራ ሁለቱንና ጳውሎስን የሚያመለክት ሲሆን ባንዳንድ ሥፍራዎች ሰፋ ያለ ትርጉም አለው ። እዚህ ላይ ስማቸው የተዘረዘረው ፥ መጠራታቸው ከመላካቸው ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማሳየት ነው ፤ ቁ- 5 ። አሥራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል ለመወከል አሥራ ሁለት ነበሩ ፤ 19፡28 ። ምናልባት በቃል ለማስታወስ እንዲመች ማቴዎስ ብቻ በሁለት በሁለት እያደረገ ይጽፋቸዋል ። "መጀመሪያው" ፥ እርሱ መሪ መሆኑን ያመለክታል ። ማቴዎስ ጴጥሮስን አተኩሮ ይመለከተው ነበር ፤ 16፡17-19 ። "ቀራጪ" ፥ በዚህ ቃል የተጠቀመ ማቴዎስ ብቻ ነው ። ወንጌሉን የጻፈው ሐዋርያው ማቴዎስ ከሆነ ይህን ቃል የተጠቀመው እርሱ አንድ ጊዜ የተናቀ እንደነበረ ለማስታወስ ይሆናል ። "ታዴዎስ" ፥ ማርቆስም ፥ በዚህ ስም ጠርቶታል ፤ ሉቃስ ግን የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ብሎ ጽፎአል ። 4/ "ቀነናዊውም" ፥ ልክ እንደ ማርቆስ ሲሆን ሉቃስ ቀናተኛው ብሎ ይጠራዋል ። ቃሉ ምናልባት ቃንአን ከሚለው ከአራም ቋንቋ የመጣ ይሆናል ። እነዚህ ቀናተኞች የተባሉት ወገኖች ተዋጊ የሆኑ ብሔረተኞች ነበሩ ። "የአስቆሮቱ" ፥ ብዙ ጊዜ ቆርዮስ ከተባለው ከተማ የወጣ መሆኑን ያሳያል ተብሎ ተተርጉሞአል ። ምናልባት ሐሰተኛ የሚል ትርጉም ካለው አስቆርያ ከሚለው ከአራም ቋንቋ የመጣ ይሆናል ። "አሳልፎ የሰጠው" ፥ ሥራው ከስሙ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያሳያል ። ምናልባትም ስሙ በዝርዝሩ መጨረሻ ላይ የተጻፈው ከሃዲ ስለነበረ ነው ፤ ነገር ግን ስሙ ፥ ቀናተኛ ከተባለው ከስምዖን ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ። የይሁዳ ንጉሥ ከወጣበት ከይሁዳ ነገድ ለሐዋርያነት የተጠራ እርሱ ብቻ ነበረ ።

## የመልእክቱ አደራ 10፡5-42

ማቴዎስ ይህንን ክፍል የጻፈው ከብዙ የተለያዩ ሥፍራዎች አጠራቅሞ ሲሆን ፥ ኢየሱስ በልዩ ልዩ አጋጣሚ ሁኔታዎች የተናገራቸውን ትምህርቶች ሳይሆን አይቀርም ፤ ስለዚህም ለተልዕኮ ትምህርት ተስማሚ እንዲሆኑ ባንድ ላይ ተቀነባብረዋል ። ማር- 6፡8-11 ፥ ሉቃስ

9፡1-5 ፣ 10፡1-12 ከቁ- 9-16 ጋር ይመሳሰላሉ ። ቁ- 17-25ን የሚያስተጋቡ አሳቦች በማር- 13ና በሉቃስ 21 ውስጥም ይገኛሉ ። ቁ- 26-39 ከሉቃስ 12፡2-9 ፣ 51-53 ፣ 14፡26 ፣ 17፡33 ጋር ተመሳሳይ ናቸው ። ቁ- 5-8ና 40-42 የሚገኙት በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ።

5/ በሐዋርያት ዘመን ወንጌል የተነገረው በመጀመሪያ ለአይሁድ ነው ፤ ቀጥሎ ደግሞ ለግሪክ ሰዎች ነው ፤ ሮሜ 1፡16 ። የኢየሱስ ተልእኮ አይሁዶችን ንስሐ እንዲገቡና የመሲሁ ተከታዮች በመሆን ወደ ሰዎች ሁሉ ወንጌልን የማድረስ ግዴታ እንዳለባቸው ለማስረዳት ስለነበረ ከሐዋርያት ተልእኮ ይልቅ የኢየሱስ ተልእኮ ለአይሁዶች ደኅንነት የበለጠ ትኩረት ነበረው ፤ 28፡18-20 ፣ የሐዋ- 1፡8 ። 6/ "ወደ ጠፉት በጎች" ፣ እነዚህ ምናልባት ገጠር ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሲሆኑ እንደ ደንቆሮ የተቆጠሩና የተናቁ ነበሩ ። 7/ የስብከታቸው ይዘት የዮሐንስንና የኢየሱስን ይመስላል ፤ 3፡2 ፣ 4፡17 ። 8/ መፈወስ ወንጌልን ከማስፋፋት ሥራ ጋር በአንድነት የሚሄድ ሲሆን ፣ ከስብከታቸው ጋር የተያያዘ ነበረ ። ሶስተኛው የኢየሱስ ሥራ የሆነውን ማስተማርን ለማከናወን የነበራቸው ዕውቀት በቂ ስላልነበረ ማስተማር አስቸጋሪ ሆኖባቸው ነበር ። "ሙታንን አስነሱ" ፣ እነዚህ ቃላት ባንዳንድ ብራናዎች ውስጥ አይገኙም ፤ ነገር ግን ሐዋርያት ጌታቸው የሠራውን ዓይነት ሥራ እንዳይሠሩ የተደረገባቸው እገዳ የለም ፤ ዮሐ- 14፡12 ። "በከንቱ የተቀበላችሁትን በከንቱ ስጡ" ፣ የይቅርታ ስጦታንና የመፈወስንም ኃይል ከኢየሱስ ያለ ዋጋ ተቀብለዋል ፤ ስለዚህም ይቅርታን ማወጅና በተሰጣቸውም የመፈወስ ኃይል ያለ ዋጋ መፈወስና ሌላውንም እንዲሁ መሥራት አለባቸው ።

9-10/ "ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና" ፣ በፍጥነት መሄድና ሰዎችም እነርሱን የመርዳት ግዴታ ስለነበረባቸው ብዙ ሳይይዙ መጓዝ አለባቸው ። የወንጌል ስብከት በዋጋ ሳይሆን በነጻ የሚሰጥ ቢሆንም የሚሰበክላቸው የአገሩ አማኞች ፣ መንገደኞች የሆኑትን ወንጌላውያን በእንግድነት የመቀበል ግዴታ አለባቸው ፤ 1 ቆሮ- 9፡14 ፣ 1 ጢሞ- 5፡18 ። "ወይም በትር" ፣ በማር 6፡8 ላይ አንድ በትር ተፈቅዶአል ። ሉቃስ ከማቴዎስ ጋር ይስማማል ። ኢየሱስ በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ መምሪያዎች ሰጥቶ ይሆናል ። ቢሆንም በተቻለ መጠን እጅግ ጥቂት የሆነ ጓዝ መያዝ ነበረባቸው ። 11/ "የሚገባው" ፣ ምናልባት ስብከቱን ለመቀበል ዝግጁ ለሆኑና እንግድነትም ለመቀበል ፈቃደኞች ለሆኑ የሚል ስሜት ይኖረው ይሆናል ። 12/ "ሰላምታ ስጡ" ፣ 'ለዚህ ቤት ሰላም ይሁን' የሚለውን የሰላምታ አሰጣጥ ሳያመለክት አይቀርም ። 13/ የሰላምታው አሰጣጥ ሰዎች በልማድ የሚያቀርቡት ዓይነት አይደለም ። አጸፋውን የመለሱት ሰዎች ልዩ ዓይነት ሰላም ያገኛሉ ። 14/ "የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ" ፣ ሐዋርያት በበኩላቸው በፍጹም እንደተውአቸው የሚያሳይ ምልክት እንዲሆን ነው ። 15/ "ሰዶምና ገሞራ" ፣ ለመንፈሳዊ ርኩሰት የታጠቁ የእግዚአብሔርንም መልእክተኞች ላለመስማት የቆሙ ምሳሌዎች ነበሩ ፤ ዘፍጥ- 19፡4-9 ፣ ሕዝ- 16፡48-50 ፣ ማቴ- 11፡23 ። "በፍርድ ቀን" ፤ ምናልባት የመጨረሻውን ቀን የሚያመለክት ይሆናል ፤ ነገር ግን ከ66-70 ዓ/ም ለነበረው አስፈሪ የአይሁድ ጦርነት ፍርድ ፍንጭ የሚሰጥ ይሆናል ።

16/ "እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል" ፣ በአንድ አንጻር ራሳቸውን ከጉዳት ለመጠበቅ እንደ ኤደን ገነት እባብ ብልህ መሆን አለባቸው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ሊያደርግላቸው ባለው ጥበቃና እንክብካቤ ተስፋ በማድረግ በየዋህነት ሊታዘዙት እንደሚገባ ያመለክታል ። 17/ "ከሰዎች" ፣ በጠቅላላው የሰው ልጅ ዘር ከሚሰነዝርባቸው ነገር ሁሉ እንዲጠነቀቁ ምክር ተሰጥቶአቸዋል ። "ወደ ሸንጎ" ፣ የአጥቢያው ፍርድ ቤት ማለት ነው ። ግርፋቱ እንደተለመደው ሰላሳ ዘጠኝ ጅራፍ ነው ፤ 2 ቆሮ- 11፡24 ። 18/ መልእክቱ ከአይሁዳውያን አልፎ መሄድ አለበት ። ብዙውን ጊዜ እነርሱ ስለ ወንጌል ምስክርነት የሚሰጡት እሥር ቤት በሚሆኑበት ጊዜ ይሆናል ፤ የሐዋ- 23፡11 ፣ 25፡11 ። 19/ "አትጨነቁ" ፣ 6፡25-36 ተመልከቱ ። ቁሳቁሳዊ ነገርንም ሆነ ወይም ቃላትን ስለማግኘት ያለውን ጭንቀት የሚያስታግሥ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ። 21/ ወንጌል የቤተ ሰብ አባሎችን ያለያያል ፤ ቁ- 34-36 ። 22/ ሰዎችን ሁሉ የሚጠሉ ናቸው የሚለውን ክስ መሸከምና በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠሉ መሆን ለዓለም የፍቅርን ምሥራች ለሚያበስሩ ሰዎች እጅግ ከባድ ነበረ ። "ስለ ስሜ" ፣ የኔ ስለሆናችሁና የክርስቲያንነትንም ስም ስለተሸከማችሁ ማለት ነው ፤ 1 ጴጥ- 4፡14 ። "እስከ መጨረሻ" ፣ የዘመኑ መጨረሻ ሳይሆን ምናልባት በመከራ ውስጥ በማለፍ እስከ ሕይወት መጨረሻ ማለት ይሆናል ፤ 24፡9ና 13 ።

23/ ይህን ቁጥር መተርጎም በጣም አስቸጋሪ ነው ። አንዳንድ ምሁራን ኢየሱስ በሕይወቱ ጊዜ የዘመንን ፍጻሜ ይጠባበቅ ስለነበረና በርሱም የሕይወት ዘመን የዘመን ፍጻሜ ስላልሆነ ኢየሱስ በትምህርቱ ተሳስቶ አል ብለው ቁጥሩን ተርጉመዋል ። ማቴዎስ ግን እንዲህ እንዳላሰበ ግልጽ ነው ፤ ስለዚህ ለዚህ ጥቅስ ሊሰጠው የሚችለው መልካም ትርጉም ፣ "የሰው ልጅ" በአይሁድ ጦርነት ጊዜ በሮማውያን አማካይነት ለፍርድ እስኪመጣ ድረስ "የእሥራኤል ከተማዎች" ዞረው አይዘልቁም የሚል ነው ። በኢሳ- 44፡28 ፣ 45፡1 ላይ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ የእግዚአብሔር እረኛና የተቀባ ተብሎአል ። 24-25/ ሐዋርያት የሚጠሉበትን ምክንያት ገልጾ ያስረዳል ፤ ዮሐ- 15፡18-21 ። "ብዔል ዜቡል" 12፡22-32 ተመልከቱ ።

26/ "እንግዲህ አትፍሩአቸው" ፣ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው በሐዋርያት መሰደብ ላይ ሳይሆን ፣ በሚቀጥለው ክፍለ ምንባብ በተጠቀሰው ግልጽ አድርገው መስበክ በሚያስፈልጋቸው ነጥብ ላይ የሚያተኩር ሳይሆን አይቀርም ። 27/ ባንዳንድ በኩል ኢየሱስ ካደረገው ይበልጥ ፣ ሐዋርያት ሰፋ ያለ አገልግሎት እንደሚኖራቸው ይገልጻል ። 28/ "ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን" ፣ ስለ ሰይጣን ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር የሚያስረዳ ነው ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተሳሰብ ነፍስ በክርስቶስ አማካይነት አዲስ ሕይወት ካላገኙ በስተቀር ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ትለ

ያለች ፤ 1 ጢሞ- 6፡16 ፥ 2 ጢሞ- 1፡10 ። የሐኖን ሸለቆ የኢየሩሳሌም የቆሻሻ መጣያ ሥፍራ እንደነበረ ሁሉ እንዲሁም ገሃነም የነፍስ የሥቃይ ቦታ ነው ። 29/ እግዚአብሔር ለሁሉ እጅግ አስፈሪ ዳኛ እንደሆነ እንደዚሁም በርሱ ለሚተማመኑበት ሁሉ አፍቃሪ አባት ነው ፤ 6፡26 ። 30/ እግዚአብሔር አብ ፥ በመንከባከብና በማፍቀር እንዴት አድርጎ እንደሚይዝ በጉልህ ያሳያል ። 31/ ተመሳሳይ መልስ በ6፡30 ይገኛል ። 32/ በማርቆስና በሉቃስ ውስጥ ስለ እኔ የሚመሰክር በማለት ፈንታ ስለ ሰው ልጅ የሚመሰክር ብሎ ኢየሱስ እንዳስተማረ ተጽፎአል ። ኢየሱስ በዚህ ዓይነት አገላለጽ ሲጠቀም ስለ ራሱ ጠቅሶ እንዳመለከተ ማቴዎስ ያሳያል ። በግልጽ መመስከር የአንድ ሐዋርያ ዓይነተኛ ምልክቱ ነው ፤ ሮሜ 10፡9-11 ። "አባቴ" ሲል በቁ- 29 ውስጥ ካለው አባታችሁ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው ፤ ነገር ግን በግንኙነቱ ላይ ሁልጊዜ ልዩነት አለ ። አባታችሁ የሚለው ለሐዋርያት እንጂ ለኢየሱስ ጭምር አይደለም ፤ 6፡8 ።

34/ ኢየሱስ የሰላም ንጉሥ ሆኖ መጣ ፤ የርሱም የመጨረሻው ዓላማ በምድር ላይ "ሰላም" ለማድረግ ነው ፤ ሉቃስ 2፡14 ። ሰዎች ለወንጌል ጥሪ የሚሰጡት መልስ የተለያየ በመሆኑ ውጤቱ "ሰይፍ" ይሆናል ፤ ሉቃስ ሰይፍ የሚለውን ቃል መለያየት ብሎ ተርጉሞታል ። 35-36/ እነዚህ ቁጥሮች የተመሰረቱት በሚክ- 7፡5-7 ላይ ሲሆን ፥ ሰው ታማኝ ሆኖ ሊገኝ አለመቻሉንና የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያነጻጽራሉ ። የኤልያስ መምጣት ዋና ዓላማ በቤተ ሰብ ውስጥ እርቅ እንዲኖር ነበረ ፤ ሚል 4፡6 ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ወንጌል ሲሰበክ ወዲያውኑ የሚከተለው ውጤት የእርቅ ተጻራሪ የሆነ መለያየት ነው ። 37-38/ ከሉቃስ 14፡25-27 ጋር ይመሳሰላሉ ፤ ሉቃስ ባይጠላ ሲል ተጻራሪነቱን አጉልቶ ያሳያል ። "ለኔ ሲሆን" ፥ የኔ ገንዘብ ወይም የኔ ሐዋርያ ማለት ነው ። "መስቀሉን የማይዝ" ፥ መላ ሰውነቱን መሥዋዕት አድርጎ የማይሰጥ ማለት ነው ። 39/ "ነፍሱንም" ፥ የራሱን ነፍስ ወይም በፍጹም ራሱን ማለት ነው ። የተፈጠረለትን ዓላማ ሊይዝ የሚችለው በክርስቶስ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ የሆነ ግንኙነት ያለው ሰው ብቻ ነው ። ቁ- 38-39 በማቴ- 16፡24 በድጋሚ ተጽፈው ይገኛሉ ።

ባንድ የአይሁድ ሕግ መጽሐፍ ፡— የሰው ልጅ ወኪል የላኪውን ያህል መብት አለው ተብሎ ተጽፎአል ። እንግዲህ ቁ- 40 ፥ ሐዋርያት የኢየሱስ ወኪሎች በመሆናቸው ፥ ተልእኮአቸው የቱን ያህል ከባድ ኃላፊነት እንደነበረበት ያሳያል ። 41/ "በነቢይ ስም የሚቀበል" ፥ 1 ነገሥት 17፡9-24ንና 2 ነገ- 4፡8-37ን ተመልከቱ ። "በጻድቅ ስም" ፥ እንደ ነቢይ መናገሩንና ሳይሆን ፥ በትክክለኛ ሕይወቱ መመስከሩን ያመለክት ይሆናል ። 13፡17 ደግሞ ስለ ነቢያትና ስለ ጻድቃን ያስተምራል ። 42/ "ከነዚህ ከታናናሾቹ" ፡ ምናልባት ትሑት ስለሆኑ አማኞች ጠቅሶ መናገሩ ይሆናል ። እጅግ ጥቂት የሆነው የቸርነት ሥራ በውነት ዋጋ አለው ፤ 25፡42 ።

## ክርስቶስ የሚጠይቃቸው ነገሮች 11፡1-12፡50

ማቴዎስ በምዕ- 10 ከተሰጠው የማስተማርን ታሪክ ከያዘው የተልእኮ ትእዛዝ በኋላ ፥ ስለ ማስተማር የሚናገሩና ብዙ ነገሮችን የያዙ ሁለት ምዕራፎች ያቀርብልናል ። እዚህ ላይ የተሰበሰቡት ታሪኮች የኢየሱስን መሲህነትና የእስራኤልንም ያለማመን ሁኔታ ያሳያሉ ። የክርስቶስ መንግሥት ለእስራኤል የታወቀው ፡— 1/ በመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት ፥ ምዕ- 3 ። 2/ በኢየሱስ ትምህርት ፥ ምዕ- 5-7 ። 3/ በኢየሱስ ተግባራት ፥ ምዕ 8-9 ። 4/ በሐዋርያት ስብከት ነው ፤ ምዕ- 10 ። እዚህ ላይ እስራኤል በፈሪሳውያን ተመስላ መሲህን አለመቀበሏ ተገልጾአል ። በዚህም ምክንያት ወንጌልን ለአሕዛብ ለማቅረብ የመጀመሪያው ርምጃ ተወሰደ ፤ 12፡18-21 ።

## ኢየሱስና ዮሐንስ 11፡1-19

ማቴዎስ አገናኝ አሳብ ከጻፈ በኋላ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ስለ መጐብኘታቸው ይገልጽና ኢየሱስ ስለ ዮሐንስ የተናገረውን ያወሳል ። ይህ ክፍል ከሉቃስ 7፡18-35 ጋር በቅርብ ይመሳሰላል ። ቁ- 12፡13 ልዩ ቢሆንም ከሉቃስ 16፡16 ጋር ተቀራራቢነት አላቸው ።

1/ ይህ ቁጥር ከሚከተለው ክፍል ይልቅ ከፊተኛው ጋር በበለጠ ሁኔታ በግልጽ የተያያዘ ነው ፤ 7፡28 ። 2/ ዮሐንስ በሄሮድስ — አንቲጳስ ታስሮ ነበር ፤ 4፡12 ። እንደ ዩሲፉስ አተራረክ ከጨው ባሕር በስተ ምሥራቅ በሚገኘው ማኬራዮስ በሚባለው ምሽግ ውስጥ ይጠበቅ ነበር ። በኋላም በሄሮድስ ትእዛዝ ተገደለ ፤ 14፡1-12 ። "የክርስቶስ ሥራ" ፥ ወንጌላዊው የኢየሱስን ተግባራት የጠቆመበት አገላለጽ ነው ። ዮሐንስ የኢየሱስን ተግባራት ጥቅም ይጠራጠር ነበር ። 3/ "የሚመጣው" ፥ ምናልባት ግልጽ ባልሆነ መንገድ መሲህን የሚያተኩር አጠራር ሊሆን ይችላል ። ዮሐንስ ራሱ ስለሚመጣው ሰው ተናግሮ ነበር ፤ 3፡11 ። መሲሁ ማን እንደሆነ እንጂ ስለ መምጣቱ ምንም ጥርጥር አልነበረውም ። ምናልባት ዮሐንስ መሲህ ሲመጣ ፍርድን በሥራ ላይ ማዋል ይጀምራል ፤ እኔንም ከወህኒ ቤት ያወጣኛል የሚል ተስፋ ሳይኖረው አልቀረም ፤ 3፡12 ። 4/ ሉቃስ በዚያን ሰዓት የተደረገውን የፈውስ ሥራ ጽፎአል ፤ ነገር ግን የኢየሱስ ቃላትና ሥራዎች በጠቅላላው አስረጂዎች ናቸው ። 5/ እነዚህ በኢሳ- 29፡18 ፥ 35፡5 ፥ 61፡1 አስቀድመው የተነገሩት የመሲህ ሥራዎች ሲሆኑ ፥ የመሲሁ አገልግሎት በይቅርታ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ዮሐንስን የሚያስታውሱ ናቸው ። የዮሐንስ አገልግሎት ግን ጎልቶ ይታይ የነበረው በፍርድ ላይ ነው ። 6/ "የማይሰናከል" ፥ ተራው ሕዝብ ስለ መሲህ ያላቸውን አሳብ ኢየሱስ ባለማሟላቱ የተፈጠረውን መሰናከል ሳያመለክት አልቀረም ፤ 13፡21ና 57 ፥ 15፡12 ።

7-8/ ዮሐንስ ለሰዎች አሳብ ወይም ለምቹ ኑሮ የሚ ያጎነብስ ሰው አልነበረም ። 9-10/ በፍርድ ቃላቱና በበረሃ የቀኖና ኑሮ በመኖሩ በዘመኑ የነበረውን ቅምጥል ማኅበራዊ ኑሮ የሚቃወም "ነቢይ" ነበረ ። ሌሎች ነቢያት በአጠቃላይ አነጋገር የተናገሩለትን መሲህ እርሱ አረጋግጦ ማሳየት ስለነበረበት "ከነቢያት የሚ በልጥ" ሰው ነበረ ። ሚክያስ አስቀድሞ የተናገረለት "መልእክተኛና" መንገድ የሚጠርግ ሰው ነበረ ፤ ሚል- 3፡1 ፣ ዘጸ- 23፡20 ። 11/ "ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም" ፣ ምክንያቱም በአምላካዊ ሹመት የሥራ ሰው በመሆኑ ነው ። መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን ዘመን አማኝ በመሆኑ ማንኛውም የአ ዲስ ኪዳን ዘመን አማኝ ከርሱ ይልቅ ዕድለኛ ነው 13፡16 ። ቁ- 12ን ለመተርጎም እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው ። ሉቃስ 16፡16 ተመሳሳይ ቢሆንም የአነጋገሩ ቅደም ተከተል ለየት ያለ በመሆኑ በሌላ አጋጣሚ የተ ነገረ ሊሆን ይችላል ። ቢያዜታይ ፣ የሚለው "ትገፋ ለች" ፣ ተብሎ የተተረጐመ የግሪኩ ቃል ምናልባት ተደራጊ ግሥ ሊሆን ይችላል ። ተደራጊ ግሥ ሆኖ ከተ ተረጐመ ፣ ቀናተኞችና ተከታዮቻቸው መንግሥቱን ለመያዝ ሞክረዋል ማለት ነው ፤ ዮሐ- 6፡15 ፤ ወይም ብዙ ሰዎች በናፍቆት ሊገቡባት ተጋፍተዋል ማለት ነው ። ይሁን እንጂ ብዙዎች ተደንቀው ቢከተሉም አብዛኞቹ ተረድተው ለመቀበል ዝግጁዎች የነበሩ አይመስልም ። ምናልባት መንግሥተ ሰማያት እየገ ፋች መጥታለች ማለቱ ይሆናል ፤ ስለ ክርስቶስ መን ግሥት የተነሡት ሥር ነቀል ጥያቄዎች የአይሁድን ኑሮ አናግተዋል ። ግሡን እንደ ተደራጊ ቆጥሮ መተር ጐም ሳይሻል አይቀርም ። ቁ- 14-15 የሚገኙት በማቴ ዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። ዮሐንስ እንደገና በሥጋ የመጣ ኤልያስ አይደለም ፤ ዮሐ- 1፡21 ። ነገር ግን በሚልክያስ በተነበየው ትንቢት መሠረት የኤልያስን ሥራ ፈጽ ሞአል ።

16/ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ የማዳኑ ምስክር የነበረው ትውልድ ምርጥ ትው ልድ እንደነበረ ሁሉ "ይህ ትውልድ" ደግሞ በአዲሱ ኪዳን ዘመን የተፈጸመውን የእግዚአብሔርን የመቤ ዠቱን ሥራ በማየቱ ዕድለኛ ነው ፤ ዘዳ- 1፡35 ፣ 32፡5ና 20 ፣ መዝ- 94፡10 ፣ ማቴ- 12፡39 ፣ 41ና 45 ፣ 16፡4 ፣ 17፡17 ፣ 23፡36 ፣ 24፡34 ፣ የሐዋ- 2፡40 ፣ ዕብ- 3፡10 ። ከዚህ የተነሣ ወንጌልን ሲሰሙ ልዩ ኃላፊነት አለባ ቸው ። 17/ ከኢየሱስ ጋር የሠርግ ደስታ ተሳታፊዎች ለመሆን ፈቃደኞች አልሆኑም ፤ ወይም ከዮሐንስ ጋር ሙሾ ለማውጣት አልወደዱም ። 18-19/ ጾምን የሚያ መለክት ተመሳሳይ ትምህርት በ9፡14-17 ውስጥ ይገ ኛል ። 9፡10-13 ኢየሱስ ከኃጢአተኞች ጋር መተባበሩን ያሳያል ። ጥበብ "በልጆችዋ ጸደቀች" ፣ ልጆች በማለት ፈንታ ሉቃስ ሥራዎች ብሎ ጽፎአል ፤ ይኸውም የቃ ሉን አሳብ ሲተረጉም ነው ። "ጸደቀች" ማለት እው ነት ሆና ተገኘች ማለት ይመስላል ፤ ነገር ግን ይህ ሐቅ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ጠቅላላው ታሪክ ሲታሰብ ነው ። ልጆች የሚለው ቃል ዮሐንስና ኢየሱስ ያከናወኑአ ቸውን ሥራዎች ያመለክታል ፤ እነዚያም ሥራዎች ለተናገሩአቸው ቃላት ማስረጃ ነበሩ ። እዚህ ላይ ጥበብ ማንነት እንዳላት ተደርጋ ተቆጥራለች ፤ ሉቃስ 11፡49 ። የመጥምቁ ዮሐንስን ሥራ በተጨማሪ የሚያብራሩ መረጃዎች በማቴ- 3፡1-17 ፣ 14፡1-12 ፣ 21፡23-32 ይገኛሉ ።

## ወንጌልን አለመቀበልና ኢየሱስ ያደረገው ጥሪ 11፡20-30

ይህ ክፍል 1/ መልካሙን የመንግሥተ ሰማያት ዜና አንቀበልም ባሉ ከተማዎች ላይ የተሰጠ የፍርድን ውሳኔ የያዘ ነው ፤ ቁ- 20-24 ፣ ሉቃስ 10፡13-15 ። 2/ እውነት ስለ መገለጹ ለእግዚአብሔር የቀረበ ምሥጋና ይገኝበ ታል ፤ ቁ- 25-27 ፣ ሉቃስ 10፡21 ። 3/ እንዲሁም በማቴ ዎስ ብቻ የሚገኘው ክርስቶስን ለሚቀበሉት እርሱ ምን እንደሚሰጣቸው የሚገልጽ አነጋገር አለበት ፤ ቁ- 28-30 ።

20/ "የሚበዙ ተአምራት የተደረገባቸውን" ፣ ኢየ ሱስ በገሊላ ባሕር ሰሜናዊ ጫፍ በምትገኘው ትንሽ ከተማ ላይ ብዙ ተአምራት እንዳደረገ ተገልጾአል ። 21/ "ኮራዚ" ፣ ከቅፍርናሆም በስተ ሰሜን 5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች ፤ ቤተ ሳይዳ ደግሞ ከቅፍርናሆም ጥቂት ራቅ ብላ በስተ ምዕራብ በኩል ትገኛለች ። "ጢሮስና ሲዶና" ፣ የፊንቄ ከተማዎች ሲሆኑ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የርኩሰትና የመንፈሳዊ ኩራት ምሳሌዎች ነበሩ ፤ ኢሳ- 23 ፣ ሕዝ- 26-28 ። 22/ "በፍርድ ቀን" ፣ ጊዜያዊና ወደፊት የሚያመለክት ትርጉም ሊኖረው ይችላል ፤ 10፡15 ። 23/ በኢሳ- 14፡12-15 ላይ የተመሰ ረተው በዚያ ሲሆን ባቢሎን የሰይጣን ምሳሌ ነው ። ጢሮስን የሚጠቁም ተመሳሳይ ጥቅስ በሕዝ- 28፡2-8 ይገ ኛል ። በ9፡1 ውስጥ የኢየሱስ የገዛ ራሱ ከተማ ተብላ የተጠራችው ቅፍርናሆም የሚደርስባት ፍርድ ፣ የእግ ዚአብሔር ሕዝብ መዝሙራቸውን ለመዘመር ያልቻሉ ባት ባቢሎን ከሚደርስባት ፍርድ የከፋ ይሆናል ፤ መዝ- 136፡4 ። "ሰዶም" ፣ የረከሰችና የእግዚአብሔርን መልእክተኞች የገፋች ሌላይቱ ከተማ ነበረች ፤ ዘፍጥ- 19፡1-29 ፤ ማቴ- 10፡15 ።

25-27/ የዚህ አነጋገር ሁኔታ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከተጻፈው ጋር ይመሳሰላል ፤ ዮሐ- 3፡35 ፣ 17፡2 ። ንግግሩ ከዮሐንስ ጋር በመመሳሰሉ ምክንያት ብዙ ተመ ራማሪዎች ማቴዎስ የጻፈው አይደለም ብለው ቢናገሩም ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ አጻጻፍ ሁኔታ ለማስተማሩ ዋና ማስ ረጃ ሊሆን ይችላል ። በዚህ ውስጥ ብዙ የአይሁድን አስተሳሰብ የሚያንጸባርቁ ዐረፍተ ነገሮች ሲገኙበት ፣ ወደ አራም ቋንቋ ሲተረጎም ብዙ ቤት የሚመቱ ቃላት ይገኙበታል ። በ24፡36 ውስጥ አባትና ልጅ የሚለው አጠራር ያለ ምንም ቅጽል ተጠቅሶ ይገኛል ። ይህም የሚያሳየው በእግዚአብሔርና በክርስቶስ መሐከል ያለ ውን ልዩ የሆነ ግንኙነት ነው ። "አባት" በሰማይና በምድር ላይ ፍጹም የሆነ ሥልጣን አለው ። ይህንንም ሥልጣን ለልጁ ሰጥቶታል ፤ 28፡18 ። ስለዚህ ይህንን

ግንኙነት ለመግለጽ ሥልጣን አለው ። የራሱን ቃላትና ሥራዎች ትርጉም ማለት ኢየሱስ የተናገራቸውንና ያደረጋቸውን ፣ "ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች" መሰወርን መረጠ ። ኢየሱስ "ጥበበኞች" ብሎ የጠራቸው እነርሱ ራሳቸው በሚጠቀሙበት አገላለጽ በመጠቀም ነው ። "ለሕጻናት" ፣ አምነው ለመቀበል በመንፈስ ዝግጁ ለሆኑት ምሥጢሩን ለመግለጽ ፈቅዶአል ፤ 18፡3 ። አምላካዊው እውነት በጠቅላላ ከአብ ወደ ኢየሱስ ተላልፎአል ፤ ዮሐ- 5፡20 ። የዚህ እውነት ዋና ነጥብ አብንና ወልድን ማወቅ ነው ። ይህም ከእግዚአብሔር የሚገኝ ስጦታ ሲሆን ከዕውቀት በላይ የሆነና ሰው በግል ከእግዚአብሔር ጋር ከሚያደርገው ግንኙነት የሚያገኘው ነው ፤ ዮሐ- 17፡3 ። የአብና የወልድ የበላይነት ሥልጣን "ፈቃድህና ከሚፈቅድ" በሚሉት ቃላት ውስጥ ተገልጾአል ። 16፡16 ደግሞ ስለዚህ ዓይነት መገለጽ ያስተምራል ። 28-30/ "ወደ እኔ ኑ" ፣ በኢሳ- 55፡1-3 ውስጥ ከሚገኙት ቃላት ጋር ይመሳሰላል ። "ሁሉ" ፣ ጥሪው አጠቃላይ ስለሆነ ማንንም አያስቀርም ። "ዕረፍት" ፣ ይህ ተስፋ የተሰጠው ሥራ ለመፍታት ሳይሆን ፣ ለአገልግሎት አዲስ "ቀንበር" ለመሸከም ነው ። ፈሪሳውያን በሕግ ያለውን ጥቅም ስላልተረዱና በልባቸው ስላልተቀበሉት ቀንበር ብለው ጠሩት ። የዚህ ቀንበር ሰጭ ቸር በመሆኑ የርሱን ቀንበር መሸከም ሥነ ምግባራዊውን መመሪያ በደስታ መቀበል ማለት ነው ። በኢሳ- 42፡2-4ና 53፡6-9 እንደ ተገለጸው መከራ እንደሚቀበለው አገልጋይ ፣ "እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ" ብሎ ተናገረ ። የክርስቶስ አነጋገር ትእዛዙን ለመፈጸም አስቸጋሪ ቢያስመስለውም ፣ ተቀባዩ ምንም ክብደት አይሰማውም ፤ 7፡13-15 ። አስገራሚ የሆነው አምላካዊ ስጦታው ይህ ነው ።

## ስለ ሰንበት የተነሣ ክርክር 12፡1-14

ከዚህ ክፍል ምንባብ ጋር ማር- 2፡28-3፡6ንና ሉቃስ 6፡1-11ን አንብቡ ። ፈሪሳውያን ስለ ሰንበት አከባበር የተሰጠውን ትእዛዝ ሲተነትኑ የሕግን ቀንበር እጅግ በጣም ከባድ አደረጉት ። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ሁለት ታሪኮች ፣ ምግብን በማዘጋጀትና በመፈወስ አማካይነት የሰውን ችግር ለማቃለል እንደተቻለ በተለያዩ ምሳሌዎች አሳይተዋል ።

1-2/ እንደ አገሩ ልማድ ከሆነ ፣ በሰው የእህል አዝመራ ውስጥ ገብቶ እሸት መቅጠፍ ይፈቀድ ነበር ፤ ዘዳ 23፡25 ። ነገር ግን ፈሪሳውያን ሰንበትን ለማክበር ብለው ይህን እንደ ጥፋት ቆጠሩት ። 3-4/ "ዳዊት የመሥዋዕቱን ኅብስት" እንደ በላ የተነገረው በ1 ሳሙ- 21፡1-6 ውስጥ ነው ። ከፍ ያለውን ሕግ ለማክበር ማለትም የሰውን ችግር ለማቃለል ፣ አነስ ያለውን ትእዛዝ ተላለፈ ። 5/ "ካህናት" በሰንበት ቀን አንዳንድ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር ፤ ዘኍ- 28፡9ና 10 ። ፈሪሳውያን መሥዋዕትን ማቅረብ ሰንበትን ከማክበር የበለጠ መሆኑን ተረድተው ነበር ። 6/ "ከመቅደስ የሚበልጥ" ፣ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሲመጣ የእግዚአብሔር መንግሥት ሊገለጥ ጀመረ ማለት ነው ። ዳዊትና ካህናት የሰውን ችግር ለማስወገድ የሰንበትን ሥርዓት መሻር ከተፈቀደላቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመጣው የቱን ያህል ሥርዓት መሻር ይችል ይሆን ? 7/ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሆሴዕ 6፡6 ጠቃሚ የትንቢት መመሪያ ይዞአል ፤ ደግሞም በ9፡13 ውስጥ ተጠቅሶአል ። "ኃጢአት የሌለባቸውን" ፣ ካህናት በሰንበት ቀን መሥዋዕት በሚያቀርቧቸው ጥፋተኛ እንደማይሆኑ ፈሪሳውያን ያስተምሩ ነበር ፤ ቁ- 5 ። 8/ ማቴዎስና ሉቃስ ሰንበት የተሠራው ለሰው ነው የሚለውን የማርቆስን ሐረግ ይተውታል ። "የሰው ልጅ" ፣ እዚህ ላይ የሚያመለክተው እውነተኛውን ሰው ኢየሱስን ነው ። ዳዊት የሠራውን ሥራ ሳይፈረድበት ለመሥራት ከቻለ ፣ መሲህማ ስለ ሰንበት ሕግ እውነተኛውን ትርጉም ለመስጠት የቱን ያህል ይችል ይሆን ? 10/ ኢየሱስ ሕግን በግልጽና በአዲስ ሁኔታ በመተርጐም የታወቀ ነበረ ። ነገር ግን ፈሪሳውያን ፣ በዚህም አቅጣጫም ኢየሱስን ለማሳሳት ጥረት ያደርጉ ነበር ። የሰው ሕይወት በአደጋ ላይ በሚገኝበት ጊዜ "በሰንበት መፈወስ ተፈቅዶአል" የሚለው መመሪያ በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ቢኖረውም ፣ ሰውየው እስከ ተከታዩ ቀን ድረስ ቢቆይ ኖሮ ባልተጎዳም ነበር ። 11-12/ ይህን ክርክር የመዘገበ ማቴዎስ ብቻ ነው ፤ ነገር ግን ከሉቃስ 13፡15 ጋር ይመሳሰላል ። ፈሪሳውያን በሰንበት እንስሳን ለማዳን ይፈቅዱ ነበር ፤ ነገር ግን በኩምራን ገዳም የሚገኘው ደንብ ፣ የአንድ ሰው እንስሳ ጉድጓድ ወይም ገደል ቢገባበት በሰንበት ቀን ሊያወጣው አይገባውም ይላል ። ሰው ከእንስሳ ስለሚበልጥ ኢየሱስ በፈጸመው ሥራ ጥፋተኛ አለመሆኑን አስረዳቸው ፤ 10፡31 ። ምንም እንኳ አጣዳፊ ነገር ባይኖርም "በሰንበት መልካም መሥራት" ጥሩ አጋጣሚ ነው ። 14/ ፈሪሳውያን ከሄሮድስ ወገን ጋር እንደተማከሩበት ማርቆስ ይነግረናል።"እንዲያጠፉት"፤ እነዚህ በጣም የተለያዩ ሁለት ወገኖችና የመሪዎች ወኪሎች ሕይወትንና ፈውስን የሚሰጠውን ኢየሱስን ለማጥፋት በምክር ተስማሙ ።

## በተጨማሪ የተፈጸመ የመፈወስ ሥራና ንትርክ 12፡15-37

ቁ- 15-16 ፤ ተመሳሳይ ድርጊት ከሚገልጸው ከማር- 3፡7-12 ጋር ሲነጻጸር አጭር ነው ፤ ሉቃስ 6፡17-19 ። ቁ- 17-21 የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። ቁ- 22-32 ከማር- 3፡22-30 ፣ ከሉቃስ 11፡17-23 ፣ 12፡10 ጋር ይመሳሰላል ። ቁ- 33-37 ፣ ከ7፡16-20 ፣ ከሉቃስ 6፡43-45 ጋር ይመሳሰላሉ ። ፈሪሳውያን ካደቡበት በኋላ ኢየሱስ ሌሎችን ሰዎች ከመፈወሱም በላይ ሥራው በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተተነበየ መሆኑን አስረዳቸው ። የኢየሱስ የመፈወስ ሥራዎች በሰይጣን ኃይል የተደረጉ ናቸው የሚለው ክስ ኢየሱስን ከፈሪሳውያን ጋር ካጋጨው በኋላ ኢየሱስ ቃላትና ጠባይ ስለአላቸው ግንኙነት ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጠ ።

15/ ኢየሱስ ስለተደረገበትም አድማ አውቆ ከዚያ ፈቀቅ አለ ። እንደገናም ደግሞ ብዙ ሕዝብ ተከተለው ፤ እንደገናም የመፈወሱን ሥራ ለሁሉም ያዳርስ ነበር ፤ 8፡16 ። አስፈላጊ ያልሆነ ዝና ለማትረፍ አልፈቀደም ፤

8፡4 ፣ 9፡30 ። 18-21/ እነዚህ ጥቅሶች ግልጽ ባልሆነ መንገድ በጥምቀቱ ጊዜ ፣ 3፡17 ፣ ደግሞም በተራራው ላይ በተለወጠ ጊዜ ሲጠቀሱ ፣ 17፡5 ፣ የዕብራውያንን አጻጻፍ በመከተል ከተጻፈው ከኢሳ- 42፡1-4 የተወሰዱ ናቸው ። እዚህ ላይ ረጅም የሆነ ጥቅስ የተጠቀሰበት ዋነኛው ምክንያት አገልግሎቱ ትሑት ከመሆኑ የተነሣ ለተናቁትና ከዚያም አልፎ ለአሕዛብ መድረሱን ለመጠቆም ነው ። "ብላቴናዬ" ፣ ይህ ቃል እሥራኤልን ወይም በጠቅላላው የታመኑትን ቅሬታዎች ወይም መሲህን ያመለክታል ተብሎ ተተርጉሞአል ፤ ምናልባት ነቢዩ የተናገረው ሶስቱንም ለማመልከት ይሆናል ። ማቴዎስ ኢየሱስ እውነተኛው የእሥራኤል ምሳሌ እንደሆነ አመልክቶአል ፤ 2፡15 ። "አይከራከርም አይጮህምም" ፣ ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ በክርክር ውስጥ ቢገባም ፣ ኢየሱስ ንትርክን እንደማይፈልግ የሚያስረዳ ነው ፤ የርሱንም መሲህነት በተሳሳተ መንገድ ሊያሳውቅ አልፈለገም ። "ፍርድን ድል ለመንሣት እስኪያወጣ" ፣ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ዘዴዎች እውነተኛ መሆናቸው መገለጡ አንዳንዴ አስፈላጊ ሆኖ ይታያል ። የዚህ እውነተኛነት የሚገለጸው ኢየሱስ በከፊል ለተገለሉት የምሥራችን የሚያበስር ሲሆን ፣ ፍጹም ገለጻ የሚገኘው ወንጌል ለአሕዛብ ሲሰበክ ነው ።

22/ ሉቃስ የክርክሩን ሁኔታ ቢያቀርብም ማቴዎስ ብቻ "ዲዳው ሰው ዕውር" እንደነበረ ይናገራል ። 23/ "ኢየሱስን የዳዊት ልጅ ይሆንን ?" ብለው ሕዝቡ እንደተገረሙ የጻፈው ማቴዎስ ብቻ ነው ፤ 9፡27 ። 24/ ምንጊዜም ለማናቸውም መልካም ነገር የተጣመመ ትርጉም መስጠት ይቻላል ። "በብዔል ዜቡል" ፣ በከነዓን ሰዎች ቋንቋ የቤት ጌታ ወይም የተከበረ ጌታ ማለት ሳይሆን አይቀርም ፤ 2 ነገ- 1፡2 ላይ የአቃሮን አምላክ ብዔል ዜቡል ወይም የዝምቦች አምላክ ተብሎ ተጠርቶአል ። ምናልባት የእስራኤል ሰዎች ሊያፌዙበት ፈልገው የመጨረሻውን ፊደል አውቀው ለውጠውት ይሆናል ። አይሁድ የፍልስጥኤማውያንን አምላክ "እንደ አጋንንት አለቃ" እንጂ እንደ አምላክ አድርገው አይቆጥሩትም ነበር ። 25-26/ ኢየሱስ ክርክራቸው መሠረተ ቢስ መሆኑን ያሳያቸዋል ።

27/ ኢየሱስ በሰይጣን ቀስቃሽነት ስላለመሥራቱ የተሰጠው ኃይለኛ ማስተባበያ ፣ የፈሪሳውያን "ልጆች" ማለት ተከታዮች አጋንንት ማውጣታቸው ነው ። ዳሩ ግን ከኢየሱስ አሠራር ባነሰ ሁኔታ የተከናወነ ሳይሆን አይቀርም ፤ የሐዋ- 19፡13-16 ። 28/ "በእግዚአብሔር መንፈስ" ፣ ሉቃስ የእግዚአብሔር ጣት ብሎ የተናገረውን አሳብ ፣ ማቴዎስ በእግዚአብሔር መንፈስ ብሎ ለአንባብያን ተርጉሞታል ። ይህ አባባል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከታላቁ የመቤዠት ሥራ በፊት የተፈጸመውን የሚገልጽ ነው ፤ ዘጸ- 8፡19 ። ኢየሱስ የፈጸማቸው ተአምራት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለሚፈጸመው ታላቅ የመቤዠት ሥራ ዋዜማዎች ናቸው ። "ወደ እናንተ ደርሳለች" ፣ በግሪኩ ግሥ ፣ አስቀድማ መጥታለች የሚል ትርጉም አለው ። ገና መድረስዋ ነው ፤ ነገር ግን በፍጹም ሙላቷ አይደለም ። ኃይሏ እንዲገለጥ መስቀልና ትንሣኤ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው ። 29/ የኢየሱስ አገልግሎት ወደ ሞት ግዛት ውስጥ ገብቶ ምርኮኞችን ነጻ ከማውጣቱ የሰይጣንን ሥራ የሚያስርና ሥራውን ሁሉ የሚያቆም ነው ፤ ዕብ- 2፡14-18 ። 30/ ከሰይጣን ጋር የሚደረገው ጦርነት የክርስቶስን ተልእኮ በሙሉ ልብ መደገፍን ይጠይቃል ። በቁ- 30 ላይ "ከኔ ጋር" ማለቱ እርሱን መደገፋቸውን የሚያመለክት ነው ። በማር- 9፡40ና በሉቃስ 9፡50 ባለው ተመሳሳይ አባባል እኛን ማለቱ ከቡድኑ ጋር መተባበር እንደሚያስፈልግ ያሳያል ።

31/ "መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ" ፣ መልካሙን ነገር ሁሉ ክፉ አድርጎ መቁጠርን የሚጠቁም ይመስላል ፤ ማር- 3፡30 ። "አይሰረይለትም" ፣ ምክንያቱም በዚያ ጸንተው የሚኖሩ ሁሉ ይቅርታ በማይገኝበት ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን ስለሚያኖሩ ነው ፤ ዮሐ- 3፡19-21 ። 32/ "በሰው ልጅ ላይ" ፣ ምናልባት ሕዝቡ ሰው ብቻ መስሎአቸው አምላካዊ ጠባዩን ሳያዩ ሊቀሩ ይችላሉ ፤ ነገር ግን በአእምሮ ከመካድ ልዩ ነው ። 33/ "የዛፍ" ተፈጥሮ የፍሬውን ሁኔታ ይወስናል ። ፈሪሳውያን ፍሬውን መልካም በማድረግ ዛፉን መልካም የሚያደርጉ መስሎአቸው ነበር ። ኢየሱስ ሊቀድም የሚገባውን ዋና ነገር አሳያቸው ። 34/ ምንጊዜም ቢሆን ክፉ ጠባይ ክፉ አነጋገርን ማፍራቱ አይቀርም ። ፈሪሳውያን በ3፡7ና 23፡33 ላይ "እፉኝት" ተብለው ተጠርተዋል ። 36-37/ ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚናገሩት "ከንቱ" ነገር ከንቱ የሆነውን ጠባያቸውን በትክክል ያመለክታል ። ፈሪሳውያን ስለ ኢየሱስ የተናገሩት ከንቱ ንግግር ማንነታቸውን ገልጾአል ። በመጨረሻም የሚያጸድቃቸው ወይም ለሚኰንናቸው ሥራዎቹ ማስረጃ ይሆናል ። ባሕርዩን የሚገልጡት ጥቃቅን መስለው የሚታዩት ሥራዎች የኩነኔ መግለጫዎች መሆናቸው በ25፡31-46 ተገልጾአል ።

## በሙሉ ልብ ስለመከተል የቀረቡ ትእዛዞች 12፡38-50

በሙሉ ልብ ስለመከተል የቀረቡ ትእዛዞች 12፡38-50

ከቁ- 38-42 ጋር ሉቃስ 11፡16ና 29-32ን ፣ ከቁ- 43-45 ጋር ሉቃስ 11፡24-26ን ፣ ከቁ- 46-50 ጋር ማር- 3፡31-35ና ሉቃስ 8፡19-21ን አወዳድሩ ። ስለ ንስሐ መግባትና ስለ ደቀ መዝሙርነት ያቀረባቸው ሶስት ጥሪዎች ፣ ከአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች ጋር ወደ አለመግባባት ደረጃ አደረሱት ፤ ከዚያም አልፎ ወንጌልን ለአሕዛብ በመስበኩ ምክንያት ደጋፊዎችንና ተቃዋሚዎችን ያስነሣውን አገልግሎቱን ያብራራሉ ።

38-39/ "ምልክት" ፣ ኢየሱስ ለነርሱ ሠርቶ ሊያሳያቸው ያልፈለገው አንድ እንደብርቅ የሚቆጠር ድርጊት ነው ፤ 4፡5-7 ፤ ዮሐ- 4፡48 ፣ 1 ቆሮ- 1፡22 ። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ምልክቶች የተባሉትን ብዙ ተአምራት አይተው ነበር ፤ ነገር ግን ሰው ብርቅ ነገሮችን አይቶ በቃኝ ስለማይል ወደ እምነት ይመራዋል ለማለት አስቸጋሪ ነው ፤ ሉቃስ 16፡30 ። ከእግዚአብሔር በመራቅ ምልክትን በመፈለግ ላይ የተመሠረተ እምነት የነበራቸው አመን

ዝራዎች ነበሩ ። "ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በስተቀር"፣ ምንም እንኳ ከሲኦል ሆድ አምልጦ በራሱ ሰውነት ምልክትን ቢያሳይም ፤ ዋናው ፣ ምልክት ሰዎችን ወደ ንስሐ የመለሰው የዮናስ ስብከት ነበረ ዮናስ 2፡22 1 ጴጥ- 3፡18-20 ። 40/ ይህ የዮናስን ታሪክ መላ ትርጉሙን አውጥቶ ያሳያል ። በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ግን ጠቅላላ አነጋገሩ ብቻ ይገኛል ። "በዓሣ አንባሪ" ፣ ታላቅ ዓሣ ነበረ ፤ ዮናስ 1፡7 ። "ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት" ፣ የአይሁድ ባሕላዊ አስተሳሰብ ይመስላል ። በሶስተኛው ቀን የተደረገውን የክርስቶስን ትንሣኤ ለማስተባበል የሚያመለክት አይደለም ፤ 16፡21 ። 41/ "የሚበልጥ" ፣ በመሲሁ ሰውነት የተመሰለ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው ። "የነነዌ ሰዎች" ፣ እሕዛብ ሆነው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጨቋኞች ነበሩ ። 42/ "ንግሥተ አዜብ" ፣ እውነትን ለማወቅ ከነበራት ምኞት የተነሣ ከዓረብ አገር ከሳባ ተነሥታ ረጅም ጉዞ ያደረገች ንግሥት ነች ፤ 1 ነገ- 10፡1-10 ። "የዚህ ትውልድ" ሰዎች በመካከላቸው የተደረገውን እጅግ ከፍ ያለውን መንፈሳዊ ገለጻ አልተቀበሉም ።

43-45/ ምንም እንኳ እውነተኛው ነገር ለግላዊ ሁኔታ የተመለከተ ቢሆንም አነጋገሩ የሚጠቅሰው በአጠቃላይ አይሁዳውያንን ነው ። ከዮሐንስ አገልግሎት የተነሣ አንድ ዓይነት የተሃድሶ ንቅናቄ ታይቶ ነበር ። ከዚያ በኋላ ኢየሱስ አጋንንትን አስወጣ ። ነገር ግን ንስሐ ከገባ በኋላ በእግዚአብሔር መንፈስ ያልተለወጠ ሰው በበለጠ መንፈሳዊ ውድቀት ውስጥ ሊነከር ይችላል ። የአጋንንት መኖሪያቸው "ውኃ የሌለበት" በረሃ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር ። 46/ "ወንድሞች" ፣ ምናልባት የዮሴፍና የማርያም ታናናሽ ልጆች ይሆናሉ ። በዚህን ጊዜ ዮሴፍ ሞቶ እንደነበረ ይታሰባል ። በብዙ ብራናዎች ውስጥ ቁ- 47 ተጽፎ አይገኝም ። 50/ እዚህ ላይ የተቆጠረው ዝምድና የአካል ሳይሆን ሥነ ምግባራዊና መንፈሳዊ ዝምድና ነው ። ከርሱ ጋር ከአንድ "አባት" እንደ ተወለዱ ልጆች መሆንና ፈቃዱንም ማድረግ ማለት ነው ፤ 5፡43-48 ፣ 6፡9 ፣ ሉቃስ 11፡28 ።

## ስለ መንግሥተ ሰማያት የተነገሩ ምሳሌዎች 13፡1-52

ቀደም ሲል በቀረቡት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት ታሪኮች እምነትንና አለማመንን አነጻጽረዋል ። አሁን መንግሥተ ሰማያትን የሚያመለክቱ ሰባት ምሳሌዎች ይህን ውጥረት በተለያዩ መልኮች ይገልጻሉ ። በቁ- 1-23 የሚገኘው የዘሪው ምሳሌና ትርጉሙ እንዲሁም በምሳሌ ማስተማር ያስፈለገበት ምክንያት በማር- 4፡1-20 ውስጥ ከተገለጸው ጋር ይስማማል ፤ ሉቃስ 8፡ 4-15 ። ነገር ግን ቁ- 16፡17 ከሉቃስ 10፡23-24 ጋር ይመሳሰላል ። በቁ- 24-30 ያለው የእንክርዳዱ ምሳሌና ትርጉሙ ቁ- 36-43 የሚገኘው በማቴዎስ ብቻ ነው ። በቁ- 31-32 ያለው የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ በማርቆስ 4፡30-32 ላይ ተደግሞ ይገኛል ፤ ሉቃስ 13፡18 ። የእርሾው ምሳሌ በሉቃስ 13፡20 ውስጥ ይገኛል ፤ ቁ- 33 ። በምሳሌ የመጠቀም ልማድ ቁ- 34 በማርቆስ ውስጥ ተጠቅሶ ሲገኝ ማርቆስ ማብራሪያ ጥቅስ ጨምሯል ፤ ማር- 4፡33-34 ። የመደምደሚያ ቁጥሮች —51ና 52 ፣ የመዝገብ ምሳሌ —ቁ- 44 ፣ የዕንቁ ምሳሌ —ቁ-45 ፣ እንዲሁም የመረብ ምሳሌ —ቁ-47-50 የሚገኙት በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ።

ኢየሱስ በአደባባይ ከሚሰጣቸው ትምህርቶችና በግል ከሚሰጣቸው የተለዩ እንደነበሩ ማቴዎስ በሶስተኛው የንግግር ቅንብር ውስጥ በግልጽ ያስረዳል ። የምሳሌ ጥቅም መንፈሳዊ ወይም ሥነ ምግባራዊ ሐቅን መግለጥ ነበረ ። በዝርዝር ከሚገልጽ ከአንድ የተረት አባባል የተለየ ነው ። ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ንኡስ ነጥቦች ቢኖሩም አንድ ምሳሌ አንድ ዓይነተኛ ግብ አለው ፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ በአጋጣሚ ጊዜ ተረት ነክ የሆነ ትምህርት አላስተማረም ብሎ መካድ አያስፈልግም ። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የአንድ ምሳሌ ዋና ዓላማ ፣ ሰዎችን ስለአንድ ጉዳይ በሚያስቅ - 17-3-5 ፣ ወይም በሚያሳዝን አኳኋን— 2 ሳሙ- 12፡1-7 ፣ ማቴ- 21፡33-41 ፣ ወደ ቁርጠኛ ውሳኔ ማምጣት ነው ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ምሳሌዎች በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በመካከላቸው የመጣችውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ስለሚቀበሉት ሁኔታ የሚያስተምሩ ናቸው ። በዘመናችን ያሉት አንዳንድ ምሁራን ፣ ምሳሌና ተረት በፍጹም የተለያዩ ነገሮች ናቸው የሚል አሳብ አቅርበዋል ፤ ስለዚህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ፣ ኢየሱስ የሰጠውን ምሳሌ በሚገባ ባለመረዳቷ የተናገረውን በቀጥታ በምሳሌ ረገድ በመጠቀም ፈንታ ዝርዝር አሳብ በመስጠቷ ከዋና ፍሬ ነገር ወጣች ፣ ስለዚህ የዘሪውና የእንክርዳዱ ምሳሌ የኢየሱስ ሳይሆን የርስዋ ነው ብለው አስተምረዋል ። ይህ መላምት የኢየሱስ የቅርብ ተከታዮቹ እንኳን የምሳሌውን ትርጉም አልተረዱም ስለሚል ችግሩን ያባብሰዋል ። የምሳሌ ቁም ነገር የክርስቶስን መንግሥት መምጣትና ድል ማድረግ ማብሰር ነው ብንልም የሰሚዎችን መልሶች የሚገልጡት ሐረጎች የኢየሱስ አይደሉም ለማለት አንገደድም ።

ከቁ- 1-9 ባሉት ጥቅሶች የተነገረው ምሳሌ ትርጉም በቁ- 18-23 ውስጥ ይገኛል ። 10-15/ ምናልባት ቁ- 12 በሌላ ጊዜ የተነገረ ቢሆንም እነዚህ ቁጥሮች ለመተርጎም በጣም አስቸጋሪ በመሆናቸው ምክንያት በኋላ ላለመጻፋቸው በቂ ማረጋገጫ ነው ፤ ማር- 4፡25 ። "ተሰጥቶአችኋል" ፣ በማናቸውም መንፈሳዊ መገለጽ ውስጥ የእግዚአብሔር የሰጭነት ሥልጣን የተጠበቀ መሆን አለበት ፤ 11፡27 ። "አልተሰጣቸውም" ፣ ውጤቱ የተገለጠው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። ማቴዎስ "እያዩ ስለማያዩ" ብሎ ሲናገር ማርቆስና ሉቃስ ደግሞ እንዳያዩ ይላሉ ፣ በአራም ቋንቋ ተነግሮ እንደሆነ ሁለቱም ትርጉሞች ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ ። በአነጋገሩ ውስጥ ትርጉሙ የተለያየ አይደለም ። ምሳሌዎች የተሰጡት ሐቁን ለመቀበል ያልተዘጋጁት ሰዎች እንዳይረዱት ተደርጎ ይመስላል ። ይህንን ለመደገፍ ኢሳ- 6፡9ን የጠቀሰው ማቴዎስ ብቻ ነው ፤ ዮሐ- 12፡39-41 ፣ የሐዋ- 28፡26 ። ምሳሌዎች ፣ የማያምኑትን ሰዎች እንዳ

ያምኑ ለማድረግ የተሰጡ ናቸው ብሎ መገመት አይገ ባም ። ነገር ግን ምናልባት የነበረውን ሁኔታ ለማጠና ከር የተሰጡ ይሆናሉ ፣ ዮሐ- 9፡39 ፣ 3፡17-19 ። አለማመ ን ታላቅ ፍርድ የሚያስከትል መሆኑን ምሳሌው ይጠ ቁማል ፤ ስለዚህ ሰዎች ሐቁን ሳይረዱ ምሳሌውን ቢያ ስተውሉ ፣ ምሳሌዎች ወንጌልን የመስበኪያ ሥዕላዊ ዘዴ ናቸው የሚለው አስተያየት ለኢሳ- 6፡9 አተጋቢ ትርጉም አይሆንም ። ቁ- 16ና 17 ሐዋርያት በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ቅዱሳን የበለጠ ዕድል እንዳገኙ ያመለ ክታሉ ፤ ዕብ- 11፡39 ። ሉቃስ "ጻድቃን" በማለት ፈንታ ንጉሦች ይላል ። 18-23/ ወንጌልን የሚሰሙትን ልዩ ልዩ ዓይነት ሰዎችን ያሳያል ፡— 1ኛው ተመልካች ብቻ ነው ፣ 2ኛው ውስጠ ባዶ ነው ፤ 3ኛው ስግብግብ ሲሆን 4ኛው ተቀባይ ልብ ያለው ነው ። ዘሩ ያው ነው ፤ መሬቱ ግን የተለያየ ነው ። "ከፉው" ፣ ተቃውሞ ከሰ ይጣን ይመጣል ፤ 6፡13 ። ከዓለም ውስጥ "መከራና ስደት" ይነሣሉ ፤ 24፡9-13 ። በዓለም አሳብና ባለጠግ ነት በመታለል ሰዎች ወንጌልን እንደማይታዘዙ ያመ ለክታል ፤ 19፡23 ። ዘሩ የተዘራው መጀመሪያ በኢየ ሱስ ቀጥሎ ደግሞ በሐዋርያት ነው ። ብዙ ዘር ቢባክ ንም የተትረፈረፈ መከር ይታፈሳል ።

24/ "በእርሻው - - - የዘራውን ሰው" ፣ መንግሥትንና ሰውን ለማወዳደር ሳይሆን የነገሩን ሁኔታ ለማነጻጸር ነው ። በምስጢር ከሚያድገው ዘር ምሳሌ ጋር ተመሳ ሳይነት አለው ፤ ማር- 4፡26-29 ። ነገር ግን ልዩነቶቹ ብዙ ስለሆኑ ካንድ ታሪክ የመነጩ ናቸው ማለት አያስ ችልም ። ከ24-30 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የሚገኘው ምሳሌ ከ36-46 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ተብራርቶአል ። 31-32/ አጀማመሩ ምንም አነስተኛና የማያስደንቅ ቢሆንም መጨረሻው ያልተጠበቀና አስገራሚ ይሆ ናል ። በይሁዳ የሰናፍጭ ተክል ሶስት ሜትርና ከዚያም ይበልጥ ሊያድግ ይችላል ። "የሰማይ ወፎች" ፣ በጠ ቅላላው የአሕዛብ መንግሥታት ናቸው ፤ ዳን- 4፡20-22 ። በኢየሱስ ዘመን የነበሩት ሰዎች ወንጌል ምን ያህል እንደሚስፋፋ ለማወቅ ያዳግታቸው ነበር ። 33/ የመ ንግሥተ ሰማያት የሥራ ውጤት ጥልቅና ሰፊ ነበረ ፤ ወንጌል በተዳረሰባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ ሁሉ ለውጥ ሳያስከትል አይቀርም ። "እርሾ" ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የመጥፎ ነገር ምሳሌ ቢሆንም በዚህ ውስጥ ግን ትርጉሙ ይህ አይደለም ።

34-35/ በምሳሌ መናገሩ የትንቢት ፍጻሜ እንደሆነ አመለከታቸው ። አንዳንድ ብራናዎች "ነቢዩ" በማ ለት ፈንታ ኢሳይያስ ይላሉ ፤ ይህ ግን ልክ አይደለም ። ምናልባት ማቴዎስ ከመዝ- 77፡2 ጠቅሶ ይሆናል ፤ መዝሙሩን የጻፈው አሳፍ በ1 ዜና- 25፡2 ነቢይ ተብሎ ተጠርቷል ። ነገር ግን በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ባለ መዝሙሩ ነቢይ ሆኖ ተናገረ ። አሳፍ በብሉይ ኪዳን መሠረት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲቤዥና በኪዳኑ መሠረት እንደሚፈርድላቸው የገባውን የእግዚአብሔ ርን ቃል ኪዳን ይገልጻል ፤ ጥቅሱ ከዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የተገኘ ነው ። 36-43/ "እንክርዳዱ" ፣ የሚያመ ለክተው አረምን ሲሆን ከስንዴ ጋር በጣም ይመሳሰ ላል ። "በዓለም መጨረሻ ፣ ምሳሌው ያለ ወቅቱ መከር መሰብሰብ እንደማይገባ ያስጠንቅቃል ፤ ቁ- 28-30ና 1 ቆሮ- 4፡5 ። የሰው ልጅ "መልካም ዘርንና ዲያብሎ ስም እንክርዳድን" ስለሚዘራ የመልካምና የክፉ ቅይጥ የሆነ ኅብረተ ሰብ ይፈጠራል ፤ በመጨረሻው የመከር ጊዜ ግን እውነቱ ተገልጾ ሰዎች አመጸኞችና ጻድቃን ተብለው ለሁለት ይከፈላሉ ። ይህ በሰው ልጅና በመላ እክቱ የሚደረግ የመጨረሻው መለያ ነው ፤ 24፡30 ፣ 25፡31-46 ። ተቀባይነት ያላገኙት ይሠቃያሉ ፤ 3፡12 ፣ 22፡13ና 25፡30 ። ተቀባይነት ያገኙት ደግሞ እንደ ከዋክብት ያበራሉ ፤ ዳን- 12፡3 ።

44-46/ ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሲል ሁሉን ነገር የሚሰጥ መሆኑን ያስተምራሉ ብለው አንዳንዶች ለእ ነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ያወጡት ትርጉም ትክክል ላይ ሆን ይችላል ። ይልቁንም የመንግሥተ ሰማያት ጥቅም የማይለካ በመሆኑ መንግሥተ ሰማያት ለማግኘት ማና ቸውም ዓይነት መሥዋዕትነት ቢከፈል በዛ ለማለት የማይቻል መሆኑን ያስተምራሉ ፤ 16፡24-27 ። በነዚህ በሁለቱ መካከል የትርጉም ልዩነት ቢኖር የመጀመሪ ያው አንድ ሰው መንግሥተ ሰማያትን ሳይፈልግ እን ዲያው እንደደረሰበት ያሳያል ፤ ሁለተኛው ደግሞ ሌላ ሰው ተመራምሮ ከመድረሱ በፊት በማናቸውም ዓይ ነት መንገድ ይፈልግ እንደነበረ ያሳያል ። 47-50/ የመ ረቡ ምሳሌ ከእንክርዳዱ ጋር የሚመሳሰል ትርጉም አለው ። ከባሕር ውስጥ የሚሰበሰብ ታላቅ መከር አለ ፤ ዮሐ- 21፡11 ። ነገር ግን የሚጠመደው ቅልቅል ዓይነት ስለሆነ በዓለም መጨረሻ ላይ ከዚያ ውስጥ የሚለዩ አሉ ። 51-52/ ሐዋርያት መረዳት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ያሳያል ። እነዚያ ትምህርቱን የተረዱት ሰዎች ፣ የኦሪትን ሕግ እንደሚያውቁ ጻፎች ሆነው በወንጌል ትምህርት የሠለጠኑ በመሆናቸው "የመንግሥተ ሰማ ያት ደቀ መዛሙርት" ይባሉ ነበር ። ማቴዎስ በዚህ ምሳሌ ውስጥ የራሱን ተግባር ገልጾአል የሚል አስተ ያየት ተሰጥቶአል ።

## ክርስቶስን ስላለመቀበላቸው 13፡53-17፡27

ማቴዎስ እምነትንና አለማመንን የሚያስረዱ ምሳሌ ዎችን ከሰበሰበ በኋላ የማርቆስን ቅደም ተከተል በመ ጠበቅ ኢየሱስ እንዲጠላና እንዲሞት ያደረገውን ፣ ከአይ ሁድ መሪዎች ጋር እየተፋፋመ የሄደውን ግጭት ይገል ጻል ። ማቴዎስ የማርቆስን ቅደም ተከተል እየጠበቀ ፣ ጴጥሮስ በውኃ ላይ ስለመሄዱ— 14፡28-31 ፤ በፈሪሳ ውያን ላይ ትችት ስለመስጠቱ — 15፡12-14 ፣ ለጴጥሮስ ስለተሰጠው ተስፋ — 16፡17-19 ፣ ለቤተ መቅደስ ስለ ሚከፈል ግብር — 17፡24-27 ፣ ጨምሮ ጽፎአል ። በነ ዚህ በሶስቱ ውስጥ ጴጥሮስ በግልጽ ሲሠራ ይታያል ። ይህ የወንጌሉ ክፍል ባንድ በኩል ከፍተኛ ነጥብ ወደ ሆነው በተራራው ላይ ወደመለወጡ የሚመሩትን ተአ ምራትና የጴጥሮስን ምስክርነት ሲገልጽ በሌላ በኩል ደግሞ በገዛ ቤቱ ውስጥ እንደተገፋ ፣ ዮሐንስንም እንዳ ልተቀበሉት ፣ ከፈሪሳውያን ጋር የተፈጠረውን ክርክር ፣ ሐዋርያት ታማኞች አለመሆናቸውንና የኢየሱስን መከ ራና ሞት የሚጠቁመውን ትንቢት ይገልጻል ።

## ኢየሱስን ስለመበቀላቸውና ስለ ዮሐንስ መገደል 13፡53-14፡12

ከዚህ ክፍል ጋር ማር- 6፡1-6 ፥ 14-29ንና ሉቃስ 9፡7ን አንብቡ ። ማቴዎስ ኢየሱስን ስላለመቀበላቸው የጻፈው ታሪክ ከማርቆስ ጋር ይመሳሰላል ፤ ነገር ግን ስለ ዮሐንስ አሟሟት የሰጠው ገለጻ አጭር ነው ። ሉቃስ የአለመቀበላቸውን ታሪክ አይጨምርም ፤ ምክንያቱም በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ተመሳሳይ የሆነ ታሪክ ሰጥቶ ስለነበረ ነው ፤ ሉቃስ 4፡16-30 ። በጨረፍታ ብቻ የዮሐንስን አሟሟት ይጠቅሳል ፤ ሉቃስ 9፡7-9 ።

ቁ- 53 ምሳሌዎችን ከሚቀጥለው ንግግር ጋር ያያይዛል ፤ 11፡1 ። 54/ "ወደ ገዛ አገሩም" ፥ ወዳደገበት አገር ወደ ናዝሬት ማለት ሳይሆን አይቀርም ፤ 2፡23 ። ማንኛውም አይሁዳዊ "በምኩራባቸው ያስተምራቸው ዘንድ" ይጋበዝ ነበር ። "ጥበብ" ፥ ምናልባት የክርስቶስን የማስተማር ችሎታ ሊጠቁም ይችላል ፤ ነገር ግን ተአምራት በዚያ ሠርቶ እንደሆን በግልጽ አይታወቅም ። 55/ "የጸራቢ ልጅ" ፥ ማርቆስ አናጢ ይላል ። ተክቶን የሚለው የግሪኩ ቃል ግንበኛ የሚል ትርጉም አለው ። የዮሴፍ ስም አለመጠቀሱ እንደሞተ ሊያመለክት ይችላል ፤ 12፡46 ። 56/ "እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው ?" በመካከላቸውና ዝነኛ ባልሆነች ከተማ በማደጉ ኢየሱስ የሚሠራውን ድንቅ ሥራ ለማመን አስቸጋሪ ሆነባቸው ። 57/ ከዚህ የተነሣ "ተሰናከሉበትም" ፥ ስለዚህ በርሱ ላለማመናቸው አንዳንድ ምክንያቶች ፈለጉ ። "ነቢይ" ፥ ምንም እንኳ አነጋገሩ በባሕላቸው የታወቀ ቢሆንም ኢየሱስ ይህንን ስም ለራሱ መጠሪያ እንዲሆን አድርጎታል ። "ከገዛ ቤቱ" ፥ ዮሐ- 7፡5 የወንድሞቹን አለማመን ይገልጻል ። 58/ በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም ብሎ ማርቆስ በደፈናው ቢጽፍም ጥፋታቸውን ለማቅለል ብሎ ጥቂት የታመሙ ሰዎችን እንደፈወሰ አመልክቶአል ።

14፡1/ ምንም እንኳ የራሱ ወገኖች ባያምኑበትም "የኢየሱስ ዝና" እስከ "ሄሮድስ" ግዛት ደረሰ ። ይኸኛው ሄሮድስ ፥ ከአባቱ ግዛት የገሊላንና የፔሪያን አውራጃዎች ይገዛ የነበረው የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ሄሮድስ አንቲጳስ ነው ። 2/ ኢየሱስና ዮሐንስ ባንድ ጊዜ አለማገልገላቸውን ያመለክታል ፤ 4፡12 ። ሄሮድስ ሁለቱም በአንድ ጊዜ መሥራታቸውን ሰምቶ ቢሆን ኖሮ ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ባልኖረው ነበር ። ሰዎች ዮሐንስ ከሞት ተነሥቶአል የሚል መሠረተ ቢስ እምነት እንደ ነበራቸው ሉቃስ ጽፎአል ። "ኃይል በርሱ ይደረጋል" ፥ ኢየሱስ የፈጸማቸውን ተአምራት መጥቀሱ ይመስላል ። ዮሐንስ ተአምራትን ሠርቶ አላሳየም ፥ ዮሐ- 10፡41 ። ሄሮድስ ከዓመጸኛ አስተሳሰቡ የተነሣ ኢየሱስንና ዮሐንስን ለመለየት አልቻለም ይሆናል ። 3/ ዩሲፈስ የተባለው ደራሲ ሲጽፍ ዮሐንስ የአመፅ እንቅስቃሴ ያስነሣል ተብሎ በመጠርጠሩ ታስሮ ነበር ይላል ። ይህ ለምክንያት የተደረገ ሲሆን ዋናው ምክንያት ግን ግላዊ ነበረ ። "ፊልጶስ" ፥ በሉቃስ 3፡1 ላይ የተጠቀሰው አይደለም ። 4/ ዘሌ- 18፡16ና 20-21 ይህን ዓይነት ድርጊት ይከለክላል ፤ ይህ ዘመድን እንደማግባት የሚቆጠር ነበር ። 5/ "ሊገድለው ወዶ ሳለ" ፥ ሄሮድስ በደስታ ያዳምጠው ነበር ፤ ነገር ግን እርሱን ለመግደል የፈለገችው ሄሮድያዳ ነበረች ሲል ማርቆስ አመልክቶአል ። በወንጀል በተወሳሰበ ሁኔታ ውስጥ የምክንያቶቹ መደባለቅ አዲስ ነገር አይሆንም ። የካህናት አለቆችና መሪዎች በዮሐንስ ዝና ምክንያት እንደዚሁ ፈርተው ነበር ፤ 21፡26 ። 6/ በዚህ ዓይነት ግብዣ የሚገኙ ወንዶች ብቻ ነበሩ ፤ ስለዚህ ዘፈኗ አሳፋሪ መልክ ሳይኖረው አልቀረም ። "የሄሮድያዳ ሴት ልጅ" ፥ በኋላ አጐቷ የሆነው የአራተኛውን ክፍል ገዢ ፊልጶስን አግብታ የነበረችው ሳሎሜ ሳትሆን አትቀርም ። ይህ ሰው አባቱ ከገዛው ግዛት አንድ ሩብ ስለተሰጠው የአራተኛው ክፍል ገዢ ተብሎ ተጠራ ። 7/ ይህን የመሰለ የጥድፊያ መሐላ ሊያደርግ የቻለው ምናልባት በስካር ምክንያት ሊሆን ይችላል ። 8/ ሄሮድያዳ ይህን የመሰለ አጋጣሚ ጊዜ ትጠብቅ ነበር ። 10/ ዮሴፈስ ዮሐንስ ከጨው ባሕር በስተምሥራቅ በምትገኘው ማኬሩስ በምትባል ምሽግ ውስጥ ታስሮ እንደነበረ ጽፎአል ፤ ወህኒ ቤቱም ፥ እዚያ ከሚገኘው የቤተ መንግሥት ግንብ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ። 12/ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ያደረጉት ድርጊት ጀብዱ ነበረ ። "መጥተው ለኢየሱስ አወሩለት" የሚለውን የመዘገበ ማቴዎስ ብቻ ነው ። ጥቂቶች ገና ዮሐንስን ቢከተሉም ፥ ኢየሱስ ለሚበዙት መሪያቸው ሆነ ፥ የሐዋ- 18፡24-19፡7 ።

## አምስት ሺህ ሰዎችን መመገቡና በባሕር ላይ መሄዱ 14፡13-36

ከዚህ ክፍል ጋር ማር- 6፡31-56ና ሉቃስ 9፡10-17ን አንብቡ ። ሉቃስ ሕዝቡን ስለመመገቡ ብቻ ጽፎአል ። የኢየሱስን ሕማማት በሚገልጡባቸው ዘገባዎች ውስጥ አራቱ ወንጌሎች ሙሉ በሙሉ የሚስማሙት በዚህ ተአምር ላይ ስለሆነ ልዩ ትኩረት የሰጡት መሆኑን ሳያመለክት አይቀርም ።

ቁ- 13 ታሪኩን ከቁ- 2 ጋር ያገናኘዋል ። ቁ- 3-12 ሄሮድስ በምን ምክንያት እንደ ተጨነቀ ይገልጻሉ ። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ሄሮድስን ለመጋፈጥ ዝግጁ አልነበረም ። ሄሮድስ እውነትን ለመቀበል የመጨረሻ ዕድል እንደተሰጠው ሉቃስ ያመለክታል ፤ ሉቃስ 13፡31-33ና 23፡6-12 ። ኢየሱስ ግን ከሕዝቡ ተለይቶ ሊሄድ አልቻለም ። 14/ ማርቆስ ኢየሱስ ያዘነው ሕዝቡ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች ስለነበሩ ነው ሲል ጽፎአል ።

15-18/ እነዚህ ቁጥሮች በደቀ መዛሙርቱ መካከል እምነትን መቀስቀስ የቱን ያህል አስቸጋሪ እንደነበረ ይናገራሉ ፤ ቢሆንም ታዛዦች ነበሩ ። "አምስት እንጀራ" ፥ አብዛኞቹ ሰዎች የበሉት የገብስ እንጀራ ሳይሆን አይቀርም ፤ ዓሣውም የደረቀ ወይም የተቀመመና የሚጣፍጥ ሳይሆን አይቀርም ። 19/ እነዚህ ሶስት ድርጊቶች ማለት ማንሣት ፥ መባረክና እንዲሁም መቁረስ በአይሁድ ምግብ ጊዜ የተለመዱ አሠራሮች ቢሆኑም ከመጨረሻውም እራት ጋር የተያያዙ ሳይሆኑ አይቀሩም ፤ 26፡26 ። "ባረከ" ፥ እግዚአብሔርን አመሰገነ ማለት ነው ።

20/ ምግቡ ካስፈላጊው በላይ ሆኖ መገኘቱ በታሪኩ ውስጥ ልዩ ትኩረት ያለው ነጥብ ነው ፤ 2 ነገ- 4፡42-44 ። ምንም እንኳ ይህ ለተራቡ ሰዎች የተደረገ ተአምር ቢሆንም ኢየሱስ የሚሠራው እንጀራንና ዓሣን ሁልጊዜ በሚባርክ በፈጣሪ ኃይል መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ሆኗል ። እዚህ ላይ የመፍጠር ሥራ በፍጥነት ተከናውኗል ። በዓለም መጨረሻ ወደሚደረገው ፣ በራዕይ 19፡9 ውስጥ ወደተጠቀሰው ወደ በጉ ሠርግ እራት ያመለክታል ። ዮሐንስ ስለዚህ ተአምር በጻፈው መግለጫ ውስጥ ኢየሱስ ከተአምሩ በኋላ እስራኤላውያን በበረሃ መና ስለመመገባቸው መናገሩን አመልክቶአል ። ማርቆስ በለመለመው ሣር ፣ በተሰበሰቡት ወንዶችና በቡድን በቡድን በመቀመጣቸው ላይ ማተኮሩ ፣ መሲህ በፋሲካ ወራት ይመጣል ብለው ሰዎች ተስፋ ስላደረጉ፣ ኢየሱስን ንጉሣቸው ለማድረግ ማቀዳቸውን ይገልጻል ብለው ብዙዎች አሳብ አቅርበዋል ። የዮሐንስ አተራረክ ለዚህ ትርጉም ብርቱ ድጋፍ ሲሰጥ የማቴዎስ አጻጻፍ ግን ድጋፍ አይሰጥም ። 21/ "በቀር" ፣ የግሪኩ ኮርስ የሚለው ቃል ሴቶችና ልጆች አለመገኘታቸውን ሊያመለክት ይችላል ፤ ነገር ግን በዚህ ውስጥ ትርጉሙ ይህ አይደለም ።

22-23/ ቁ- 13ን ተመልከቱ ። ኢየሱስ ብቻውን ሆኖ የሚጸልይበት አመቺ ጊዜ ለማግኘት የማያቋርጥ ፍላጎት ነበረው ። "ወደ ማዶ" ፣ ወደ የትኛው የሐይቅ ክፍል እንደሚሻገሩ አልታወቀም ። 25/ "በአራተኛው ክፍል" ፣ ከሌሊቱ 9 እስከ 12 ሰዓት ይሆናል ። "በባሕር ላይ እየሄደ" ፣ ግሪኩ በባሕሩ ዳር ተብሎ ሊተረጐም ይቻላል ፤ ነገር ግን ይህ ትርጉም ከሁኔታው ጋር አይስማማም ። ኢየሱስ በተፈጥሮ ላይ ያለው ኃይል በጉልህ ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጸላቸው ይመስላል ። 27/ "እኔ ነኝ" ፣ በግሪኩ አለሁ—ዘፀ- 3፡14 ፣ ወይም እኔ እርሱ ነኝ ፤ ኢሳ- 41፡4 ፣ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል ። ይህ አነጋገር በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብዙ ጊዜ አምላክ መሆኑን ሳያመለክት አይቀርም ፤ ነገር ግን እዚህ ላይ ዋናው አሳብ ይህ አይደለም ።

28/ ጴጥሮስ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት በችኰላ የመፈጸም ልማድ አለው ። 30-31/ ጴጥሮስ ሌላ ጊዜ አድርጎት እንደነበረው ፣ የሚደርስበትን ችግር በመርሳት ከአቅሙ በላይ የሆነውን ነገር አደርገዋለሁ ብሎ ቃል ገብቶ ነበር ፤ 26፡33-35 ። አንዳንድ ተመራማሪዎች እነዚህ ቁጥሮች የጴጥሮስን ሕይወት ታሪክ ያንጸባርቃሉ ብለው ቢያስቡም ፣ የማቴዎስ አሳብ ይህ እንዳልነበረ ግልጽ ነው ። 32/ 8፡26ን ተመልከቱ ። 33/ "በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ፣ ይህ አነጋገር በማርቆስ ወንጌል ውስጥ አይገኝም ። ጴጥሮስ ኢየሱስ የሠራውን ተአምር ከማየቱ የተነሣ ያወጣለት መጠሪያ ስም ሳይሆን አይቀርም ፤ 8፡27 ። የሆነ ሆኖ ጴጥሮስ በቂሣርያ ፊልጶስዩስ እንደሰጠው ምስክርነት ዓይነት ላይሆን ይችላል ፤ 16፡16 ። "ጌንሳሬጥ" ፣ በቅፍርናሆም ደቡብ ምዕራብ አቅራቢያ የምትገኝ ምድር ናት ። 36/ "የልብሱን ጫፍ ብቻ ሊዳስሱ" ፣ ጫፍ የሚለው የሚያመለክተው በአሪት ሕግ መሠረት በልብስ ላይ የተደረገውን ዘርፍ ሳይሆን አይቀርም ፤ 9፡20 ፣ ዘኁ- 15፡38 ። ይህንንም ያደረገችው በፍርሃት ሳይሆን በእውነት ከኢየሱስ ጋር ለመተዋወቅ ናፍቆት ያላት መሆኗን ለማመልከት ሊሆን ይችላል ።

## ስለ ሽማግሌዎች ወግና ሥርዓት 15፡1-20

በሉቃስ 6፡39 ላይ እንደተመለከተው ከቁ- 12-14 ካለው በስተቀር ይህ ክፍል ከማር- 7፡1-23 ጋር ተመሳሳይነት አለው ። ይህ ክፍለ ምንባብ ስለ እውነተኛ ሃይማኖት ትርጉም ከፈሪሳውያን ጋር እየተፋፋመ ስለሄደው ጸብ በሚገባ የሚያስረዳ ነው ።

1/ "ከኢየሩሳሌም" ፣ የገሊላው አገልግሎት በኢየሩሳሌም ውስጥ ከተሰማ በኋላ በሰዎች አእምሮ ውስጥ አድናቆትን ፈጠረ ። ምናልባት ኢየሱስን የአይሁድ ትምህርት ቤት መሪ አድርገው በመቁጠር ለተነሣው ክርክር ልዩ አስተያየት ይሰጣል ብለው ጠይቀውት ይሆናል ። 2/ "የሽማግሌዎች ወግ" ፣ ከታላላቆቹ የአይሁድ መምህራን የሚገኝ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚቆጠር ብቻ ሳይሆን ፣ ብዙውን ጊዜም መጻሕፍትን የሚተረጉም የአፈ ታሪክ ትምህርት ነው ። ከሐዋርያት ዘመን ቀጥሎ በነበረው ጊዜ ተሰብስቦ በመጽሐፍ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ ሚሽና ተብሎ ተጠራ። በነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ በሚሽና ውስጥ የሚገኘው ትምህርት ከአሪት ሕግ ጋር እኩል ነበረ ።

"እጃቸውን አይታጠቡም" ፣ የአሪት ሕግ ካህናት ራሳቸውን ከርኩሰት እንዲያነጹ ያዛል ፤ ዘሌ- 22፡1-16 ። ፈሪሳውያን ይህን ሕግ ያወጡት ሰዎች ሁሉ ካህናት ናቸው በማለት ሳይሆን አይቀርም ። 3/ የኢየሱስ ጥያቄ የፈሪሳውያንን ዋና ስሕተት ከመግለጹ ሌላ ትምህርታቸው ሥራቸውን የሚቃረን መሆኑን ያመለክታል ። ቁ- 4 ከዘጸ- 20፡12ና 21፡17 የተወሰደ ነው ።

5/ ማቴዎስ የአይሁድን ባሕል አላብራራም ፤ ደግሞ በማርቆስ የተጻፈውን ቁርባን የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ዘልሎታል ። አንድ ሰው ወላጆቹን በገንዘብ ለመርዳት ግዴታ ከመፈጸም ይልቅ ገንዘቤን ለቤተ መቅደስ ሰጥቼዋለሁ ብሎ ከግዴታው ነጻ ከሆነ በኋላ ለግል ጥቅሙ ያውለዋል ። በመጀመሪያ ምዕት ዓመት መጨረሻ ላይ የአይሁድ መምህራን ኢየሱስ በዚህ ላይ ያስተማረውን ትምህርት የደገፉ መሆናቸውን መጽሐፎቻቸው ይመሰክራሉ ። 6/ "ሻራችሁ" ፣ በሥራ ላይ አላዋላችሁትም ማለት ነው ፤ የኢየሱስ ዓላማ ግን የሕግ ፍጻሜ መሆን ነበረ ፤ 5፡17 ። 7-9/ ጥቅሱ የተመሠረተው በኢሳ- 29፡13 ላይ ነው ። ሰው ለራሱ በሚደነግገው ሥርዓት ላይ መደገፍ ጥቅም ቢስ መሆኑን ያመለክታል ። 10/ በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የተናገራቸው ቃላትና ያደረጋቸው ሥራዎች ሊሰጥ ላለው መመሪያ ልዩ ትኩረት ይሰጡታል ። 11/ የኢየሱስ አባባል ፣ በዘሌ- 11 ላይ ንጹሕና ንጹሕ ስላልሆኑ ምግቦች የተሰጠው ሕግ የማይለወጥ የሥነ ምግባር መመሪያ አለመሆኑን ያሳያል ፤ በማር- 7፡19 ላይ የሚገኘው ሐተታ ይህንን ትርጉም ይደግፋል ። 13/ "ያልተከለው ተክል" ፣ ይህ አባባል የፈሪሳውያንን ትምህርት ሳይሆን ፈሪሳውያንን

ራሳቸውን ይጠቁማል ፤ ኢሳ- 60፡21 ። 14/ ፈሪሳውያን የሙሴን ሕግ እንዳያበራ እያጨለሙ እኛ እናበራለን ብለው መመካታቸው እንደ ፌዝ የሚቆጠር ነው ፤ ሮሜ 2፡17-24 ። እነርሱና ደቀ መዛሙርታቸው ወደ መንፈሳዊ ጥፋት ጎዳና ይጓዛሉ ። 15/ "ምሳሌውን" ፣ ቁ- 11ን ያመለክታል ። 18/ "ከአፍ" ፣ እዚህ ላይ የሚ ያመለክተው የምግብን መግቢያ ሳይሆን ከመንፈሳዊ ርኩሰት ጋር የተቆጠረውን የሰውን "ልብ" ማለትም ሰው አስተሳሰቡንና ፈቃዱን የሚገልጽበትን መሣሪያ ነው ። 19/ ማቴዎስ ሰባት ዓይነት ኃጢአቶችን ብቻ ሲጽፍ ፣ ማርቆስ አሥራ ሶስት ጽፎአል ። ይሁን እንጂ በውሸት መመስከር የሚለው በማርቆስ ውስጥ አልተ ጠቀሰም ። 20/ "መብላትስ" ፣ ይህ ማጠቃለያ የሚ ገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ሲሆን ምናልባት ለማስ ታወሻ ያህል በሌላ ሰው እጅ ተጽፎ ይሆናል ።

## ሕመምተኞችን እንደገና ስለመፈወስና አ ራት ሺህ ሰዎችን ስለመመገቡ 15፡21-39

ይህ ክፍል ከአንዳንድ ለውጦችና የቃላት ማሳጠር በስተቀር ከማር- 7፡24-8፡10 ጋር ይመሳሰላል ። ተመ ሳሳይ ገለጻ በሉቃስ ውስጥ አይገኝም ። በዚህ ክፍለ ምንባብ ውስጥ ከአሕዛብ ወገን የሆነ ሰው የመፈወሱ ታሪክ ፣ ስለፈውስ አጠቃላይ መግለጫና ስለተሰበሰበው አራት ሺህ ሕዝብ መመገብ የተጻፈ ዘገባ እናገኛለን ።

21/ ኢየሱስ በአራት ከሚመኩት ከራሱ ሕዝብ ገለል ብሎ በአሕዛብ አገር ወደሚገኙት በክፋታቸው በጣም ወደታወቁት ወደ ሁለት ከተማዎች ተጠጋ ፤ 11፡22 ። 22/ "ከነናዊት" ፤ ከነዓናውያን ከዘመነ ኢያሱ በፊት በእስራኤል አገር ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ሲሆኑ የእስራ ኤላውያንን ባሕል ያበላሻሉ ተብለው ይጠሉ ነበር ፤ ዕዝራ 9፡1 ። የሆነ ሆኖ ይህችን የመሰለች እስራኤላዊት ያልሆነች ሴት "የዳዊት ልጅ" ብላ ኢየሱስን መጥራቷ ያስደንቃል ። 24/ ይህ የኢየሱስ አጠቃላይ መመሪያ ሲሆን አንዳንዴ ከዚሁ መመሪያ ውጭ ለመሥራት ፈቀደ ፤ 10፡5 ። 26/ ምናልባት ኢየሱስ ይህን የተናገረው እምነቷ እያደገ መሄዱን ባየ ጊዜ ሊያነቃቃት ሳይሆን አይቀርም ። ብዙ አይሁዶች አሕዛብን እንደ "ውሾች" ይቆጥሩአቸው ነበር ፤ 7፡6 ። 27/ የሰጠችውም መልስ እምነቷንና ትሕትናዋን ገለጸ ። 28/ በ8-13 እንደተገለ ጸው የዚህችን ሴት ልጅ የፈወሰው ከሩቅ ሆኖ ነው ። 30-31/ ማርቆስ ድርጊቱን በመዘገበበት ጊዜ የተፈወሰ አንድ ሰው ብቻ መሆኑን አስገንዝቧል ። ስለፈውስ ሥራው ሌሎች አጠቃላይ ገለጻዎች በ4፡23 ፣ በ9፡35ና በ19፡2 ተሰጥተዋል ። "የእስራኤልንም አምላክ" ፣ ይህ ሐረግ የፈውስ ሥራ በተፈጸመበት ሥፍራ ብዙ አሕዛብ እንደነበሩ ያስረዳል ። 32-39/ ብዙ ምሁራን ይህ ክፍል ስለ 5000ው ሰዎች መመገብ በድጋሚ የተ ጻፈ ነው ቢሉም ብዙ ልዩነቶች ተገኝተውበታል ፤ ማርቆስ አጭር አድርጎ በጻፈው ወንጌሉ ውስጥ ሁለቱን በመጥቀሱ የተለያዩ ድርጊቶች እንደተፈጸሙ ማመኑን ይገልጻል ። ማቴዎስ በጻፈው ታሪክ ውስጥ ፣ ሐዋርያት ኢየሱስ ቀደም ሲል ቁጥራቸው ከዚህ ለበለጡ ሰዎች ምግብ ማቅረቡን እያወቁ እንደገና ከየት እናገኛለን ብለው ጥያቄ ማቅረባቸው ግራ የሚያጋባ ነጥብ ነው ፤ ነገር ግን ግልጽ አድርገው ያላስረዱበት ምክንያት ሊኖር ይችላል ፤ 16፡9-12 ። ምናልባት ከነዚህ 5000 ሰዎች አብዛኞቹ አሕዛብ ነበሩ ። "መጌዶል" ፣ ይህ ስም የትኛውን አካባቢ እንደሚጠቅስ አልታወቀም ።

## ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን 16፡1-12

ይህ ክፍል ከማር- 8፡11-21 ጋር ይመሳሰላል ፤ ይሁን እንጂ ማቴዎስ ምልክቶችን በማስመልከት በሉቃስ 12፡54-56 የሚገኘውን አባባልና በክፍለ ምንባቡ መጨ ረሻ ላይ ያለውን ማብራሪያ ጨምሮአል ።

1/ ከዚህም በፊት ይህን የመሰለ ጥያቄ ቀርቦ ነበር ፤ 12፡38-42 ። አሁን በጉዳዩ ሰዱቃውያን ተጨምረዋል ። 2-3/ የቁጥር 2 ግማሽና ቁ- 3 በአንዳንድ ብራናዎች ውስጥ አይገኙም ። በሉቃስ ከተጠቀሰው የተለየ የአየር ሁኔታ ተጠቅሶአል ፤ አሳቡ ግን አንድ ነው ። በሰማይ ያሉትን ምልክቶች አይተው የአየርን ሁኔታ መረዳት መቻላቸው ነገር ግን መንፈሳዊውን ሁኔታ ሊረዱ አለመቻላቸው አስወቅሶአቸዋል ። 6/ "እርሾ" ፣ አብዛኛውን ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ መጥፎነትን ያመለክታል ፤ 1 ቆሮ- 5፡8 ። 7/ ተአምር በተደረገበት ወቅት በመንፈሳዊ ቃላት ስለመጠቀም የተነሣው አለመግባባት በዮሐንስ 6፡25-58 ይበልጥ ተዘርዝሮ ተገልጾአል ። 8-10/ ሁለ ቱን የመመገብ ተአምራት ከተመለከቱ በኋላ ስለ ዕለት እንጀራ መቸገር አያስፈልጋቸውም ነበር ። 11-12/ አከራካሪው ነጥብ "ትምህርታቸው" መሆን አለበት ። ብዙ ጊዜ የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን አስተሳሰብ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርትና ሕይወት አበላሽቶአል ።

## ስለ መሲህ የተሰጠ ምስክርነትና ያስከተ ለው ጥሪ 16፡13-28

ከዚህ ክፍል ጋር ማርቆስ 8፡27-9፡1ና ሉቃስ 9፡18-27 አንብቡ ። ለጴጥሮስ የተሰጠው ቃል በማርቆስ ውስጥ ተጽፎ አይገኝም ፤ ቁ- 17-19 ። ማርቆስ ኢየሱስን ስለ መካድ የጻፈው ዘገባ በማቴዎስ ውስጥ ባይገኝም ተመ ሳሳይ ቃል በ10፡32-33 ውስጥ ይገኛል ። ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ መሲሕነት የሰጠው ምስክርነት ለመጀመሪያ ዎቹ ሶስት ወንጌሎች ስለመሲህነቱ ለመጻፍ መነሻ ሆኖአቸዋል ፤ ምክንያቱም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በመስቀል የሚሞት መሆኑ ግልጽ እየሆነ ስለ መጣ ነው ።

13/ "ፊልጶስ ቂሣሪያ" ፣ ቀድሞ የግሪክን አምላክ የፓንን ስም ለማስጠራት ፓኔአስ ተብላ ትጠራ ነበር ። የአራተኛው ክፍል ገዢ የነበረው ፊልጶስ ሲመሠርታት ለአውግስጦስ ክብር መታሰቢያ እንድትሆን ቂሣሪያ ማለትም የንጉሥ ከተማ ብሎ ጠራት ። ለቂሣር አውግ ስጦስ ብዙ ከተማዎች ስለ ተሠሩ ፊልጶስ የሚል መለያ ስም ተሰጣት ። በእንደዚህ ያለ አውራጃ ውስጥ ስለ አይሁድ መሲህ የመጀመሪያው እውነተኛ ምስክርነት መሰጠቱ የሚያስደንቅ ነው ። "የሰው ልጅ" ፣ በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ እኔ የሚል ትርጉም አለው ። 14/

ከዚህ ቀደም ሰዎች የዮሐንስንና የኢየሱስን ሥራ ለይ ተው ማወቅ ተስኖአቸው ነበር ፤ 14፡2 ። "ኤልያስ" ተመልሶ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ ነበር ፤ ሚል- 4፡5 ። ማቴዎስ ብቻ ኤርምያስን ይጠቅሳል ፤ በ2፡17ና በ27፡9 ውስጥ ትንቢተ ኤርምያስ ተጠቅሶአል ። ኢየሱስ እንደ ሙሴ ነቢይ ሆኖ ተቆጥሮ ነበር ፤ ዘዳ- 18፡15 ፣ የሐዋ- 3፡22 ። 15/ ሐዋርያት የሌሎችን ሰዎች አሳብ ከመግለጽ ይልቅ የራሳቸውን ቆርጠው መግለጽ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖአቸዋል ። 16/ አስቀድሞ እንዲህ ያለ ምስክርነት ለመስጠት ቢቃጡም — 14፡33 ፣ ይህ አነጋገር አሰላስ ለው ስለ ኢየሱስ ማንነት ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጹትን እምነታቸውን ያመለክታል ። ምንም እንኳ ሉቃስ ከእግ ዚአብሔር የተቀባህ ነህ ቢልም ማቴዎስ ብቻ "የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" የሚል ቃል ጨምሮበታል ። "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው አነጋገር በአስተሳ ሰባቸው ሙሉ ክርስቲያናዊ ትርጉም ባይኖረውም አይ ሁድ ከነበራቸው ተስፋ በላይ የሆነ ትርጉም ነበረው ። "ስምዖን ጴጥሮስም" ፣ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው መሪ ነቱን ሲወስድ እርስ በርሳቸው ስለ ኢየሱስ መሲህነት ለተነጋገሩት ለ12ቱ አፈ ቀላጤ ሆነ ።

17-19/ አንዳንድ ምሁራን እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ የተናገራቸው አይደሉም ብለው አሳብ አቅርበዋል ። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ከዚህ ላይና ከምዕ- 18፡17 በቀር በወንጌሎች በሌላ ቦታ ስላልተጠቀሰ እዚህ ላይ መጨመሩ ፣ ማቴዎስ ቤተ ክርስቲያንን የመደገፍ አዝ ማሚያ እንዳለው ያሳያል ይላሉ ። አዲስ ኪዳን ስለ ጴጥሮስ ማዕረግ የሚያስተምረው ትምህርት በዚህ ላይ ካለው ጋር ሲነጻጸር የማይቃረን ሆኖ ይገኛል ። በኩምራን ገዳም የተገኙት ብራናዎች ኢየሱስ ማኅበረ ሰብን የማቋቋም ዕቅድ አልነበረውም የሚለውን ተቃ ውሞ ውድቅ አድርገውታል ። በቁ- 17፡18 ላይ ለጴጥሮስ የተሰጠው ምስጋና በቁ- 23 ከቀረበው ወቀሳ ጋር ሲነ ጻጸር የሚያስደንቅ ተመሳሳይነት አለው ሲሉ አንዳንድ ተርጓሚዎች አመልክተዋል ።

17/ "የዮና ልጅ ስምዖን" ፤ በአራም ቋንቋ ሙሉ ስሙ፤ነው ። "ሥጋና ደም" ፣ ሰብዓዊ ተፈጥሮ ማለት ነው ለጳውሎስ ተመሳሳይ ራዕይ ተሰጠው ፤ ገላ- 1፡16-18 ። 18/ "ጴጥሮስ" ፣ በግሪኩ ድንጋይ ማለት ነው ፤ እዚህ ላይ ስሙ አለት ከሚለው ቃል ጋር የተያ ያዘ ነው ። በአራም ቋንቋ ኬፋ ማለት ድንጋይ ወይም አለት ማለት ነው ፤ በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ጴጥ ሮስ ኬፋ ተብሎ ተጠርቶአል ፤ ዮሐ- 1፡42 ፣ 1 ቆሮ- 1፡12 ፣ 3፡22 ፣ 9፡5 ፣ 15፡5ና ገላ- 2፡9 ። ስሙ እዚህ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጴጥሮስ እንደተሰጠ አያመለክትም ፤ ዮሐ- 1፡42 ፣ ማር- 3፡16 ። ነገር ግን አሁን ስሙ አዲስ ትርጉም አገኘ ። አንዳንዶች ይህን አነጋገር ከትንሣኤ በኋላ እንደተነገረ አድርገው ሊቆጥሩት አስበው ነበር ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ይህን ስም ለስምዖን በአገልግሎት ጊዜ ሰጥቶ የትርጉሙን ምክንያት አልገለጸላቸው እንደ ሆነ የሚያስገርም ነው ። ተመሳሳይ ስም ለአብርሃም ተሰጥቶታል ፤ ኢሳ- 51፡1 ። ነገር ግን ስሙ ለጴጥሮስ የተሰጠው በልዩ ምክንያት ነው ። ኢየሱስ የማዕዘን ድንጋይ ፣ ኢሳ- 28፡16 ፣ 1 ጴጥ- 2፡8 ፣ ኤፌ- 2፡20 ፣ የተ ጣለ ድንጋይ ፣ መዝ- 117፡22 ፣ ማቴ- 21፡42 ፣ 1 ጴጥ- 2፡7 ፣ የማሰናከያ አለት ፣ ኢሳ- 8፡14 ፣ ሮሜ 9፡32 ፣ 1 ጴጥ- 2፡8 ፣ የመሠረት ድንጋይ ተብሎ ተጠርቶአል ፤ 1 ቆሮ- 3፡11 ። አንዳንድ ምሁራን በቁ- 18 ላይ አለቱ ኢየሱስ ነው ብለው ይተረጉሙታል ፤ ነገር ግን ይህ ትርጉም ከአሳቡ ጋር አይስማማም ። የጴጥሮስን እም ነት ወይም የጴጥሮስን ምስክርነት የሚያመለክት አይ መስልም ። ያለ ጥርጥር ጴጥሮስ ራሱ አለት መሆን አለበት ፤ ነገር ግን ጴጥሮስ መስካሪው ፣ ታማኙና ታዛዡ ሲሆን ነው ። የሹመቱ ወራሽ ለሚሆን ሰው የተደረገ ለት ለመሆኑ የሚያስረዳ አንዳች ማስረጃ አይገኝም ፤ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች በኋላ ደጋግሞ ሌላ መሠረት መጣል ያስፈልጋል ማለት የማይታሰብ ነው ። ጴጥሮስ የተሰጠውን ሥልጣን ከቀሩት ሐዋርያት ጋር እንደምን አድርጎ እንደ ሠራበት በ18፡18 ውስጥ በግልጽ ተመልክቶአል ። በሐዋርያት ሥራ በመጀመሪያ ዎቹ ምዕራፎች ውስጥ የጴጥሮስ የመሪነት ተግባር ምን እንደሆነ ተገልጾአል ። "ቤተ ክርስቲያን" ፣ የራሴ ቤተ ክርስቲያን ሲል ከእስራኤል ሕዝብ ተለይታ የም ትታወቅ ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ነች ብለን መተ ርጐም አያስፈልግም ይሆናል ። በመጀመሪያ ደረጃ በእ ግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ እንደ ቅሬታ ሆኖ የሚሠራ የኢየሱስን የራሱን ማኅበር የሚጠቅስ ሲሆን ቤተ ክር ስቲያን ያለ ጥርጥር ተስፋፍታ ማደጓን ያመለክታል ። "የገሃነም ደጆች" ፣ የሲኦል ወይም የሞት ደጆች ማለት ነው ። ቃላቱ ሕዝቅያስ በጻፈው መዝሙር ውስጥ ይገ ኛሉ ፤ ኢሳ- 38፡10 ። "ደጆች" የሚለው ቃል የሚያመ ለክተው ፣ የአንድን ምሽግ ወይም የወኅኒ ቤትን ምሳሌ ሲሆን ፣ በውስጡ ሙታንን ዘግቶ የያዘና ከውጭ ሊያድኑ የሚመጡትን እንዳይገቡ የሚከለክል ነው ። ይህ የሚያ ስረዳው ፣ ቤተ ክርስቲያን አጥቂ እንደሆነችና ጌታዋም የሰይጣንን ግዛት ሁሉ እንደሚገርክ ነው 12፡29 ፣ 1 ጴጥ- 3፡18-20 ።

19/ "የመንግሥት ሰማያትን መክፈቻዎች" ፣ ሐረጉ የተመሠረተው ፣ አዛዡ ሳምናስ በኤልያቄም ተተክቶ ሥልጣኑ ለርሱ እንደተላለፈ በሚያመለክተው ፣ የዳ ዊትን ቤት መክፈቻ በጫንቃው ላይ አኖራለሁ፤ እርሱም ይከፍታል የሚዘጋ የለም ፤ እርሱም ይዘጋል ፣ የሚከፍ ትም የለም በሚለው በኢሳ- 22፡15-25 ላይ ነው ። ይህ በራዕይ 3፡7 ላይ በቀጥታ ስለ ኢየሱስ ተጠቅሶ ይገኛል ። በአይሁድ መምህራን አነጋገር ማሰርና መፍታት የሥነ ምግባር መምሪያዎችን መደንገግ የሚያመለክት ሲሆን አብዛኞቹ ተርጓሚዎች ፣ ቁልፎቹ የሚያመለክቱት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የማስተዳደር ሥል ጣን እንጂ በውጭ ያሉትን ሰዎች የመክፈት ኃይል አይደለም ብለው ይተረጉሙታል ። እንግዲህ ይህ ከሆነ ለጴጥሮስና ከርሱም ጋር ለተባበሩት ሐዋርያት ወንጌ ልን የመስበክ ብቻ ሳይሆን የሐዋርያትን ትምህርት የመመሥረት ጭምር ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል ። የተ ሰጠው ተስፋ ትርጉም ጴጥሮስ የሚናገረውን ሁሉ እግ ዚአብሔር ያጸድቀዋል ማለት አይደለም ፤ ገላ- 2፡11 ። ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ፈቃድ የተሠሩት ነገሮች ዘላቂ የሆነ መብት ይኖራቸዋል ማለት ነው ። እነዚህ ቁጥሮች ከኢሳይያስ ጋር የሚመሳሰሉበት ብዙ ጥቅሶች ሲኖሩ ዋቸው በሌላ በኩል ደግሞ ከ1 ጴጥሮስ ጋር የሚያያዙ

በት ብዙ መንገዶች አሉአቸው ። 20/ ምንም እንኳ ከባድ ምስክርነት ቢሆንም ዜናው ተቀጣጥሎ ወደ ውጭ እንዳይወጣ ተከለከለ ። ሰዎች ራሳቸው ተመራምረው ቢደርሱበት ይሻላል ።

21/ እርሱ ማን እንደሆነ ካወቁበት “ከዚያን ቀን ጀምሮ” አዲስ የሆነ ጥልቅ ትምህርት ለመስጠት ይቻላል ። ምስክርነቱ እንደተሰጠ ወዲያውኑ በሥቃይ አንጻር መተርጐም አስፈላጊ ሆነ ። “ይሄድ ዘንድ” ፥ ምክንያቱም ስለርሱ ተጽፎአልና ። ምንም እንኳ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቢሆንም ኢየሱስ በተሰቀለና ከሞት በተነሣ ጊዜ ሐዋርያት መደንገጣቸው የሚያስገርም አይደለም ። 22/ “ወደርሱ ወስዶ” ፥ ከሌሎች በላይ ተረድቻለሁ በሚል አሳብ ላይ ተመርኩዞ ለኢ.የሱስ ምክር ለመስጠት አሰበ ። ባገኘው ምርቃት በመኩራቱ ለመረዳት ሳይችል ቀረ ። 23/ “ሰይጣን” ፥ ከዚህ ቀደም ሲል የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ለጴጥሮስ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር ፤ ቁ- 19 ። አሁን ግን ለአጭር ጊዜ ሰይጣን ተጠቀመበት ፤ ማር- 5፡9 ። የመስቀል መከራ እንዳይደርስበት በድጋሚ ይሞክር ነበር ፤ 4፡1-11 ። “እንቅፋት” ፥ በጠባዩ መለዋወጥ ምክንያት የዓለት ድንጋይ የተባለው ሰው — ቁ- 18 ፥ የእንቅፋት ድንጋይ ሊሆን ቻለ ። ኢየሱስ ለሰዎች የመሠረትና የማሰናከያ ድንጋይ ሁለቱንም ሊሆን የቻለው ሰዎች ስለ እርሱ ባደረጉት ምርጫ መሠረት ነው ፤ 1 ጴጥ- 2፡6-8 ። ምንም እንኳ ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር የመጣ ራዕይ ቢገለጽለትም — ቁ- 17 ፥ ያሁኑ አስተሳሰቡ ፍጹም ሰብዓዊ ነው ።

24/ የሐዋርያ አካሄድ እንደ መምህሩ መሆን ይገባዋል ። “ራሱን ይካድ” ፥ የራሱን ነጻ ውሳኔ እምቢ ብሎ እንደመተው የሚቆጠር ነው ። “መስቀሉን ተሸክሞ” ፥ ይኸውም በቀራንዮ ጎዳና ላይ መገኘት ማለት ነው ፤ 27፡32 ። 25/ “ነፍሱን” ፥ ሕይወቱን ማለት ነው ፤ 10፡39 ። ይህ ቁጥር የሚያስረዳው ፥ ሰው ለክርስቶስ ብሎ የራሱን ደህንነትና ጥበቃ ከተወ በእውነት ፍጹም ሕይወት እንደሚያገኝ ነው ። 26/ ሰው ባለው ንብረት መሠረት መንፈሳዊ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ፈጽሞ አይችልም ፤ 6፡25 ። 27/ “ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል” ፥ ከመዝ- 61፡12ና ከምሳሌ 24፡12 ላይ የተወሰዱትን እነዚህን ቃላት የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው ። ሥራዎች የሰውን ሁኔታ የሚገልጹ ናቸው ፤ 7፡21 ። 28/ “የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ” ፥ ማርቆስ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ስትመጣ ብሎ ጽፎአል ። ቀደም ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተመለከቱትን ዓይነተኛ ድርጊቶች ለማረጋገጥ የሚፈጽመውን ሥራ ሳይጠቁም አይቀርም ። አንዳንድ ምሁራን ይህን ጥቅስ ሲተረጉሙ ፥ ኢየሱስ ምንም ዳግመኛ እንደሚመጣ ቢናገርም ተመልሶ ስለሚመጣበት ትክክለኛ ጊዜ ተሳስቷል ብለው ይናገራሉ ፤ ነገር ግን የሚመለስበትን ቀን ገልጾ ለማስረዳት ባለመፈለጉ ምክንያት ፥ በዚህ ቦታ ላይ ከአድማጮቹ መካከል አንዳንዶቹ ከመሞታቸው በፊት እንደሚመለስ የተናገረ አይመስልም ፤ 24፡36 ። ይህ ጥቅስ በተራራ ላይ የተገለጸውን የሚያመለክት ነው ብለው የገመቱ አሉ ፤ ነገር ግን በተራራ ላይ የተገለጸው ከስድስት ቀን በኋላ ስለነበረ ሞትን ስለማይቀምሱት የተናገረው ከዚህ ትርጉም ጋር አይስማማም ። ኢየሱስ ሞትን ከቀመሰና እንደዚሁም ሌሎቹ ሞትን ለመቅመስ ፈቃደኝነታቸውን ከገለጹ በኋላ የሰው ልጅ በመንግሥቱ በሚመጣበት ጊዜ ከሚፈጸሙት ዋና ዋና ድርጊቶች አንዱ ሳይሆን አይቀርም ፤ 26፡35 ። ማርቆስ የተጠቀመበት በኃይል የሚለው ቃል ከትንሣኤውና እንዲሁም ከበዓለ ሃምሳ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከሁለቱ አንዳቸውን ሊያመለክት ይችላል ፤ ሮሜ 1፡4 ፥ የሐዋ- 1፡8 ።

## ጌታ በተራራ ላይ መለወጡና ውጤቶቹ 17፡1-27

ማቴዎስ ጥቂት ቃላት ቢጨምርምና አንዳንድ ገለጻዎችን ቢያሳጥርም ይህ ክፍለ ምንባብ ከማር -9፡2-32፥ከሉቃስ 9፡28-44 ና 17፡5 ጋር በቅርብ ይመሳሰላል ። ቁ- 24-27 በማቴዎስ ብቻ ይገኛሉ ። መሲሁን ክብሩን የሚያንጸባርቅ ድርጊት የፈጸመው ማለትም በተራራ ላይ የተለወጠው ከጴጥሮስ ምስክርነት በኋላ መሆኑን የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወንጌሎች ይመሰክራሉ ። በተራራ ላይ የመለወጡ ዓላማ ከጥምቀቱና ከትንሣኤው ከዕርገቱና ከዳግም ምጽአቱ ጋር ተያይዞአል ። አንዳንድ ምሁራን ድርጊቱ መሠረት የሌለው ነው ወይም ከትንሣኤው በኋላ የተደረገ ሆኖ ሳለ በስሕተት በዚህ ሥፍራ ተጽፎአል የሚል አሳብ ያቀርባሉ ። ይህ ለሶስቱ ሐዋርያት ብቻ የተሰጠው ልዩ ገለጻ ከትንሣኤ በኋላ የተደረገ ሊሆን የሚችል አይመስልም ፤ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት በዚህ መንገድ ለነርሱ እንዲገለጽላቸው የፈለገበት ምክንያት ሊኖረው ይችላል ። ማቴዎስ በተራራ ላይ ከመገለጹ ታሪክ ቀጥሎ የኤልያስን መምጣት የሚናገር ትንቢት ፥ አንድ የመፈወስ ታሪክና ስለሚደርስበት መከራ ተጨማሪ ትንቢት ጽፎአል ። ከዚህ በኋላ ለቤተ መቅደስ ስለሚገባው ቀረጥ ሁኔታ ጨምሮ ጽፎአል ።

1/ “ከስድስት ቀን በኋላ” ፥ በዘጸ- 24፡9-18 ውስጥ ደመናው ለስድስት ቀን ተራራውን ካለበሰው በኋላ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን እንደተናገረ ተጽፎአል ። “ጴጥሮስ ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ” ፥ እነዚህ በጣም ቅርብ የሆኑ የኢየሱስ ተከታዮች ነበሩ ፤ 20፡20 ፥ 26፡37 ። “ተራራ” ፥ የታቦር ተራራ ወይም በቂሣርያ ፊልጵስዩስ አጠገብ የሚገኘው የአርሞን ዔም ተራራ ሊሆን ይችላል ። አምላካዊ ራዕይ የታየበት ቦታ ነበረ ። 2/ “በፊታቸው ተለወጠ” ፥ ተመሳሳይ የግሪክ ቃል በሮሜ 12፡2ና በ2 ቆሮ- 3፡18 ውስጥ ይገኛል ። በተራራው ላይ የኢየሱስ እውነተኛ አምላካዊ መልክ በከፊል ተገለጸ ፤ ፊል- 2፡6 ። “ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ” ፥ የሙሴ ፊት አምላካዊ ብርሃን የሚያንጸባርቅ ሲሆን — ዘጸ 34፡29-35 ፥ ኢየሱስ ግን የብርሃን ምንጭ ነው ። “ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ” ፥ ይህ የሆነው መሲህ ካህን መሆኑን ለማገለጽ ሳይሆን አይቀርም ፤ ዘካ- 3፡4-5 ። 3/ “ሙሴና ኤልያስ” ሕግንና ነቢያትን የሚወክሉ ናቸው ፤ አንዳቸውም የት እንደተቀበሩ አልታወቀም ፤ ዘዳ- 34፡6 ፥ 2 ነገ- 2፡11 ። እያንዳንዳቸው በተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግረው ነበር ፤ ዘጸ- 31፡18 ፥ 1 ነገ- 19፡9-18 ።

4/ ጴጥሮስ በተራራው ላይ ብዙ ጊዜ ለመቆየት ፈለገ ። ማርቆስ ብቻ በጣም ፈርቶ ነበርና የሚለውን አያውቅም ነበር ሲል ጽፎአል ። ዳስ ለመሥራት ማሰ ባቸው ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ለመጸለይና በዓ ሉን ለማክበር ወደ ቤተ መቅደስ ይመጣሉ ከሚለው ትንቢት ጋር የተያያዘ ይሆናል ፤ ዘካ- 14፡16-19 ። 5/ "ብሩህ ደመና" ፣ እግዚአብሔር መገኘቱ የሚታወ ቅበት ምልክት ነበር ። "በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" ፣ ይህ በኢየሱስ ጥምቀት ጊዜ የተነገ ረውን ቃል ያስታውሳል ፤3፡17 ። "በርሱ ደስ የሚለኝ" ፣ ከጥምቀቱ ጋር በግልጽ የሚያያዙትን ቃላት ዘርዝሮ የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው ። "እርሱን ስሙት" ፣ በዘዳ- 18፡15 ውስጥ ያለውን ማለት አንድ ቀን ሙሴን የሚ መስል ነቢይ ይመጣል የሚለውን ትንቢት ሳያስተጋባ አይቀርም ። በአንዳንድ መንገዶች ኤልያስ በዘመኑ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ሆኖ ነበረ ። 6/ እነዚህ ቁጥሮች የሚገኙት በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ሲሆን ማርቆስ የኢ. የሱስ ክብር መገለጹ ያስከተለውን ፍርሃት በማብራ ራት ጽፎአል ።

9/ "ያያችሁትን" ፣ ከሕልም የበለጠ ሁኔታ እንደ ተመለከቱ ይገልጻል ። ክርስቶስ ከሞት ከመነሣቱ በፊት ለሌሎች ቢነገር ትርጉም የሌለው ይሆናል ። 10-13/ አንዳንዶች ድርጊቱን ሲተረጉሙ ፣ ኢየሱስ ራሱን ዝቅ አድርጎ መምጣቱ ፣ በክብር ተመልሶ ለመምጣቱ ዝግጅት በመሆኑ የኤልያስን ተግባር ያንጸባርቃል ብለ ዋል ። አንዳንድ የኢየሱስ ሥራዎች ከዮሐንስ ሥራዎች ይልቅ ስለ ኤልያስ ለተነገረው ትንቢት ፍጻሜ ቢሆ ኑም ፣ ሚልክያስ ስለ ኤልያስ የተናገረው ትንቢት በመ ጥምቁ ዮሐንስ ላይ የተፈጸመ መሆኑን ወንጌሉ በሙሉ ያሳያል ፤ ሚል- 3፡1 ፣ 4፡5 ። በቁጥር 13 ውስጥ ማቴዎስ ይህንን በግልጽ ዘርዝሮ አስረድቶአል ።

14/ ኢየሱስ አንዳንዴ ከሕዝቡ በመገለል ፣ አንዳንዴ ከሕዝቡ ጋር በመደባለቅ ያገለግል ነበር ። ደቀ መዛ ሙርቱ ከኢየሱስ ጋር ብቻቸውን ከመሆን ወደ ሕዝቡ ተመለሱ ፤ ቁ- 8 ። 16/ ክብሩ ከተገለጠበት ተራራ ሲወ ርዱ በተራራው ሥር ኃፍረትና ድካም ገጠማቸው ።

17/ "የማታምን ጠማማ ትውልድ ሆይ" ፣ ሙሴ ከግ ብፅ ስለወጣው ትውልድ የተናገረውን ቃል የሚያስተ ጋባ ይመስላል ፤ ዘዳ- 32፡5 ፣ ማቴ- 11፡16 ። ኢየሱስ ሁልጊዜ በሥጋው ከነርሱ ጋር የሌለበትን ኑሮ መኖር ንና ከሩቅ ሆኖ የሚሰጣቸውን ኃይል መለማመድ የግድ ስለሚያስፈልጋቸው አሁን በመካከላቸው ባልተገኘ በት ሰዓት ችግሩን ለመወጣት ባለመቻላቸው አዘነ ። 18/ "ገሠጸው" ፣ ጋኔኑን ማለት ነው ። 19-20/ ታሪ ኩን ባጭሩ የሚያቀርበው ማቴዎስ ፣ ከማርቆስ ይልቅ

ግልጽ በሆነ መንገድ የደቀ መዛሙርትን የእምነት ማነስ ያሳያል ። በዚህ ጊዜ ማቴዎስ የወቀሳው ተካፋይ ነበረ ፤ ነገር ግን ማርቆስ ወንጌሉን ሲጽፍ ተባባሪ የነ በረው ጴጥሮስ በዚያን ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አል ነበረም ። "ይህ ተራራ" ፣ ማንኛውንም ዓይነት የማይ ነቃነቅ መሰናክልን የሚያመለክት ነው ፤ 21፡21 ። ቁጥር 21 በታወቁት ብራናዎች ውስጥ አይገኝም ።

22-23/ የሚመጡትን ሥቃዩንና ሞቱን ደጋግሞ የጠቆማቸው አስፈላጊነታቸውን ገና ስላልተረዱ ነው ፤ 16፡21ና 20፡18-20 ። 24-27/ ይህ ታሪክ ኢየሱስ የቤተ መቅደስን ቀረጥ መክፈል እንዳለበት የሚያምን እው ነተኛ አይሁድ ሆኖ ሳለ ለመክፈል የሚያስገድደው አምላካዊ ግዳጅ የሌለበት መሆኑን ያሳያል ። የሮም መንግሥት ዜጎች ባልሆኑት ሁሉ ከባድ ግብር የሚያስ ከትል መሆኑ መጠቀሱ ለሰሚዎች ሁሉ ግልጽ ይሆ ናል ። 26/ "ልጆች ነጻ ናቸው" ፣ ገላ- 4፡21-31 ተመ ልከቱ ። 27/ "እንዳናሰናክላቸው" ፣ በአዲስ ክርስቲያ ኖች ላይ ችግር እንዳንፈጥርባቸው ማለት ነው ፤ 1 ቆሮ- 8፡9-13 ። ምንም እንኳ እርሱ ከቤተ መቅደስ የላቀ ቢሆንም — 12፡6 ፣ ከሕዝቡ ሃይማኖታዊ ግዳጆች ጋር ራሱን ለማመሳሰል ፈቃደኛ ነበረ ፤ 3፡15 ። በዚያን ጊዜ ሕዝቡ በእስታቴር እኩሌታው አይጠቀሙም ነበር ፤ ስለዚህ ጴጥሮስ ለራሱና ለኢየሱስ ሁለት "ዲናር" ለመክፈል አንድ እስታቴር ከፈለ ። ተአምር የፈጸመ ይመስላል ፤ ነገር ግን በወንጌሎች ውስጥ ተአምር በግ ልጽ ለሕዝብ ያልታየበት ሁኔታ ይህ ብቻ ነው ። ድርጊ ቱን በብዙ ሌላ መንገዶች ለመተርጐም ሙከራ ተደርጎ ብዙ አልተሳካም ። ወንጌሉ ከ70 ዓ/ም በፊት የተጻፈ ቢሆን ኖሮ ታሪኩ የበለጠ ትኩረት ይሰጠው ነበር ፤ ሆኖም ይህ ድርጊት ወንጌሉ ከ70 ዓ/ም በፊት መጻፉን ሊያመለክት አይችልም ።

## የቤተ ክርስቲያን አኗኗር 18፡1-35

ይህ በማቴዎስ ካሉት አምስት ንግግሮች አራተኛው ሲሆን በክርስቲያን ወንድማማችነት መካከል ያለውን ግንኙነት ሲያብራራ በተለይም በሁለት ዋና ዋና ጠባ ዮች በትሕትናና በይቅርታ አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል ። ቁ- 1-5 ከማር- 9፡33-37 ጋር ይመሳሰላል ፤ ደግሞ ከሉ ቃስ 9፡46-48 ጋር አነጻጽሩት ። ቁ- 6-9 ከማር- 9፡42-48 ጋር ይመሳሰላል ፤ እርሱንም ከሉቃስ 17፡1-3 ጋር አነ ጻጽሩት ። ቁ- 10-14 ከሉቃስ 15፡1-10 ጋር ይመሳሰላል ። ቁ- 15-22 ደግሞ ከሉቃስ 17፡3 ጋር ይመሳሰላል ። ቁ- 23-25 የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ።

1/ "በዚያች ሰዓት" ፣ ቅደም ተከተሉ እንደ ማር ቆስ በመሆኑ ይህ አባባል ምዕራፎቹን የሚያያይዝ ብቻ አይደለም ፣ በተጨማሪም ማቴዎስ ስለ ቀረጥ ከጻፈው ታሪክ አንጻር ሲታይ ጥያቄው ተስማሚ ነው ። ማቴዎስ ደቀ መዛሙርት እርስ በርሳቸው መጣላታቸውን በታ ሪኩ ውስጥ አልጨመረም ። በኩምራን ገዳም የኑሮ ሥርዓት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የራሱን የሥራ ድርሻ እየሠራ እንዲኖር እንጂ የሌላውን እንዳይመኝ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር ፤ "እያንዳንዱ እስራኤላዊ በዘላለማዊ ዕቅድ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ይወቅ ። ማንም ሰው ቢሆን ከተወሰነለት ሥፍራ ዝቅ ሊል ወይም ከፍ ሊል አይችልም" ተብሎ ባንድ መጽሐፋቸው ተጽፎ አል ። በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ ታላቅ የሚሆነው ከትእዛዛቱ ውስጥ አነስተኛይቱን የሚፈጽምና የሚያ ስተምር ነው ፤ 5፡19ና 11፡11 ። 3/ "ካልተመለሳችሁ" ፣ ሕይወታችሁን በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ካላ ደረጋችሁ ማለት ነው ። "እንደ ሕጻን ካልሆናችሁ" ፣

ራስን በእግዚአብሔር ላይ በመጣልና በትሕትና አንጻር እንጂ ጥፋተኛ ባለመሆን አይደለም ፤ ማር- 10:15 ። “አትገቡም” ፥ እንደ ሕጻን የመሆን ጠባይ በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ የሚያስፈልገውን ታላቅ ለመሆን ብቻ ሳይሆን ወደ ውስጡም ለመግባት ጭምር ነው ፤ ዮሐ- 3:3-5 ። 4/ ኢየሱስ ስለ ታላቅነት ያስተማረው ትምህርት ፥ ሰዎች ስለ ታላቅነት ከሚያስተምሩት ትምህርት የተለየ ነው ፤ 5:3-12 ፥ 20:25-28 ።

5/ ደቀ መዝሙር እንደ ሕጻን ሆኖ የእግዚአብሔርን መንግሥት መቀበል ብቻ ሳይሆን አንድን ሕጻን በኢየሱስ ስም መቀበል መቻል አለበት ። ከሁሉ በላይ ደካማ የሆነውን ሰው እንደ መሣሪያ መቁጠር ሳይሆን እንደ ሰብዓዊ ፍጡር ማክበር አለበት ፤ 10:40ና 25:40 ። 6/ “ቢያሰናክል” ፥ በደለኛ ቢያደርገው እንደ ማለት ነው ። የአይሁድ መምህራን የናባጥ ልጅ ኢዮርብአም እስራኤላውያንን እንዲበድሉ በማድረጉ ከኃጢአተኞች ሁሉ የከፋ አድርገው ይቆጥሩት ነበር ፤ 1 ነገ- 14:16 ። ሌሎችን በማሰናከል በመንፈሳዊ ኃላፊነት ከመጠየቅ ይልቅ ማንኛውም አስፈሪ ሥጋዊ ቅጣት መቀበል ይመረጣል ። 7/ ይህ ጥቅስ ክፉ ነገር የማይቀር መሆኑንና አድራጊዎች የሞራል ተጠያቂነት ያለባቸው መሆኑን በመግለጽ ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለነዚህ ሁለት ነጥቦች ያለውን ትምህርት ያመለክታል ። 8-9/ የነዚህ ጥቅሶች ፍሬ ነገር በ5:29-30 ውስጥ ይገኛል ። እዚህ ላይ ማቴዎስም እንደ ማርቆስ የማሰናከያ አለት ከሚለው አነጋገር ጋር የተያያዙ ብዙ አባባሎችን ይሰበስባል ። ይኸኛው ጥቅስ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መንፈሳዊ ሕይወት እንክብካቤ የሚያስፈልገው መሆኑን ያስተምራል ።

10/ ይህ ቁጥር የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። “ታናናሾች” ፥ ሕጻናት ማለቱ ላይሆን ይችላል ፤ በእምነት ደካማ የሆኑቱ ሁሉ ሊሆኑ ይችላሉ ። እያንዳንዱ አማኝ ጉዳዩን ለእግዚአብሔር የሚያቀርብለት ጠባቂ መልአክ እንዳለው ታስቦ ይሆናል ፤ መዝ- 90:11 ፥ የሐዋ- 12:15 ። 12-13/ ሉቃስ 15:1-7 ንስሐ በሚገባ ሰው ምክንያት በሰማይ ስለሚኖረው ደስታ ሲናገር በዚህ ሥፍራ ግን የሚያተኩረው በእያንዳንዱ ግለሰብ ክቡርነት ላይ ነው ። አባባሎቹ ምናልባት በተለያዩ ጊዜያት የተነገሩ ይሆናሉ ። 14/ እግዚአብሔር አንድም ሰው እንኳ እንዳይጠፋና ለእያንዳንዱም ክርስቲያን ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚፈልግ መሆኑን ያመለክታል ።

15/ “ወንድምህ” ፥ እግዚአብሔርን እንደ አባታቸው የሚቆጥሩ ሰዎች ባሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ ያለ ወንድም ነው ። “ቢበድልህ” ፥ አንተን ቢበድል የሚለው አሳብ በታወቁት ብራናዎች ውስጥ አይገኝም ። “ህ” የሚለው ፊደል በግሡ ላይ ባይጨመር በግል ላይ ብቻ ሳይመሠረት በሌላ ላይ የሚደረገውን ኃጢአት ያጠቃልላል ማለት ነው ። በግል ደረጃ ከበዳዩ ጋር መመካከር የፍቅር የመጀመሪያ ርምጃ ነው ፤ ዘሌ- 19:17-20 ። “ገንዘብ አደረግኸው” ፥ የቤተ ክርስቲያን አካል መሆኑ እንዲቀጥል ማለት ሊሆን ይችላል ። 16/ ሰው ስላጠፋው ጥፋት ከአንድ ወንድም የቀረበውን ወቀሳ ለመቀበል ካልፈቀደ የሚቀጥለው ምክርና ወቀሳ ሊሰጠው የሚገባው በብዙዎች ዘንድ ነው ። ስለዚህ እውነቱን ለማወቅና ለማስታረቅ “ሁለት ወይም ሶስት ምስክሮች” መጠራት አለባቸው ። ይህ ዘዴ ችግሩን ባያቃልለው በደሉ ለቤተ ክርስቲያን አባሎች በይፋ መገለጽ አለበት ፤ ዘዳ- 19:15 ። 17/ “ቤተ ክርስቲያን” ፥ በአንድ አካባቢ የምትገኝ የአማኞች ማኅበረሰብ ናት ። ቤተ ክርስቲያንን አለመስማት የሚያስከትለው መወገዝን ነው ፤ 1 ቆሮ- 5:4 ፤ 1 ጢሞ- 1:20 ። አሕዛብና ቀራጮች ከእግዚአብሔር ሕዝቦች የተገለሉ ሆነው ቢቆጠሩም ወንጌልን በመቀበል ላይ ነበሩ ፤ 21:31 ፥ 43 ። 18/ በ16:19 ላይ የተሰጠውን ሐተታ እዩ ፤ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ የሚያስተላልፋቸው የአስተዳደር ድንጋጌዎች ከሥነ ምግባር ሕግ እኩል መከበር አለባቸው ። 19-20/ በምድር የሚደረገው ነገር በሰማይም ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያደርገው አስፈላጊ ነገር ፥— በጸሎት በሚገባ መስማማት ፥ በክርስቶስ ስም መሰብሰብና የርሱ ሕልውና መገኘት ነው ። ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያን ማኅበረሰብ እረኛና መካሪ እንደመሆኗ መጠን የመቆጣጠር ግዴታ አለባት ። ቁጥጥሩ በክርስቶስ ፈቃድ መሠረት በሚደረግበት ሥፍራ የክርስቶስ ሥልጣን ይኖረዋል ።

21:22/ “ሰባ ጊዜ ሰባት” ፥ ግሪኩ ሰባ ሰባት ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ። የኦሪት ሕግ ለየበደሉ ተመጣጣኝ ቅጣት ይገባዋል ብሎ ወሰነ ፤ ዘጸ- 21:4 ፥ ማቴ- 5:38 ። ከዚያ በፊት በቀሉ ያልተወሰነ ነበረ ፤ ለምሳሌ ፥ ቃየልን ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል ፤ ላሜህን ግን ሰባ ሰባት እጥፍ ፥ ዘፍጥ- 4:24 ። አሁን ግን በቀል ሳይሆን ይቅርታ ያልተወሰነ ነው ። 23/ ይህ ምሳሌ ይቅርታ መደጋገሙን ሳይሆን ሰፊ መሆኑን በግልጽ ያሳያል ፥ በተጨማሪም በጌታ ጸሎት ውስጥ ያለውን የይቅርታ ልመና ያብራራል ፤ 6:12ና 14 ። 24/ “እልፍ መክሊት” ፥ 10 ሺህ እንደ ማለት ነው ። ቁጥሩ በሰው ታሪክ ውስጥ እውነት አይመስልም ፤ ነገር ግን የሰውን ኃጢአት ብዛትና የአምላክን የኃጢአት ይቅርታ ብዛት በጉልህ ያሳያል ። 28/ “መቶ ዲናር” ፥ ጥቂት ገንዘብ ማለት ነው ። 32/ “ክፉ” ፥ ንፉግ ማለት ነው ። ለራሱ የዕዳውን ይቅርታ ስለተቀበለ ከንደኛው ላይ የነበረውን ዕዳ በማስገደድ መጠየቅ አልነበረበትም ፤ ሁለቱም ዕዳዎች ፍጹም የማይመጣጠኑ ነበሩ ። 33/ የእግዚአብሔር ምሕረት ለሰው ምሕረት ብቸኛና እውነተኛ መሠረት ነው ፤ 5:43-48 ። 35/ “እንዲሁ ደግሞ” ፥ ለእያንዳንዱ ጥቃቅን ቃል ልዩ ትርጉም ማውጣት አያስፈልግም ። ነገር ግን ይቅር የማይል ሰው ከእግዚአብሔር ይቅርታን እንደማያገኝ ግልጽ ነው ። ክርስቶስ ካደረገው ሥራ የተነሣ ኃጢአቱ ይቅር የተባለለት ሰው ሌሎች በትሕትና በማክበሩ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንና በምሕረቱ ላይ የሚታመን መሆኑን በማያጠራጥር መንገድ ያሳያል ።

## ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞና ያቀረበው ጥሪ 19:1-22:46

መሲሁ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖር የሚቻለውን ሕይወት አሳይቷል ፤ ቅድስቲቱ ከተማና በውስጧ የሚያገለግሉ የአይሁድ ሽማግሌዎች የክርስቶስ መንግሥት ማዕከልና ምንጭ ሆነው እንዲገኙ ለማድረግ ኢየሱስ

ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ። የማቴዎስ ዘገባ ከማር- 10:1-12:37 ጋር ይመሳሰላል ፤ ነገር ግን ማቴዎስ የሚከተሉትን ትምህርቶች ጨምሯል ፡— 1/ ስለ ጃንደረባነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ፣ 19:10-12 ። 2/ ስለ ወይኑ አትክልት ሠራተኞች ፣ 20:1-16 ። 3/ በመቅደስ ውስጥ ስለ ጮኹት ሕጻናት ፣ 21:14-17 ። 4/ ስለ ሁለቱ ልጆች ምሳሌ 21:28-32 ፣ 5/ ስለ ንጉሡ ሠርግ አይጨምርም ፤ 22:1-14 ። በጊዜያዊና በዘላለማዊ ፍርድ ላይ የሚያተኩረው በቁ- 23-25 የተገለጸው የትምህርት ርዕስ ፣ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ማድረግ ከሚያስፈልጋቸው ውሳኔ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የውጥረት ስሜት ያለበት ክፍለ ምንባብ ነው ።

## ጋብቻና ልጆች 19:1-15

አለማግባትን ከሚያብራራው ከቁ- 10-12 በስተቀር ከማር- 10:1-16 ጋር ይመሳሰላል ። ስለ ልጆች የተነገረው በሉቃስ 18:15-17 ውስጥም አለ ። ኢየሱስ በተራራው ስብከት ውስጥ ስለ ፍቺ መግለጫ ሰጠ ፤ 5:31 ። እዚህም ላይ በክርክር ጊዜ እንደገና ተመሳሳይ አሳብ ቀርቦአል ።

1/ "ኢየሱስም ይህን ነገር ከፈጸመ በኋላ" ፣ 7:28 ፣ 11:1 ፣ 13:53 ፣ 26:1ን ተመልከቱ ። 2/ "ብዙ ሕዝብ" ወደ ፋሲካ በዓል በመሄድ ላይ የነበሩ ሕዝብ ሊሆኑ ይችላሉ ። 3/ "በሆነው ምክንያት" ፣ ዘዳ- 24:1 ለሚገኘው በአሳፋሪ ምክንያት ለሚለው ሐረግ ከታወቁት የአይሁድ ት/ቤቶች የተለያዩ ትርጉሞች ይሰጡ ነበር ። ሂላል የተባለው መምህር ማንኛውም ባሏን የሚያስከፋ ድርጊት ብሎ ሲተረጉመው ፣ ሻማይ የተባለው መምህር ደግሞ የጋብቻን ሕግ አለመጠበቅ ብቻ ነው ብሎ ተርጉሞታል ። 4/ ኢየሱስ ከሕግ በፊት የነበረውን ጊዜ በመጥቀስ ሁለቱ ፆታዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጠሩ መሆናቸውን አሳያቸው ፤ ገላ- 3:17 ፣ ዘፍጥ- 1:27 ። 5/ "የሚለውን ቃል" ፣ እግዚአብሔር የተናገረውና ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰ ጥቅስ አድርጎ መተርጎም ልክ ሳይሆን አይቀርም ፤ ዘፍ- 2:24 ። ወይም የኢየሱስን ቃል ሊያመለክት ይችላል ። "አንድ" ፣ በግብረ ሥጋ የሆነ አንድነት ማለት ነው ። በተዋወቁት ወዳጆች የተፈጸመ ግንኙነት ጥልቅ እንደመሆኑ መጠን ዘፍጥ- 4:1 ፤ በሰብዓዊ ደረጃ ያላቸው አንድነት ፣ በክርስቶስና በክርስቲያን መካከል ካለው አንድነት ጋር ይመጣጠናል ፤ 1 ቆሮ- 6:16 ። 6/ ዓላማው ግልጽ ነው ፤ "ሰው እግዚአብሔር ያጣመረውን" መለየት የለበትም ።

7/ የኢየሱስ አነጋገር ፍችን ከነጭራሹ የሚቃወም ይመስላል ። ይህ ከሆነ የአሪትን ሕግ መጣስ ይመስላል ፤ ዘዳ- 24:1-14 ። 8/ "ስለልባችሁ ጥንካሬ" ፣ ሙሴ በማይታዘዙ ሰዎች ላይ ሕግን ማውጣት ነበረበት ። ሚስቶቻቸውን እንዲፈቱ "ፈቀደላቸው" ሲል ባሎቻቸውም ብለው እንዳያባርሩአቸው ለመከልከል ሕግ ሰጠ ማለቱ ነበረ ፤ ይህን አሳብ ቁ- 7 ላይ ካለው "አዘዘ" ከሚለው አሳባቸው ጋር አነጻጽሩ ። 9/ ኢየሱስ የሻይሜን ት/ቤት አተረጓጐም ይደግፋል ። ማርቆስ ያለዝሙት ምክንያት የሚለውን በማቴ- 5:32ና 19:9 ላይ የሚገኘውን ሐረግ ባለመጥቀሱ ብዙ ጥያቄ ፈጥሮአል ። ምናልባት ማርቆስ በአእምሮ ይዞ ያልጻፈውን ማቴዎስ በግልጽ ጽፎታል ። ማርቆስ ሚስት ባሏን ለመፍታት እንደምትችል የጻፈውን ማቴዎስ አልጠቀሰም ፤ ይህ ዓይነቱ ባሕል በአይሁድ ዘንድ ያልተለመደ ሲሆን በግሪኮችና በሮማውያን ዘንድ ግን የታወቀ ነበረ ። በዚህ ሥፍራ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ዓላማ በግልጽ ተጠቅሶአል ፤ ነገር ግን ዓላማው ባልተሳካበት ጊዜ የኅብረተሰቡ አስተዳደር ፍቺ መፍቀድ አይችልም የሚል መመሪያ አልሰጠም ። 10/ ሰዎች የዓላማውን ግብ ከመምታት የቱን ያህል ወደ ኋላ እንደቀሩ ያሳያል ። 11-12/ ላብዛኞቹ አይሁዶች ጋብቻ ግዴታ ነበረ ። አንዳንድ አይሁዳውያን በብሕትውና ለመኖር ፈቅደው ስለነበረ ያላገቡ ሰዎች ነበሩ ። "ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች" ፣ አንዳንድ የጥንት ክርስቲያኖች ይህን መመሪያ ቃል በቃል ተርጉመውት ነበር ። "የመንግሥተ ሰማያት" ጥሪ ጥብቅ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ለሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተሰጡ ሰብዓዊ ልምምዶች እንኳ መሠዋት የሚያስፈልጋቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ያሳያል ። ነገር ግን ሊቀበለው ለሚችል የተሰጠ ነው ፤ ብልጫ ያለው ኑሮ ሳይሆን የተለየ አገልግሎት ነው ፤ 1 ቆሮ- 7:7 ።

13-15/ እነዚህ ወላጆች ከአንድ ታላቅ መምህር ልዩ በረከት ይገኛል የሚል ግምት ሳይኖራቸው አልቀረም ። "ደቀ መዛሙርቱ" ፣ ይህን ማድረግ አስፈላጊ ስላልሆነ ሳይሆን ፣ ሥራ በጣም የበዛበት ስለ መሰላቸው ሕዝቡን ገሥጸው ይሆናል ። "መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና" ፤ ለሕጻናትና የሕጻን ዓይነት እምነት ላላቸው ነው ፤ 18:3 ። ማቴዎስ በማርቆስ ውስጥ የሚገኘውን የዚህን ተመሳሳይ ሳይጠቅስ ትቶታል ። ይህ አባባል ሕጻናትን የክርስቲያን ማኅበረሰብ አካል አድርጎ ለመቁጠር ማረጋገጫ ይሆናል ፤ 1 ቆሮ- 7:14 ። ከሐዋርያት ዘመን በኋላ አትከልክሉአቸው" የሚለው ቃል ከጥምቀት ነክ ትምህርት ጋር ተያይዞ ቢገኝም — 3:14 ፣ የሐዋ- 8:36 ፣ 10:47 አድራጎቱ ራሱ የሕጻናት ጥምቀት ምሳሌ ሊሆን አይችልም ።

## ሀብትና ሽልማት 19:16-20:16

19:16-30 ከማር- 10:17-31 ጋር የሚመሳሰል ነው ፤ ሉቃስ 18:18-30 ። ይሁን እንጂ ማቴዎስ በቁ- 28 ውስጥ ደቀ መዛሙርት በእስራኤል ላይ የሚፈርዱ መሆናቸውን የሚገልጽ አነጋገር ጨምሮበታል ፤ ተመሳሳይ አባባል በሉቃስ 22:28-30 ውስጥም ይገኛል ። በ20:1-16 ያለው የወይኑ አትክልት ሠራተኞች ምሳሌ የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። የቁሳቁስ ሀብት አደገኛነትና ሰው ባልጠበቀው ጊዜ እውነተኛ መንፈሳዊ ሽልማቶች የሚያገኝ መሆኑ ተጠቅሶአል ።

16-17/ ታሪኩ በማቴዎስ ውስጥ የቀረበው በማርቆስና በሉቃስ ውስጥ ከሚገኘው በተለየ መንገድ በጥያቄና መልስ ነው ። ማርቆስ ቸር መምህርና ለምን ቸር ትሉኛ

ላችሁ በሚል ጥያቄና መልስ አቅርቦታል ። ማቴዎስ ግን የሚያተኩረው በኢየሱስ ቸርነት ላይ ሳይሆን ቸርነትን ለማስተማር ባለው ሥልጣን ላይ ነው ። ሕጉ "መልካም" የሆነውን ነገር ቀደም ብሎ ገልጾታል ፤ ሚክ- 6፡8 ። "ትእዛዛትን ጠብቅ" ፡ ሰው "ወደ ሕይወት የመግባትን' መንገድ የሚያገኘው ሕግን በማክበር ነው በማለት የሰጠው መልስ ከኢየሱስ የተለመደ አይደለም ። ኢየሱስ ሰውየው የያዘው መንገድ ትክክለኛ እንዳልሆነ ለማሳየት ጥያቄውን ባቀረበበት መንገድ መልሶለት ይሆናል ። 18-19/ "የትኞቹን" ፡ የሚለው ቃል ሰውየው በአሳቡ ለአንዳንድ ሕጎች የበለጠ ዋጋ እንደሰጠና ሁሉን በእኩል እንዳልጠበቀ ያሳያል ። ኢየሱስ ለሌሎች ሰዎች ማድረግ የሚገባውን የሚገልጹ አምስት ሕጎችን ይሰጠዋል ፤ ደግሞ ማቴዎስ ብቻ የጻፈውን የተቀሩትን ሁሉ የሚያጠቃልለውን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚለውን ይጨምርበታል ፤ ዘሌ- 19፡18 ፡ ማቴ- 22፡37-39 ፡ ሮሜ 13፡9 ። 20/ "ደግሞስ የሚጎድለኝ ነገር ምንድር ነው" የለዘብተኛነት ጥያቄ ሳይሆን የጎደለው ነገር መኖሩ እንደተሰማው የሚያሳይ አጠያየቅ ነው ። 21/ "ፍጹም" ፡ ሌሎች ወንጌላውያን በዚህ ቃል ስላልተጠቀሙ ማቴዎስ የነበረውን ሁለት የሥነ ምግባር ደረጃዎችን የመፍጠር ዝንባሌ ይገልጻል የሚለው አሳብ ቀርቦአል ። ሆኖም ደቀ መዛሙርት ሁሉ ፍጹምነትን የግድ ዓላማቸው ሊያደርጉ ይገባል ፤ 5፡48 ። የቀረበለት ጥሪ ከገንዘቡ በመስጠትና ራሱንም ከሙሉ ልቡ ለክርስቶስ በማስረከብ ለባልንጀራው ያለውን ፍቅር እንዲያረጋግጥ ነበረ ። ክርስቲያን ከገንዘቡ በላይ የክርስቶስን ጌታነት ከፍ ማድረግ አለበት የሚለው ትምህርት ለሰው ሁሉ የተሰጠ ቢሆንም ፤ ላለማግባት የተሰጠው የትእዛዝ መመሪያ ለአንድ ሰው ብቻ እንደነበረ ሁሉ ፡ እንዲሁም ያለውን ሁሉ ሸጦ ሽያጩን ለድሆች መስጠት ከጥቂቶች ብቻ የሚጠየቅ ተግባር ነው ።

23/ ሀብታሞች ጨቋኞች ናቸው የሚል አባባል ቢኖርም — ሉቃስ 1፡53 — ብዙ አይሁዶች ሀብት ለጻድቃን የሚሰጥ ሽልማት ነው ብለው ያስቡ ነበር ። 24/ በግሪክ ቋንቋ ውስጥ ግመልና ገመድ የሚሉት ቃላት ተቀራራቢ ድምጽ ስላላቸው በግመል ፈንታ ገመድ መባል አለበት ፤ ወይም ደግሞ ግመል ካላጎነበሰ በስተቀር ሊያልፍባት የማይችል የመርፌ ቀዳዳ በመባል የምትጠራ ትንሽ የሆነች የከተማ መግቢያ በር ነበረች የሚል ትርጉም ለዚህ ጥቅስ ተሰጥቷል ። ከሁለቱ ትርጉሞች ማንኛውም ሊሆን ይችላል ፤ ሆኖም ማንኛውንም ለመደገፍ አጥጋቢ ማስረጃ አይገኝም ። ኢየሱስ አሳቡን ለማስረዳት ይህን የሚያስቅ ምሳሌ ተጠቅሞ ይሆናል ። በ7፡4ና 23፡24 ውስጥ ግመል የተጠቀሰው ከግዙፍነቱ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም ። 25/ ደቀ መዛሙርቱ ፡ ሀብት የመንፈሳዊ ኑሮ ሽልማት መሆኑን ሳይገምቱ አልቀሩም ። 26/ ደኅንነት በሰው ጥረት የማይገኝ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ፤ ስለዚህ ለሚቀበል ለማንኛውም ሰው ይሰጣል ።

27/ ጴጥሮስ በቸልተኝነት የተናገረው አስተያየት ይመስላል ፤ 4፡18-22 ። 28/ "አዲስ ዓለም" ፡ የዓለም አዲስ ልደት ማለት ነው ፤ ኢሳ 65፡17 ፡ 66፡22 ፡ ሮሜ 8፡18-22 ፡ ራዕይ 21፡1-5 ። ዩሲፈስ በዚህ ቃል የተጠቀመው የእስራኤልን ምድር አዲስ ልደት ለማመልከት ነበረ ። "የሰው ልጅ" ፡ የሁሉ ፈራጅ ነው ፤ 25፡31 ። አሥራ ሁለቱ ደግሞ የአዲሲቱ እስራኤል ሽማግሌዎች በመሆን ከርሱ ጋር ተባብረዋል ። "መፍረድ" ማለት መግዛት ወይም ማስተዳደር ማለት ነው ፡ መዝ- 2፡10 ። 29/ "ስለ ስሜ" ፡ እነዚህ ነገሮች በዚህ ምክንያት ሲደረጉ በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ የበለጠ የሚያረካ ብልጽግናና ዝምድና አለ ። "የዘላለም ሕይወት" ስጦታ ነው እንጂ ሽልማት አይደለም ፤ ነገር ግን እነዚሁ ከፍተኛውን መሥዋዕት ያቀረቡት ሰዎች ፡ ይበልጥ የውጤቱ በረከት ተሳታፊዎች ይሆናሉ ። እነዚህን ሽልማቶች መመኘት እንደ ሥጋዊ ምኞት አይቆጠርም ፤ 6፡4 ። 30/ የእግዚአብሔር አመለካከት የሰውን ከፍተኛ ግምት ውድቅ ያደርገዋል ፤ ይህም በሚመጣው ዓለም ግልጽ ይሆናል ፤ 20፡16 ።

20፡1-16/ ይህ ምሳሌ የመንግሥተ ሰማያትን እውነታ ለመግለጽ በሰዎች ዘንድ በማይደረግ የደመወዝ አከፋፈል ይጠቀማል ። እንደ ሌሎቹ ምሳሌዎች ሁሉ ብዙው ዝርዝር ታሪኩን ለማሳመር የተጨመረ ነው እንጂ ለእያንዳንዱ ዝርዝር መንፈሳዊ ትርጉም እንድናወጣለት አይደለም ። የምሳሌው ቁም ነገር ፡ ሰዎች ምንም የተለያዩ መንፈሳዊ መብቶች ቢኖሩአቸውም — 19፡29 — በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን የዘላለም ሕይወት የሚቀበሉ መሆናቸውን መግለጽ ነው ። "ዲናር" ፡ የአንድ ሙያተኛ የቀን ደመወዝ ነበረ ። ይህ የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ ፡ የተለያየ የሞራል ደረጃና መንፈሳዊ መብት ያላቸውን ሰዎች ወደ አገልግሎቱ የሚጠራ እግዚአብሔር ነው ፤ ስለዚህም ማንም ሰው ከሌላው በላይ ማግኘት አለብኝ ብሎ ሊጠይቀው አይችልም ። እግዚአብሔር የተናገረውን የሚሰጥ ስለሆነ ፡ በአሰጣጡ ረገድ ትክክለኛ ነው ፤ ቁ- 13 ። ፍትሕ ሳይዛባ ልግስና ሊጨምርበት ስለሚችል የፈለገውን ለመስጠት ፍጹም ሥልጣን አለው ፤ ቁ- 14 ። በተለይም በእስራኤል ውስጥ ሥልጣን የነበራቸው ሰዎች የእግዚአብሔር ልግስና የተሰጠው ለሌሎች በመሆኑ ተበሳጭተው ነበር ፤ ቁ- 12ና 15 ። የሚያመሰግኑት ከሚያጉረመርሙ ይልቅ የተባረኩ ሆኑ ፤ ቁ- 16 ። የምሳሌው ቁም ነገር የአባካኙን ልጅ ታላቅ ወንድም ታሪክ የሚመስል ነው ፤ ሉቃስ 15፡25-32 ።

## የመሲህ ሥቃይና ፍቅር 20፡17-34

ይህ ክፍል በዕውሩ ሰው ፈውስ ውስጥ ካለው አንዳንድ ልዩነት በስተቀር ማር- 10፡32-52ን ይመስላል ፤ ሉቃስ 18፡31-43 ። በዚህ ክፍል ምንባብ ውስጥ ኢየሱስ መሲሕ እንደሚሰቀልና ታላቅነት የሚገኘው በማገልገል መሆኑን አስተማረ ፤ በርጤሜዎስ ከአሳዛኝ ዕውርነት መላቀቁ ተገልጾአል ።

17-19/"አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ብቻቸውን አቅርቦ ፡ ያን ጊዜ ኢየሱስ የሰጠው ትምህርት መሲሕነቱን ለተረዱት ብቻ በግል የሚቀርብ ነበረ ። ይህ ስለ

ሞቱና ስለ ትንሣኤው ለሶስተኛ ጊዜ የተነገረ ትንቢት ነው ፤ 16፡21 ፣ 17፡22 ። ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ አልፎ የሚሰጥና የሚሰቀል መሆኑ በግልጽ የተነገረበት ሥፍራ ነው ። 20/ "የዘብዴዎስ ልጆች እናት" ፣ በማርቆስ ውስጥ አልተጠቀሰችም ፤ ያዕቆብና ዮሐንስ ብቻ ተጠቅሰዋል ። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት በነያዕቆብ ላይ በመቆጣታቸው — ቁ- 24 — አንዳንድ ምሁራን ማቴዎስ ልጆቹን ሳይሆን እናታቸውን ጥፋተኛ ለማድረግ ሞክሮአል ማለታቸው መሠረተ ቢስ መሆኑን ያሳያል ። 21/ ክብር ያለ ሥቃይ የሚገኝና ኢየሱስም በመንግሥተ ሰማያት ያሉትን ቦታዎች የሚሰጥ መሰላቸው ። 22/ ከመከራ ማምለጥ እንደማይችሉ አለመረዳታቸው አንደኛ ስሕተታቸው ነበር ። "ጽዋው" ፣ የመከራ ጽዋ ነው ፤ 26፡39 ፤ ኢሳ- 51፡17 ። በተጨማሪም ማርቆስ መከራውን ጥምቀት ብሎ ይጠራዋል ። 23/ ያዕቆብ በእምነቱ ምክንያት ሞተ ፤ የሐዋ- 12፡2 ። ምናልባት ዮሐንስ እስኪ ያረጅ ድረስ ሳይኖር አልቀረም ። ኢየሱስ በጌቴሴማኔ ሞትን በተጋፈጠ ጊዜ ሁለቱም ሸሹ ። በመንግሥተ ሰማያት ሥፍራን "ያዘጋጀ አባቱ" ነው ። ኢየሱስ በመንግሥተ ሰማያት ከሁለቱ የትኛው እንደሚበልጥ ማወቁን አልገለጸም ።

24/ ሌሎቹም እንደ ያዕቆብና ዮሐንስ የራስን ማስቀደም ጉጉት ታይቶባቸዋል ። 25/ በብዙ ኅብረተ ሰቦች ውስጥ ሥልጣን የሚፈለገው ለግል ጥቅም ነው ። 26/ "በእናንተስ እንደዚህ አይደለም" ፣ የመንግሥተ ሰማያት መመዘኛዎች ፍጹም ልዩ ናቸው ። ታላቅነት የሚታየው በማገልገል ነው ። አገልጋይ ተብሎ የተተረጐመው ዲያቆኖስ የሚለው የግሪኩ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለክርስትና አገልግሎት በብዛት የተጠቀሰ ሲሆን እያንዳንዱ አገልጋይ እውነተኛ ትርጉሙን ማስታወስ አለበት ። 28/ የማገልገል ትርጉም መሠረት የሆነው "የሰው ልጅ" ምሳሌና የርሱ አስታራቂ ሞት ነው ። አይሁድ አንድ ጻድቅ ቢሞት የሌሎችን ዕዳ ይከፍላል የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው ። ያሁኑ ጥቅስ የተመሠረተው ኢሳ- 53፡10-12 ላይ ሳይሆን አይቀርም ። ላይትሮን የሚለው "ቤዛ" ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል ለማን እንደተከፈለ ሳይናገር ከፍ ያለ ዋጋ በመክፈሉ ነጻ መውጣትን ያመለክታል ። "ለብዙዎች" የሚለው የዳኑትን የሚወስን ሳይሆን ሁሉን የሚያጠቃልል ነው ፤ 26፡26 ። አንቲ የሚለው የግሪኩ መስተዋድድ እኩል ወይም ምትክ የሚል አሳብ አለው ። በሥነ ምግባር ትምህርት ውስጥ እንኳ ታላቅ መንፈሳዊ እውነትን ማስተማር ይቻላል ፤ ፊል- 2፡1-11 ። ኢየሱስ ትሑትና ሥቃይ ሊቀበል ያለው የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑ እንዲሁም ሁሉ ከኃጢአታቸው የሚድኑበትን መንገድ ለማዘጋጀት ራሱን መሥዋዕት ለማድረግ መቻሉ ተዘርዝሮአል ።

29-34/ 9፡27-31 እዩ ። የማቴዎስ ዘገባ ከማርቆስ አጠር ይላል ። ሁለተኛው ሰው ዕውር እንደነበረ ቢጠቅስም ስሙ በርጠሜዎስ መሆኑን አልገለጸም ። "የዳዊት ልጅ" የሚለው ጩኸት አሁን ልዩ ትርጉም ያለው አባባል ነው ፤ 9፡27 ። "አዘኔላቸውና ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ" ፣ ይህንን የጠቀሰው ማቴዎስ ብቻ ነው ። በቅርቡ ወደ ሞት የሚመራው የኢየሱስ ራስን የመስጠት ፍቅር እዚህ ላይ ይታያል ።

## ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ መግባትና ቤተ መቅደሱን ማጽዳት 21፡1-17

በዚህ ክፍል ማቴዎስ ከማርቆስ ጋር መስማማቱን ይቀጥላል ፤ ነገር ግን ማቴዎስ የበለስዋን ዛፍ መረገም የጻፈው ማርቆስ ያቀረበውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ አይደለም ። እንዲሁም በቤተ መቅደስ ውስጥ ልጆች የጮኹትን ጩኸት ይጨምራል ፤ ማር- 11፡1-11 ፣ 15-17 ፣ ሉቃስ 19፡28-40 ፣ 45 ። በተጨማሪም በማቴዎስ ጽሑፍ በተደጋጋሚ የሚገኘውን የተባለው ይፈጸም ዘንድ የሚለውን አባባል ያስገባል ። የመሲሑ ወደ ዋናይቱ ከተማ መግባት ታላቅ ሕዝባዊ ፍቅር ቀሰቀሰ ፤ ነገር ግን ማቴዎስ በአህያ ላይ መቀመጡ የመሲሑ ሥራ ሰላማዊ መሆኑን ቢያሳይም በዝባዦቹን ከቤተ መቅደስ በማባረሩ በደልን የማይታገሥ መሆኑን ሊገልጽ ችሎአል ።

1/ "የደብረ ዘይት ተራራ" ፣ መሲሕ በዚህ ተራራ ላይ ይገለጣል ብለው አይሁድ ይጠብቁ ነበር ። "ቤተፋጌ" ፣ ምናልባት ኮረብታው በስተምሥራቅ ያለና ከኢየሩሳሌም ሆኖ የማይታይ ሥፍራ ይሆናል ። 2/ "በፊታችሁ ያለችው መንደር" ፣ ቤተፋጌ ወይም ቢታንያ ልትሆን ትችላለች ። "ታገኛላችሁ" ፣ ቀደም ብሎ ከወዳጆቹ ጋር ስለተነጋገሩበት ይሆናል ። 3/ "ጌታ" ፣ ኢየሱስን ወይም እግዚአብሔርን ወይም የአህያዋን ጌታ ያመለክት ይሆናል ። 5/ "ይፈጸም ዘንድ" ፣ ጥቅሱ ከኢሳ- 62፡11ና 9፡9 የተውጣጣ ነው ። ጥቅሱ አንድን እንስሳ ብቻ የሚያመለክት መሆኑ አያጠራጥርም ፤ ብዙዎቹ ምሁራን ማቴዎስ ይህን በደንብ ስላልተረዳ ሁለተኛ እንስሳ ጠቀሰ ይላሉ ፤ ቁ- 2ና 7 ። ወንጌላዊው የግሪኩንና የዕብራይስጡን ብሉይ ኪዳን አጠናቅቆ ያወቀ ስለሆነ አልተረዳም ማለቱ እውነት አይመስልም ። ማቴዎስ ማንም ያልተቀመጠበት የሚለውን ማርቆስ የጻፈውን ሐረግ አልጨመረም ፤ ምናልባት እናቲቱን የጠቀሰው በትርምስምስ ሕዝብ መካከል ውርንጫይቱን ለማረጋጋት አስፈላጊ ስለነበረች ይሆናል ። በዘካ- 9፡9 ላይ "አህያ" የሚለው የግሪኩ ቃል ወንድ አህያን ያመለክታል ፤ ማቴዎስ ግሪኩን ሲተረጉም ይህን ቢገነዘብ ኖሮ በታሪኩ ውስጥ ከሴት አህያ ጋር አያመሳስለውም ነበር ።

7/ "ተቀመጠባቸውም" ፣ ብዙ ትርጓሜዎች ይህን ቃል በልብሶቹ ላይ ተቀመጠ ከማለት ይልቅ በእንስሳቱ ላይ ተቀመጠ ብለው መተርጎማቸው የሚያስገርም ነው ። 8/ "ልብሳቸውንም አነጠፉ" ፣ 2 ነገ- 9፡13 እዩ ። "ከዛፍ ጫፍ ጫፉን" ፣ እንደ ንጉሥ የተቀበሉት መሆኑን ያመለክታል ። "ሆሳዕና" ፣ አሁን አድነን ማለት ሲሆን በተለምዶ የምሥጋና ጩኸት ነበረ ። "በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው" ፤ ከመዝ- 117፡26 የተወሰደ ጥቅስ ነው ። ይህ በዳስ በዓል ፣ በምረቃ በዓልና በፋሲካ በዓል የሚዘመር የምሥጋና ክፍል ነው መዝ- 112-117 ። የመዝሙሩ በረከት ወደ ፋሲካ በዓል በሚመጡ ተሳላሚዎች ሁሉ ላይ ነበረ ። ይህ መዝሙር

በተለይ ከሁሉ በላይ ለሆነው ተሳላሚና ወደ መንግሥቱ ለመግባት ለመጣው "ለዳዊት ልጅ" የሚስማማ ነው ። ይህ ድርጊት የተፈጸመው በፋሲካ በዓል ጊዜ ሳይሆን በሌላ በዓል ጊዜ ነው የሚል አጠያያቂ አሳብ ቀርቦ አል ፤ በዚህ ቦታ ግን ድርጊቱ ልዩ ትርጉም የሚያቀር በው በፋሲካ ጊዜ ቢደረግ ነው ። 10-11/ "መላው ከተማ - - - ተናወጠ" ፣ ይህ ዐረፍተ ነገርና የሕዝቡ ጥያቄና መልስ የሚገኙት በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። የገሊላ ሕዝብ የራሳቸው አገር ነቢይ አድርገው ቢቆጥ ሩትም ፣ የተፈጸመው ነገር ሁሉ መሲሕ መሆኑን አጉ ልቶ ያሳያል ፤ ከዘካርያስ የተጠቀሰው ክፍለ ምንባብ ፣ ግዛቱ ሰላም የሠፈነበት ዓለም አቀፍ ግዛት መሆኑን ያመለክታል ።

12/ "መቅደስ" ፣ ሥፍራው በሞላው ቤተ መቅደስ ቢባልም በተለይ በአደባባዩ ውስጥ አሕዛብ ብቻ የሚሰ በሰቡበት ሥፍራ ነበረ ። "ገንዘብ ለዋጮች" ፣ የቤተ መቅደስ ግብር የሚከፈልበትን የውጭ አገር ገንዘብ የሚለውጡ ነበሩ ። በገበያቸውም ብዙ ያተርፉ ነበር ። "የርግብ ሻጮች" ፣ የድሆች መሥዋዕት የሚሆኑ ርግ ቦችን ይሸጡ ነበር ፤ ሉቃስ 2፡24 ። ይህን በመሰለው ንግድ ብዙ ገንዘብ በግፍ ይወሰድ ነበር ። 13/ ይህ ትንቢ ታዊ ድርጊት መሲሕ ለመፍረድ የሚመጣ መሆኑን ያሳ ያል ፤ ሚል- 3፡1-5 ። ኢየሱስም ኢሳይያስ 56፡7ና ኤር-7፡ 11 ይጠቅሳል ። ማቴዎስ ከመጀመሪያው ጥቅስ ለሰዎች ሁሉ የሚለውን ሐረግ ቢተውም የአይሁድ አንባቢዎች ጥቅሱ የአሕዛብን አደባባይ የሚያመለክት መሆኑን ሳያውቁ አልቀሩም ። ሁለተኛው ጥቅስ የተጠቀሰው ክፍለ ምንባቡ በሕዝቡና በቤተ መቅደሱ ላይ የሚመ ጣውን ፍርድ የሚጠቁም ስለሆነ ነው ። የሁለቱ ጥቅስ አጠቃላይ አሳባቸው አሮጌው ሥርዓት በአዲሱ መተ ካቱን ይገልጻል ፤ ቁ- 43 ። 14-16/ "ዕውሮችና አንካ ሶች" ፣ ዳዊት አልተቀረቀረላቸውም ፤ ነገር ግን የዳዊት ልጅ ይፈውሳቸዋል ፤ 2 ሳሙ- 5፡8 ። ልጆቹ ፣ ምን እንደ ተናገሩ ሳይረዱ ሕዝቡ ይጮኹ የነበረውን በመድገም ጮኹ ፤ ሆኖም ፈጣሪ ለሆነው ለእግዚአብሔር የም ሥጋና መግለጫ ስለነበረ አይከለከልም ፤ ሉቃስ 19፡39 ፤ መዝ- 8፡2 ። ኢየሱስ በአድራጎቱ የሕዝቡንና የልጆቹን የምስጋና ጩኸት በመቀበሉ ፣ ተመሥርቶ ለነበረው ሥርዓት አንገብጋቢ ጥያቄ ፈጠረ ። 17/ "ከከተማ - - ወጣ" ፣ ብዙዎቹ ተሳላሚዎች ከማደሪያ እጥረት የተ ነሳ ከከተማ ክልል ውጭ ያድሩ ነበር ።

## ፍርድ በአይሁድ መሪዎችና በሕዝቡ ላይ 21 ፡ 18 - 22 ፡ 14

ማቴዎስና ማርቆስ በጽሑፋቸው ውስጥ የበለስዋን መረገም በተለያዩ ቅደም ተከተሎች ያቀርባሉ ፤ 21፡ 18-22 ። ይሁን እንጂ በዚህ ክፍለ ምንባብ ውስጥ ያቀ ረቡአቸው ሶስት ዘገባዎች ፣ የበለስዋ መረገም ፣ ኢየሱስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ያቀረበው ጥያቄና በአይሁድ መሪ ዎች ላይ የተሰነዘረው ፍርድ ሲሆኑ ፣ ዋና አሳባቸው ተመሳሳይ ነው ፤ 21፡23-22 ፡14 ፣ ማር- 11፡12-14 ፣ 20-33 ፣ ሉቃስ 20፡1-8 ። የሁለቱ ልጆች ምሳሌና ስለ ዮሐንስ የተጠቀሰው ታሪክ በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ፤ ቁ- 28-32 ። የከፉዎች ገበሬዎቹ ምሳሌ — ቁ- 33-46 ፣ ከማር- 12፡1-12 ጋር ተመሳሳይ ነው ፤ ሉቃስ 20፡9-19 እዩ ። የንጉሡ ሠርግ ምሳሌ በሉቃስ ውስጥ ከተጻፈው ጋር በጥቂቱ ቢመሳሰልም እንኳን የሚገኘው በማቴ ዎስ ውስጥ ነው ፤ 22፡1-14 ፣ ሉቃስ 14፡15-24 ። በእግ ዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚመጣውን ፍርድ በለስዋን በማድረቅ ካሳሰባቸው በኋላ በሶስት ምሳሌዎች አሳ ቡን ጠንከር አድርጎ ገለጸላቸው ።

18-19/ "የበለስ ዛፍ" ፣ በለሲቱ የበሰለ ፍሬዋን የም ትሰጥበት ወቅት ባይሆንም እንኳ ትንንሽ የሚበላ ፍሬ መያዝ ነበረባት ። በሆሴዕ 9፡10 ውስጥ በለስ የእስራ ኤል ምሳሌ ሲሆን የአሁኑ ክፍለ ምንባብ ቃል ኪዳኑን በመጣስዋ ስለሚደርስባት ፍርድ ይናገራል ። ማቴዎስ "ያን ጊዜውን" ደረቀች ይላል ። ተአምር ሲፈጸም ውጤቱን ወዲያውኑ ማየት የተለመደ ነበረ ፤ 8፡3 ፣ 20፡ 34 ። ይህ ድርጊት ምንም ያልተጠበቀ ቢሆንም እምነት በሌላት እስራኤል ላይ የሚመጣውን ፍርድ እንደሚያሳይ አያጠራጥርም ፤ በሉቃስ 13፡6-9 ከሚገኘው ምሳሌ ጋር አነጻጽሩት ። 20-22/ እምነት የሚያስገኘውን ወሰን የሌለውን የእግዚአብሔርን ኃይል ያመለክታል ፣ 17፡19። 23/ "እነዚህን" ፣ የቤተ መቅደሱን መጽዳትና ከርሱ ጋር የተያያዘውን ድርጊት በይበልጥ የሚመለከት ሊሆን ይችላል ፤ ሆኖም ቃሉና ድርጊቶቹ የነቢይ ዓይነት በመሆናቸው ትምህርቱንም ሊጨምር ይችላል ። አንድ ሰው ነቢይ ወይም መምህር ሆኖ ሲመጣ በምን ሥልጣን ትሠራለህ ብለው እንደሚጠይቁት ሁሉ የኢየሱስንም ሥልጣን ለማወቅ ፈለጉ ። 25/ "የዮሐንስ ጥምቀት" ፣ አንዳንድ ጊዜ እንደማምለጫ መልስ ተቆጥሮ ይተረጉ ማል ፤ ነገር ግን ዮሐንስ በቀጥታ በእግዚአብሔር እንደ ተጠራ ኢየሱስም በእግዚአብሔር ተጠርቶአል ማለት ሊሆን ይችላል ፤ ወይም ሕግንና ነቢያትን ከሚወክለው ከዮሐንስ እጅ ኢየሱስ ሰማያዊ ሥልጣን የተቀበለበትና አምላካዊ ድምጽ የተነገረበት በጥምቀት ጊዜ ነበረ ማለት ነው ፤ 3፡13-17 ። 27/ መምህራን ለመሆን የማይ በቁ መሆናቸውን በመግለጻቸው ኢየሱስ ስለ ሥልጣኑ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አያስፈልገውም ።

28-32/ ታሪኩ ሃይማኖተኞች ነን በሚሉና በተገለሉት መካከል ያለውን ልዩነት በጉልህ ያሳያል ። በዚህ አንጻር የዮሐንስም ሆነ የኢየሱስ አገልግሎት ሰዎችን ስለ ከፋፈላቸው የጠበቁትን ሊያገኙ አልቻሉም ። እንደ ገና ኋለኞች ፊተኞች ፣ ፊተኞችም ኋለኞች ናቸው ፤ 20፡16 ።

33-46/ ይህ ምሳሌ እስራኤልን የሚጠቁም መሆኑ አያጠራጥርም ፤ ምክንያቱም እስራኤል በኢሳ- 5፡1-7 በወይን ቦታ ተመስላለች ፤ መዝ- 79፡8-11 ። 33-36/ "ገበሬዎች" ፣ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑትን ነቢያት የሚገድሉ የአይሁድ መሪዎች ናቸው ፤ ኤር- 7፡25 ። 37/ "በኋላ ፣ በልጁ" ፣ በመጨረሻ በኢየሱስ በኩል ያቀረበውን ልመና ያመለክታል ። 38/ "ርስቱ" ፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእስራኤልን ሕዝብ — መዝ- 32፡12 ፣ ወይም የተስፋይቱን ምድር የሚያመለክት ቃል ነው ፤ መዝ- 104፡11 ። 41/ ለኢየሱስ ጥያቄ ጉባ

ዓው መልስ እንደሰጠ የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው ። ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ሰዎችን እንደሚያስቆጣቸው በግ ልጽ ያሳያል ፤ 2 ሳሙ- 12፡1-6 ። 42/ ከመዝ- 117፡22 የተጠቀሰ ነው ። ኢየሱስ በድንጋይ ስለ መመሰሉ የሐዋ- 4፡11 ፣ ሮሜ 9፡33 ፣ ኤፌ- 2፡20ና 1 ጴጥ- 2፡7ን ተመ ልከቱ ። 43/ በማቴዎስ ውስጥ የምሳሌው ትርጉም ግልጽ ነው ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት በአገር ደረጃ ከተ ቋቋመው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ተወስዶ በመንፈሳዊ ደረጃ ለተቋቋመው ፣ ማለት ፍሬዋን ለሚያደርገው ሕዝብ ትሰጣለች ። 45-46/ አሁን ጉዳዩ "ለሊቀ ካህናትና ለፈሪሳውያን" ግልጽ ሆኖ ነበረ ፤ ነገር ግን በዮሐንስ ላይ ከመናገር እንደተቆጠቡ ሁሉ አሁንም በኢየሱስ ላይ ርምጃ ከመውሰድ ተቆጥበዋል ፤ ቁ- 26 ።

22፡1-14/ ምሳሌው ከቀደሞች ገበሬዎቹ ከተሰኘው ምሳሌ ጋር ይመሳሰላል ። 1/ "ሠርጉ" ፣ ከራዕይ 19፡9 ጋር የተያያዘ አሳብ ነው ። ጥሪው ከአንድ ጊዜ በላይ ተልኮአል ፤ ነገር ግን የተጠሩት ሰዎች በዕለታዊ ተግ ባራቸው ላይ መዋልን መረጡ ። 6-7/ አንዳንድ ምሁራን እነዚህ ቁጥሮች ከምሳሌው ጋር አብረው ስለማይሄዱ አንድ አንባቢ 21፡35-36ን መሠረት በማድረግ የኢየ ሩሳሌምን ውድቀት የሚያመለክት ማስታወሻ አድርጎ በብራናው ጠርዝ ከጻፈው በኋላ ባልታወቀ ጊዜ በመጽ ሐፉ ውስጥ ተጨመረ የሚል አሳብ ያቀርባሉ ። 9/ ጥሪው ለተገለሉት ሁሉ ነው እንጂ አሕዛብን ብቻ የሚ ጠቅስ አይደለም ። 10/ "ክፉዎች" ፣ 13፡47ን ተመል ከቱ ። 11/ "የሠርጉ ልብስ" ፣ ተጋባዡ ማምጣት የነ በረበት እውነተኛ የመሆኑ ማስረጃ የሆነ የመልካም ሥራው ምሳሌ ይሁን ወይም ጋባዡ መስጠት የነበረበት ይቅርታ የመስጠቱ ምልክት ይሁን በግልጽ አይታወ ቅም ። 14/ "የተጠሩት ብዙዎች" ፣ ጥሪው በወንጌል በኩል የሚቀርብ ጥሪ ሲሆን ለይስሙላ ብቻ ተቀበሉት እንጂ በእግዚአብሔር አልተመረጡም ።

## ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ጋር የተደረገ ክርክር 22፡15-46

ይህ ክፍል ምንባብ ከማር- 12፡13-37 ጋር በጣም ይመሳሰላል ፤ ሉቃስ 20፡20-44 እዩ ። ማቴዎስ ግን የሕግ አዋቂውን ጥያቄ ያሳጥረዋል ። ኢየሱስ ከአይሁድ መሪዎች ጋር ባደረገው የመጨረሻው ክርክር ስለ ግብር ቁ- 15-22 ፣ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት — ቁ- 23-33 ፣ ደግሞ ከሁሉ ስለሚበልጠው ሕግ ላቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ሰጠ ፤ ቁ- 34-40 ። እርሱም ደግሞ ስለ መሲሕ ምን አስተያየት እንዳላቸው ይጠይቃቸዋል ፤ ቁ- 41-46 ።

15-22/ "የሄሮድስ ወገኖች" የመጡት በአገር ላይ አምጸአል ብለው ለመክሰስ እንዲያመቻቸው ምክንያት ለማግኘት መሆኑ አያጠራጥርም ። 17/ "ተፈቅዶአልን?' ይህ የግብር መክፈል ጉዳይ በአይሁድ ዘንድ ትልቅ ክርክር ያስነሣ ነበር ። 20/ "መልክና ጽሕፈት" ፣ ቄሳ ርን የማምለክ ዝንባሌ አለው በማለታቸው አይሁድ ይህን ገንዘብ ይጠሉ ነበረ ። 21/ "የቄሣርን ለቄሣር" ፣ ይህ የችግሩን እምብርት የሚነካና ጥበብ የተሞላበት መልስ ነበረ ። ቄሣር ሕጋዊ መንግሥትን ይወክላል ፤ ከዚህም የተነሣ ገንዘብ የርሱ በመሆኑ ግብር ማስከፈል ይችላል ። ነገር ግን ሰው የእግዚአብሔር መልክና ምስል ስላለበት ሕይወቱ በቅድሚያ ለአምላካዊ ፈቃድ መገ ዛት አለበት ።

23-33/ "ሰዱቃውያን" እምነታቸውን ሙሉ በሙሉ በአምስቱ የኦሪት መጻሕፍት ላይ መሠረቱ ። ጥያቄያ ቸው ዘር ለመተካት ሲባል ወንድም የወንድሙን ሚስት ያግባ በሚለው ጋብቻ ላይ የተመሠረተ ነበረ ፤ ዘዳ- 25፡5 ። 29-33/ የትንሣኤን ትምህርት ለመቃወም ያቀ ረቡት አሳብ ፣ በምትመጣዋ በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ ያለው አኗኗር በምድር ላይ ካለው የተለየ እንደ ሚሆን በሚያሳየው መልስ ተሽሮአል ። "መላእክት" ፣ ሰዱቃውያን በመላእክትም አያምኑም ፤ የሐዋ- 23፡8 ። መላእክት ቁሳዊ ያልሆነ አካል ያላቸው ፍጥረቶች እንደመሆናቸው መጠን በሚመጣው ሕይወት ሰዎች የሚኖራቸው አካል ከነዚሁ ከመላእክት አካል ጋር የተመሳሰለ እንደሆነ እንረዳለን ። ሰዱቃውያን ኢየሱስ የጠቀሰውን ዘጸ- 3፡6ን ሕጋችን ብለው ቢመኩበትም በርግጥ ትርጉሙን አላወቁትም ። እግዚአብሔር ስለ ራሱ በሚናገርበት ጊዜ የአባቶች አምላክ መሆኑን ይገልጻል ። ነገር ግን አባቶች ከሞቱ ብዙ ዘመን አልፎ አል ። ይህ እንግዲህ በአንድ ዓይነት መንገድ አሁንም በሕይወት አሉ ማለት ነው ። "የአብርሃም አምላክ" ፣ የመቤዠት ቃል ኪዳን የሚጠብቅ መሆኑን ለማሳየት ተደጋግሞ የተጠቀሰ ሐረግ ሲሆን ለዚህ ትምህርት በተለይ ተስማሚ ነው ።

34-40/ የቀረበው ጥያቄ በጣም አከራካሪ ነበር ፤ ነገር ግን እርሱን ለመፈተን ሙከራ የተደረገው ምናል ባት ከጥላቻ የተነሣ ሳይሆን አልቀረም ። ዘዳ- 6፡5 ከዘሌ- 19፡18 ጋር መጣመሩ በአይሁድ ሃይማኖት ጽሑፍ ውስጥ እንግዳ ነገር አልነበረም ። ኢየሱስ የብ ሉይ ኪዳን ቁም ነገር ፍቅር መሆኑን ያሳያል ። 41-45/ ስለ መሲሕ ያላቸው አስተያየት በርግጥ ምን እንደሆነ መጠየቅ ነበረባቸው ። ማቴዎስ ኢየሱስ "የዳዊት ልጅ ነው" የሚለውን አሳብ ብዙ ጊዜ ጠቅሶአል ፤ 1፡1 ወዘተ ። ነገር ግን ይህ ለርሱ የሚበቃው ስያሜ አይደ ለም ፤ ጌታም ነውና ። መዝ- 109፡1ን መጥቀሱ ችግር ፈጥሮአል ። የዳዊት መዝሙር ተብሎ ቢጠራም እንኳ በበለጠ ለዘማሪው ጌታ ከዳዊት ወገን ለሚመጣው ንጉሥ የቀረበ የምሥጋና መዝሙር ይመስላል ። ነገር ግን የአይሁድ መምህራን መዝሙሩን የተረዱት መሲ ሕን ያመለክታል ብለው ነው ፤ እውነተኛ ፍጻሜ ያገኘ ውም ከዳዊት በሚበልጠው ነው ። መዝሙሩ በዕብራ ውያን መልእክት ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሶአል ። 46/ የጥያቄው ጊዜ አብቅቶአል ። በክርክር ሊያሸንፉት አልቻሉም ። ከዚያም ቀጥሎ በሰው ጉልበት ሲጠቀሙ ይታያሉ ፤ 26፡47 ።

## የክርስቶስ ማስጠንቀቂያዎችና የፍርድ ትንቢት 23፡1-25፡46

በዚህ ሥፍራ ማቴዎስ ኢየሱስ ስለ ፍርድ የተናገረ ውን አምስተኛውን ንግግር ያቀርብልናል ፤ የምዕራፍ 23

ንግግር በጸፎችና በፈሪሳውያን ላይ የተሰጠውን ነቀፋና በዚያ ትውልድ ላይ የሚመጣውን ፍርድ ይዞአል ። ከንግግሩ ብዙ ነጥቦች በማቴዎስ ብቻ የሚገኙና ለአይሁድ ክርስቲያኖች ከተጻፈው ወንጌል ጋር የሚስማሙ ናቸው ። ምዕራፍ 24 ማርቆስ ምዕ- 13ን ይመስላል ፤ የተጨመሩት ጥቂት ነገሮች ደግሞ ከሉቃስ 21 ጋር ይመሳሰላሉ ። በአይሁዶች ላይ በሚመጣው የመጨረሻው ፍርድ ላይ ያተኩራል ። ምዕ- 25 የመጨረሻውን ፍርድ የሚያመለክቱና በማቴዎስ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ሶስት ምሳሌዎች ይዞአል ። እነዚህ ምዕራፎች የሚያተኩሩት በወደፊቱ የክርስቶስ ምጽአት ላይ ከሆነ ፥ ወንጌሉ በጠቅላላ በዚህና በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመገለጥዋ መካከል የተስተካከለ ትምህርት ያቀርባል ። እያንዳንዱ ወንጌላዊ የኢየሱስን ንግግር ሲመርጥ የራሱ የሆነ አመለካከት እንዳለው ቢታመንም ፥ ማቴዎስ ስለ መጨረሻው ዘመን የጻፈው ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ለመመልከት አይደለም ፤ ስለዚህ ይህን አሳብ የበለጠ ከፍ የሚያደርገው ክፍል የማቴዎስ አይደለም ማለት መሠረተ ቢስ ክርክር ነው ።

## ወዮታዎች ፥ በጸፎችና በፈሪሳውያን ላይ 23 ፥ 1 -39

ይህ ክፍል በማር- 12፥38-40 ያለውን ለጸፎች የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ የሚተካ የንግግሮች ስብስብ ነው ። በሉቃስ 11፥37-52 ውስጥ ለሚገኙት ማስጠንቀቂያዎች ብዙ ተመሳሳዮች አሉ ፤ የመጨረሻዎቹ ሶስት ቁጥሮችም ከሉቃስ 13፥34 ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው ። በጸፎችና በፈሪሳውያን ላይ የተሰነዘረ ማስጠንቀቂያ አለ ፤ ቁ- 1-12 ፤ ለኢየሩሳሌም ካለቀሰው ለቅሶ በፊት ቁ- 37-39 ፥ ሰባት ወዮታዎች አሉ ፤ ቁ- 13-36 ። ምዕራፉ በሙሴ መዝሙር ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል ፤ ዘዳ- 32 ።

1/ "በዚያን ጊዜ ኢየሱስ - - - ነገራቸው" ፥ ይህ ምዕራፍ ያለፈው የክርክር ምዕራፍ ቅጥያ ነው ከማለት ይልቅ የአዲስ ንግግር መክፈቻ ነው ማለቱ ይሻላል ። "የሙሴ ወንበር" ፥ በየምኵራቡ ውስጥ መምህር ተቀምጦ የሚያስተምርበትን ወንበር ይጠቁማል ። 3/ "ያዘዙአችሁን ሁሉ" ፥ 15፥1-20ን በማሰብ ይህንን አባባል ቃል በቃል መተርጎም ይከብዳል ። በሙሴ ሕግ መሠረት ሲያስተምሩ ማለቱ ሊሆን ይችላል ። "እየተናገሩ አያደርጉትምና" ፥ ወላዋይነት አሳሳቢ መሆኑን የተረዱ ፈሪሳውያን ስለነበሩ ይህ አነጋገር ፈሪሳውያንን በሙሉ የሚያጠቃልል ላይሆን ይችላል ። 4/ የፈሪሳውያንን ሸክምና ቀምበር ኢየሱስ በ11፥28-30 ከተናገረው ጋር አነጻጽሩት ። 5/ "ለሰው እንዲታዩ" ፥ 6፥1 ፥ 5 ፥ 16 ። "አሸንክታብ" ፥ የአሪትን ጥቅሶች የያዙ ትንንሽ ክታቦች ናቸው ፤ ዘጸ- 13፥16 ፥ ዘዳ- 6፥8 ፥ 11፥18 ። አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት ለጸሎት ብቻ ነበረ ። "ዘርፍ" ፥ በልብስ ግርጌ እንደ ጌጥ የሚሰፋ ነው ፤ 9፥20 ። 6-7/ እነዚህ ነገሮች ሁሉ አንድ ሰው ከፍተኛ የሕግ ዕውቀት እንዳለው የሚያሳዩ ምልክቶች ሆነው ይቆጠሩ ነበር ። 8-10/ በአይሁዶች አነጋገር "መምህር" ወይም ረቢ ማለት ከእኔ የሚልቅ ማለት ነው ። "አባት" ፥ ምናልባት የጥንቶቹ መምህራን መጠሪያ ይሆናል ። ጌታ ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል መምህር ከሚለው ማዕረግ በላይ የሆነ ነው ። እውነተኛ መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸው እግዚአብሔርና ክርስቶስ ስለሆኑ እነዚህ ቃላት አንዳቸውም መብትን አያመለክቱም ። የአባባሉ ዋና አሳብ ቃላቱ እንዳይጠቀሱ መከልከል ላይሆን ይችላል ፤ ነገር ግን የተከለከለው ፥ ተማሪው በመምህሩ ፥ መምህሩ ደግሞ በተከታዮቹ ሙገሳ እንዳይመካ ነው ። 11-12/ ሰዎች ከፍተኛ ዋጋ ላልሰጡት ነገር ኢየሱስ ከፍተኛ ዋጋ ሲሰጠው እናየዋለን ፤ 20፥25-28 ።

13/ "ወዮላችሁ" ፥ ይህ ፈሪሳውያንን በደንብ የሚመረምር ፍርድ ነው ፤ ሆኖም የተደረገው በፍቅር ነው ። በወዮታዎችና በቡራኬዎች መካከል ተመሳሳይነት አለ ፤ 5፥1-12 ። ወደ ሰማያዊ መንግሥቱ አለመግባት መጥፎ ዕድል ነው ፤ ሌሎች እንዳይገቡ መከልከል ደግሞ ከዚያ የከፋ ነው ። ቁ- 14 በብዙ ብራናዎች ውስጥ ባለመገኘቱ ምክንያት ቢታለፍ ይሻላል ። 15/ ፈሪሳውያን ኢየሱስ ያቀረበውን ምሥራች ለመቀበል ባለመፈለግ ብቻ ሳይወሰኑ በቅንዓት ተነሣሥተው ወደ ተዛባ ጎዳና የሚመራ ትምህርት በማስተማር ተከታዮችን ይሰበስቡ ነበር ። እነዚህ ተከታዮች ፥ ከአሕዛብ ወገን ሲሆን ለአዲስ ገቢዎች የሚሰጠውን ጥምቀትና ግዝረት በመቀበል ልክ እንደ አይሁዶች የተቆጠሩ ነበሩ ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ የተባሉት ሰዎች ይህንን ጥምቀትና ግዝረት ለመቀበል አሻፈረኝ ባዮች ነበሩ ። 16-22/ በትክላ በተቀደሱ ነገሮች መማልን ለማስቀረት ስለሆነ አሳቡ የመምህራኑ ዓላማ ጥሩ ነበረ ፤ ነገር ግን ከባሕሉ የተነሣ የተፈቀዱት መሐላዎችን የሚቆጣጠሩ መመሪያዎችን ማውጣት ነበረባቸው ። ሁሉ ነገር የሚገኘው ከእግዚአብሔር ስለሆነና ቁጥጥራቸው የሰውን ተንኰል ሊገታ ባለመቻሉ ኢየሱስ መሐላን ከነጭራሹ ከለከለ ፤ 5፥33-37 ። 23-24/ ፈሪሳውያን አሪት ከሚያዘው በላይ ሠሩ ፤ ዘዳ- 14፥22 ። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ማድረግ አልወደዱም ፤ ሚክ- 6፥8 ። ኢየሱስ ለመንፈሳዊ ይዞታ ያላቸውን የተዛባ አስተያየታቸውን ለመግለጽ ፥ ላለመርከስ ብለው ትንኞችን ሲያጠሩ በጣም እርኩስ የሆነውን ግመል ይውጣሉ ብሎ ወቀሳቸው ፤ ዘሌ- 11፥41 ፥ 19፥24 ።

25-26/ ፈሪሳውያን ጠቃሚና ቀላል ነገሮችን የመለየት ችሎታ አጥተው ብቻ ሳይሆን ሃይማኖትን ውጫዊ ሥርዓት አድርገው ቆጥረውት ይታያሉ ፤ 15፥10 ። ቁ- 27-28 አስመሳይ የሆነውን እውነት ከሆነው ጋር የሚያነጻጽሩ በመሆናቸው ከፍ ብለው ከተጻፉት ቁጥሮች ጋር ይመሳሰላሉ ። በላያቸው ወድቀው እንዳይረክሱ "መቃብሮችን በኖራ ይለስኑ ነበር" ። "ዓመፀኝነት" ፥ ሕግን በጥንቃቄ እንጠብቀዋለን እያሉ ሕገ ወጥ መሆናቸውን ያመለክታል ።

29-33/ የእግዚአብሔርን መልእክተኞች ስለ መግደል አዝማሚያቸው 21፥33-43ንና ዕብ- 11፥22-38ን ተመልከቱ ። ምን ጊዜም በሕይወት ያለ ነቢይን ከመስማት ይልቅ የሞተውን ነቢይ ማክበር ይቀላል ። መቃ

ብሮችን በመለሰን የነቢያት ገዳዮች ልጆች መሆናቸውን በራሳቸው ላይ ይመሰክራሉ ። የማይገነዘቡት ነገር እንደ አባቶቻቸው ዓመፀኞች መሆናቸውን ነው ። 32/ "ሙሉ" ፥ የወገናቸውን ዓመፀኛነት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርሱት ዋነኛውን ነቢይና ጻድቁን ማለት ክርስቶስን በመግደላቸው ነው ። 33/ ፍርዳቸው የማያ ዳግም ነው ፤ 3፥7 ።

34-36/ ሉቃስ ይህንን ክፍል ምንባብ የእግዚአብሔር ጥበብ በማለት ያስተዋውቀናል ፤ ሉቃስ 11፥49 ። ነገር ግን የሚጠቅሰው ከምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም ። "ነቢያት" ፥ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሳይ ሆኑ አይቀሩም ፤ 1 ቆሮ- 12፥28 ። ዕድላቸው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ካስጠነቀቀው ጋር ተመሳሳይ ነው ፤ ማቴ- 10፥17 ፥ 23 ። በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው "ዘካርያስ" የዩዳሔ ልጅ ነው ተብሎ ይገመታል ፤ 2 ዜና- 24፥20-22 ። በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ውስጥ 2 ዜና- የመጨረሻ መጽሐፍ ስለሆነ አቤል የመጀመሪያ ሰማ ዕት ሲሆን ዘካርያስ ደግሞ የመጨረሻ ሰማዕት ነው ፤ ዘፍ- 4፥8 ። "የበራክዩ ልጅ ዘካሪያስ" ነቢይ ነበረ ፤ ዘካ- 1፥1 ። መገደሉን የሚገልጽ ታሪክ አይገኝም ። ሁለቱ ስሞች ተማትተው ይሆን ? ዩሲፈስ በታሪክ መጽሐፉ እንደጠቀሰው ፥ ኢየሩሳሌም ከመከበቧ በፊት በቤተ መቅደስ ውስጥ የተገደለ ሌላ ዘካሪያስ ነበረ ። "ይህ ትውልድ" መሲሑን በመግደሉ ፥ ልበ ደንዳና ነቱን ከከፍተኛ ደረጃ አደረሰ ፤ ለዘመናት የቆየው በደል በአይሁድ ጦርነት ጊዜ በደረሰው ድንጋጤ በቀሉ ተከ ፍሎአል ለማለት ይቻላል ፤ 11፥16 ።

37-39/ አሳዛኝና አፍቃሪ የሆነ የትንቢት ቃል ነው ። "ኢየሩሳሌም" ፥ የተቃውሞ መዲና ስለ መሆኗ ሉቃስ 13፥33ን ተመልከቱ ። "ስንት ጊዜ" ፥ ኢየሱስ ከዚህ በፊት ኢየሩሳሌምን መጎብኘቱን የሚያሳስብ ሐረግ ሲሆን ዮሐንስ ካቀረበው ዘገባ ጋር የሚስማማ ነው ። በሃይማኖት ሰበብ ውጭአዊ ድርጊቶች በመፈጸም ጥቅም ያገኙ ስለነበረ ከሚያገኙት ጥቅም ላለመለየት ሲሉ እነርሱን ከተበተኑበት ለመሰብሰብ በሥጋ ተገ ልጦ የመጣውን እግዚአብሔርን አለመቀበላቸው ጥቅም ያገኙበት ለነበረው ለቤተ መቅደስ መፍረስ ምክንያት ሆነ ፤ ዮሐ- 11፥47-53 ። 1 ነገ- 9፥7 ፥ ኤር- 12፥7 ፥ 22፥5 ስለ ቤተ መቅደስ መፍረስ መግለጫ ይሰጣሉ ። "በጌታ ስም የሚመጣ" ፥ ይህ አባባል አዲስ ትርጉም እስኪ ኖረው ድረስ ሊያድናት ይችል የነበረው እንደገና አይ ታይም ፤ 21፥9 ።

## የኢየሩሳሌም ውድቀትና የሰው ልጅ መምጣት 24፥1-42

ይህ ክፍለ ምንባብ ከማር- 13፥1-32 ጋር ይመሳሰ ላል ፤ ሉቃስ 21፥5-33 እዩ ። ቁ- 10-13 በማርቆስ ውስጥ ከሚገኘው የተለየ ነው ። ቁ- 26-28ና 37-42 በማርቆስ ውስጥ ባይገኙም ከሉቃስ 17፥23-37 ጋር ይመሳሰላሉ ። ከመግቢያው በኋላ — ቁ- 1-3 ፥ ስለ ሁከት ፤ — ቁ-4-8 ፥ ስለ ስደትና ወንጌልን ስለማሰራጨት — ቁ- 9-14 ፥ እንዲሁም ስለ ታላቁ መከራ የተሰጡ ትምህርቶች አሉ ፤ ቁ- 15-28 ። እነዚህ በምድር ላይ የሚፈጸመውን ፍርድ ያመለክታሉ ። ከዚያም በኋላ የሰው ልጅ የመጨረሻ ውን ፍርድ ለመፍረድ ይመጣል ፤ ቁ- 29-31 ። በቁ- 32-36 የሁለቱ የፍርድ ገጽታዎች ተያይዘው ተገል ጸዋል ። በድንገተኛ መዓት አንጻር የቀረቡ ብዙ ማስጠ ንቀቂያዎችም አሉ ።

1-2/ "ደቀ መዛሙርት" ፥ ደቀ መዛሙርት ከገጠር እንደመጡ ተሳላሚዎች የቤተ መቅደሱን ሕንጻ በአ ክብሮት ይመለከቱት ነበር ። ኢየሱስ በአንጻሩ ሰዎች እንደሚገባ ስላልተጠቀሙበት በመቅደሱ ላይ የሚመ ጣውን ፍርድ አርቆ በግልጽ ተመለከተ ፤ 21፥12 ። ቁ- 3 በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት ምልክቶች እንዳሉ ያሳያል ፤ እነርሱም ፥— የቤተ መቅደስ መፍረስና የሰው ልጅ መምጣት ናቸው ። ማቴዎስ መጨረሻውን የሚያ መለክቱትን ሁለት ምልክቶች ግልጽ የሚያደርጋቸው ይመስላል ። ዳግም ምጽአት ትርጉም ያለውን ፓሩሲያ የሚለውንና የዓለም መጨረሻ የሚለውን ሁለቱንም ሐረጎች የተጠቀመባቸው ማቴዎስ ብቻ ነው ፤ ቁ- 27 ፥ 37 ፥ 39 ፥ 13፥39 ፥ 49 ፥ 28፥20 ። 5/ በአንደኛው ምዕት ዓመት ብዙ መሲሕ ነን ባዮች ነበሩ ፤ 7፥15 ። 6/ "ጦር ነት" ፥ ከ66-70 ዓ/ም ከነበረው የአይሁዶች ጦርነት የተለየ ሌላ ጦርነት ሊያመለክት ይችላል ። ብዙ ድርጊ ቶች ቢታዩም "መጨረሻው" ገና ነው ። 8/ "የምጥ ጣር መጀመሪያ" ፥ የአዲሱ ዘመን መግቢያ ምልክቶች ናቸው ፤ ኢሳ- 26፥16-19 ፥ ሚክ- 4፥9 ።

ቁ- 9 ማር- 13፥9-13ን አሳጥሮ ያቀርባል ፤ 10፥17-21 ። 10-12/ በማቴዎስ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ሲሆን ፥ በክርስ ቲያኑ ኅብረተሰብ ላይ ሊመጡ የሚችሉትን መዓቶች ይዘረዝራል ፤ ለምሳሌ ፥— ክህደት ፥ ውስጣዊ ጥላቻ ፥ ጥርጣሬ ፤ ፍቅር ማጣት ወዘተ ። 13/ ጸንተው ለሚቆሙ ግን ፍጹም ደኅንነት ይሆንላቸዋል ። 14/ በዓለም ሁሉ ወንጌል መሰበኩ የዓለም ፍጻሜ የመቃረቡ ምልክት ነው ። 15/ "የጥፋት ርኩሰት" ፥ ኢየሩሳሌምን ለመከ በብ የሚዘጋጀውን ብዙ ጊዜ ይመለክ የነበረውን የሮማ ውያንን ሰንደቅ ዓላማ የሚያመለክት ይመስላል ፤ ዳን- 9፥27 ፥ ሉቃስ 21፥20 ። "አንባቢው ያስተውል" ፥ ወን ጌላውያኑ ይህ ሊገለጥ የሚገባው ምስጢር ነው ይላሉ ፤ ማቴዎስ ደግሞ መልሱን በየትኛውም መጽሐፍ ውስጥ እንደሚያገኙ ይነግራቸዋል ። 16/ በዚህ አባባል መሠ ረት በ68 ዓ/ም ብዙ ክርስቲያኖች ከዮርዳኖስ ማዶ ወዳ ለችው ወደ ፔላ ሸሹ ። ቁ- 17-20 ሊመጣ ያለውን ስቃ ይና በፍጥነት የመሸሽን አስፈላጊነት ያብራራል ። "ሰንበት" ፥ ይህ ቃል በማርቆስ ውስጥ አይገኝም ። ነገር ግን ከአይሁድ ወገን ያመኑት የሚያስቡበት ጉዳይ ነው ። ቁ- 21/ በዚህ ትውልድ ላይ የሚመጣውን የመ ጨረሻውን ቀን ሥቃይ ያመለክታል ፤ 23፥36 ። ከዚያ ወዲህ የነበሩ ጦርነቶች መጠናቸው የጨመረ ቢሆንም በአይሁድ ጦርነት ውስጥ የነበረው ሥቃይ በቃላት ሊገለጽ ከሚቻለው በላይ ነበረ ።

22/ "ስለተመረጡት" ብሎ የተወሰነው የመከራው ጊዜ ማጠር 2ኛ ባሮክ በተባለው መጽሐፍ 20፥1 ላይ ይገኛል ። 23-25/ በእንደዚህ ዓይነቱ የመከራ ጊዜ አስ መሳይ ነጻ አውጭዎች ይኖራሉ ። 26-27/ "የሰው

ልጅ መምጣት” በምስጢር ሳይሆን በግልጽና ድንገ
ተኛ ይሆናል ። 28/ “አሞራዎች” ፤ በሚበሰብሰው የአይ
ሁዶች ሬሳ ላይ ሽው ብሎ ለመውረድ የተዘጋጀውን
“የሮማውያንን ሰንደቅ ዓላማ ያመለክታል ። 29-31/
“ወዲያው” ፤ ምናልባት መጨረሻው በቀጥታ ከኢየሩ
ሳሌም ውድቀት በኋላ የሚመጣ ይመስል ይሆናል ።
አንዳንድ ምሁራን ፤ ቁ- 29፡31ን ግልጽ በሆነ ምሳሌያዊ
አነጋገር የኢየሩሳሌምን ውድቀት ያመለክታሉ በማለት
ገምተዋል ፤ ነገር ግን ቁ- 29-31 የመጨረሻውን ጊዜ
ሳያመለክቱ አይቀሩም ። ብዙም ጊዜ በማርቆስ ወንጌል
ውስጥ “ወዲያው” የሚለው ቃል አሁኑኑ የሚሆነውን
ነገር አያመለክትም ፤ በዚህ ላይ ትርጉሙ ያው ሊሆን
ይችላል ። በመጨረሻው ሰዓት ዓለምና ሥነ ፍጥረት
ይዛባል ፤ “የሰው ልጅ ይገለጻል” ፤ ዳን- 7፡13 ፤ መሲ
ሑን የሰቀሉት ሰዎች የሥቃይ ጩኸት ያሰማሉ ፤ ዘካ-
12፡10-14 ፤ ከምድር ዙሪያ ሁሉ “የተመረጡት” በመ
ለከት ድምጽ ይሰበሰባሉ ፤ ዘዳ- 30፡4 ፤ ኢሳ- 27፡13 ፤
1 ተሰ- 4፡16 ።

32-33/ በአይሁዶች ጦርነት ውስጥ የነበረው ሥቃይ
የመጨረሻው ቀን መምጣቱ የማይቀር ለመሆኑ ትክ
ክለኛ ማረጋገጫ ነው ። “የበለስ ዛፍ” ፤ እስራኤልን
የሚያመለክት እንደሆነና የጫፉም ማቆጥቆጥ ንስሐ
መግባቷን የሚያመለክት ነው የሚለው ትርጉም ልክ
ላይሆን ይችላል ። 34/ “ይህ ትውልድ” ፤ የአይሁድን
ዘር ወይም የሰውን ዘር ወይም እግዚአብሔር ሕዝቡን
ከግብጽ መቤዠቱን እንዳዩት የመጨረሻውን ቀን
የሚያዩትን ሰዎች ያመለክታል ተብሎ ተተርጉሞአል ።
በሙሴ ዘመን የነበሩት ሕዝብ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ከግብጽ የመቤዠቱ ምስክር እንደነበሩ ሁሉ በኢየሱ
ስም ዘመን የነበሩት ሰዎች እግዚአብሔር በክርስቶስ
በኩል ሰዎችን የመቤዠቱ ምስክሮች እንደሆኑ ሳያሳይ
አይቀርም ፤ 12፡41 ፤ 45 ፤ 23፡34-36 ። “ይህ ሁሉ” ፤
ኢየሱስ ከተናገረ የአንድ ሰው ዕድሜ የሚያህል —
መዝ- 94፡10 — ማለትም አርባ ዓመታት ካለፉ በኋላ
የተፈጸሙትንና ከኢየሩሳሌም ውድቀት ጋር የተያያዙ
ትን ነገሮች የሚጠቅስ ነው ። 35/ ዓለምና መላው ሥነ
ፍጥረት እንኳን ሲናወጥ የኢየሱስ ቃል ነዋሪ መሆኑን
ያመለክታል ፤ 5፡18 ።

36/ “ያን ቀን” ፤ መጨረሻውን ሳያሳይ አይቀርም ።
ኢየሱስ ቀኑን በእውነት የማያውቅ ከሆነ ፤ በቁ- 34
ያለው ቃል ያንን ቀን ያመለክታል ብለን መተርጎም
ትክክል ላይሆን ይችላል ። “ልጅም ቢሆን” ፤ በጥቂት
ብራናዎች ተጽፎ ባይገኝም የማቴዎስ ቃል ሳይሆን
አይቀርም ፤ ደግሞም በማርቆስ ውስጥም አለ ። ማንም
ጸሐፊ ያላንዳች ማስረጃ ኢየሱስ ይህንን የመሰለ ቃል
ተናገረ ብሎ አይጽፍም ነበር ። በእንዲህ ያለ ጊዜ አላ
ውቅም ብሎ በተናገረው አለማወቅና በሥልጣን ሲያስ
ተምር ሊሳሳት ይችላል በሚለው መሐከል ያለው ልዩ
ነት በግልጽ መታየት አለበት ። 37-39/ “የኖህ” ታሪክ
ካልተዘጋጁት የጥፋቱን መምጣት ድንገተኛነት ለማስ
ጠንቀቅ የተነገረ እንጂ ምሳሌያዊ ሆኖ የቀረበ አይደ
ለም ፤ ዘፍጥ- 6፡9 ፤ 1 ጴጥ- 3፡19-21 ። 40-41/ ምጽአቱ
በውጫዊ ሁኔታቸው በሚመሳሰሉና በአንድ ላይ በሚ
ሠሩ ሰዎች መካከል መከፋፈልን ይፈጥራል ። 42/
ይህ ሁሉ የሚያሳየው “መንቃት” አስፈላጊ መሆኑን
ነው ።

## ስለ ፍርድ የተነገሩ አምስት ምሳሌዎች 24 ፡ 43 - 25 ፡ 46

በዚህ ክፍል የሚገኘው ስለ ባለቤትና ስለ ሌባ የሚ
ናገረው የመጀመሪያው ምሳሌ — ቁ- 43-44 ፤ ከሉቃስ
12፡39 ጋር በጣም ይመሳሰላል ። የታማኙ ሎሌ ምሳሌ
ደግሞ — ቁ- 45-51 ፤ በሉቃስ 12፡42-46 ጋር ይመሳ
ሰላል ። በማር- 13፡33-37 ተመሳሳይ አሳቦች አሉ ።
የመከሊቱ ምሳሌ በጥቂቱ ሉቃስ ካቀረበው ምሳሌ ቢመ
ሳሰልም እንኳን የአሥሩ ቆነጃጅት ፤ የበጎቹና የፍየሎቹ
ምሳሌዎች የሚገኙት በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ፤
25፡1-13 ፤ ቁ- 14-30 ፤ ቁ- 31-46 ። እያንዳንዱ ምሳሌ
ከሚመጣው ፍርድ አንጻር ታማኝ ነትን ወይም ንቁነትን
ያሳስባል ።

24፡43-44/ ንስሐ ካልገቡ በስተቀር በምጽአቱ ጊዜ
በሰው ልጅ ለሚፈረድባቸው ሰዎች የተሰጡ ማስጠንቀ
ቂያዎች ናቸው ። 1 ተሰ- 5፡2-6 ፤ ራዕይ 3፡3 ። ኢየሱስ
ቁ- 45-51ን የተናገረው ለአንድ ለተወሰነ ቡድን ይሆን
እንደሆነ አይታወቅም ፤ ስለዚህ ማስጠንቀቂያው ደቀ
መዛሙርትን በአጠቃላይ ሳይመለከት አይቀርም ማለት
ነው ። በታማኝነትና በትጋት ሌሎችን የማገልገል
ውጤት ተጨማሪ ኃላፊነትን መቀበል ነው ። በቤተ
ክርስቲያን ሥልጣን መባለግ የማይሻር ቅጣትን ያስከ
ትላል ።

25፡1-13/ በዚህ ምሳሌ ውስጥ በግልጽ በሰው ደረጃ
የሚተረጎሙ ነጥቦች አሉ ። “ሙሽራው” መሲሑ ሲሆን
ሙሽራውንና ሙሽራይቱን እስከ ቤታቸው ድረስ ለማ
ጀብ የሚወጡት “ቆነጃጅት” አስመሳይ ክርስቲያኖችን
ይወክላሉ ። ሙሽራይቱ የሚለው ቃል ባንዳንድ ብራና
ዎች ውስጥ ተጽፎ አይገኝም ። “መብራት” ፤ እንደ ችቦ
ያለ ነገር ነው ፤ ራዕይ 4፡5 ፤ 8፡10 ። “ሊጠፉብን ነው” ፤
ችቦውን ለማቀጣጠል ዘይት ስላለቀባቸው ሳይሆን ችቦ
ውን በደረቁ ለመለኮስ በመሞከራቸውና ተጨማሪ ዘይት
ባለመያዛቸው ነው ። “ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸ
ውና ተኙ” ፤ ልዩነቱ በጊዜው ዝግጅት ባደረጉትና ሳይ
ዘጋጁ ቀርተው ሁከት ሲመጣ በሌሎች ለመደገፍ በሞከ
ሩት መካከል ነው ። መንፈሳዊ ዝግጅት በሁከት ጊዜ
ሊደረግ የሚችል ነገር ስላይደለ “ልባሞቹ” የሰጡት
መልስ እንደ እውነተኞች እንጂ እንደ ራስ ወዳዶች አያስ
ቆጥራቸውም ። ሰነፎቹ ተዘጋባቸው ፤ ምክንያቱም ሙሽ
ራው እነማን እንደሆኑ አላወቃቸውምና ፤ 7፡21-23 ።

ከቁ- 14-30 ያሉት ጥቅሶች ኢየሱስ በሌለበት ጊዜ
የእግዚአብሔርን ስጦታ በአገልግሎት ውስጥ መጠቀም
አስፈላጊ መሆኑን ያሳያሉ ። የመጀመሪያዎቹ ሁለት
አገልጋዮች ተሰጥአዋቸውን ለጌታቸው ሲሉ ስለተጠቀ
ሙበት “በጎና ታማኝ” ነበሩ ። ሶስተኛው ግን ብጥለው
ያስቀጣኛል ብሎ ስለ ፈራ ለጌታው ትርፍ ማስገኘቱ

ጥቅም ያለው አልመሰለውም ። የበጐውና የታማኙ አገል ጋይ ተቃራኔ ማለትም "ክፉና" ሀኬተኛ አገልጋይ ሆኖ በመገኘቱ ተፈረደበት ፤ ቁ- 26 ። ክፉ ሰው የገብጋባነት ባሕርይ አለው ፣ 20፡15 ። "ታውቃለህ" ፣ ጥያቄ ነው ፤ ቁ- 26 ። ትክክለኛ ነኝ ብሎ በመገመት ከዚህ የተሻለ ድርጊት በፈጸመ ነበር ። ምሳሌው ለተለያዩ ሰዎች የተለ ያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች እንደተሰጡ ያስረዳል ። መንፈ ሳዊ ስጦታዎቻቸውን የሚጠቀሙበት ሌላ ይጨመርላ ቸዋል ፤ በተለይም ሊመጣ ባለው ሕይወት ውስጥ ይህን ተጨማሪ ስጦታ ያገኛል ። በተቀበሉት ስጦታ ያላገለ ገሉት ደግሞ የማይጠቅሙ ሆነው ይጣላሉ ።

31-46/ ይህ የመጨረሻው ፍርድ ሥዕላዊ መግለጫ ነው እንጂ ምሳሌ ብቻ አይደለም ፤ ነገር ግን "በፍየልና" በበግ መከፈላቸው የግለሰቦች ፍርድ ቢመስልም እን ኳን — ሕዝ- 34፡17 ፣ "አሕዛብን ሁሉ" የሚመለከት ዓለም አቀፍ ጉዳይ ነው ፤ ቁ- 32 ። ከሁሉ ለሚያንሱ ለክርስቶስ ' ወንድሞች" የሚደረግ ትንሽ ደግነት ለርሱ የሚደረግ ነው ፤ ቁ- 40 ፣ 10፡40-42 ። "ወንድሞች" የሚ ለው ሰዎችን ሁሉ እንጂ ክርስቲያኖችን ብቻ አያመለክ ትም ። የሕያው እምነት ውጤት እንጂ ተቀባይነት ማግኛ ስላይደሉ ጻድቃን የሠሩአቸውን እነዚህን ታና ናሽ የደግነት ሥራዎችን ዋጋ እንደሚያሳጧቸው መል ካም ተግባራት አድርገው አልቆጠሩአቸውም ። እንዲ ሁም ሌሎቹ አላደረጉአቸውም ። "ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀውን መንግሥት" መምረጥ ወይም "ለሰይጣንና ለመላእክቱ በተዘጋጀው" እሳት መውደቅ የማያዳግም ውሳኔ ነው ። እሳቱ ለሰይጣን እንጂ ለሰው ልጅ የተዘጋጀ አልነበረም ። 46/ "ዘላለም" ፣ ዓይነቱን እንጂ የጊዜውን እርዝማኔ የሚጠቅስ አይደለም ። የሚመ ጣውን ዘመን ያመለክታል ፤ ያለው መከፋፈል ለሰዎች የመጨረሻ መሆኑን ያሳያል ።

## የክርስቶስ ሥቃይና ሞት 26 ፡ 1-27 ፡ 66

ወንጌሎች በሙሉ የሐዋርያት ዋና ትምህርት ስለ ሆነው ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ብዙ ይናገራሉ። ክርስቶስ ሞቶ የተነሣው በፋሲካ ሰሞን መሆኑ ሞቱና ትንሣኤው በብሉይ ኪዳን በዘጸአት መጽሐፍ ውስጥ አስቀድሞ የተነገሩት ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ ሆኖ እንዲ ቆጠር አደረገው ። የእግዚአብሔር መንግሥት የተመሠ ረተችው በእነዚህ ድርጊቶች ላይ ነው ። ሙሉ በሙሉ ባይገልጡአትም ሕይወትን መለወጥ በሚችለው ፍቅርና ኃይል ውስጥ ታየች ። ከዚህ ቀደም በወንጌሎች ውስጥ የሚገኙት እውነት የማይመስሉ ነገር ግን እውነት የሆኑ ነገሮች በዚህ ሥፍራ ጎልተው ይታያሉ ፤ ምክንያቱም ሕይወት ለዓለም ሊገኝ የቻለው ፣ መሲሑ በራሱ ሕዝ ቦች አነሳሽነት በሮማውያን እጅ በመሞቱ ነው ። የሉ ቃስ ዘገባ ትንሽ ለየት ያለ ቢሆንም ማቴዎስ የሚከተሉ ትን አጫጭር የሆኑትን ታሪኮች በመጨመሩ ከማርቆስ ጋር ይመሳሰላል ፡— 1/ ሰይፍና መላእክቱ — ቁ- 52-54 ፣ 2/ የይሁዳ ሞት — ቁ- 3-10 ፣ 3/ ጲላጦስን የሚመለ ከቱ አንዳንድ ነገሮች — ቁ- 19ና 24 ፣ 4/ የቅዱሳን መነሣት — ቁ- 51-53 ፣ 5/ እንዲሁም የመቃብሩ መጠ በቅ — ቁ- 62-66 ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

## የኢየሱስ በሽቶ መቀባትና አልፎ መሰጠት 26፡1-16

የኢየሱስ በሽቶ መቀባትና አልፎ መሰጠት 26፡1-6

ይህ ክፍል ምንባብ ከማር- 14፡1-11 ጋር በጣም ይመ ሳሰላል ፤ ሉቃስ 22፡1-16 ። ሉቃስ በምዕ- 7፡36-50 የተ ለየ ዓይነት መቀባት ስለጠቀሰ በሽቶ የመቀባቱን ታሪክ አልጻፈም ። ሊቀ ካህናትና ሽማግሌዎች ወደ ዶለቱበ ትና ይሁዳም አሳልፎ ሊሰጠው ወዳዘጋጀው ሞት ኢየ ሱስ ራሱ አውቆ መሄዱ የሚራቸውን እስከፊነት በገ ሐድ ይገልጸል ።

1/ ከዚህ ጥቅስ ጋር የሚከተሉትን አወዳድሩ ፡— 7፡28 ፣ 11፡1 ፣ 13፡53 ፣ 19፡1 ። 2/ ኢየሱስ በፋሲካና በሞቱ መካከል ያለውን ግንኙነት እንደሚያውቅ የተና ገረው ማቴዎስ ብቻ ነው ። ፋሲካ የአይሁድ ታላቅ በዓል ነበረ ። እሥራኤል በራስዋ አገር አንድ ሕዝብ እንደምትሆንና ለዓለምም የበረከት ምንጭ እንደምት ሆን የሚገልጽ ፣ እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር የወጡ በትን ጊዜ ለማስታወስ በየዓመቱ የሚከበር በዓል ነበረ ፤ ዘጸ- 12 ፣ 1 ቆሮ- 5፡7 ። "ከሁለት ቀን በኋላ" ፣ ይህ ቀን ረቡዕ መሆኑን ያሳያል ። 3/ "ቀያፋ" ፣ ከ18-36 ዓ/ም ሊቀ ካህን ነበረ ። 5/ "በበዓል አይሁን" ፣ ምናል ባት ይህ ዕቅዳቸው ይሁዳ ከነርሱ ጋር በመቀራረቡ ምክንያት ተሽሮ ይሆናል ። የሰጡት መልስ በዓሉን ማክበራቸውን ሳይሆን የሮምን መንግሥት መፍራታ ቸውን ያሳያል ። በበዓሉ ላይ ከነበሩት ብዙ ገሊላውያን የተነሣ ብጥብጥ ይነሣል የሚል ፍርሃት ነበራቸው ።

6-13/ ሴቲቱ ፍቅሯን ለመግለጽ ወይም በግል ደረጃ እርሱን ንጉሥ መሆኑን ለማስታወቅ ኢየሱስን ዋጋው እጅግ በበዛ ሽቱ የቀባችው ይመስላል ፤ ቁ- 7 ፣ 1 ሳሙ- 10፡1 ፣ 1 ነገ- 1፡38 ፣ 2 ነገ- 9፡4-10 ። ሞቱ ስለተቃረበ ኢየሱስ ለመቃብሩ እንዳዘጋጀችው አድርጎ ተመለከ ተው ፤ መሲሑ የሚጠባበቀው ይህን ነውና ፤ ቁ- 12 ። "ይህ ሁሉ ጥፋት" ፣ የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ያለ አግ ባብ የተጠየቀ አልነበረም ፤ ሆኖም ኢየሱስን መውደድ እያደር ለድሆች ይበልጥ ጥቅም አስገኝቶላቸዋል ። የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ማዕከላዊ ነጥብ ያለው ወንጌል በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታወጅበት ጊዜ ሁሉ የዚህች ሴት ድርጊት የሚታወስ በመሆኑ ሌሎችን የሚቀሰቅስ ሆኖአል ።

14-16/ "ከአሥራ ሁለቱ አንዱ" ፣ ይሁዳ በዚህ ስም መጠራቱ ድርጊቱ እጅግ በጣም አሳዛኝ መሆኑን ያመ ለክታል ። በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወንጌሎች ውስጥ ይሁዳን ላነሣሣው ነገር ምንም ምክንያት አልተሰጠም ፤ ነገር ግን ዮሐ- 12፡4-6 ተመልከቱ ። "ምን ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ ?" የሚለውን የይሁዳን ጥያቄና በግልጽ የተጠቀሰውን ዋጋ የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው ፤ ዘካ- 11፡12፤ ከትንቢተ ዘካርያስ የተወሰዱት ጥቅሶች በሚከተሉት ሥፍራዎች ይገኛሉ ፡— 21፡5 ፣ 24፡30 ፣ 26፡31 ፣ 27፡9 ።

## የመጨረሻው እራት 26 ፡ 17-29

ይህ ክፍል ከማር- 14፡12-27 ጋር ይቀራረባል ፤ ከሉ ቃስ 22፡7-30 ጋር አነጻጽሩት ። ኢየሱስ በፋሲካ እራት

እንጸር ሲመጣ ያለውን ሞት ያብራራል ፤ አሳልፎ የሚ ሰጠው ይሁዳ መሆኑን ያስታውቃል ።

17-19/ "የቂጣው በዓል የመጀመሪያው ቀንና" የፋ ሲካ በዓል የሚከበሩት በአንድ ቀን ሲሆን ከዚያ ቀን ቀጥሎ ባሉት ሰባት ቀናት በተከታታይ የሚበላው ቂጣ ነው ። የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወንጌሎች በዚያ ሌሊት ኢየሱስ የፋሲካን በዓል በማክበር የፋሲካን ምግብ እንደ በላ ያለጥርጥር ያሳያሉ ። የነርሱን አቀራረብ የዮሐንስ ወንጌል ካቀረበው ጋር ለማስማማት ትንሽ ያስቸግራል ፤ ነገር ግን ሁለት ዓይነት የቀን መቁጠሪያ ዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። የትኛውም ወንጌላዊ ስለ ኢየሱስ የመጨረሻ ቀን የሰጠው አስተያየት ተሳስቶአል ብሎ መናገር አይቻልም ፤ ወይም መንፈሳዊ ትምህርት ለመ ስጠት ሲል ለውጦታል ማለትም ትክክል አይመስልም ። "ጊዜዬ ቀርቦአል" ፣ ኢየሱስ ስለ ሞቱ መቃረብ የነበ ረውን አሳብ ያመለክታል ። 20/ "አሥራ ሁለቱ" ፣ በዚያ ሥፍራ ከኢየሱስ ጋር ብቻቸውን ያሉ ይመስላል ። 22/ "እጅግ አዝነው" ነበር ፤ በአንድ በኩል ኢየሱስ አልፎ ስለሚሰጥ በሌላ በኩል ደግሞ ከመካከላቸው አንዱ አሳልፎ ስለሚሰጠው ሊሆን ይችላል ። "እኔ እሆንን ?" አይደለሁም የሚል ስሜት ያለው ጥያቄ ሲሆን ምናልባትም እሆናለሁ የሚል ስሜት ያዘለ ሊሆን ይችላል ። 24/ በዚህ ጥቅስ ውስጥ የእግዚአብሔር አስቀድሞ የመወሰን ችሎታና የሰው ሥነ ምግባራዊ ኃላፊነት ተጣምረዋል ፤ በ18፡7 ውስጥ ተመሳሳይ አሳብ ይገኛል ። ይሁዳ ኢየሱስን "መምህር" ማለትም ረቢ ብሎ ሲጠራው ሌሎቹ ጌታ ይሉታል ። "አንተ አልህ" ፤ አዎን ይሁዳ አንተ እንዳልከው ነው ማለት ነው ፤ የይ ሁዳ ከክፍል መውጣት አልተጠቀሰም ።

26/ ኢየሱስ አንድ የቤት ባለቤት በማንኛውም የም ግብ ጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ አደረገ ። እንጀራውን ስለሰጠው እግዚአብሔርን "ባረከ" ። በማቴዎስና በማ ርቆስ ውስጥ ያሉት የትእዛዝ ቃሎች አጫጭር ናቸው ። "ብሉ" የሚለው ትእዛዝ ደግሞ በማርቆስ ውስጥ አይ ገኝም ። "ይህ ሥጋዬ ነው" ፣ በመቁረስና በመብላት አማካይነት ሞቱን ፣ ሥጋ በመልበሱና በሥቃዩ ደግሞ የነርሱን ሕይወት እንደሚያድን ያሳያል ፤ ዮሐ- 6፡53-58 ። እንጀራው ሥጋው ነው ለማለት ባይቻልም በእ ምነት ስንቀበለው በሕይወታችን ውስጥ ለመሥራት ኃይል ያለው ምሳሌ ነው ። 28/ "ይህ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው" ፤ ዘጸ- 24፡8ን ያስተጋባል ። በሲና ተራራ የተሰጠው የቀድሞው ቃል ኪዳን ከግብፅ ከመውጣታ ቸው ድርጊት ጋር የተያያዘ ነው ። "አዲስ" የሚለው ቃል በሲና ተራራ በተሰጠው ቃል ኪዳን ውስጥ ከተጠ ቀሰው ደም ጋር ለማነጻጸር የተጨመረ ቃል ሊሆን ይችላል ፤ በአንዳንድ ብራናዎች ውስጥ አይገኝም ። "ብዙዎች" ፣ ሁሉን የሚያቅፍ እንጂ ማንንም የሚያ ገልል አይደለም ፤ 20፡28 ፣ ኢሳ- 53፡11 ። "ለኃጢአት ይቅርታ" ፣ ይህ የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ፤ በ3፡2 ላይ የሚገኘውን የዮሐንስን ጥምቀት ሲጠቅስ እነዚህን ቃላት ስላልጻፈ የእውነተኛ ይቅርታ መሠረት የክርስቶስ የመቤዠት ሞት መሆኑን ለማመልከት የሚ ፈልግ ይመስላል ። 29/ እራቱ በራዕይ 19፡9 ላይ የተመ ለከተውን ግብዣና እስራኤል ከግብፅ መውጣታቸውን ያመለክታል ፤ 14፡13-21 ።

## ጌቴሴማኔ 26 ፡ 30-56

ክፍለ ምንባቡ ከማር- 14፡26-52 ጋር በጣም ይመ ሳሰላል ፤ ሉቃስ 22፡31-53 ። የደቀ መዛሙርቱ ክህደት ከተገለጸ በኋላ — ቁ- 30-35 ፣ ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ በመቀበል - ቁ- 36-46 ፣ ለመታሰር ፈቃደኛ መሆኑ ተገ ልጾአል ፤ ቁ- 47-56 ።

30/ "መዝሙሩ" ፣ ምናልባት የዘመሩት ከመዝ- 114-117 ያሉትን መዝሙራት ሳይሆን አይቀርም ። 31/ "እመታለሁ" ፣ ጥቅሱ ከዘካ- 13፡7 የተወሰደ ሲሆን ኢየሱስ ትእዛዝ ለነበረው ቃል ትንቢታዊ መልክ ሰጥ ቶታል ። ይህ ጥቅስ ሊፈጸም ያለው ነገር ሁሉ በእግዚአ ብሔር ቁጥጥር ሥር እንደሆነ ለማሳየት ታስቦ የተነገረ ይሆናል ። 32/ "ገሊላ" ፣ 28፡7ና 10ን ተመልከቱ ። 33-35/ "ጴጥሮስ" ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ከመሰከረ በኋላ እንደታበየ ሁሉ ፣ አሁንም እንደገና ያላግባብ ሲፎክር ይገኛል ፤ 16፡13-19 ። ለመመስከር የመጀመሪያ የሆነው ለመካድም የመጀመሪያው ሆነ ። 36/ "ጌቴሴማኔ" ፣ የዘይት መጭመቂያ ማለት ሲሆን ከቄድሮን ሸለቆ በስተምሥራቅ የሚገኝ አነስተኛ የወ ይራ ደን ነበረ ። 37/ "ጴጥሮስና ሁለቱ የዘብዴዎስ ልጆች" ፣ ክብሩን የመሰከሩት ሰዎች አሁንም ሥቃዩን ይመሰክራሉ ፤ 17፡1 ። 37-38/ እንዲያዝን ያደረገው ባንድ በኩል የገዛ ወገኖቹ ተቃውሞ በሌላ በኩል ደግሞ በፊቱ የሚጠብቀውን የሥቃይ ሞት ተደቅኖ መታየቱ ነው ። "ከእኔ ጋር" ፣ ይህን ቃል በዚህና በቁ- 40 ውስጥ የጠቀሰው ማቴዎስ ብቻ ነው ። ኢየሱስ ለምርመራ ሲቀ ርብ አብሮት የሚሆን የሰው አጋዥ ይፈልግ ነበር ። 39/ "ጽዋው" ፣ ሥቃይንና ሞትን ያሳያል ፤ 20፡22 ፤ ኢሳ- 51፡22 ። 41-42/ "አባቴ" ፣ "ፈቃድህ ትሁን" ፣ "ወደፈተና እንዳትገቡ" ፣ በ6፡9-13 ያለውን የጌታን ጸሎት ያንጸባርቃሉ ። ደቀ መዛሙርቱ ሊገጥማቸው ያለውን ችግር ሁሉ እርሱ ራሱ በሥጋው ተቀበለ ። "ሥጋ ደካማ ነው" ፣ ዕብ- 5፡7-10 ይህንን አሳብ ያብ ራራል ። 45/ "እንግዲያስ ተኙ ዕረፉም" ፣ በጥያቄ መልክ የቀረበ ሳይሆን አይቀርም ።

47/ "ከአሥራ ሁለቱ አንዱ" ፣ ይሁዳ በዚህ አነጋገር መጠቀሱ ፣ ኢየሱስ ያለበትን ማወቁንና የበደሉን ታላ ቅነት ያሳያል ፤ ቁ- 14 ። 48/ ለበዓሉ የመጡ ብዙ ሰዎች ስለነበሩ ፣ ግብግብ እንዳይፈጠርና በጨለማው ምክን ያት ተሳስተው ሌላ ሰው እንዳይይዙ ፣ ምልክት አስፈ ላጊ ነበረ ። 49/ አንድ ተማሪ ለመምህሩ ሰላምታ የሚ ሰጠው በዚህ ዓይነት ነበረ ። 50/ "ወዳጄ ሆይ" ፣ ፍቅር የሞላበት ግሣጼ ሊሆን ይችላል ፤ ወይም በግሪኩ የመጣ ህበትን ጉዳይ ፈጽም ተብሎ ሊተረጉም ይችላል ። ከአ ባቱ ጋር በጸሎት ስለቆየ ትግሉ ተጠናቅቆአል ፤ አሁን ምንም ቢመጣ ሰላምና ደስታ አለው ። 51/ "ሰይፉን የመዘዘው" ፣ ጴጥሮስን ያመለክታል ፤ ዮሐ- 18፡10 ። ሉቃስና ዮሐንስ ኢየሱስ ሰውየውን እንደፈወሰ ጠቅሰ ዋል ። 52-54/ እነዚህን አባባሎች የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው ። "ሰይፍ የሚያነሡ" ፣ አባባሉ አመጽ አመጽን

ይወልዳል የሚል ትርጉም አለው ። የአይሁድ ሽማግሌዎች በአመጽ ስለተጠቀሙ ወዲያውኑ ብድራታቸውን ተቀበሉ ፤ 27፡25 ። 53/ መላእክት ትናንሾችን የሚጠብቁ ከሆነ — 18፡10 ፥ የእግዚአብሔርን ልጅ ለመጠበቅ በምን ያህል ኃይልና ቁጥር ይመጡ ይሆን ! 54/ "መጻሕፍት" ፥ ስለ ሥቃዩና ስለ ሞቱ በተደጋጋሚ የተጻፈባቸው እንደ መዝ- 21ና ኢሳ- 53 ያሉ ክፍሎች ናቸው ። 55/ "ወንበዴ" ፥ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ ማለት ሲሆን ምናልባት ኢየሱስን በዚህ ጠርጥረውት ይሆናል ፤ ይሁዳም አሳልፎ የሰጠው እንደዚህ ዓይነት ሰው በማስመሰል ይሆናል ። 56/ "ነቢያት" ፥ የዳዊትን መዝሙር የሚያጠቃልል ሰፋ ያለ ትርጉም ያለው ቃል ሊሆን ይችላል ፤ 13፡35 ። ኢየሱስ አዋኪ የሆነውን ፈተና ለብቻው እንዲጋፈጥ ተደረገ ።

## በቀያፋ ፊት የተደረገው ምርመራ 26፡57-75

በአንዳንድ ቦታዎች የማቴዎስ ታሪክ አጭር ቢሆንም እንኳን ፥ ይህ ክፍል ከማር- 14፡53-72 ጋር በጣም ይቀራረባል ፤ ሉቃስ 22፡54-71ን አንብቡ ። አሁን የሃይማኖት መሪዎች ተቀባይነት ካላገኘውና ካላወቁት መሲህ ጋር ተጋጥመዋል ። ኢየሱስ መሲህ መሆኑን በሚመሰክርበት ጊዜ የሞት ፍርድ ተፈረደበት ፤ ዋናው ደቀ መዝሙርም ከዳው ።

57/ የአይሁድ ሸንጎ ያደረገው ስብሰባ ብዙ አሻሚ ጥያቄዎች ፈጥሮአል ፤ የሞት ፍርድ ውሳኔ የሚያስተላልፈው ስብሰባ ከ12 ሰዓት በኋላ መደረግ አይገባውም ነበር ፤ እንዲሁም በበዓል ዋዜማ ወይም በሰንበት ዋዜማ መሰብሰብ አይፈቀድለትም ነበር ። ስለዚህ ይህ ስብሰባ ፥ ኢየሱስን እንደ ሀሰተኛ መሲሕ በመቁጠር ለጲላጦስ አሳልፎ ለመስጠት ተብሎ በችኮላ የተደረገ ሕገወጥ ስብሰባ የነበረ ይመስላል ። 59-61/ አንድን ክስ ለመቀጠል ሁለት ምስክሮች ያስፈልጉ ነበር ፤ ዘዳ- 19፡15 ። ኢየሱስ ቤተ መቅደስ ስለሆነው ስለ ሰውነቱ መፍረስና እንደገና መነሣት ተናግሮ ስለነበረ በዚህ ጉዳይ የሰጡት ምስክርነት ሙሉ በሙሉ ሀሰት አልነበረም ፤ ዮሐ- 2፡19 ። ኢየሱስ ስለተናገረው የተሳሳተ ትርጉም ሰጥተውት ነበር ፤ የሐዋ- 6፡13 ። 63/ ኢሳ- 53፡7 በሚገባ ይህን ቁጥር ያብራራል ። ከዚያ በኋላ "የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ" መሆኑን እንዲናገር አስማሉት ። 64-65/ "አንተ አልህ" ፤ በማርቆስ ውስጥ እንደተጠቀሰው ቀጥተኛ አነጋገር እኔ ነኝ ማለት ነው ። ማረጋገጫው ከመዝ- 109፡1ና ከዳን- 7፡14 የተውጣጣ ነው ። "ከእንግዲህ ወዲህ" ፥ በቅርቡ የሚሆንን ነገር ያመለክታል ። በዳን- 7 ውስጥ የሰው ልጅ የተባለው ወደ እግዚአብሔር እንዳረገ ሁሉ ይህ ዐረፍተ ነገር በሙሉ የኢየሱስን መክበርና ድል ማድረግ ሳይጠቁም አይቀርም ። የሆነ ሆኖ ሁለት ክፍሎች ያሉትን ድርጊት ማለትም መክበሩንና በግርማ መመለሱን ሳይገልጽ አይቀርም ፤ 24፡30 ። "ስድብ" ፤ የሚቀጥለውን ሐረግ ስለተናገረ ነው ። "በኃይል ቀኝ መቀመጥ" ፥ በተዘዋዋሪ መንገድ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጥ ማለት ነው ። ቁ- 66፡68 ሸንጎው ምንም ዓይነት ሕጋዊ ፍርድ ሳይሰጥ ፥ በኢየሱስ ላይ ያላቸውን አስተያየት ከሰነዘሩ በኋላ እሥረኛው የተዘበተበት መሆኑን ያሳያል ።

69-75/ ይህ ታሪክ ከጴጥሮስ የተገኘ መሆኑ አያጠራጥርም ። ትምክህቱ ከንቱ መሆኑ ተረጋገጠ ፤ የኢየሱስም ትንቢት እውነት ሆነ ፤ ቁ- 33-35 ። ጴጥሮስ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆኑ የታወቀው ፥ በሕይወቱ ጥራት ሳይሆን — የሐዋ- 4፡13 ፥ በአነጋገሩ ዘይቤ ነበረ ። ኢየሱስ ዓለት ትሆናለህ ብሎ የጠራው ጴጥሮስ አንድ ጊዜ በገረዶች ፊት አንድ ጊዜ ደግሞ በሕዝብ ፊት ጌታውን አላውቀውም ብሎ ካደ ። ወጥቶ ማልቀሱ አያስደንቅም ።

## የይሁዳ መሞትና ኢየሱስ ለምርመራ በጲላጦስ ፊት መቅረቡ 27፡1-31

ይህ ክፍል ከማር- 15፡1-20 ጋር በጣም ይመሳሰላል ፤ ሉቃስ 23፡2-5ና 17-25 አንብቡ ። ማቴዎስ ስለ ይሁዳ ሞት — ቁ- 3-10 ፥ እንዲሁም ስለ ጲላጦስ ተጨማሪ ማብራሪያ ሰጥቶአል ፤ ቁ- 19ና 24 ። ሊቀ ካህናትና ሽማግሌዎች ኢየሱስን ለሞት አሳልፈው ለመስጠት የመጨረሻ ርምጃ ሲወስዱ ፥ ለነርሱ አሳልፎ የሰጣቸው ደግሞ በጸጸት ራሱን ይገድላል ። መሲህ ነኝ የሚለው ሰው መልስ ባለመስጠቱ ጲላጦስ ግራ ተጋባ ። ለእሥረኛ በሚደረገው ዓመታዊ ምሕረት ሊፈታው ይሞክራል ፤ ነገር ግን በመጨረሻ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ ብሎአል ብለው የከሰሱት ሰዎች ግፊት ስላበዙበት በርሱ ላይ መፍረድ ግድ ሆነበት ።

2/ "ጲላጦስ" ፥ ከ26-36 ዓ/ም የይሁዳና የሰማሪያ ገዢ ነበረ ። ዋና መሥሪያ ቤቱ የሚገኘው በቂሣሪያ ነበረ ፤ ነገር ግን ሁከት ይነሣል ተብሎ በሚታሰብበት በማንኛውም ጊዜ በኢየሩሳሌም መገኘት ነበረበት ። 3-10/ የሐዋ- 1፡16-20 የይሁዳን ሞት በልዩ ቃላት ያቀርበዋል ። በዚህ ቦታ ተፀፀተ ተብሎ የተተረጐመው ቃል በሙሉ ልብ ወደ እግዚአብሔር መመለሱን አያሳይም ፤ አዘነ እንደ ማለት ነው ። 4/ ሊቀ ካህናቱ ሞራል ቀርቶ የሰብአዊ ርህራሄ ሽታ እንኳ አልነበራቸውም ። 9-10/ ይህ ከኤርምያስና ከዘካርያስ የተጠቀሰ ነው ። ዋናው የተጠቀሰው ክፍል ፥ ሠላሳ ብር የሆነው ደመወዝ ወደ መዝገብ ተጨምሮአል የሚለው ከዘካ- 11፡12 ነው ። ዕብራይስጡ ለሸክላ ሠሪው የተሰጠ ይላል ። "በኤርምያስ" የሚለው ቃል አንዳንድ ችግር ፈጥሮአል ፤ ምናልባት ሙሉ በሙሉ ከዘካርያስ የተወሰደ ስለሚመስል ጥቅሱ የተጠቀሰበት በግልጽ እንዲታወቅ የመጽሐፉ ስም በተጨማሪ ተሰጥቶአል ። ይህንንም አሳብ ያቀረቡት ኤር- 32፡6-15 የእርሻው መግዛት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከምርኮ ወደ ገዛ ምድራቸው መመለሳቸውን ስለሚያሳይ ነው ። ሁለቱም ክፍሎች ስለ አዲስ ኪዳን ከሚጠቅሱ ክፍለ ምንባቦች አካባቢ ይገኛሉ ፤ ኤር- 31፡31-34 ፥ ዘካ- 11፡10 ። ነቢዩ ሥፍራውን በንጹሐን ደም የሞሉትን የይሁዳ ሕዝብ ፍርድ ለማመልከት ሄኖም በተባለው ሸለቆ ውስጥ ገንቦ መስበሩን የሚገልጸውን ኤር- 19፡1-13ን ሊጠቅስ ይችላል ።

11-14/ "የአይሁድ ንጉሥ" ፥ ብጥብጥ ለማስነሻ

የጮኹት ጩኸት ነው ። በዚህ አጋጣሚ ኢየሱስ ራሱን በማስመልከት የዚህን ቃል ትርጉም መናገሩ ምንም ዋጋ የለውም ። 16/ በርባን ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ መሆኑን ሉቃስና ማርቆስ ቢጠቅሱም ማቴዎስ አልጠቀሰም ። 19/ 1፡20 ፣ 2፡12 ፣ 13 ፣ 19 ስለ ሕልም ይናገራሉ ። 20/ ሕዝቡን ለማሳመን ካህናት ምን ዓይነት ክርክር እንዳቀረቡ አናውቅም ፤ ነገር ግን ምናልባት ኢየሱስን ቤተ መቅደስንና ሕግን የሚቃወም አድርገው ሳያቀርቡት አልቀሩም ፤ 26፡61 ፣ የሐዋ- 6፡13 ።

24-25/ እነዚህን ቁጥሮች የመዘገበ ማቴዎስ ብቻ ነው ። በአይሁድ ባሕል መሠረት እጅን መታጠብ በደልን ማስወገድ ነበረ ፤ ዘዳ- 21፡6 ፣ መዝ- 72፡13 ። ነገር ግን ጲላጦስ እጁን የታጠበው ተስፋ በመቁረጥ ወይም በማሾፍ ሊሆን ይችላል ። በ70 ዓ/ም በሆነው በአይሁድ ጦርነት የተፈጸመውን የኢየሱስን ሞት ውጤት ለመቀበል በመስማማት ሕዝቡ አስከፊ ጩኸት ጮኹ ። ይህ በይበልጥ የአይሁድ ስሜት ያለው የማቴዎስ ወንጌል "ሕዝቡ በሙሉ" እንደጮኹ ያመለክታል ። በኋላ በተነሡ ትውልዶች በተሳሳተ መንገድ በመተርጐሙ አባባሉ በብዙ አይሁዶች ላይ ስደት የማስነሻ ምክንያት ሆኖአል ። 26/ ምናልባት ጲላጦስ በመጨረሻው የተስማማው ለንጉሥ ነገሥቱ ታማኝነቱን ለመግለጥ በመፈለጉ ይሆናል ፤ ዮሐ- 19፡12 ። 27-31/ ይህ የሥጋና የአእምሮ ጭካኔ ነው ። "ጭፍራ" ፣ ብዙ ተመልካቾች እንደነበሩ ያመለክታል ። "ቀይ ልብስ" ፣ ምናልባት የወታደር ካባ ይሆናል ። "የሾህ አክሊል" ፣ ሮማውያን አምላካቸውን በሚወክሉት ሰዎች ላይ የደፉት አክሊል ሳይሆን አይቀርም ።

## ስቅለት 27፡32-56

ይህ ክፍል የቅዱሳንን ትንሣኤ ከመጨመሩ በቀር- ቁ- 51-53 ፣ ከማር- 15፡21-41 ጋር በጣም ይመሳሰላል ፤ ሉቃስ 23፡26-49ን አንብቡ ። በኢየሱስ ላይ የደረሰው ዘበት ፣ ሥቃይና ተቃውሞ እጅግ ከፍተኛ የሆነ መከራ ቢሆንም ፣ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ መሰቀሉና ከአባቱ መለየቱ የከፋ ሥቃይ ነበረ ። ሆኖም በዚህ አሳዛኝ ትዕይንት ውስጥ እንኳ የሕይወትና የእምነት የተስፋና የፍቅር ምልክቶች ነበሩ ።

32/ "ስምዖን" ፣ በዚህ ላይ ስሙ መጠቀሱ ፣ በኋላ ክርስቲያን እንደሆነ ሳያመለክት አልቀረም ። ማርቆስ ወንጌሉን በጻፈለት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እስክንድሮስና ሩፎስ የታወቁ ሰዎች ስለነበሩ ስምዖን የሚለውን ስም ብቻ ከመጻፍ ይልቅ የእስክንድሮስና የሩፎስን አባት ስምዖን ብሎ ጽፎአል ። መሸከም የሚቻለው "የመስቀሉ" ክፍል አግድም ያለው ነው ። 34/ "በሐሞት የተደባለቀ ወይን ጠጅ" ፣ ሥቃዩ እንዳይሰማቸው ለተሰቀሉ ሰዎች የሚሰጥ ነበረ ። ማቴዎስ የመዝ- 68፡21ን መፈጸም ለማሳየት "ሐሞት" ብሎ ይጠራዋል። ኢየሱስ የሥቃዩን ጽዋ እየተሰማው እስከ ዝቃጩ ድረስ ለመጠጣት ፈቃደኛ ሆነ ፤ 26፡29 ። 35/ የመዝ- 21፡18 ፍጻሜ ነበረ ። ወታደሮች ለሥራቸው ዋጋ አድርገው የእሥረኞችን ልብስ የመውሰድ ልምድ ነበራቸው ። 37-38/ የኢየሱስ ወንጀል ተጠቅሶአል ፤ የወንበዴዎቹ ግን አልተጠቀሰም ። ምናልባት እነዚህ ወንበዴዎች የነጻ አውጭ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዮች በመሆናቸው ፣ ሮማውያን ኢየሱስን በዚህ ዓይን የተመለከቱት ይመስላል ። 40/ ዮሐ- 2፡19ና ማቴ- 26፡61 ይህን ጥቅስ ያብራራሉ ። "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ" ፣ 4፡3 ፣ 6 ። 42/ ፍጹም ደኅንነት ለሌሎች ለመስጠት የሚችለው ራሱን አሳልፎ በመስጠት ብቻ ነበረ ፤ 20፡28 ። 43/ "በእግዚአብሔር ታምኖአል" ፣ ከመዝ- 21፡8 የተጠቀሰ ነው ።

45/ "በምድር ሁሉ" ፣ በተስፋይቱ ምድር ማለት ነው ፤ ከግብፅ በወጡ ጊዜ በግብፅ ላይ ከሆነው ጨለማ ጋር አነጻጽሩት ፤ ዘጸ- 10፡21 ። በፋሲካ ጊዜ ሙሉ ጨረቃ ስለነበረ የፀሐይ ግርዶሽ ነበረ ለማለት አይቻልም ። 46/ "ኤሎሄ ኤሎሄ" ፣ ከመዝ- 21፡1 የተጠቀሰ ነው ። ኢየሱስ አሁን እንደ ልማዱ አባቴ ብሎ አይጣራም ። ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት በመሸከሙ መዝሙረኛው ዳዊት የተናገረው ታላቅ ሥቃይ ሙሉ በሙሉ ይሰማዋል ። መዝሙረኛው ድል ስለማድረግ የተናገረውን ማቴዎስ አልጠቀሰም ። 48/ "ሆምጣጤ" ፣ ምንም የወታደር መጠጥ ቢሆንም በዚህ ላይ የተጠቀሰው የመዝ- 68፡21 ፍጻሜ በመሆኑ ነው ። 50/ ኢየሱስ በሞትም እንኳን ድል አድራጊ ነው ።

51-53/ ማርቆስ ወደ እግዚአብሔር መግባትን የሚያመለክተውን የመጋረጃውን መቀደድ ሲጽፍ ዕብ- 10፡19 ፣ ስለ ቅዱሳኑ መነሣት የተናገረው ማቴዎስ ብቻ ነው ። የግሪኩ ቃላት የሚያመለክቱት በዚህ ጊዜ ቅዱሳኑ ከሞት ቢነሡም ከመቃብር የወጡት ግን ክርስቶስ ራሱ ከተነሣ በኋላ ነው ። ክርስቶስ ከሙታን በኩር ነው ፤ ቆላ- 1፡18 ፣ 1 ቆሮ- 15፡20 ። የቅዱሳኑ ትንሣኤ እንደ አልዓዛር ትንሣኤ ካልሆነ በስተቀር ከኢየሱስ ቀደም ብለው ተነሡ ማለት ትንሽ ያስቸግራል ። "ለብዙዎች ታዩ" ፣ እነዚህ ቁጥሮች ቃል በቃል መተርጐም እንዳለባቸውና በመጨረሻ የሚሆነውን አጠቃላይ ትንሣኤ የሚጠቁሙ መሆናቸውን ያሳያል ። 54/ "የመቶ አለቃው" ፣ ከአሕዛብ ወገን በመሆኑ ስለ ክርስቶስ ያለው ዕውቀት የተወሰነ ቢሆንም ካየው ነገር የተነሣ የክርስቶስ ወገኖች የነበሩት መሪዎች ለማላገጥ በተናገሩዋቸው ቃላት ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክራል ፤ ቁ- 40 ፣ 43 ። 56/ "የዘብዴዎስ የልጆቹ እናት" ፣ ምናልባት ማርቆስ ሰሎሜ ብሎ የሚጠራት ሴት ሳትሆን አትቀርም ፤ 20፡20ን ተመልከቱ ።

## ቀብሩና የመቃብሩ መጠበቅ 27፡57-66

ማርቆስ በ15፡42-47 ውስጥ ስለ ቀብሩ ከጻፈው ይልቅ ማቴዎስ በዚህ ክፍለ ምንባብ ውስጥ ያቀረበው አጠር ያለ ነው ፤ ሉቃስ 23፡50-56 አንብቡ ። ማቴዎስ ግን ጠባቂዎች መመደባቸውን ይጨምራል ። አይሁድ ትንሣኤውን ስለካዱ ይህ ክፍል ኢየሱስ በርግጥ እንደሞተ በጉልህ ያሳያል ።

57/ "ዮሴፍ" ፣ በዚህ ሥፍራና በዮሐ- 19፡38 ውስጥ በግልጽ ደቀ መዝሙር መሆኑ ተገልጾአል ። ጲላጦስን ሄዶ ለመጠየቅ ድፍረት የሰጠው ስቅለቱ ይመስላል ። ምድሪቱን ያረክሳል የሚል እምነት ስለ ነበረ ሬሳ በመስቀል ማደር አይገባውም ነበር ፤ ዘዳ- 21፡22-23 ።

60/ "አዲስ መቃብር" ፣ ብዙ ጊዜ ሀብታሞች በሕይወት እያሉ መቃብራቸውን ያሠሩ ነበር ። ኢየሱስ በማርያም ማሕጸን ለማደር የመጀመሪያው እንደነበረ ሁሉ ፣ በዚህ መቃብር ለማረፍም የመጀመሪያው ሆነ ፤ 1፡18-25 ። "ታላቅ ድንጋይ" ፣ መቃብሩ እንዳይዘረፍ ለመከላከል የተደረገ ነው ። 61 / ይህ ድፍረታቸውንና ፍቅራቸውን ያሳያል ፤ እንዲሁም በኋላ ተሳስተው ወደ ሌላ መቃብር እንደማይሄዱ በግልጽ ያመለክታል ። 62-66/ ግቴዎስ ሰንበት መሆኑን ያልጠቀሰው ሆነ ብሎ ይመስላል ። ከሶስት ቀን በኋላ እነሣለሁ ፣ ከልብ ለመቀበል ቢያቅታቸውም እንኳ ኢየሱስ የተናገረውን አስታወሱ ። "ጠባቆች አሉአችሁ" ፣ ትርጉሙ ይህ ከሆነ የቤተ መቅደስን ፖሊሶች ሊያመለክት ይችላል ። ግሡ በትእዛዝ የሚነበብ ከሆነ ሮማዊ ወታደሮች ሰጥቶአቸዋል ማለት ነው ።

## የክርስቶስ ትንሣኤ 28፡1-20

የወንጌሉ ሁለተኛ አጋማሽ ስለ ክርስቶስ መስቀልና በሕዝቡ ቀስቃሽነት በተፈጸመው አሳፋሪ በሆነው የመሲህ ሞት ምክንያት የኢየሱስ ተከታዮች ተስፋ ወደ መቁረጥ ስለ መድረሳቸው ይናገራል ። ነገር ግን ኢየሱስ ስለ ሞቱ ሲናገር ስለ ትንሣኤውም ተናግሮ ነበር ፤ 16፡21 ፣ 17፡9 ፣ 23 ፣ 20፡19 ። ማቴዎስ የመጨረሻና አጭር በሆነው በዚህ ምዕራፍ ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ መቃብሩ ባዶ በመሆኑ ለደቀ መዛሙርቱ በመገለጹና ለቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ የሆነ ተልዕኮ በመስጠቱ ምክንያት ሐዘን እንዴት ወደ ደስታ እንደተለወጠ ያሳያል ።

## ትንሣኤ 28፡1-10

ምንም ታሪኩ ከማር - 16፡1-18 ጋር በጣም ቢመሳሰልም ራሱን የቻለ ነው ፤ ሉቃስ 24፡1-11ን አንብቡ ። ማቴዎስ ድርጊቱ ተአምር መሆኑን በጉልህ ያሳያል ።

1/ ማቴዎስ መቃብሩ በሴቶቹና በዘበኞቹ ይጠበቅ እንደነበረ መግለጹን ይቀጥላል ። 2-4/ ድንጋዩ እንደ ተንከባለለ የገለጸው ማቴዎስ ብቻ ነው ። የመሬት መናወጡና መልአኩ ሴቶቹ መቃብሩ ባዶ መሆኑን እንዲያዩ እንዳደረጉአቸው እንጂ ኢየሱስ ከመቃብር እንዲወጣ ድንጋዩን እንዳንከባለሉለት አልተገለጸም ። 5/ "መልአኩ" ፣ በማርቆስ ውስጥ ነጭ ልብስ የለበሰ ሰው የተባለው ነው ። "አትፍሩ" ፣ እምላካዊ ግርማና ኃይል ቢገለጽም ታማኞቹ ሴቶች ያላመኑት ዘበኞች የፈሩትን ያህል አልፈሩም ። 6/ "እንደተናገሩ" ፣ 16፡21 ፣ 17፡9 ፣ 23 ፣ 20፡19 ተመልከቱ ። 7/ ዜናው በፍጥነት መሠራጨት አለበት ። "ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል" ፣ ይህ ማለት ፈጽሞ ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣም ማለት አይደለም ፤ 26፡32 ። 8/ ይህን ጥቅስ በማር- 16፡8 ከተጠቀሰው ከድንጋጤ የተነሣ ከሆነው ፀጥታ ጋር አወዳድሩ ። 9/ "ደስ ይበላችሁ አላቸው" ፣ ሴቶቹን እንጂ ደቀ መዛሙርቱን አይደለም ። መልሳቸው የርሱን እምላካዊ ኃይል መገንዘባቸውን ያሳያል ። 10/ "ለወንድሞቼ" ፣ 12፡49 ፣ 25፡40 ። ቃሉ አሥራ አንዱን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ይጨምራል ። "በዚያም ያዩኛል" ፤ ምስክሮቹ አድርጎ ሊሾማቸው የታየበት ዋነኛው ጊዜ መሆኑ ነው ።

## የዘበኞቹ በጉቦ መደለል 28፡11-15

ይህ የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ። የልደቱ ታሪክ የአይሁድ አሉባልታ ትክክል አለመሆኑን እንዳስረዳ ሁሉ ፣ አሁንም ይህ ክፍል አይሁድ ስለ ትንሣኤው ያላቸውን ክህደት ያጋልጣል ።

11/ "የሆነውን ሁሉ" ፣ የተመለከቱትን ነገር ሁሉ ፤ ቁ- 2-4 ። 13/ ስለ ባዶው መቃብር ሊነገር የሚቻለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው ። 14/ ምንም ዘበኞቹ የሮማውያን ወታደሮች ቢሆኑ ፣ ጲላጦስ ጠባቂዎቹን የመቆጣጠሩን ኃላፊነት የሰጠው ለአይሁድ ሸንጎ ስለነበረ በግዳጃቸው ላይ ሆነው ስላንቀላፉ ጲላጦስ ላይቀጣቸው ይችላል ። 15/ ይህ ነጥብ ወንጌሉ የተጻፈበትን ጊዜ ለማወቅ ብዙ አይረዳንም ።

## የመጨረሻው ትእዛዝ 28፡16-20

ይህ ክፍል የሚገኘው በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ።

16/ የትኛው ተራራ እንደሆነ ግልጽ አይደለም ። ምናልባት ስብከቱን የሰበከበት — 5፡1 ፣ ወይም የተለወጠበት ተራራ ሊሆን ይችላል ፤ 17፡1 ። 17-18/ በደቀ መዛሙርቱም መካከል እንኳን የማመንና ያለማመን ሁኔታ የነበረ ይመስላል ፤ ምናልባት ኢየሱስ "እስከ መጣ" ድረስ እርግጠኛ አልነበሩም ይሆናል ። አሁን ኢየሱስ ፣ ሰይጣንን በማምለክ ወይም በተሳሳተ መንገድ በመንጠቅ ሳይሆን — 4፡8 ፣ ከአባቱ አጠቃላይ የሆነ ሥልጣን በስጦታ መልክ ተቀብሎአል ። ምንም እንኳን ውርሱን ሙሉ በሙሉ ባይረከብም ፣ መሲሑ ሥልጣኑን ተቀዳጅቶአል ፤ 24፡30 ። 19/ "አሕዛብን ሁሉ - - - ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው" ፤ የኢየሱስ አጠቃላይ ሥልጣን የቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ተልእኮ መንሥኤ ነው ። የክርስቲያን ጥምቀት የሚፈጸመው ኢየሱስ በሰጠው በዚህ ትእዛዝ መሠረት ነው ። ይህ ትእዛዝ በኢየሱስ ባይሰጥ ኖሮ ከበዓለ ሃምሳ ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወዲያውኑ ማጥመቅ አይጀምሩም ነበር ፤ የሐዋ-2፡38-41 ። በስሙ መጠመቃቸው የርሱ መሆናቸውን ስለሚያመለክት በርሱ ስም ይፈጸም ነበር ፤ የሐዋ-2፡38 ፣ 8፡16 ። ብዙም ሳይቆይ በሥላሴ ስም ይፈጸም ጀመር ። "በአብ ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ" ፣ ይህ የሥርዓት ጥምቀት መፈጸሚያ ቃል ሳይሆን ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የማን መሆናቸውን ለመግለጽ የተሰጠ ሳይሆን አይቀርም ። 20/ ኢየሱስ እንደ ሙሴ በመሆን ትእዛዛቱን እንዲታዘዙት አጥብቆ ያሳስባል ። ኢየሱስ ራሱ የማስተማር አገልግሎት እንደነበረው ሁሉ አገልጋዮቹም መታዘዝን የማስተማር አገልግሎት አላቸው ። በወንጌል መጀመሪያ ላይ ራሱን ዝቅ በማድረግ ከኛ ጋር በመሆን አማኑኤል ተብሎ የተጠራው አምላክ ፤— 1፡23 ፣ አሁንም ተከብሮ "እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ" ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ይኖራል ፤ 13፡39 ፣ 40 ፣ 49 ፣ 24፡3 ። በሥጋ ተገልጾ ሥራውን ፈጽሞአል ፤ እኛም ድርሻችንን እንድንሠራ ከኛ ጋር ነው ።

# የወንጌሉ ጥቅም

የማቴዎስ ወንጌል ከሌሎቹ ወንጌሎች ሁሉ ይልቅ በክርስቲያኖች አስተሳሰብ ላይ ይበልጥ ለውጥን ያስከተለ ይመስላል ። ከአዲስ ኪዳን መጽሐፎች በመጀመሪያ የተጻፈው ይህ ወንጌል ነው የሚል አሳብ ከጥንት ጀምሮ አለ ። ከዚህ በላይ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉት ወንጌሎች የመጀመሪያውን ሥፍራ በመያዙ በክርስቲያኖች አስተሳሰብ ቅድሚያ ተሰጥቶታል ። ከሁለተኛው ምዕት ዓመት ወዲህም ከወንጌሎች ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀስ የነበረው ይኸው የማቴዎስ ወንጌል እንደሆነ ተደርሶበታል ። አብዛኛውን ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን አምልኮ የሚሠራበት ይኸው ወንጌል ነው ። ይዘቱ በርዕስ በርዕስ በመቀነባበሩና ኢየሱስ ያስተማራቸውን የትህምርቶቹን ስብስቦች ለምሳሌ የተራራውን ስብከት በሚገባ የያዘ በመሆኑ በዘመናት ሁሉ በየትም ሥፍራ ባሉት ክርስቲያኖች ዘንድ ጠቃሚነቱ ተመስክሯል ። ባለፉት 100 ዓመታት የማርቆስ ወንጌል በቅድሚያ ተጽፎአል የሚለው የምሁራን አስተሳሰብ የማቴዎስን ወንጌል ችላ እንዲባል አድርጎታል ። ነገር ግን የማቴዎስ ወንጌል ልዩ አስተዋፅኦ ስላለው እንደገና ከማርቆስ ጋር እኩል ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት ይገመታል ።

## የወንጌሉ መነሻ ምንጭ

በማቴዎስ በማርቆስና በሉቃስ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል መካከል ያለው ግንኙነት "ባለ አራት ድርብ ወንጌል" በተሰኘው ድርሰት ተብራርቶአል ፤ (ገጽ ተመልከቱ) ። በዚህ ማብራሪያ ውስጥ የማቴዎስ መሠረታዊ ምንጭ ማርቆስ መሆኑ ተረጋግጦአል ። ይህ ወንጌል በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኙት ታሪኮች አብዛኞቹን በአጭሩ ሲገልጽ ከማርቆስ ወንጌል ያልጠቀሳቸው 55 ጥቅሶች ብቻ ናቸው ። አብዛኛውን ጊዜ ለውጦች የተደረጉት ታሪኩን ለማሳመር ፣ ቃላቱንና የጽሕፈት ዘዴውን ለማሻሻል ፣ ማርቆስ አጠር አድርጎ የጻፋቸውን ግልጽ ለማድረግና ለማብራራት ነው ።

በሉቃስ ውስጥ ካሉት ትምህርቶች ብዙዎቹ በማቴዎስ ውስጥ ይገኛሉ ። አንዳንድ ምሁራን በሉቃስና በማቴዎስ ብቻ የሚገኙት ጥቅሶች "ልዩ የጋራ ምንጭ" ከተሰኘ ስብስብ የተቀዱ ናቸው ብለው ይገምታሉ ። ይህ "ልዩ የጋራ ምንጭ" ተብሎ የተጠራው ስብስብ ምን ዓይነት ጽሑፍ እንደነበረ ለመዘርዘር ያስቸግራል ። በማርቆስ ወንጌል ብዙ ታሪኮች አሉ ፤ ነገር ግን ማቴዎስ ኢየሱስ ያስተማራቸውን ትምህርቶች ለማቅረብ በመፈለጉ የማርቆስን ወንጌል ቅደም ተከተል አልጠበቀም ።

በወንጌሉ ከሚገኙት 1050 ጥቅሶች ውስጥ 500 ያህሉ ከማርቆስ ወንጌል የተወሰዱ ሲሆኑ 250ው ደግሞ "ልዩ የጋራ ምንጭ" ከተሰኘው ስብስብ የተቀዱ ናቸው ።

በሌሎቹ ወንጌሎች ውስጥ ያልተገኙት 300 ጥቅሶች የማቴዎስ አስተዋጽኦ ተብለው ይጠራሉ ። እነዚህ 300 ጥቅሶች የወንጌሉንም ጸባይ ለየት ያደርጉታል ። እነዚህ የጥቅስ ቅንብሮች ማቴዎስ ከሌሎች ሰዎች ባገኘው ታሪክ ላይ የተመሠረቱ ሳይሆኑ አይቀሩም ። የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች የሚገኙባቸው ክፍለ ምንባቦች ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ ይሆናሉ ። እነሆ ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሱት ምንባቦች "የምስክርነት ጥቅሶች" ተብሎ ከተጠራው ስብስብ የተገኙ ናቸው የሚለውን አሳብ ለመደገፍ በቂ ማስረጃ አልተገኘም ።

## የመጽሐፉ አቀራረብና ይዘት

ማቴዎስ በታላቅ ጥንቃቄ የወንጌሉን ይዘት በቅደም ተከተል ማቅረቡ ግልጽ ቢሆንም ፣ ምሁራን ስለ ማቴዎስ ንድፈ አሳብ የተለያዩ አስተያየቶችን በመሰንዘራቸው ሊስማሙ አልቻሉም ። በወንጌሉ ውስጥ አምስት የንግግር ስብስቦች ይገኛሉ ። እነርሱም ፦ 1ኛ የተራራው ስብከት 5፡1-7 ፡27፡2ኛ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የተሰጠ የአገልግሎት ምክር 10፡1-42 ፣ 3ኛ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌዎች 13፡1-52 ፣ 4ኛ በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ ያለ ኅብረት 18፡1-35 ፣ 5ኛ ዳግም ምጽአት 24፡1-25፡46 ናቸው ። ኢየሱስ እያንዳንዱን ንግግር ካደረገ በኋላ ያስተማረውን ትምህርት በሥራ ላይ ያዋለ መሆኑን ማቴዎስ በንግግሮች መካከል ባሉት ታሪኮች ይገልጻል ። ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ወንጌሉን በምትሰብክበት ጊዜ በታሪኮቹ ተከታዮችዋን ስታስተምር ደግሞ በንግግሮቹ ተጠቅማለች የሚል ግምት አለ ።

ትምህርቱ በርእስ በርእስ የተሰበሰበ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም ። የመጀመሪያው የንግግር ቅንብር ሥነ ምግባራዊ ፣ ሁለተኛው አገልግሎታዊ ፣ ሶስተኛው ስብከታዊ ፣ አራተኛው ካህናዊ ሲሆን አምስተኛው ደግሞ የመጨረሻውን ዘመን የሚጠቁም ነው ። በሃይማኖት መሪዎች ላይ ዋይታዎች ያሉበት ምዕራፍ 23 ከመጨረሻው ንግግር ጋር ስምምነት ሳይኖረው አልቀረም ።

ስለ ወንጌሉ ጠቅላላ ዕቅድ በርከት ያሉ አሳቦች ቀርበዋል ፤ ነገር ግን እንደ ግጥም ሆኖ የተሰበሰበ ነው የሚለው መላምት ብዙ ድጋፍ አግኝቷል ። በመጀመሪያውና በመጨረሻው ንግግሮች እንዲሁም በሁለተኛውና በአራተኛው የርዝመትና ሰፋ ተደርጎ የመብራራት ተመሳሳይነት እንዳለ ይታያል ። ስለ መንግሥተ ሰማያት በምሳሌዎች የሚናገረው ሶስተኛውና ማዕከላዊው ክፍል ነው ። በታሪካዊ መደቦች ውስጥ ማለት በሶስተኛውና (11-12) በአራተኛው (14-17) ወይም በሁለተኛውና (8-9) በአምስተኛው (19-22) መካከል ልዩ የሆነ ተመሳሳይነት አይታይም ። በእውነት የወንጌሉ መነሻና መድረሻ ግሩም የሆነ ተመሳሳይነት አላቸው ፤ ለምሳሌ ማቴዎስ የኢየሱስን ጥምቀት (ምዕ- 3) እና ሞት (ምዕ- 27) ለማመሳሰል መፈለጉን ባናውቅም ፤

ከኢየሱስ ልደት በኋላ በመጀመሪያ ከብሉይ ኪዳን የተ ጠቀሰው ፣ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው የሚለው ጥቅስ ሲሆን (1፡23) ፣ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ የተጠቀሰው ደግሞ ፣ ሁልጊዜ ከናንተ ጋር ነኝ የሚለው ነው ፤ 28፡20 ። ለተመሳሳይ አሳብ ማር- 10፡38ንና ሉቃስ 12፡50ን አነጻጽሩ ።

የወንጌል ሐቆችን በቅደም ተከተል ለማቅረብ እን ዳሰበ ብዙ መረጃዎች ስላሉ ወንጌላዊው ከፍ ብሎ የተ ጠቀሰው ዓይነት ዓላማ ኖሮት እንደጻፈ ይታመናል ።

## የወንጌሉ መለያ ባሕርያት

የማቴዎስ ወንጌል ከሌሎቹ ወንጌሎች የሚለይባቸው ምን ዓይነት ልዩነቶች አሉት ? ባጭሩ ልዩነቶቹ ሁለት ናቸው ፦— አጻጻፉ ለየት ያለ ነው ፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ሲያብራራ አቀራረቡ ልዩ መልክ አለው ። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ፣ ማቴዎስ ያቀረበውን ትምህርት ቅደም ተከተል በማስያዝና በርዕስ በርዕስ በመከፋ ፈሉ ከማርቆስ የበለጠ አስተካክሎ ጽፎአል ። ለምሳሌ ፦ የማርቆስን አጭር ታሪኮች ሰፋ አድርጎ አብራርቶአቸ ዋል ፤ አልፎ አልፎ የነበሩትን የሰዋስውን ስሕተቶች አስተካክሏል ፤ ስለዚህም በአንባብያን አሳብ አለመግ ባባትን የሚፈጥሩትን ነጥቦች አስወግዷል ። ሌሎች ወንጌሎች የእግዚአብሔር መንግሥት ብለው የጻፉትን ማቴዎስ መንግሥተ ሰማያት ብሎ ጽፎታል ።

ይሁን እንጂ ማቴዎስ ስለ እግዚአብሔር ሥራ ያጠ ናቀራቸው ገለጻዎች ይበልጥ አሳብን የሚስቡ ናቸው ። የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መፈጸማቸውን የሚያስረዱ ጥቅሶች በቅደም ተከተል የመጥቀስ ዝንባሌው ይበልጥ ልብን የሚነካ ነው ፤ 1፡22 ፣ 2፡15 ፣ 17 ፣ 23 ፣ 4፡14-16 ፣ 8፡17 ፣ 12፡17-21 ፣ 13፡35 ፣ 21፡4 ፣ 27፡9 ። ትንቢቶቹ የሚገኙበት ክፍል ምንባብ በጥንቃቄ ከተጠና ፣ አባባሉ በምክንያት የተጠቀሰ እንጂ ባጋጣሚ የተጻፈ አለመ ሆኑን መረዳት ይቻላል ። ይህም የብሉይ ኪዳንን መፈ ጸም ያሳያል እንጂ በክርስቶስ መሻሩን ወይም መቅረ ቱን አያመለክትም ፤ 5፡17-20 ። ከዚህም በቀር በዚያ ዘመን አይሁዶች ለብሉይ ኪዳን ትርጉም ሰጥተው ካገ ኙት የበለጠ ግብረገባዊ ትምህርት ያቀርባል ፤ 5፡21-24 ፣ 27-30 ፣ 33-37 ። ኢየሱስ በግልጽ የዳዊት ልጅ በመ ሆኑ መሲህ ተብሎ ተጠርቶአል ፤ በዚህ ወንጌል ውስጥ የዳዊት ልጅ የሚለው ሐረግ ስምንት ጊዜ ይገኛል ። መሲህነቱ ይበልጥ የተገለጸው ከትንሣኤው በኋላ ቢሆ ንም — 28፡18 ፣ በሥቃዩ ጊዜ እንኳ ንጉሣዊ ሥልጣን እንደነበረው ወንጌሉ ያሳያል ፤ 26፡53 ። እንዲሁም በተ መሳሳይ ሁኔታ ማቴዎስ ኢየሱስ የሰዎችን ድካም የወ ሰደ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆነ — 8፡17 ፣ ከሕ ዝቡም ጋር ሰላማዊ ግንኙነት እንደነበረው ገልጾአል ፤ 12፡17-21 ።

በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ በመፈለጉ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የእ ስራኤልን ተቀዳሚነት ያሳያል ። የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ ከአብርሃም ጋር አያይዞታል ፤ 1፡17 ። የኢየሱስና የደቀ መዛሙርቱ አገልግሎት በተለይ ለጠፉት ለእስ ራኤል ቤት በጎች እንደ ነበረ የገለጸው ማቴዎስ ብቻ ነበረ ፤ 15፡24 ፣ 10፡5 ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሰዎች በተለይ የሃይማኖት መሪዎች የሕግን ጥቅም ባለማስተ ዋላቸው ፣ መሲህንና ነቢያትን ስለ ተቃወሙ ተገቢ የሆነውን ፍርድ ተቀብለዋል ፤ 23፡1-39 ። ነፍሰ ገዳዮቹ መደምሰስ አለባቸው ፤ ከተማቸው መቃጠል አለበት ፤ 22፡7 ። የእግዚአብሔር አገልጋይ ፍርድን ለአሕዛብ ማወጅ ነበረበት ፤ አሕዛብም በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ ፤ 12፡17-21 ። ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ የሰጠው የመ ጨረሻ ትእዛዝ ፣ ወደ አሕዛብ ሁሉ ሄደው ደቀ መዛ ሙርት እንዲያደርጉአቸው ነው ፤ 28፡19-20 ። የቀድ ሞው የእግዚአብሔር ሕዝብ አዲስ ለተመረጠው ሕዝብ ዕድሉን አስተላልፎአል ፤ 21፡43 ። በዚህ ምክንያት ማቴዎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ብዙ አስተምሯል ። ቤተ ክርስቲያን ተብሎ የተተረጐመው ኤክሌሲያ የሚለው ቃል የተገኘው በዚህ ወንጌል ብቻ ነው ። ወንጌላዊው በክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ውስጥ መገኘት ስለሚገባው ሥልጣንና ሥነ ሥርዓት ብዙ ያሰበ መሆኑ ግልጽ ነው ፤ 16፡17-19 ፣ 18፡15-18 ።

በዚህ ወንጌል ውስጥ ተአምራትን የሚያመለክቱ ዘገባዎች በብዛት ይገኛሉ ። በዓሣ አፍ ውስጥ ግብር መገኘቱ የተጻፈው በዚህ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው ፤ 17፡24-27 ። ነገር ግን የቅዱሳን መነሣትና እንዲሁም የመልአኩ የመቃብሩን ድንጋይ ማንከባለል በመጨ ረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ይገኛሉ ፤ 27፡51-53 ፣ 28፡2-4 ። የማቴዎስ ወንጌል ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽ አት ብዙ ትምህርት አለው ። ዳግም ምጽአት ተብሎ የተተረጐመው ፓሩሲያ የሚለው የግሪኩ ቃል የሚ ገኘው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው ፤ 24፡3 ፣ 27 ፣ 37 ፣ 39 ። ማቴዎስ ከማርቆስ ወንጌል በወሰዳ ቸው ታሪኮች ላይ የመጨረሻውን ዘመን የሚያመለክቱ አስተያየቶች በተደጋጋሚ ጨምሮባቸዋል ፤ ለምሳሌ 24፡30 ። የመጨረሻውን ዘመን የሚያብራሩ በርከት ያሉ ምሳሌዎች የሚገኙት በማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው ፤ 13፡24-30 ፣ 36-43 ፣ 47-50 ፣ 25፡1-46 ። ማቴዎስ ባሁኑ ዘመን በኢየሱስ አማካይነት የተሠራውን የእግ ዚአብሔርን መንግሥት ሥራ ሌሎች ወንጌሎች የተገ ለጡትን ያህል ገልጧል ፤ ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር መንግሥት አፈጻጸም ልዩ ትኩረት የሰጠ መሆኑ ግልጽ ነው ።

## ወንጌሉ የተጻፈበት ዘመንና የተገኘበት ቦታ

ከወንጌሉ የተቀዳው ግልጽ የሆነው የማቴዎስን ወን ጌል ጥንታዊነት የሚያረጋግጥ ጥቅስ በአትናቴዎስ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል ። ይህ ጽሑፍ ከ115 ዓ/ም ቀደም ብሎ እንደተጻፈ ብዙዎች ይስማማሉ ። የማቴዎስ ወን ጌል ጥንታዊነት የሚወሰነው ፣ ወንጌሉ ከማርቆስ ወን ጌል ጋር ያለው ግንኙነት ተጣርቶ ከተጠና በኋላ ነው ። ብዙዎች ማቴዎስ ፣ በማርቆስ ላይ የተመሠረተ ነው ብለው ይገምታሉ ። ማርቆስ የተጻፈው ምናልባት ጴጥ ሮስ ከሞተ ማለት ከ65 ዓ/ም በኋላ ከሆነ ማቴዎስም የተጻፈው ከዚያ በኋላ መሆን አለበት ።

ሁለተኛው ነጥብ ፣ ወንጌሉ በ70 ዓ/ም ከነበረው ከኢየሩሳሌም መፈራረስ ጋር ያለው ዝምድና ነው ። የኢየሩሳሌም መፍረስ የቀድሞውን ኪዳን ፍጻሜ በግ ልጽ ስለሚያሳይ ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው ከኢየሩ ሳሌም መፍረስ በኋላ ቢሆን ኖሮ የቤተ መቅደሱን መፍ ረስ ሳይጠቅስ አያልፍም ነበር ። ስለዚህ ወንጌሉ ከ70 ዓ/ም ወዲህ ተጽፎአል ብለው የሚከራከሩ አሉ ። ነገር ግን የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የኢየሩሳሌምን ውድቀት መጥቀስ ጠቃሚ ሆኖ ሳለ እንዳልጠቀሰው ሁሉ ማቴዎስ አውቆ አልፎት ይሆናል ። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ምሁራን ፣ ግልጽ ባልሆነ መንገድ የኢየ ሩሳሌምን መውደቅ የሚጠቁሙ ጥቅሶች አሉ በማለት ወንጌሉ ከ70 ዓ/ም ወዲያ የተጻፈ ነው ይላሉ ። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ይህን ድርጊት ለመተንበይ አልቻለም የሚለው ተቃውሞ ተጣርቶ ቢመረመር አሳቡ መሠረተ ቢስ ሊሆን ይችላል ። በ22፡7 ላይ ያለው የከተማይቱን መቃጠል የሚያመለክት ማገናዘቢያ ፣ ድርጊቱ ከተከ ናወነ በኋላ የተጨመረ ሊሆን ይችላል ።

ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት - 16፡19 ፣ 18፡17 ፣ ስለ ስደት ሁኔታዎች - 10፡22 ፣ 24፡9 ፣ ቢዘገይ ስለ ዳግም ምጽአት እርግጠኝነት የተጻፉት ክፍሎች - 24፡37-51 ፣ 25፡1-12 ፣ እንዲሁም በወንጌሉ ውስጥ የሚገኘው ጠቅላላ ስለ እግዚአብሔር የሚያስረዳው ትምህርት ፣ ወንጌሉ በመጀመሪያው ምዕት ዓመት ፍጻሜ አካባቢ የተጻፈ መሆኑን ያሳያል ተብሎ ይነገራል ። ጥቂት ምሁ ራን ፣ ምኩራቦቻቸው የሚለው ቃል — 4፡23 ፣ 9፡35 ፣ 10፡17 ፣ 12፡9 ፣ 13፡54 ፣ ክርስቲያኖች ከአይሁድ ምኩ ራብ ከተገለሉ ከ85 ዓ/ም በኋላ መጻፉን ይጠቁማል ቢሉም የሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች በቂ አይደሉም ። የወንጌሉ ይዘት ከታወቁት ካንዳንድ ታሪካዊ ድርጊ ቶች ጋር ካልተዛመደ በቀር የተጻፈበትን ዘመን መወ ሰን በጣም አዳጋች ነው ። የማቴዎስ ወንጌል በ65 ዓ/ምና በ110 ዓ/ም መካከል ተጽፎአል ማለት ይቻላል ። ከዚህ በማያያዝ ወንጌሉ የአይሁድን ባህል ማንጸባረ ቁና ከኩምራን ጽሑፎች ጋር መዛመዱ በ65 ዓ/ም ገደማ የተጻፈ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል ።

ወንጌሉ የተጻፈበት ቦታ በርግጥ አይታወቅም ። ለአይ ሁድ አንባብያን የተጻፈ መሆኑ የማያጠራጥር ነው ። ደግሞ በውስጡ የአይሁዶችን ባሕል የሚያብራራ ገለጻ አለመኖሩ የአይሁድ እምነት በተጠናከረበት ቦታ መጻ ፉን ያሳያል ፤ 15፡2 ፣ 23፡27 ። ወንጌሉ ከአራም ቋንቋ አልተተረጐመም ። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኙት የአራም ቃላት አንዳንዶቹ በማቴዎስ ስለማይገኙ ዋናው ቋንቋ ግሪክ በነበረበት ቦታ መጻፉን ሊያመለክት ይች ላል ። ስለዚህ አብዛኞቹ መምህራን በእሥራኤል አገር ለነበረ ማኅበረ ሰብ እንዳልተጻፈ ይቀበላሉ ። አንዳን ዶችም ወንጌሉ የተጻፈው በፊንቄ ውስጥ ነው ይላሉ ። ነገር ግን አብዛኞቹ በሶርያ ወይም ምናልባትም በአንጾ ኪያ ተጽፎአል የሚል አሳብ ያቀርባሉ ። በዚህ ከተማ በግሪክ ቋንቋ የሚናገሩ ከአይሁድ ወገን ያመኑ ብዙ ክርስቲያኖች ነበሩ ፤ ከተማው ሐዋርያት ለአሕዛብ ለሰጡት አገልግሎት ማዕከል ነበረ ፤ እንዲሁም ብዙ አይሁዶች ይገኙበት የነበረ ከመሆኑም በላይ ከአይሁድና ከአሕዛብ ያመኑ ክርስቲያኖች የሚገናኙበት ቦታ ነበረ ። አትናቴዎስ ከወንጌሉ ጥቅስ መጥቀሱና በወንጌሉ ውስጥ የሚታየው የጴጥሮስ ታሪክ አቀራረብ ከፍ ብሎ የቀረበውን አሳብ ሊደግፉ ይችላሉ ። ይህ ምናልባት ደህና መላምት ነው ። ነገር ግን ይህን መላምት ብንደ ግፍም በወንጌሉ ውስጥ ያሉት መረጃዎች ሁሉ ከአን ጾኪያ ተገኝተዋል ማለታችን አይደለም ። ወንጌሉ የተ ጻፈበት ቦታ በእውነት ባይታወቅም ማቴዎስ አብዛ ኞቹን መረጃዎች ያገኘው ከገሊላና ከኢየሩሳሌም ሳይ ሆን አይቀርም ።

## ጸሐፊው

ሐዋርያው ማቴዎስ ከሌሎች ወንጌሎች በፊት ይህን ወንጌል በዕብራይስጥ ወይም በአራም ቋንቋ ጽፎታል የሚለው አሳብ የቀድሞዎቹ ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ የተስማሙበት ነበረ ። አሁንም ይህ አመለካከት ብዙ ተቀባይነት እያገኘም ። በብዙዎች ዘንድ የወንጌሉ ጸሐፊ ማቴዎስ መሆኑ የሚያጠያይቅ ነው ። ማቴዎስ የዓይን ምስክርና ሐዋርያ ከሆነ ፣ ሐዋርያ ያልሆነው ማርቆስ በጻፈው ወንጌል በብዙ መጠቀሙ በቀላሉ የማይ ታለፍ ጥያቄ ፈጥሮአል ። ማርቆስ በሐዋርያው ጴጥ ሮስ አጋዥነት ሳይጽፍ አልቀረም ፤ ስለዚህ የማርቆስ ወንጌል ልክ እንደ ሐዋርያት ጽሑፍ በመሆኑ ተቀባይ ነት አለው ። ማቴዎስም በማርቆስ ወንጌል ተጠቅሞ የራሱን የሥራ ልምድ ጨምሮበት የራሱን ወንጌል ጽፎአል ። አንዳንድ ሰዎች በዚህ ወንጌል ውስጥ ብቻ የሚገኙትን ተአምራትና የመጨረሻውን ዘመን ጠቀስ ትምህርቶች በሐዋር ት የተጻፉ አይመስሉም በማለት የወንጌሉ ጸሐፊ ማቴዎስ አይደለም የሚለውን ተቃ ውሞ ያቀርባሉ ። ይህ ተቃውሞ በመጠኑ ተሰሚነት ቢያገኝም ሌሎቹ ሶስት ወንጌሎች በማርቆስ ወንጌል መለካት የለባቸውም ። ወንጌሎች እያንዳንዳቸው ኢየ ሱስ ስላደረገው ሥራና ስላስተማረው ትምህርት የተ ለያዩ ዘገባዎች ስለሚያቀርቡ ለጠቅላላው ታሪክ ልዩ ልዩ አስተዋጽኦ አላቸው ።

ከቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ የነበረው ፓፒየስ ስለ ማቴዎስ ወንጌል ሲጽፍ እንዲህ ብሏል ፡— ማቴዎስ አባባሎችን በዕብራይስጥ ቋንቋ ካቀነባበራቸው በኋላ አንባቢዎች እንደየችሎታቸው መጠን ተነተኑአቸው የሚል አስተያየት ሰጥቷል ። ማቴዎስ ሲጽፍ በማርቆ ስና በግሪክ ብሉይ ኪዳን ከመጠቀሙ የተነሣ ወንጌሉን በአራም ቋንቋ ጽፎአል የሚለው ግምት ተቀባይነት አይኖረውም ። ፓፒየስ የጠቆመው ያሁኑን የማቴዎስ ወንጌል ነው ብለው የሚገምቱት ምሁራን ከማርቆስ እያጠቃቀሰ ያንን የአራም ቋንቋ ቅጂ ሙሉ በሙሉ አሻ ሽሎታል ማለት አለባቸው ፤ ይህ ግን እውነት አይመ ስልም ። ስለዚህ ፓፒያስ ስለ ቋንቋ የገመተው ፣ ስሕ ተት መስሎ ቢታይም ስለ ማቴዎስ ጸሐፊነት ያቀረበው አሳብ ልክ ነው ፤ ወይም ፓፒየስ አባባሎች ሲል ሌላ ጽሑፍ ጠቅሞ ይሆናል ። ይህ ከሆነ አባባሎች ሲል ምን ማለቱ ነው ? ድጋፍ ያገኙ ሁለት አሳቦች አሉ ።

የመጀመሪያው ፡— ለምስክርነት ከብሉይ ኪዳን የተውጣጡ ጥቅስ ያሉበት መጽሐፍ ነው ። እንዲህ ያለ መጽሐፍ ተጠርዞ ለመገኘቱ ማስረጃ አይገኝም ። ሁለተኛው ፡— ልዩ ልዩ አባባሎች ያሉት ቅንብር ይሆናል የሚለው ነው ። ምናልባት ልዩ የጋራ ምንጭ የተባለው ጽሑፍ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ልዩ የጋራ ምንጭ ተብሎ የተጠራው ጽሑፍ የተጻፈው ወይም በቃል የተያዘ ስለ መሆኑ የታወቀ ነገር የለም ። የተጻፈም ከሆነ አንድ ወይም የበለጠ ብራና እንደሆነ አልታወቀም ። ይሁን እንጂ አባባሎች የሚለው ቃል የንግግሮችን ክምችት ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን በቀደሙት ክርስቲያናዊ ጽሑፎች ውስጥ ወንጌልን የሚጠቁም ስለሆነ ፓፒየስ አባባሎች ብሎ ሲጽፍ ወንጌልን ማመልከቱ ሳይሆን አይቀርም ።

ሐዋርያው ማቴዎስ ባንዳንድ መንገድ ስሙን ከያዘው ወንጌል ጋር ግንኙነት አለው ። ስሙ በመጽሐፍ ውስጥ ባይገኝም ፣ በ2ኛው ምዕት ዓመት በተጨመረው ርዕስ መገኘቱ በብዙ ቦታዎች ጸሐፊ መሆኑ እንደታመነበት ያስረዳል ። የወንጌሉ ጸሐፊ ማቴዎስ ካልሆነ ወንጌሉ በርሱ ስም የሚጠራበት ምንም ምክንያት የለም ፤ ኢየሱስ ሲጠራው ሌዊ በማለት ፋንታ ማቴዎስ ማለቱ ብቻ የወንጌሉ ጸሐፊ ሊያደርገው አይችልም ፤ 9፡9 ፣ ማር· 2፡14 ። ወንጌሉን ሙሉ በሙሉ የጻፈው እርሱ ባይሆንም ወንጌሉ የተገኘው እርሱ መሪ ከነበረበት ት/ቤት ነው የሚል ግምት አለ ። ወይም በወንጌሉ ውስጥ የተገኙትን ነገሮች በመሰብሰብና በማሠራጨት ታላቅ ድርሻ ኖሮት ይሆናል ። ወንጌሉ በርዕስ በርዕስ መጻፉ የቀረጥ ሰብሳቢን የአመዘጋገብ ዘዴ ያንጸባርቃል የሚል አሳብ ቀርቦአል ። የሆነ ሆኖ ጸሐፊው ፤ የመንግሥተ ሰማያት ደቀ መዝሙር የሆነ ጸሐፊ ሁሉ ከመዝገቡ አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል የሚለውን የኢየሱስን አባባል ሲመዘግብ በአእምሮው የራሱ ተግባር ትዝ ሳይለው አልቀረም ፤ 13፡52 ።

## ዓ ላ ማ

የክርስቶስን ተግባራትና ቃላት የሰበሰቡት ወንጌሎች ጠቅላላ ዓላማ ፣ አንባቢዎች አምነውበት በርሱ በኩል ሕይወት እንዲያገኙ መሆኑ በዮሐንስ ተገልጾአል ፤ ዮሐ· 20፡31 ። ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ እስካረገበት ቀን ድረስ የሚለው የሐዋርያት ስብከተ ወንጌል ይዘትና የማቴዎስ ወንጌል ይዘት አንድ ናቸው ፤ የሐዋ· 1፡22 ። በርሱ ወንጌል ውስጥ ያሉትን ልዩ ጸባያት በመመርመር የማቴዎስን ልዩ ዓላማ መረዳት ይቻላል ።

በብሉይ ኪዳን ትንቢት መፈጸም ላይ የሚያተኩረው የአይሁድ አስተሳሰብ ያለበት ወንጌል ፣ ያላመኑትን አይሁድ ጥያቄ ለመመለስ ታቅዶ የተጻፈ ይመስላል ። የተባለው እንዲፈጸም ከሚሉት አባባሎች ስድስቱ ፣ የኢየሱስን ልደትና ሕጻንነቱን ወይም ሞቱን ያመለክታሉ ፤ ምክንያቱም የተሰቀለው መሲህ ለነርሱ እንቅፋት ከመሆኑ በላይ ስለ ልደቱ አሉባልታ ሳይሰራጭ አልቀረም ። እነዚህ ሁለት ነጥቦች አብዛኞቹን አይሁዶች ከማመን ያደናቅፉአቸው ነበር ። አይሁዶች ስለ ትንሣኤው ልዩ ትርጉም ለመስጠት ስለሞከሩ በትንሣኤው እውነተኝነት ላይ ትኩረት ተደርጎአል ፤ 27፡62-66 ፣ 28፡11-15 ። በቀጥታ ከውጭ ላሉት ሰዎች ሳይሆን ክርስቲያኖች በጠለቀ ሁኔታ የክርስቶስን ሥራ ተረድተው ላላቸው እምነት መልስ ለመስጠት እንዲችሉ የተጻፈ ይመስላል ።

የማቴዎስ ወንጌል በርዕስ በርዕስ ተቀነባብሮ በቅደም ተከተል በመጻፉ ምክንያት ለማስተማሪያ በጣም ይጠቅማል ። የአይሁድ መምህራን ት/ቤትን ከሚመስል ጉባዔ የመነጨ መሆኑና አለመሆኑ ባይታወቅም ፣ ሥነ ምግባራዊና ለክርስቲያን ማኅበረ ሰብ የሚጠቅም የአስተዳደር ምክር በማቅረብ ረገድ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተጻፉት የአማካሪ መምሪያ መጽሐፍ ይመስላል ። ከሌሎች ወንጌሎች ይልቅም በቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ሥርዓት ጠቃሚ ሆኖ ቢገኝም የመነጨው ከክርስቲያን ማኅበረ ሰብ አምልኮ ነው ለማለት አያስደፍርም ።

ለማጠቃለል ያህል ፣ በአንደኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ ገደማ በእስራኤል አካባቢ ከማያምኑ አይሁዶች ጋር የቀረበ ግንኙነት ላላቸው አማኞች በአይሁዳዊ ጸሐፊ ተጻፈ ብለን ይህንን ክፍል ለመደምደም እንችላለን ። ወንጌሉ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች እንዴት አድርጎ እንደፈጸመ በማስረዳት ፣ ቀድሞ ለእስራኤል ከተሰጠው ቃል ኪዳን ጋር በማያያዝና በማሻሻል ፣ በመንፈሳዊ መሠረት ላይ የተመሠረተችውንና ሰዎች ሁሉ የሚካፈሉባትን የቤተ ክርስቲያንን አቋም ያሳያል ። ክርስቲያኖች ኢየሱስ እውነተኛ ንጉሣቸው መሆኑን እንዲረዱና ክርስቲያን ያልሆኑ አይሁዶች የሚያቀርቡት ተቃውሞ ትክክል አለመሆኑን መግለጽ እንዲችሉ የተጻፈ ወንጌል ነው ።